# የዮሐንስ ወንጌል

## መግቢያ

### ጸሐፊው

የዚህ ወንጌል ጸሐፊ፣ "ኢየሱስ ይወደው የነበር ደቀ መዝሙር" ሐዋርያው ዮሐንስ ነው (13፥23፤ 19፥26፤ 20፥2፤ 21፥7:20:24):: ሐዋርያው በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ታዋቂ ሰው ቢሆንም በዚህ ወንጌል ውስጥ ስሙ አልተጠቀሰም፤ ስለ መሲሑ አመጣጥ የተሰነዘረውን የተለመደ አመለካከት መግለጹ (1፥20-21፤ 7፥40-42)፣ በአይሁድና በሰማርያ ሰዎች መካከል ስለ ነበረው ቅራኔ ማውሳቱ (4፥9)፣ ስለ አይሁድ ልማድ፣ ለምሳሌ በስምንተኛው ቀን ስለ መገረዝ፣ ለማዝረትም በጊዜው ከሰንበት ይልቅ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንደ ነበር መጥቀሱ (የ7፥22 ማብ ይመ)፣ ጸሐፊው የአይሁድን ሥርዐት በሚገባ እንደሚያውቅ ያመለክታል:: ዮሐንስ የፍስልጥኤምን ምድር መልክአ ምድራዊ አቀ ማመጥ ያውቃል (11፥8፤ 2፥1፤ 2፥12):: ወንጌሉ ብዙ የዐይን ምስክር ማስረጃዎችንም ዐቅፎአል (2፥6፤ 13፥26፤ 21፥8:11)::

### ዓላማና ትኩረት

አንዳንድ ተርጓሚዎች የዮሐንስ ዓላማ የግሪክ ሊቃውንት የክርስትናን መልእክት እንዲቀበሉት አድርጎ ማቅረብ ነው ይላሉ:: ሌሎች ግን በተቀሩት ወንጌሎች ላይ ተጨማሪ አድርጎ ለማቅረብ፣ አንዳንድ የስሕተት ትምህርቶችን ለመቋቋም፣ የመጥምቁ ዮሐንስ ተከታዮች ነን የሚሉትን ለመቃ ወም የተጻፈ ወንጌል ነው ይላሉ:: ነገር ግን ጸሐፊው ራሱ፣ "ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚ አብሔር ልጅ እንደ ሆነ እንድታምኑ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት እንዲኖራችሁ ይህ ተጽፎአል" ዮሐ (20፥31) በማለት ዋና ዓላማውን ግልጽ አድርጎአል:: ዮሐንስ ወንጌሉን ሲጽፍ በሐሳቡ ውስጥ አን ዳንድ ለትምህርተ ኑፋቄ የተጋለጡ የግሪክ ተደራሲያን ሊኖሩ ቢችሉም፣ ዋና ዓላማው ግን ወንጌልን ማስ ራጨት ነው:: "እንድታምኑ" የሚለው ቃል "በእምነት ጸንታችሁ እንድትኖሩ" የሚል መልእክትም እንዳለው መረዳት ይቻላል፤ ይኸውም የዚህ ወንጌል ዓላማ አማኞችን ማነጽና ያላመኑትን ወደ ክርስ ቶስ ማምጣት እንደ ሆነ ያሳያል::

የዚህ ወንጌል ዋና ዋና የትኩረት ነጥቦች ለመረዳት የ1፥4:7:9:14:19:49፤ 2፥4:11፤ 3፥27፤ 4፥34፤ 6፥35፤13፥1-17:26፤13፥31፤17፥12:5፤20፥31 ማብ ይመ::

### የተጻፈበት ዘመን

የዮሐንስ ወንጌል መቼ እንደ ተጻፈ የሚጠቁሙ ሁለት አመለካከቶች ቀርበዋል፤

1. ትውፊታዊው አመለካከት፣ ይህ ወንጌል በመጀመሪያው መቶኛ ዓመት ማብቂያ፣ በ85 ዓ.ም. ገደማ ወይም ከዚያ በኋላ እንደ ተጻፈ ያሳያል፤
2. ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ አንዳንድ ምሁራን ከላይ ከተጠቀሰው ዘመን በፊት ያለ ጊዜን አመልክተዋል፤ በዚህም መሠረት፣ ምናልባት ከ50 እስከ 70 ዓ.ም. ባለው ጊዜ እንደ ተጻፈ ይናገራሉ::

ዮሐንስ ለመጀመሪያዎቹ ወንጌሎች ድጋፍ ለመስጠት ይህን ወንጌል ጽፎታል የሚለው የመጀ መሪያው አመለካከት ነው፤ ይህም አመለካከት የእስክንድርያውን የቀሌምንጦስን ሐሳብ መሠረት ያደ ረገ ሊሆን፤ በዚህ አመለካከት መሠረት ይህ ወንጌል ከመጀመሪያዎቹ ከሦስት ወንጌሎች ቀጥሎ የተጻፈ ወንጌል ነው:: አራተኛ የሆነው ይህ ወንጌል ያደገ ትምህርተ መለኮት የሚገኝበት መሆኑ፣ ከሌሎቹ በኋላ መጻፉን ያመለክታል የሚል ማስረጃም ቀርቦአል::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህም፣ ዮሐንስ ይህን ወንጌል የጻፈው ሌሎችን ወንጌሎች ሐሳብ ላይ ሳይንተራስ ነው የሚል ሐሳብ በመኖሩ፣ ሁለተኛው አመለካከት ተቀባይነት አግኝቶአል:: ይህ ከላይ የተጠቀሰውን የቀሌምንጦስን አመለካከት የሚቃረን አይደለም:: ሁለተኛውን አመለካከት የሚደግፉትም ይህ ወንጌል በትምህርተ መለኮት ይዘቱ የላቀ መሆኑ ከሌሎች ወንጌሎች በኋላ ለመጻፉ በቂ ማስረጃ ሊሆን እንደ ማይችል ያመለክታሉ:: በ57 ዓ.ም. ገደማ የተጻፈው የሮሜ መልእክት እንደዚህ ወንጌል የላቀ ትምህርተ መለኮት አለው:: በተጨማሪም በ5፥2 ላይ በጎች በር አጠገብ፣ ቤተ ሳይዳ የተባለች አንዲት መጠመቂያ "ነበረች" ሳይሆን "አለች" ብሎ መጻፉ፣ ኢየሩሳሌም ከመፍረሷ (70 ዓ.ም.) በፊት የነበረውን ጊዜ ሳያመለክት አይቀርም:: ይሁን እንጂ፣ አንዳንዶች ዮሐንስ ቀደም ሲል የታየ ሁኔታን በአሁን ጊዜ ግስ ጽፎአል ይላሉ::

### አስተዋፅኦ

1. መግቢያ (1፥1-18)
2. የኢየሱስ አገልግሎት ጅማሬ (1፥9-51)
   - ሀ. የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት (1፥19-34)
   - ለ. ኢየሱስ ከእነ ጴጥሮስ ጋር መገናኘቱ (1፥35-51)
3. የኢየሱስ ህዝድ አገልግሎት፣ ምልክቶችና ትምህርቶች (ም 2-11)
   - ሀ. ውሃን ወደ ወይን ጠጅ መለወጡ (2፥1-11)

ለ. ቤተ መቅደሱን ማንጻቱ (2፥12-25)
ሐ. ከኒቆዲሞስ ጋር ያደረገው ንግግር (3፥1-21)
መ. ከመጥምቁ ዮሐንስ ጋር ጎን ለጎን ማገልገሉ (3፥22-4፥3)
ሠ. ኢየሱስ በሰማርያ በውሃ ጉድጓዱ አጠገብ (4፥4-42)
ረ. የሹሙን ልጅ መፈወሱ (4፥43-54)
ሰ. ለአይሁድ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጉዞ (ም 5)
ሸ. አምስት ሺህ ሰዎችን መመገቡና "የሕይወት እንጀራነቱ" (ም 6)
ቀ. ኢየሱስ በዳስ በዓል ላይ (ም 7-8)
በ. ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው መፈወሱ (ም 9)
ተ. የመልካሙ እረኛ ምሳሌ (10፥1-21)
ቸ. በመታደስ በዓል የተነሣው ክርክር (10፥22-39)
ኀ. በዮርዳኖስ ማዶ የሰጠው አገልግሎት (10፥40-42)
ነ. አልዓዛርን ከሞት ማስነሣቱ (ም 11)

4. የሕማማት ሳምንት (ም 12-19)
   ሀ. የኢየሱስ እግር በሽቶ መቀባት (12፥1-11)
   ለ. ወደ ኢየሩሳሌም በክብር መግባቱ (12፥12-19)
   ሐ. የግሪክ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መምጣት (12፥20-36)
   መ. የአይሁድ አለማመን (12፥37-50)
   ሠ. የስንብት ትምህርቶቹ (ም 13-17)
      1. በመጨረሻው እራት ጊዜ የተሰጠ ትምህርት (ም 13-14)
      2. በጌቴሴማኒ መንገድ የተሰጠው ትምህርት (ም 15-16)
      3. የኢየሱስ የምልጃ ጸሎት (ም 17)
   ረ. ኢየሱስ ዐልፎ መሰጠቱና መያዙ (18፥1-12)
   ሰ. ኢየሱስ በፍርድ ወንበር ፊት (18፥13-19፥15)
   ሸ. የኢየሱስ መሰቀልና መቀበር (19፥16-42)
5. ትንሣኤ (20፥1-29)
6. ወንጌሉ የተጻፈበት ዓላማ (20፥30-31)
7. ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ ዐደራ (ም 21)

## ቃል ሥጋ ሆነ

1 በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚ
አብሔር ጋር ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር
ነበረ። 2 እርሱም በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር
ጋር ነበረ።
3 ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ ከተፈጠ
ረው ሁሉ ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም
የለም። 4 ሕይወት በእርሱ ነበረች፤ ይህች ሕይ
ወት የሰው ብርሃን ነበረች። 5 ብርሃንም በጨ
ለማ ያበራል፤ ጨለማውም አላሸነፈውም።[ሀ]
6 ከእግዚአብሔር የተላከ ዮሐንስ የተባለ አንድ
ሰው ነበረ። 7 ሰዎች ሁሉ በእርሱ በኩል
እንዲያምኑ፣ ስለ ብርሃን ምስክር ሆኖ ለመቆም
መጣ፤ 8 ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ
እርሱ ራሱ ብርሃን አልነበረም። 9 ለሰው ሁሉ
ብርሃን ሰጪ የሆነው እውነተኛው ብርሃን
ወደ ዓለም እየመጣ ነበር።[ለ]
10 እርሱ በዓለም ውስጥ ነበረ፤ ዓለም
የተፈጠረው በእርሱ ቢሆንም እንኳ፣ ዓለም
አላወቀውም። 11 ወደ ራሱ ወገኖች መጣ፤
የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም፤ 12 ለተቀ
በሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚ
አብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው።
13 እነዚህም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፣
ከደም[ሐ] ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወ
ንድ ፈቃድ አልተወለዱም።
14 ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም አደረ፤
እኛም ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ ከአባቱ
ዘንድ የመጣውን የአንድያ[መ] ልጅን ክብር
አየን።
15 ዮሐንስም፣ "'ከእኔ በኋላ የሚመጣው
ከእኔ በፊት ስለ ነበረ ከእኔ ይልቃል' ብዬ
የመሰከርሁለት እርሱ ነው" በማለት ጮኾ
ስለ እርሱ መሰከረ። 16 ከእርሱ ሙላት
ሁላችንም በጸጋ ላይ ጸጋ ተቀብለናል፤
17 ሕግ በሙሴ በኩል ተሰጥቶ ነበር፤ ጸጋና
እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መጣ።
18 ከቶውንም እግዚአብሔርን ያየ ማንም የለም፤
ነገር ግን በአብ እቅፍ ያለው አንድያ ልጁ[ሠ]

1፥1 ኢሳ55፥11፤ ዮሐ17፥5፤ፊል2፥6፤ 1ዮሐ1፥2፤ራእ19፥13
1፥2 ዘፍ1፥1፤ ዮሐ 8፥58፤17፥5:24፤ 1ዮሐ1፥1፤ራእ1፥8
1፥3 ቁ10፤1ቆሮ 8፥6፤ቈላ1፥16፤ዕብ 1፥2
1፥4 መዝ36፥9፤ ዮሐ3፥19፤5፥26፤6፥5 7፤8፥12፤ 9፥5፤ 11፥25፤ 12፥46፤ ሐሥ 3፥15፤ ዕብ 7፥16፤ 1ዮሐ1፥1:2፤ 5፥20፤ራእ 1፥18፤
1፥5 መዝ18፥28፤ ዮሐ3፥19
1፥6 ማቴ3፥1
1፥7 ቁ12:15:19: 32 ዮሐ 3፥15:26፤ 5፥33
1፥9 ኢሳ49፥6፤ 1ዮሐ 2፥8
1፥10 ቁ 3
1፥11 ኢሳ53፥3
1፥12 ቁ7፤ዘዳ 14፥1፤ዮሐ3፥15፤ ሮሜ8፥14:21፤ ኤፌ 5፥1፤1ዮሐ3፥1:2፤ 3፥23
1፥13 ዮሐ3፥6፤ ቲቶ3፥5፤1ጴጥ1፥23፤ 1ዮሐ3፥9፤4፥7፤ 5፥1:4፤ ያዕ1፥18
1፥14 ዘፀ33፥18፤40፥34፤ማቴ3፥11፤ ዮሐ14፥6፤ሮሜ3፥24፤ ገላ4፥4፤ፊል2፥7:8፤1ጢሞ3፥16፤ዕብ2፥14፤ 1ዮሐ1፥1:2፤4፥2
1፥15 ቁ7:30፤ማቴ3፥11
1፥16 ሮሜ3፥24፤ኤፌ1፥23፤ ቈላ1፥19፤ 2፥9
1፥17 ቁ14፤ዘዳ 32፥46፤ዮሐ7፥19
1፥18 ዘፀ33፥20፤ ዮሐ3፥16:18፤6፥46፤ቈላ1፥15፤1ጢሞ6፥ 16፤1ዮሐ4፥9:12

[ሀ] 5 ወይም *ጨለማው ግን አላወቀውም*
[ለ] 9 ወይም *ይህ ወደ ዓለም ለሚመጣ ሰው ብርሃን የሚሰጥ እውነተኛው ብርሃን ነበረ*
[ሐ] 13 ወይም *ከሰው ውሳኔ*
[መ] 14 ወይም አንድ ልጁ የሆነው
[ሠ] 18 አንዳንድ ቅጆች *አንድ ልጁ* ይላሉ

1፥1 *በመጀመሪያ፤* ዘፍ 1፥1 ይመ። *ቃል፤* ግሪኮች 'ቃል' የተሰኘውን የሐሳብ መግለጫ ለተነገረው፣ ለተሰማው ብቻ ሳይሆን፣ ላልተነገረው፣ ላልተሰማውና ገና በአእምሮ ውስጥ ላለው ሐሳብ ጭምር ይጠቀሙበታል። ፍጥረተ ዓለምን በተመለከተ ሲጠቀሙበት ግን የፍጥረትን ሥርዐት የሚመራውን ሕግ በማሰብ ነው። አይሁድ ግን 'ቃል' የሚለውን የሐሳብ መግለጫ የሚጠቀሙበት እግዚአብሔርን በተመለከተ ነው። ስለዚህም ዮሐንስ የተጠቀመው አይሁድም ሆኑ አሕዛብ በሚረዱት ቃል ነው። *ከእግዚአብሔር ጋር፤* ቃል ከአብ ልዩ ነው። *እግዚአብሔር ነበረ፤* ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ነው (የሮሜ 9፥5 ማብ ይመ)። የወንጌሉ መግቢያ (ቁ 1-18) የሚጀምረውም የሚጨርሰውም የጌታን አምላክነት በማጽናት ነው (የቁ 18 ማብ ይመ)።

1፥4 *ሕይወት፤* በዚህ ወንጌል ዐበይት ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ ነው። ይህ ቃል በዮሐንስ ወንጌል አብዝቶ ተጠቅሷል፤ ሕይወት የሚገኘው ከክርስቶስ ነው (10፥28)፤ እንዲያውም ጌታ ራሱ ሕይወት ነው (14፥6)። *የሰው ብርሃን፤* ይህ ወንጌል፣ 'ብርሃንን' የእውነተኛው መንፈሳዊ ብርሃን ምንጭ ከሆነው ከክርስቶስ ጋር ያያይዘዋል። ክርስቶስ ለሰው ሁሉ ብሩህ ተስፋን የሚሰጥ "የዓለም ብርሃን" ነው (8፥12)። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተገለጠው የሕይወትና የብርሃን ምንጭ እርሱ ነው (መዝ 36፥9)።

1፥5 *ጨለማ፤* በብርሃንና በጨለማ መካከል ያለው ጉልህ ንጽጽር የዚህ ወንጌል መሪ ሐሳብ ነው (ለምሳሌ 12፥35 ይመ)። በሰይጣን ግዛት ሥር ያለውን ክፉና ኀጢአተኛ ዓለም ያመለክታል።

1፥6 *ዮሐንስ፤* በዚህ ወንጌል ውስጥ፣ 'ዮሐንስ' የሚለው ስም ምንጊዜም የሚያመለክተው መጥምቁ ዮሐንስን ነው።

1፥7 *ሰዎች ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ፤* ሰዎች በመጥምቁ ዮሐንስ 'እንዲያምኑ' ሳይሆን በእርሱ አማካይነት በኢየሱስ እንዲያምኑ ነው። የወንጌሉ ጸሓፊ ዓላማም ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ ለማድረግ ነው (20፥31)። *ምስክር ሆኖ ለመቆም፤* የመጥምቁ ዮሐንስ ዋና አገልግሎት ስለ ኢየሱስ መመስከር ነበር (10፥41)። 'ምስክርነት' የዚህ ወንጌል ሌላው መሪ ሐሳብ ነው። ዮሐንስ ከማንኛውም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በላቀ ሁኔታ፣ ኢየሱስን በተመለከተ መገለጽ ያለበት እውነት በበቂ ምስክር የተደገፈ መሆኑን በአጽንዖት ያስረዳል።

*1፥9፤* ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ ሥጋ መልበስ (ትሥጉት) ያመለክታል። *ዓለም፤* ከሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይልቅ በዚህ ወንጌል ብዙ ትኩረት የተሰጠው ሌላው ተደጋጋሚ ቃል ነው። ቃሉ ፍጥረተ ዓለምን፣ ምድርን፣ በምድር ላይ የሚኖረውን ሕዝብ፣ አብዛኛውን ሕዝብ፣ እግዚአብሔርን የሚቃወመውን ሕዝብ፣ ወይም ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋር የሚቃረነውን ሰብአዊ ሥርዐት ሊያመለክት ይችላል። ዮሐንስ ለሐሳቡ አጽንዖት የሚሰጠው ቃሉን በመደጋገም ሲሆን አንዱን ትርጕም ሳያብራራ ወደ ሌላው ትርጕም ይሸጋገራል። (ለምሳሌ 17፥5፡ 14-15 እና ማብ ይመ)።

1፥12 *መብት ሰጣቸው፤* የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባል መሆን የሚቻለው የእግዚአብሔር ስጦታ በሆነው በጸጋ ብቻ ነው (ኤፌ 2፥8-9 ይመ)። ቁ13 በአጽንዖት እንደሚያሳየው ጸጋ የሰው የበጎ ሥራ ውጤት አይደለም፤ ይሁን እንጂ 'ለተቀበሉትና...ላመኑት' የተሰኘው ሐረግ በግልጽ እንደሚያሳየው ጸጋ ማግኘት ከሰው የመቀበል ፍላጎት ጋር የተሳሰረ ነው።

1፥14 *ሥጋ፤* ቃሉ የተለመደ ቢሆንም የክርስቶስን በእውን ሰው የመሆን ሐቅ የሚያጸና ነው። *ሆነ፤* 'ቃል' ሥጋ ከመሆኑ በፊት ሕልውና ስለ ነበረው ሽግግርን ያመለክታል። *በመካከላችን አደረ...ክብር አየን፤* የግሪኩ አባባል 'በመካከላችን አደረ' ሲል፣ "ድንኳን ወይም ማደሪያ ድንኳን" ከተባለው ቃል ወይም ሐረግ ጋር ያያይዘዋል። የዮሐንስ ጽሑፍ አይሁድ የሆኑትን አንባቢዎች በእግዚአብሔር ክብር ተሞልቶ የነበረውን የመገናኛ ድንኳን ያስታውሳቸዋል (ዘፀ 40፥34-35)። ክርስቶስ ባደረገው ታምራት፣ እንዲሁም በሞቱና በትንሣኤው ክብሩን ለደቀ መዛሙርቱ ገልጧል (2፥11 ይመ)። *ጸጋንና እውነትን፤* እነዚህ ቃላት በዕብራይስጥ ዘወትር በአቻነት የሚተረጐሙት "የማይለወጥ ፍቅርና ታማኝነት" በመባል ነው (የመዝ 26፥3፤ የምሳ 16፥6 ማብ ይመ)። *ጸጋ፤* ዮሐንስ ከመግቢያው (ቁ 1-18) በኋላ ለሐሳብ መግለጫነት ባያውለውም፣ መሠረታዊ የሆነ ክርስቲያናዊ ሐሳብን የያዘ ቃል ነው (የዮና 4፥2፤ የገላ 1፥3፤ የኤፌ 1፥2 ማብ ይመ)። *እውነት፤* ዮሐንስ፣ እውነት ከሆነው ከኢየሱስ ጋር (14፥6) ያስተሳሰረው ይህ ቃል ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል።

1፥15 *ከእኔ በፊት ስለ ነበረ፤* በጥንት ዘመንም የዕድሜ ብልጫ ያለው ማንም ሰው ታናሽ ከሆነው ሰው በይበልጥ ከበሬታ ተሰጥቶት ታላቅ ሰው ይባል ነበር። በተለመደው አመለካከት ከሆነ፣ ሰዎች በዕድሜ ታላቅ የሆነውን ዮሐንስን በዕድሜ ታናሽ ከሆነው ከኢየሱስ ይበልጥ ባከበሩት ነበር። መጥምቁ ዮሐንስ በዕድሜ ታላቅ ቢመስልም፣ ኢየሱስ በሥጋ ከመገለጡ በፊት፣ 'በቃልነቱ' አስቀድሞ ስለ ነበረ፣ ኢየሱስ ታላቁ እንደ ሆነ ያስጠረዳል፤ አባባሉም የጌታን ቅድመ ዓለም ሕልውና የሚያመለክት ነው።

1፥18 *አንድያ...አምላክ፤* የክርስቶስን አምላክነት በግልጽ የሚያሳይ ነው (ቁ 1፥14 እና ማብ እንዲሁም 3፥16 ይመ)።

የሆነው አምላክ እርሱ ገለጠው::

## መጥምቁ ዮሐንስ ራሱ ክርስቶስ እንዳልሆነ ተናገረ

19 አይሁድ፣ ማንነቱን እንዲጠይቁት ካህና
ትንና ሌዋውያንን ከኢየሩሳሌም ወደ እርሱ
ሲልኩ፣ ዮሐንስ የሰጠው ምስክርነት
ይህ ነበር::
20 ከመመስከርም ወደ ኋላ አላለም፤ “እኔ ክር
ስቶስ[a] አይደለሁም” ብሎ በግልጽ መሰከረ::
21 እነርሱም፣ “ታዲያ አንተ ማን ነህ? ኤል
ያስ ነህ?” ብለው ጠየቁት::
እርሱም፣ “አይደለሁም” አለ::
እነርሱም፣ “ታዲያ ነቢዩ ነህ?” አሉት::
እርሱም፣ “አይደለሁም” ሲል መለሰ::
22 በመጨረሻም፣ “እንግዲያስ ማን ነህ?
ለላኩን ሰዎች መልስ እንድንሰጥ ስለ ራስህ
ምን ትላለህ?” አሉት::
23 ዮሐንስም በነቢዩ በኢሳይያስ እንደተነ
ገረው፣ “‘ለጌታ መንገድ አቅኑለት’ እያለ
በምድረ በዳ የሚጮኽ ድምፅ እኔ ነኝ” ሲል
መለሰ::
24 ከተላኩትም ፈሪሳውያን አንዳንዶቹ፣
25 “ታዲያ፣ ክርስቶስ ወይም ኤልያስ ወይም
ነቢዩ ካልሆንህ፤ ለምን ታጠምቃለህ?” ብለው
ጠየቁት::
26 ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤
“እኔ በውሃ[b] አጠምቃለሁ፤ እናንተ የማታ
ውቁት ግን በመካከላችሁ ቆሟል፤ 27 ከእኔ
በኋላ የሚመጣው፣ የጫማውን ማሰሪያ ለመፍ
ታት እንኳ የማልበቃ እርሱ ነው::”
28 ይህ ሁሉ የሆነው ዮሐንስ ሲያጠምቅ
በነበረበት ከዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ ነበር::

## የእግዚአብሔር በግ

29 ዮሐንስ በማግሥቱ፣ ኢየሱስ ወደ እርሱ
ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፤ “እነሆ! የዓ
ለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር
በግ፤ 30 ‘ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት
ስለ ነበር ከእኔ ይልቃል’ ያልሁት እርሱ ነው፤
31 እኔ ራሴ አላወቅሁትም ነበር፤ በውሃ እያጠ
መቅሁ የመጣሁትም እርሱ በእስራኤል ዘንድ
እንዲገለጥ ነው::”

1+19 ማቴ3+1፤ ዮሐ2+18፤ 5+10፡ 16፤6+41፡52፤7+11፤ 10+24
1+20 ሉቃ3+15፡ 16፤ዮሐ3+28
1+21 ዘዳ18+15፤ ማቴ11+14
1+23 ማቴ3+1፤ ኢሳ 40+3
1+26 ማር1+4
1+27 ቁ15፡30፤ ማር1+7
1+28 ዮሐ3+26፤ 10+40
1+29 ቁ36፤ ዘፍ22+8፤ዮሐ3+17፤ ኢሳ53+7፤1ጴጥ1+19 ራእ5+6፤13+8
1+30 ቁ15፡27

[a] 20 ወይም *መሲሕ* «ክርስቶስ» (በግሪኩ ቋንቋ እና “መሲሑ” በዕብራይስጡ ሁለቱም *የተቀባ* የሚል ትርጕም አላቸው፤ ቍ 25 ይመ::

[b] 26 ወይም *በውሃ ውስጥ* ቍ 31 እና 33 ይመ

***ገለጠው፤*** በብሉይ ኪዳን ዘመን አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳዩ ይነገራል (ለምሳሌ በዘፀ 24+9-11)፤ ይሁን እንጂ ማንም ሰው እግዚአብሔርን አይቶ እንደማይተርፍ ተነግሮናል (ዘፀ 33+20):: ስለዚህ እግዚአብሔርን በመለኮታዊ ባሕርዩ ያየ ሰው ስለሌለ፣ ያዩት ሰዎች የተመለከቱት ራሱን በገለጠበት መልክ ብቻ ነበር:: አሁን ግን ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ማንነት ገልጦታል::

1+19 ***አይሁድ፤*** ይህ ቃል በዚህ ወንጌል ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ተጠቅሷል:: በጎ በሆነ ስሜትና (ለምሳሌ 4+22) ለዚ ህም ለዚያም ሳይባል (ለምሳሌ 2+6) ለሐሳብ መግለጫነት ይውላል:: በአጠቃላይ ሲታይ ግን ኢየሱስን የሚቃወሙትን የአይሁድ መሪዎች ማንነት ለመግለጽ ዮሐንስ በዚህ ቃል ተጠ ቅሞበት እናገኛለን (ለምሳሌ 8+48):: እዚህ ላይ ግን ሥልጣን ሳይሰጠው ያስተምራል የሚባለውን የዮሐንስን እንቅስቃሴ ለመሰለል፣ ትክክለኛ ነቢይ መሆኑን ለማረጋገጥና ተከታዮቹ እየበዙ ስለሄዱ በቅናት ከአይሁድ ሸንጎ የተላኩትን መልእክተኞች ያመለክታል:: ***ሌዋውያን፤*** ከሌዊ ነገድ ሲሆኑ፣ በማደሪያው ድንኳንና በቤተ መቅደስ ለተለየ አገልግሎት የተመደቡ ናቸው (ዘኍ 3+17-37)፤ የማስተማር ኀላፊነትም ነበራቸው (2 ዜና 35+3፤ ነህ 8+7-9):: ከካህናቱ ጋር ወደ መጥምቁ ዮሐንስ የተላኩበትም ምክንያት በነበራቸው የማስተማር ኀላፊነት ሳይሆን አይቀርም::

1+20 ***እኔ/*** መጥምቁ ዮሐንስን ከሌላ ሰው ጋር ማነጻጸሪያ ቃል ነው፤ ቀጥሎ ባሉት ተከታታይ ጥቅሶች በአጽንዖት የገባው ይህ ቃል ዘወትር ከፍተኛ ክብር ከተሰጠው ከኢየሱስ ጋር በሰያፍ ንጽጽር ላይ ውሎ እናገኘዋለን::

1+21 ***ኤልያስ ነህ?... አይደለሁም፤*** አይሁድ ኤልያስ እንዳልሞተ ያውቃሉ (2 ነገ 2+11)፤ ይኸው ነቢይ ተመልሶ መጥቶ የመጨረሻውን ቀን ያውጃል ብለው ያምናሉ፤ ዮሐንስም በዚሁ መንፈስ ኤልያስ አለ መሆኑን በሚገባ ገልጿል:: ኢየሱስ በኋለኛው ዘመን ዮሐንስን ኤልያስ ነው ማለቱ (ማቴ 11+14፤ 17+10-13) ዮሐንስ የሚል 4+5 ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን ሲያመ ለክት ነው (ከሉቃ 1+17 ጋር ያነጻጽሩ):: ***ነቢዩ/*** በዘዳ 18+15፡18 የተጠቀሰው ነቢይ ማለት ነው:: አይሁድ፣ የተለያዩ ሰዎችን ከመሲሑ መምጣት ጋር ያያይዙ ስለ ነበር፣ መጥምቁ ዮሐንስ እኔ ነቢዩ አይደለሁም በማለት አበክሮ ይገልጻል:: አመጣጡ ስለ ኢየሱስ ለመመስከር ሆኖ ሳለ፣ እነርሱ ግን ስለ ራሱ ደጋግመው ይጠይቁታል:: ለተደጋጋሚው ጥያቄ አዘውትሮ የሚሰጠው መልስም እጥር ምጥን ያለና የማያሻማ ነበር::

*1+23፤* ሰዎች ንስሐ በመግባት ለመሲሑ መምጣት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ መጥምቁ ዮሐንስ ጥሪ ሲያቀርብ የጠ ቀሰው ኢሳ 40+3 ነው:: የቁምራን ሰዎችም (የሙት ባሕርን ጥቅልል የብራና መጻሕፍት ያዘጋጁ ሰዎች) በዚሁ ሐሳብ ላይ በመመሥረት መንፈሳዊ ሕይወታቸውን መርተዋል፤ ሆኖም ግን የራሳቸውን ደኅንነት በጥረታቸው በማመቻቸት፣ ከዓለም ተገልለው ለመሲሑ መምጣት ዝግጁዎች ሆነው ይጠብቁ ነበር:: ዮሐንስ ግን ሐሳቡን የጣለው ሰዎች ወደ መሲሑ (ክርስቶስ) እንዲመጡ ለማገዝ በሚያደርገው ጥረት ላይ ነበር::

1+24 ***ፈሪሳውያን፤*** ከኢየሩሳሌም ከተላኩት ወገኖች ሁሉ ይልቅ (ቍ19)፣ ዮሐንስን ጠበቅ አድርገው የመረመሩት ሲሆኑ፣ ወግ አጥባቂ ከሆነው የሃይማኖት ክፍል ነበሩ :: በተጨማሪም የማቴ 3+7፤ የማር 2+16፤ የሉቃ 5+17 ማብ ይመ::

1+25 ***ክርስቶስ፤*** ‘የተቀባ’ ማለት ነው፤ ቃሉ የግሪክ ሲሆን በእብራይስጥ መሲሕ ነው:: በብሉይ ኪዳን ዘመን *‘መቀባት’* ለአገልግሎት መለየትንና መመደብን ያመለክታል፤ በተለይም ንጉሥ (1ሳሙ 16+1፡13፤ 26+11) ወይም ካህን (ዘፀ 40+13-15፤ ዘሌ 4+3) መሆንን ያመለክታል:: ሆኖም ሰዎች ይፈልጉ የነበሩት በተለመደው ሥርዐት የተቀባ ሰው ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር የተቀባውን ብቸኛ መሲሕ ነበር::

1+27 ***የጫማውን ማሰሪያ ለመፍታት እንኳ የማልበቃ፤*** አገልጋይ የሚሠራውን ዝቅተኛ ሥራ ያመለክታል:: ደቀ መዛሙርት ለመምህሮቻቸው የተለያየ አገልግሎት ይሰጣሉ፤ የጫማ ማሰሪያ መፍታት ግን አይጠበቅባቸውም ነበር::

1+28 ***ቢታንያ፤*** በሌሎች ወንጌሎች የተጠቀሰችው ሌላዋ ቢታንያ ከኢየሩሳሌም ሦስት ኪሎ ሜትር ብቻ ርቃ ትገኛለች:: የዚችኛዋ ቢታንያ ትክክለኛ አቀማመጥ ግን ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ በኩል ከመሆኑ በቀር ግልጽ አይደለም::

1+29 ***የእግዚአብሔር በግ፤*** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ አገላለጽ የሚገኘው በዚህ ቦታና በቍ.36 ላይ ብቻ ነው:: ትክክለኛውን ትርጕም ለማመልከት አያሌ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፤ ለምሳሌ በፋሲካ *መሥዋዕት* ሆኖ የቀረበው በግ፣ ወይም በኢሳ 53+7፤ በኤር 11+19 አለዚያም በዘፍ 22+8 የተጠ ቀሰው በግ ሊሆን ይችላል:: ሆኖም አገላለጹ አንድን የተለየ *መሥዋዕት* ሳይሆን፣ አጠቃላዩን *መሥዋዕት* የሚያመለክት ይመስላል:: ኢየሱስ ለዓለም ኀጢአት ስርየት የቀረበ *መሥዋዕት* መሆኑን ዮሐንስ ይገልጻል (ከ1ቆሮ 5+7 ጋር ያነጻጽሩ):: ይህ አባባል ታሪክንና (‘የፋሲካ በግ’ ዘፀ 12+3) ትንቢትን (‘መሲሕ’ ኢሳ 53+7) አገናዝቦ የሚያቀርብ ነው::

1+31 ***እኔ...አላወቅሁትም ነበር፤*** ለእስራኤል ሕዝብ በይፋ እስኪታይ ድረስ በምድረ በዳ የኖረው መጥምቁ ዮሐንስ (ሉቃ 1+80)፣ ኢየሱስን ላያውቀው ይችላል:: ሐሳቡ ግን ቍ 32-33 የተገለጸውን ምልክት እስካየ ድረስ፣ የተጠበቀውን መሲሕ (ክርስቶስ) መሆኑን አላወቀም ነበር ማለት ነው::

32ከዚያም ዮሐንስ እንዲህ ሲል ምስክር
ነቱን ሰጠ፤ "መንፈስ እንደ ርግብ ከሰማይ
ወርዶ በእርሱ ላይ ሲያርፍ አየሁ፤ 33በውሃ
እንዳጠምቅ የላከኝም፣ 'በመንፈስ ቅዱስ
የሚያጠምቀው፣ መንፈስ ሲወርድና በርሱ
ላይ ሲያርፍ የምታየው እርሱ ነው' ብሎ
እስከ ነገረኝ ድረስ እኔም አላወቅሁትም
ነበር፤ 34አይቻለሁ፣ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ
እንደ ሆነ እመሰክራለሁ::"

**የመጀመሪያዎቹ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት**

1፥40-42 ተጓ ምብ - ማቴ 4፥18-22፤ ማር 1፥16-20፤ ሉቃ 5፥2-11

35በማግሥቱ፣ ዮሐንስ ከሁለቱ ደቀ መዛ
ሙርቱ ጋር እንደ ገና እዚያው ቦታ ነበር፤
36ኢየሱስንም በዚያ ሲያልፍ አይቶ፣ "እነሆ!
የእግዚአብሔር በግ" አለ::
37ሁለቱ ደቀ መዛሙርትም ይህን ሲናገር
ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት:: 38ኢየሱስም
ዘወር ብሎ ሲከተሉት አየና፣ "ምን ትፈል
ጋላችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው::
እነርሱም፣ "ረቢ፣ የት ትኖራለህ?" አሉት፤
'ረቢ' ማለት መምህር ማለት ነው::
39እርሱም፣ "ኑና እዩ" አላቸው::
ስለዚህ ሄደው የት እንደሚኖር አዩ፤ በዚ
ያም ዕለት አብረውት ዋሉ፤ ከቀኑም ዐሥር
ሰዓት ያህል ነበር::
40ዮሐንስ የተናገረውን ሰምተው፣ ኢየሱስን
ከተከሉት ከሁለቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ
ወንድም እንድርያስ ነበር:: 41እንድርያስ በመ
ጀመሪያ ያደረገው ወንድሙን ስምዖንን ፈልጎ፣
"መሲሑን አገኘነው" ብሎ መንገር ነው፤
'መሲሕ' ማለት ክርስቶስ ማለት ነው:: 42ወደ
ኢየሱስም አመጣው::
ኢየሱስም ተመለከተውና፣ "አንተ የዮና
ልጅ ስምዖን ነህ፤ ኬፋ ተብለህ ትጠራለህ"
አለው፤ 'ኬፋ' ማለት ጴጥሮስ ማለት ነው::[ሸ]

1፥32 ማቴ3፥16
1፥33 ማር1፥4:8
1፥34 ቍ49፤ማቴ 4፥3
1፥35 ማቴ3፥1
1፥36 ቍ29
1፥38 ቍ49፤ማቴ 3፥7
1፥41 ዮሐ4፥25
1፥42 ዘፍ17፥5: 15፤32፥28፤ 35፥10፤ ማቴ16፥18
1፥43 ማቴ4፥19፤ 10፥3፤ዮሐ6፥5-7፤ 12፥21:22፤14፥8:9
1፥44 ማቴ11፥21
1፥45 ማር1፥24፤ ሉቃ3፥23፤ 24፥27፤ ዮሐ21፥2
1፥46 ዮሐ7፥41: 42:52
1፥47 መዝ32፥2፤ ሮሜ9፥4:6
1፥49 ቍ34:38፤ ዘፍ28፥12፤ማቴ2፥2፤ 4፥3፤23፥7፤27፥42፤ ዮሐ12፥13
1፥51 ማቴ3፥16፤ 8፥20
2፥1 ማቴ12፥46፤ ዮሐ4፥46፤21፥2

**ኢየሱስ ፊልጶስንና ናትናኤልን ጠራቸው**

43በማግሥቱ፣ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ለመሄድ
ፈለገ፤ ፊልጶስንም አግኝቶ፣ "ተከተለኝ"
አለው::
44ፊልጶስም እንደ እንድርያስና እንደ ጴጥ
ሮስ ሁሉ የቤተ ሳይዳ ከተማ ሰው ነበረ::
45ፊልጶስ ናትናኤልን አግኝቶ፣ "ሙሴ በሕግ
መጻሕፍት፣ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉለትን
የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱ ኢየሱስን አግኝተነ
ዋል" አለው::
46ናትናኤልም፣ "ከናዝሬት በጎ ነገር ሊወጣ
ይችላልን?" አለ::
ፊልጶስም፣ "መጥተህ እይ" አለው::
47ኢየሱስም፣ ናትናኤል ወደ እርሱ ሲመጣ
አይቶ፣ "እነሆ፤ ተንኰል የሌለበት እውነተኛ
እስራኤላዊ" አለ::
48ናትናኤልም "እንዴት አወቅኸኝ?" ሲል
ጠየቀው::
ኢየሱስም፣ "ከበለስ ዛፍ ሥር ሳለህ፣ ገና
ፊሊጶስ ሳይጠራህ አየሁህ" ሲል መለሰለት::
49ናትናኤልም መልሶ፣ "ረቢ! አንተ የእግዚ
አብሔር ልጅ ነህ፤ አንተ የእስራኤል ንጉሥ
ነህ" አለ::
50ኢየሱስም፣ "ያመንኸው ከበለስ ዛፍ ሥር
አየሁህ ስላልሁህ ነውን?[+] ገና ከዚህ የሚበ
ልጥ ነገር ታያለህ" አለው፤ 51ጨምሮም፣ "እው
ነት እላችኋለሁ፣ ሰማይ ተከፍቶ፣ የእግዚአ
ብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና
ሲወርዱ ታያላችሁ" አለው::

**ኢየሱስ ውሃን የወይን ጠጅ አደረገ**

2 በሦስተኛው ቀን፣ በገሊላ አውራጃ፣ በቃና
ከተማ ሰርግ ነበር፤ የኢየሱስም እናት በዚያ

[ሸ]42 *ኬፋ የሚለው የአራማይክ ቃልና ጴጥሮስ የሚለው የግሪኩ ትርጕም ዐለት ማለት ነው::*
[+]50 ወይም *ከበለስ ዛፍ ሥር አየሁህ ስላልሁህ አመንህ?*

1፥32፤ ስለ ኢየሱስ ጥምቀት የማቴ 3፥15 ማብ ይመ::

1፥33 *በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቀው...እርሱ ነው፤* 'ዮሐንስ በውሃ ያጠምቅ ነበር፤ ኢየሱስ ግን በመንፈስ ያጠምቃል' ለሚለው አባባል የተለየ ቀንና ሁኔታ ተጠብቆ ከሆነ፣ በበዓለ ሃምሳ (የጰንጠቆስጤ ቀን) መንፈስ ቅዱስ የወረደ ዕለት ተፈ ጽሞአል ማለት ነው:: (ሐሥ 2)::

1፥34 *የእግዚአብሔር ልጅ፤* ቍ 14:18፤ 3፥16፤ 20፥31 ይመ::

1፥35 ሁለቱ፤ አንዱ እንድርያስ ነው (ቍ 40):: ሌላው ባይጠቀስም፣ የዚሁ ወንጌል ጸሓፊ ዮሐንስ እንደ ሆነ ከጥንት ጀምሮ ይገመታል:: *ደቀ መዛሙርቱ፤* በዮሐንስ እጅ በመጠ መቃቸውና የሃይማኖት መምህራቸው አድርገው ይቈጥሩት ስለ ነበር ነው::

1፥36 *የእግዚአብሔር በግ፤* የቍ 29 ማብ ይመ::

1፥41 *መሲሑ!* የቍ 25 ማብ ይመ::

1፥42 *ጴጥሮስ፤* ጴጥሮስ በወንጌል ውስጥ ፈጽሞ በዓለት ሊመሰል የማይችል፣ ስሜታዊና እርጋታ የሌለው ሰው ነበር:: በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ግን የቤተ ክርስቲያን ምሰሶ ሆኖ እናገኘዋለን:: ኢየሱስ ይህን ማዕረግ የሰጠው ጴጥሮስ በነበረው ተፈጥሮአዊ ባሕርይ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ወደፊት ሊኖረው በሚችለው አዲስ ባሕርይ ነበር::

1፥44 *ቤተ ሳይዳ፤* የማቴ 11፥21 ማብ ይመ::

1፥45 *የዮሴፍ ልጅ፤* ክርስቶስ ከድንግል ያለ አባት መወለዱን (ማቴ 1፥18:20:23:25፤ ሉቃ 1፥35) ለመካድ አይደለም:: ዮሴፍ በሥጋ ወላጅ አባቱ ባይሆንም ባሳዳጊነቱ የአባትነት መብት ነበረው::

1፥46 *ናዝሬት፤* 7፥52 እና የማቴ 2፥23 ማብ ይመ::

1፥47 *እውነተኛ እስራኤላዊ፤* 2፥24-25 ይመ::

1፥48 *የበለስ ዛፍ፤* ጥላው በበጋ ወቅት ለንባብና ለጸሎት አመቺ ነበር::

1፥49 *የእግዚአብሔር ልጅ፤* ቍ 14:18:34፤ 3፥16፤ 20፥31 ይመ:: ኢየሱስ አገልግሎቱን እንደ ጀመረ ናትናኤል 'የእግዚአብሔር ልጅ' በማለት ተገቢ የሆነውን የጌታን የክብር ስም ገልጧል:: ከጊዜ በኋላ ግን ይህን መጠሪያ ተቃዋሚዎቹ መዘባበቻ አድርገውታል (ማቴ 27፥40፤ ዮሐ 19፥7):: *የእስራ ኤል ንጉሥ!* 12፥13 ይመ:: በማር 15፥32 'ክርስቶስ' የሚለው ስምና 'የእስራኤል ንጉሥ' የሚለው መጠሪያ በአቻነት ተጠ ቅሰው ይገኛሉ::

1፥51 *ሰማይ ተከፍቶ፤* ደቀ መዛሙርት በኢየሱስ አገልግሎት አማካይነት፣ እግዚአብሔር ከሰማይ ስለ ኢየሱስ ማንነት በግልጽ እንደ ተናገረ ያህል ይረዳሉ ማለት ነው:: *የእግዚአብሔር መላእክት...ሲወጡና ሲወርዱ፤* ያዕቆብ በሕልሙ እንዳየው ማለት ነው (ዘፍ 28፥12 እና ማብ ይመ):: ይህም፣ ቤዛነት ወደ ዓለም የመጣው በእግዚአብሔር በተመረጠው በኢየሱስ አማካይነት መሆኑን ያሳያል፤ እውነተኛውም እስራኤላዊ እርሱ መሆኑን ማመልከቱ ሊሆን ይችላል (ቍ 47 ይመ):: *የሰው ልጅ፤* ኢየሱስ ራሱን ለማመልከት በተለይ የሚጠቀምበት መጠሪያ ነው (የማር 8፥31፤ የሉቃ 6፥5፤ 19፥10 ማብ ይመ)::

2፥1 *ሰርግ፤* በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት፣ በመካከለኛው ምሥራቅ የጋብቻ ሥነ ሥርዐት እንዴት ይከናወን እንደ ነበር

## ኢየሱስ ታምራት

| የፈውስ ታምራት | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|
| ለምጽ የነበረበት ሰው | 8÷2-4 | 1÷40-42 | 5÷12-13 | |
| የሮማ መቶ አለቃው አገልጋይ | 8÷5-13 | | 7÷1-10 | |
| የጴጥሮስ አማት | 8÷14-15 | 1÷30-31 | 4÷38-39 | |
| ሁለት የጌርጌሴኖን አገር ሰዎች | 8÷28-34 | 5÷1-15 | 8÷27-35 | |
| ሽባ የነበረው ሰው | 9÷2-7 | 2÷3-12 | 5÷18-25 | |
| ደም ይፈሳት የነበረች ሴት | 9÷20-22 | 5÷25-29 | 8÷43-48 | |
| ሁለት ዓይነ ሥውራን | 9÷27-31 | | | |
| ዲዳና በአጋንንት የተያዘ ሰው | 9÷32-33 | | | |
| አንድ እጁ ሽባ የሆነ ሰው | 12÷10-13 | 3÷1-5 | 6÷6-10 | |
| በጋኔን ተይዞ ማየትና መናገር የማይችል | 12÷22 | | 11÷14 | |
| የከነዓናዊት ሴት ልጅ | 15÷21-28 | 7÷24-30 | | |
| አጋንንት የያዘው ልጅ | 17÷14-18 | 9÷17-29 | 9÷38-43 | |
| ሁለት ዓይነ ሥውራን (የአንዱ ስም የተጠቀሰ) | 20÷29-34 | 10÷46-52 | 18÷35-43 | |
| ደንቆሮና ዲዳ ሰው | | 7÷31-37 | | |
| ርኩስ መንፈስ የያዘው | | 1÷23-26 | 4÷33-35 | |
| ቤተ ሳይዳ የነበረው ዓይነ ሥውር | | 8÷22-26 | | |
| አካለ ስንኩል ሴት | | | 13÷11-13 | |
| ሆዱ የተነፋ ሰው | | | 14÷1-4 | |
| ዐሥር ለምጻሞች | | | 17÷11-19 | |
| የሊቀ ካህናቱ አገልጋይ | | | 22÷50-51 | |
| በቅፍርናሆም የባለ ሥልጣኑ ልጅ | | | | 4÷46-54 |
| በቤተ ሳይዳ መጠመቂያ የነበረው በሽተኛ | | | | 5÷1-9 |
| ዓይነ ሥውር ሆኖ የተወለደው ሰው | | | | 9÷1-7 |
| | | | | |
| **በተፈጥሮ ላይ ሥልጣን እንዳለው የሚያሳዩ ታምራት** | | | | |
| ማዕበሉን ጸጥ ማድረግ | 8÷23-27 | 4÷37-41 | 8÷22-25 | |
| በውሃ ላይ መራመድ | 14÷25 | 6÷48-51 | | 6÷19-21 |
| 5,000 ሰዎችን መመገብ | 14÷15-21 | 6÷35-44 | 9÷12-17 | |
| 4,000 ሰዎችን መመገብ | 15÷32-38 | 8÷1-9 | | |
| ከዓሣ አፍ የተገኘ ሳንቲም | 17÷24-27 | | | |
| የደረቀችው የበለስ ዛፍ | 21÷18-22 | 11÷12-14:20-25 | | |
| የብዙ ዓሣዎች መጠመድ | | | 5÷4-11 | |
| የውሃ ወደ ወይን ጠጅ መለወጥ | | | | 2÷1-11 |
| ሌላ ብዙ ዓሣዎች መጠመድ | | | | 21÷1-11 |
| **ሙታንን የማስነሣት ታምራት** | | | | |
| የኢያኢሮስ ሴት ልጅ / | 9÷18-19:23-25 | 5÷22-24:38-42 | 8÷41-42:49-56 | |
| በናይን ከተማ የመበለቲቱ ልጅ | | | 7÷11-15 | |
| አልዓዛር | | | | 11÷1-44 |

ነበረች፤ 2ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ
ተጠርተው ነበር። 3የወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜም
የኢየሱስ እናት፣ "የወይን ጠጅ እኮ አለቀባ
ቸው" አለችው።
4ኢየሱስም፣ "አንቺ ሴት ሆይ፤ ምን አድ
ርግ ትይኛለሽ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም" አላት።
5እናቱም በዚያ የነበሩትን አገልጋዮች፣
"የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" አለቻቸው።
6በአይሁድ የመንጻት ሥርዐት መሠረት፣
ከሰባ አምስት እስከ አንድ መቶ ዐሥራ
አምስት ሊትር የሚይዙ ከድንጋይ የተሠሩ
ስድስት ጋኖች[ሀ] በዚያ ነበሩ።
7ኢየሱስ አገልጋዮቹን፣ "ጋኖቹን ውሃ ሙሏ
ቸው" አላቸው፤ እነርሱም፣ ጋኖቹን እስከ
አፋቸው ሞሏቸው።
8እርሱም፣ "ከላዩ ቀድታችሁ ለድግሱ ኀላፊ
ስጡት" አላቸው።
እነርሱም እንዳዘዛቸው አደረጉ። 9የድግሱ
ኀላፊም ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠውን ውሃ
ቀመሰ፤ ሆኖም ከየት እንደ መጣ አላወቀም፤
ውሃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ
ነበር። እርሱም ሙሽራውን ለብቻው ጠርቶ፣
10"ሰው ሁሉ በመጀመሪያ የሚያቀርበው ጥሩ
ውን የወይን ጠጅ ነው፤ እንግዶቹም ብዙ ከጠጡ
በኋላ መናኛውን የወይን ጠጅ ያቀርባል፤
አንተ ግን ጥሩውን የወይን ጠጅ እስከ አሁን
አቈይተሃል" አለው።
11ኢየሱስም ይህን የታምራዊ ምልክቶቹን
መጀመሪያ በገሊላ አውራጃ በቃና ከተማ
አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ መዛሙር
ቱም በእርሱ አመኑ።

2፥4 ማቴ8፥29፤ ዮሐ19፥26፤ 26፥18
2፥5 ዘፍ41፥55
2፥6 ማር7፥3:4፤ ዮሐ3፥25
2፥9 ዮሐ 4፥46
2፥11 ቍ23፤ ዘፀ14፥31፤ ማቴ12፥38፤ ዮሐ1፥14፤3፥2፤ 4፥48፤6፥2:14:26: 30፤12፥37፤20፥30
2፥12 ማቴ4፥13፤ 12፥46
2፥13 ዘዳ16፥1-6፤ ሉቃ2፥41፤ ዮሐ11፥55
2፥14 ዘሌ1፥14፤ ዘዳ14፥25:26
2፥16 ሉቃ2፥49
2፥17 መዝ69፥9
2፥18 ቍ11፤ ማቴ12፥38፤ዮሐ1፥19
2፥19 ማቴ16፥21፤ 26፥61፤27፥40፤ ማር 14፥58፤15፥29፤ ሐሥ6፥14

## ኢየሱስ ቤተ መቅደስን አጠራ

2፥14-16 ተጓ ምብ - ማቴ 21፥12:13፤ ማር 11፥15-17፤ ሉቃ 19፥45:46

12ከዚህ በኋላ ከእናቱ፣ ከወንድሞቹና ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር ወደ ቅፍርናሆም ወረደ፤
በዚያም ጥቂት ቀን ተቀመጡ።
13የአይሁድ ፋሲካም እንደ ተቃረበ፣ ኢየ
ሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። 14በቤተ መቅ
ደሱ አደባባይ ከብቶችን፣ በጎችንና ርግቦችን
የሚሸጡ እንዲሁም ተቀምጠው የገንዘብ
ምንዛሪ የሚያከናውኑ ሰዎች አገኘ። 15የገመድ
ጅራፍ አበጅቶ በጎችንና ከብቶችን ሁሉ ከቤተ
መቅደሱ ግቢ አባረረ፤ የመንዛሪዎችን ገንዘብ
በተነ፤ ጠረጴዞቻቸውንም ገለበጠ። 16ርግብ
ሻጮችንም፣ "እነዚህን ከዚህ አስወጧቸው፤
የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት!"
አላቸው።
17ደቀ መዛሙርቱም፣ "ለቤትህ ያለኝ ቅናት
ያቃጥለኛል" ተብሎ የተጻፈው ትዝ አላቸው።
18አይሁድም፣ "ይህን ሁሉ ለማድረግ ሥል
ጣን እንዳለህ የሚያረጋግጥ ምን ታምራዊ
ምልክት ታሳየናለህ?" አሉት።
19ኢየሱስም፣ "ይህን ቤተ መቅደስ አፍር
ሱት፤ እኔም በሦስት ቀን መልሼ አነሣዋለሁ"
ብሎ መለሰላቸው።
20አይሁድም፣ "ይህን ቤተ መቅደስ ለመ
ሥራት አርባ ስድስት ዓመት ፈጅቶአል፤ ታዲያ
አንተ እንዴት በሦስት ቀን መልሰህ ታነሣዋለህ?"

[ሀ]6 በግሪኩ *ሁለት ወይም ሦስት እንስራ*

የሚታወቀው በመጠኑ ነው። ይሁን እንጂ የጋብቻ በዓል ትልቅ ክብር የሚሰጠውና እስከ አንድ ሳምንት የሚቈይ ነበር፤ የሰርጉንም ግብዣ በሚገባ አለማስተናገድ እንደ ውርደት ይቈጠር ነበር። *ቃና*፤ የተጠቀሰው በዮሐንስ ወንጌል ብቻ ሲሆን (2፥11፤ 4፥46:50፤ 21፥2) ከገሊላ ባሕር በስተ ምዕራብ የሚገኝ ስፍራ ነበር፤ ትክክለኛ ቦታው ግን በውል አይታወቅም።

2፥3 *የወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜ*፤ በዘመኑ በነበረው ልማድ፣ ደጋሹ እንግዶቹን በሚገባ ማስተናገድ ስለ ነበረበት፣ የዚህ ሁኔታ መከሠት ትልቅ ውርደት ነበር። በዚያን ዘመን ከወይን ጠጅ በቀር ሌላ የተለመደ መጠጥ አልነበረም።

2፥4 *አንቺ ሴት ሆይ*፤ የንቀት ሳይሆን በዚያን ዘመን የአክብሮት አጠራር ነበር (19፥26)። *ጊዜዬ ገና አልደረሰም*፤ እንደዚህ ያለው አባባል በዚህ ወንጌል ውስጥ ብዙ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል (7፥6:8:30፤ 8፥20)። ይኸውም ኢየሱስ ወደ መጣበትና ወደማይቀርለት፣ በመስቀል ላይ መሥዋዕት ወደሚሆንበት፣ ዓላማ መቃረቡን ያመለክታል። በእርግጥም ጊዜው በመስቀሉና በትንሣኤው ወቅት በትክክል ተፈጽሟል (12፥23:27፤ 13፥1፤ 16፥32፤ 17፥1)።

2፥6 *የመንጻት ሥርዐት*፤ አይሁድ በዕለት ኑሮአቸው በተለያየ ሁኔታ እንረክሳለን ብለው ስለሚያምኑ፣ በእጃቸው ላይ ውሃ በማፍሰስ በዕለቱ የረከሰውን አካላቸውን ያነጻሉ። በዚህም መሠረት፣ ረዘም ላለ ጊዜ ለሚቆይና ብዙ እንግዶች ለሚስተናገዱበት ሰርግ፣ በቂ ውሃ ያስፈልግ ነበር። *የሚይዙ*፤ በዕለቱ የነበረውን መጠን ሳይሆን፣ ጋኖቹ ሊይዙ የሚችሉትን ልክ ለማመልከት ነው።

2፥11 *ምልክቶች*፤ ዮሐንስ የኢየሱስን ታምራት ሁልጊዜ ምልክቶች ይላቸዋል፤ ቃሉ የሚያመለክተው የታምሩን አስደናቂነት ሳይሆን ከታምሩ የሚገኘውን ትምህርት ነው (ለምሳሌ 4፥54፤ 6፥14፤ 9፥16፤ 11፥47 ይመ)። ታምራቱም የኢየሱስን ክብር ያሳያሉ (1፥14፤ ይመ፤ ከኢሳ 35፥1-2፤ ከኢል 3፥18፤ ከአሞ 9፥13 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥12 *ወንድሞቹ*፤ የሉቃ 8፥19 ማብ ይመ። *ወረደ*፤ በባሕሩ ዳርቻ የምትገኘው ቅፍርናሆም፣ በገሊላ አውራጃ ከነበረችው ቃና ዝቅ ብላ የምትገኝ መሆኗን ለማመልከት ነው።

2፥13 *ፋሲካ*፤ ከዓመት በዓላት አንዱ ሲሆን ማንኛውም አይሁዳዊ በኢየሩሳሌም ተገኝቶ እንዲያከብር ይጠበቅበታል (ዘፀ 12፤ ዘዳ 16፥16 ይመ፤ እንዲሁም የዘፀ 12፥11-23፤ የማቴ 26፥17: 18-30፤ የማር 14፥1:12፤ የሉቃ 22፥1፤ የዮሐ 5፥1 ማብ ይመ)።

*2፥14-17፤* የቤተ መቅደሱ መንጻት በኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን መጨረሻ ላይ እንደሆነ ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ ጽፈዋል። (የማቴ 21፥12-17 ማብ ይመ)።

2፥14 *ከብቶች፣ በጎችና ርግቦች*፤ ለመሥዋዕት ተገቢ የሆኑ ናቸው። ከሩቅ አገር ተጕዘው የሚመጡት አይሁድ በቤተ መቅደስ አካባቢ ከሚገኙትና ለመሥዋዕት ተለይተው ከተቀመጡት ከብቶች መካከል መግዛት ይችሉ ነበር። ነጋዴዎች ግን አሕዛብ ገብተው የሚጸልዩበትን የቤተ መቅደሱ ውጫዊ አደባባይ ሳይቀር መሸጫ አድርገውት ነበር። *ምንዛሪ፤* ሰዎች ይዘዋቸው የሚመጡት የገንዘብ ዓይነቶች ካህናቱ ሊቀበሉት ወደሚችሉት የገንዘብ ዓይነት መለወጥ ስለ ነበረባቸው፤ የመንዛሪዎች በዚያ ቦታ መገኘት አስፈላጊ ነበር (የማር 11፥15 ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ በቤተ መቅደስ ውስጥ ገንዘብ መመንዘር አልነበረባቸውም።

*2፥19፤* አይሁድ፣ ኢየሱስ የሚያውቁትንና የሚታየውን ቤተ መቅደስ 'አፍርሱት' ያለ መስሎአቸው ነበር፤ ይህ አለመሆኑን ግን ዮሐንስ በቍጥር 21 ይነግረናል። ዓመታት ካለፉ በኋላም ኢየሱስ 'ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሼ እሠራዋለሁ' ብሏል ተብሎ ክስ ቀርቦበታል (ማቴ 26፥60-61፤ ማር 14፥57-59)። ፌዘኞችም ጌታ በመስቀል ላይ በነበረበት ጊዜ ይህንኑ ቃል አሰምተዋል (ማቴ 27፥40፤ ማር 15፥29)። እስጢፋኖስንም በተመሳሳይ ሁኔታ የከሰሱት፣ ሐሳቡን በትክክል ካለመረዳታቸው የተነሣ ሳይሆን አልቀረም (ሐሥ 6፥14)።

2፥20 *አርባ ስድስት ዓመት*፤ ዘሩባቤል ከ500 ዓመት በፊት የሠራውን ይህን ቤተ መቅደስ ታላቁ ሄሮድስ ማደስ የጀመረው 20 ዓ.ቅ.ክ. በፊት መሆኑ ይታወቃል። አይሁድ ግን

አሉት:: 21ቤተ መቅደስ ሲል ግን፣ ስለ ገዛ
ሰውነቱ መናገሩ ነበር:: 22ከሙታንም ከተነሣ
በኋላ፣ ደቀ መዛሙርቱ ምን እንደተናገረ
አስታወሱ፤ መጻሕፍትንና ኢየሱስ ያለው
ንም ቃል አመኑ::
23በፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም ሳለ፣ ብዙ
ሰዎች ያደረገውን ታምራት አይተው በስሙ
አመኑ፤⁺ 24ኢየሱስ ግን ሰውን ሁሉ ስለሚ
ያውቅ፣ አይታመንባቸውም ነበር፤ 25በሰው
ውስጥ ያለውን ያውቅ ስለ ነበር፣ ማንም ስለ
ሰው እንዲመሰክርለት አላስፈለገውም::

## ኢየሱስ ኒቆዲሞስን አስተማረ

3 ከፈሪሳውያን ወገን፣ ከአይሁድ አለቆች
አንዱ የሆነ ኒቆዲሞስ የተባለ ሰው ነበረ፤
2በሌሊትም ወደ ኢየሱስ መጥቶ፣ “ረቢ፤ እግዚ
አብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ ሰው በቀር አንተ
የምታደርጋቸውን ታምራዊ ምልክቶች ማንም
ሊያደርግ ስለማይችል፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ
የመጣህ መምህር እንደ ሆንህ እናውቃለን”
አለው::
3ኢየሱስም መልሶ፣ “እውነት እልሃለሁ፤
ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ⁼ በቀር የእግዚ
አብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም” አለው::
4ኒቆዲሞስም፣ “ሰው ከሸመገለ በኋላ እን
ዴት ሊወለድ ይችላል? ዳግመኛ እንዲ
ወለድ ተመልሶ ወደ እናቱ ማሕፀንስ ሊገባ
ይችላልን?” አለው::
5ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እውነት
እልሃለሁ፤ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተ
ወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ
አይችልም፤ 6ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤
ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው:: 7‘ዳግ
መኛ መወለድ አለባችሁ’ ስላልሁህ አትገረም፤

2፥21 1ቆሮ6፥19
2፥22 መዝ16፥10፤ ሉቃ24፥5-8፤24፥27፤ ዮሐ12፥16፤14፥26
2፥23 ቍ11:13፤ ዮሐ3፥15
2፥25 ዘዳ31፥21፤ 1ነገ8፥39፤ኢሳ11፥3፤ ማቴ9፥4፤ዮሐ6፥61: 64፤13፥11
3፥1 ዮሐ7፥50፤ 19፥39፤ሉቃ23፥13
3፥2 ቍ11፤ ሐሥ2፥22፤10፥38፤ ማቴ23፥7፤ዮሐ2፥11፤ 10፥38፤14፥10:11
3፥3 ማቴ3፥2፤ ዮሐ1፥13
3፥5 ሐሥ22፥16፤ ቲቶ3፥5
3፥6 ዮሐ1፥13፤ 1ቆሮ15፥50
3፥8 1ቆሮ2፥14-16
3፥9 ዮሐ6፥52:60
3፥10 ሉቃ2፥46
3፥11 ቍ32፤ዮሐ 1፥18፤7፥16:17
3፥13 ቍ31፤ምሳ 30፥4፤ማቴ8፥20፤ዮሐ 6፥38:42፤ሐሥ2፥34፤ ኤፌ4፥8-10፤ ዕብ 4፥14፤ 9፥24
3፥14 ዘኁ21፥8:9፤ ዮሐ12፥32
3፥15 ቍ16:36፤ ዘፍ15፥6፤ዘኍ14፥11 ማቴ25፥46፤27፥42፤ ማር1፥15፤ዮሐ1፥7: 12፤2፥23፤5፥24፤7፥ 38፤20፥29፤20፥31፤ ሐሥ13፥39፤16፥31፤ ሮሜ3፥22፤10፥9:10፤ 1ዮሐ 5፥1:5:10
3፥16 ቍ15:36፤ ዘፍ22፥12፤ ኢሳ9፥6፤ ዮሐ1፥18፤6፥29:40፤ 11፥25:26፤ ሮሜ8፥ 32፤5፥8፤ኤፌ2፥4፤ 1ዮሐ4፥9:10
3፥17 ኢሳ53፥11፤ማቴ1፥21፤ሉቃ2፥11፤19፥10፤ ዮሐ1፥29፤ 6፥29:57፤10፥36፤11፥42፤12፥47፤17፥8:21፤ 20፥21፤ሮሜ11፥ 14፤1ጢሞ1፥15፤2፥5:6፤1ዮሐ2፥2፤3፥5

8ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰ
ማለህ፤ ነገር ግን ከየት እንደ መጣ፣ ወዴት
እንደሚሄድም አታውቅም፤ ከመንፈስም
የተወለደ ሁሉ እንደዚሁ ነው::”
9ኒቆዲሞስም፣ “ይህ እንዴት ሊሆን ይች
ላል?” ሲል ጠየቀው::
10ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “አንተ
የእስራኤል መምህር ሆነህ ሳለ እነዚህን
ነገሮች አታውቅምን? 11እውነት እልሃለሁ፤
የምናውቀውን እንናገራለን፤ ያየነውንም እን
መሰክራለን፤ እናንተ ግን ምስክርነታችንን
አትቀበሉም:: 12ስለ ምድራዊው ነገር ነግሬ
አችሁ ያላመናችሁ፣ ስለ ሰማያዊው ነገር
ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ? 13ከሰ
ማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር፣ ወደ
ሰማይ የወጣ ማንም የለም::ᵓ 14ሙሴ በም
ድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ፣ የሰው ልጅም
እንዲሁ ሊሰቀል ይገባዋል፤ 15ይኸውም በእ
ርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት
እንዲኖረው ነው::
16“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት
እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አን
ድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን
እንዲሁ ወዶአልና፤ 17እግዚአብሔር ልጁን ወደ
ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን፣ ዓለምን
በእርሱ ለማዳን ነው:: 18በእርሱ የሚያምን ሁሉ
አይፈረድበትም፤ በእርሱ የማያምን ግን በአንዱ

⁺23 ወይም *በእርሱም አመኑ*
⁼3 ወይም *ከላይ ካልተወለደ፤ ቍ 7 ይመ*
ᵓ13 ወይም *በሰማይ ካለው . . .*

46 ዓመት ሲሠራ ቆይቷል ሲሉ፣ ከጌታ ጋር ይነጋገሩ የነበሩበት ዘመን በ26 ዓ.ም. መሆኑን ያሳያል:: የቤተ መቅደሱ ሥራ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀው ግን በ64 ዓ.ም. ነው::

2፥22 *አስታወሱ፤* 14፥26 ይመ::

2፥23 *የፋሲካ በዓል፤* የቍ13 ማብ ይመ:: *በስሙ፤* በጥንት ዘመን የአንድ ሰው ስም የሰውዬውን ማንነት አካቶ ስለሚይዝ፣ ‘በስሙ ማመን’ ማለት በሰውዬው በራሱ ማመን ማለት ነው::

3፥1 *ከፈሪሳውያን...አንድ ሰው፤* የማቴ 3፥7፤ የማር 2፥16፤ የሉቃ5፥17 ማብ ይመ::

3፥2 *በሌሊት፤* ኒቆዲሞስ ምናልባት በቀን መምጣት ፈርቶ ይሆናል፤ ወይም ሕዝብ በተሰበሰበበት የግል ውይይት አስቸጋሪ ስለሚሆን፣ ከኢየሱስ ጋር ረዘም ላለ ጊዜ ለመወያየት ፈልጎ ሊሆን ይችላል:: ባለሥልጣን እንደ መሆኑ መጠን ወደ ጌታ ኢየሱስ ሰው መላክ ይችል ነበር፤ ይሁን እንጂ ራሱ ወደ ጌታ መምጣቱ ከልቡ እውነትን ለማወቅ እንደ ፈለገ ያሳያል::

3፥3 *ዳግመኛ ካልተወለደ፤* እንደ ገና ለሁለተኛ ጊዜ መወለድ ማለት ሲሆን፣ የግሪኩ ትርጉም ‘ከላይ መወለድ’ የሚለውንም ሐሳብ ሊያመለክት ይችላል:: ሁለቱም ትርጉሞች ከኢየሱስ የማዳን ሥራ ጋር ይስማማሉ:: ይህ አዲስ ልደት የሚገኘው በክርስቶስ በማመን ሲሆን፣ ይኸውም የእግዚአብሔር ሥራ ነው:: ሰው ከአባት በእናቱ በሥጋ ይወለዳል፤ ይህም የመጀመሪያ ልደት ነው:: ዳግመኛ ልደት ግን ከመንፈስ ቅዱስ መወለድ ነው::

3፥5 *ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ፤* የተለያየ ትርጉም ሊሰጠው የሚችል አባባል ነው፤ 1) ‘ከመንፈስ መወለድ’ እንደ ማለት ነው (ቍ8፤ ከቲቶ 3፥5 ጋር ያነጻጽሩ):: 2) በዚህ ላይ ውሃ፣ መንጻትን ያመለክታል:: 3) ውሃ፣ የዮሐንስን ጥምቀት (1፥31) ወይም የኢየሱስንና የደቀ መዛሙርቱን ጥምቀት (ቍ22፤ 4፥1-2) ያመለክታል:: *የእግዚአብሔር መንግሥት፤* የማቴ 3፥2 ማብ ይመ::

3፥7 *ዳግመኛ መወለድ፤* የቍ3 ማብ ይመ:: *አለባችሁ፤* ይህ ብርቱ ቃል የሚመለከተው ኒቆዲሞስን ብቻ ሳይሆን እገሌ ከእገሌ ሳይባል ሁሉንም ነው::

3፥8፤ *መንፈስ ቅዱስ ኀያል ነው፤ የሰውን ልብ በማደስ ረገድ ባሻው መንገድ ይሠራል::*

3፥11 *የምናውቀውን (እኛ)፤* ሌሎችን እንደሚጨምር ያመለክታል፤ ምናልባትም ራሱን ከደቀ መዛሙርቱ ወይም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር፣ ከነቢያት፣ ወይም ከመጻሕፍት ቃል ጋር ቈጥሮ ሊሆን *ይችላል:: ምስክርነታችንን፤* የ1፥7 ማብ ይመ::

3፥13 *የሰው ልጅ፤* የ1፥51 ማብ ይመ::

3፥14 *የሰው ልጅም...ሊሰቀል ይገባዋል፤* የ12፥31-32 ማብ ይመ::

3፥15 *የሚያምን (በእርሱ)፤* የ1፥7 ማብ ይመ:: *የዘላለም ሕይወት፤* አሁንም ሆነ ወደፊት እጅግ የላቀና ወሰን የሌለውን የደስታ ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ነው:: የዘላለም ሕይወት ሲባል የአሁኑ ሕይወት ቀጣይ ሳይሆን፣ የዓይነት ለውጥ ማለት ነው::

3፥16 *እግዚአብሔር...ዓለምን ወዶአል፤* እግዚአብሔር ዓለምን ለማዳን የፈቀደበት ዋና ምክንያት ፍቅር ነው (ከ1ዮሐ 4፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ) *ዓለም፤* (የ1፥9 ማብ ይመ):: *አንድያ ልጅ፤* 1፥14:18 ይመ፤ ከዘፍ 22፥2:16፤ ከሮሜ 8፥32 ጋር ያነጻጽሩ:: አማኞች ‘የእግዚአብሔር ልጆች’ ተብለው ቢጠሩም (2 ቆሮ 6፥18፤ ራእ 21፥7)፣ የኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነት ግን የተለየ ነው:: *መስጠት (ልጁን)፤* ኢሳ 9፥6 ይመ::

3፥18 *የሚያምን...የማያምን፤* ዮሐንስ በዚህ ላይ የሚያመለክተው የዕለት ደራሹን እምነትንና ጥርጣሬን ሳይሆን የዘለቄ

በእግዚአብሔር ልጅ ስም[ነ] ስላላመነ፣ አሁኑኑ
ተፈርዶበታል:: 19ፍርዱም ይህ ነው፤ ብርሃን
ወደ ዓለም መጣ፤ ሰዎች ግን ሥራቸው ክፉ
ስለ ነበረ፣ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ፤
20ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላል፤
አድራጎቱም እንዳይገለጥበት ወደ ብርሃን
አይመጣም:: 21በእውነት የሚመላለስ ግን
ሥራው በእግዚአብሔር የተሠራ መሆኑ በግልጽ
ይታይ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል::"[ኘ]

## መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ መሰከረ

22ከዚህ በኋላ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ
ወደ ይሁዳ አገር ሄዱ፤ እዚያም ከእነርሱ ጋር
ጥቂት ተቀመጠ፤ አጠመቀም::
23በዚህ ጊዜ ዮሐንስም በሳሌም አቅራቢያ
ሄኖን በተባለ ስፍራ ብዙ ውሃ ስለ ነበረ፣
ያጠምቅ ነበር፤ ሰዎችም ለመጠመቅ ይመጡ
ነበር:: 24ይህም የሆነው ዮሐንስ ከመታሰሩ
በፊት ነበር:: 25በአንዳንድ የዮሐንስ ደቀ
መዛሙርትና በአንድ አይሁዳዊ[አ] መካከል
ስለ መንጻት ሥርዐት ክርክር ተነሣ፤ 26ወደ
ዮሐንስም መጥተው፣ "ረቢ፤ በዮርዳኖስ ማዶ
ከአንተ ጋር የነበረው፣ ስለ እርሱም የመሰከ
ርህለት ሰው፣ እነሆ ያጠምቃል፤ ሰውም
ሁሉ ወደ እርሱ እየሄደ ነው" አሉት::
27ዮሐንስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ከላይ
ካልተሰጠው በቀር ማንም አንዳች ሊቀበል
አይችልም:: 28'እኔ ክርስቶስ[ከ] አይደለሁም፤
ነገር ግን ከእርሱ በፊት ተልኬአለሁ' እን
ዳልሁ እናንተ ራሳችሁ ትመሰክሩላችሁ::
29ሙሽራዪቱ የሙሽራው ናት፤ ድምፁን ለመ
ስማት በአጠገቡ የሚቆመው ሚዜ ግን፣ የሙሽ
ራውን ድምፅ ሲሰማ እጅግ ደስ ይለዋል፤ ያ
ደስታ የእኔ ነው፤ እርሱም አሁን ተፈጽሞአል::
30እርሱ ሊልቅ፣ እኔ ግን ላንስ ይገባል::
31"ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤
ከምድር የሆነው የምድር ነው፤ የምድሩንም
ይናገራል:: ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ
ነው፤ 32ያየውንና የሰማውን ይመሰክራል፤ ነገር
ግን ምስክርነቱን ማንም አይቀበልም፤ 33ምስክ
ርነቱንም የተቀበለ ሰው፣ እግዚአብሔር እውነተኛ
እንደ ሆነ አረጋገጠ:: 34እግዚአብሔር[ኸ] መንፈሱን
ሳይሰፍር ስለሚሰጥ፣ እግዚአብሔር የላከው
የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል:: 35አብ ወልድን
ይወዳል፤ ሁሉንም ነገር በእጁ ሰጥቶታል::
36በወልድ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት
አለው፤ በወልድ የማያምን ግን የእግዚአብሔር
ቍጣ በላዩ ይሆናል እንጂ ሕይወትን አያ
ይም::"[ወ]

## ኢየሱስ ከአንዲት ሳምራዊት ጋር ተነጋገረ

4 ፈሪሳውያን ከዮሐንስ ይልቅ ኢየሱስ ብዙ
ደቀ መዛሙርትን እንዳፈራና እንዳጠመቀ
ሰሙ፤ 2ዳሩ ግን ያጠመቀው ኢየሱስ ሳይሆን
ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ:: 3ጌታም ይህን እን
ዳወቀ ይሁዳን ለቆ ወደ ገሊላ ተመልሶ ሄደ::

3፥18 ዮሐ1፥18፤ 5፥24፤1ዮሐ4፥9
3፥19 መዝ52፥3፤ ዮሐ1፥4፤ዮሐ7፥7
3፥20 ኤፌ5፥11፡13
3፥22 ዮሐ4፥2
3፥23 ማቴ3፥1
3፥24 ማቴ4፥12፤ 14፥3
3፥25 ዮሐ2፥6
3፥26 ማቴ23፥7፤ ዮሐ1፥7
3፥28 ዮሐ1፥20፡23
3፥29 ማቴ9፥15፤ ዮሐ16፥24፤17፥13፤ ፊል2፥2፤ 1ዮሐ1፥4፤ 2ዮሐ12
3፥31 ቍ13፤ ዮሐ8፥23፤1ዮሐ4፥5
3፥32 ቍ11፤ ዮሐ8፥26፤15፥15
3፥34 ቍ17፤ ኢሳ42፥1፤ማቴ 12፥18፤ሉቃ4፥18፤ ሐሥ 10፥38
3፥35 ማቴ28፥18
3፥36 ቍ15፤ ዮሐ5፥24፤6፥47
4፥1 ዮሐ3፥22፡26
4፥3 ሉቃ7፥13፤ ዮሐ3፥22

[ነ]18 ወይም *በእግዚአብሔር አንድያ ልጅ*
[ኘ]21 አንዳንድ ተርጓሚዎች ትምህርተ ጥቅሱን ከቍጥር 15 በኋላ ያደርጋሉ
[አ]25 አንዳንድ ቅጆች *አንዳንድ አይሁድ* ይላሉ
[ከ]28 ወይም *መሲሕ*
[ኸ]34 በግሪኩ *እርሱ* ይላል
[ወ]36 አንዳንድ ተርጓሚዎች ትምእርተ ጥቅሱን ከ30 በኋላ ያደርጋሉ::

ታውን የልብ ሚዛን መረጋጋት ነው::

3፥22 *አጠመቀ*፤ በእርሱ ሥልጣንና ፈቃድ ማለት እንጂ፣ በ4፥2 መሠረት ያጠመቁት ደቀ መዛሙርቱ ብቻ ናቸው::

3፥23 *ሄኖን*፤ ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ ከስካይቶፖሊስ (ቤተ ሳን) በስተ ደቡብ በኩል ዐሥራ ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ላይ የሚገኝ ስፍራ ሳይሆን አይቀርም::

3፥25 *ስለ መንጻት ሥርዐት ክርክር*፤ የሙት ባሕር (የቁምራን) ጥቅልል የብራና ጽሑፎች እንደሚያሳዩት፣ አንዳንድ አይሁድ የመንጻቱን ሥርዐት በትክክለኛ መንገድ ለመፈጸም ልዩ ፍላጎት ነበራቸው::

3፥26 *የመሰከርህለት*፤ የ1፥7 ማብ ይመ:: ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ እንደ መሰከረ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ያውቃሉ፤ ቢሆንም መምህራቸውን ስለሚወዱ፣ በኢየሱስ ሥራ መሳካት ቅናት አድሮባቸው ነበር::

3፥27፤ በዚህ ጥቅስ ያለው ሐሳብ፣ ኢየሱስን ወይም ዮሐንስን ወይም ማንኛውንም ሰው ሊመለከት ይችላል:: *ካልተሰጠው*፤ 'መስጠት' የሚለው ሐሳብ በዚህ ወንጌል ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል፤ በተለይ አብ ለወልድ ከሰጣቸው ነገሮች አንጻር ተደጋግሞ ይገኛል::

3፥29 *ሙሽራው*፤ በጋብቻ ሥርዐት ዋነኛው ሰው ሙሽራው እንደ ሆነ ሁሉ፣ በዚህም ክፍል 'ሙሽራው'፣ የተባለው ኢየሱስ ነው:: ጓደኛ (ሚዜ) ከሙሽራው ጋር አብሮ የሚሆነው ለማገልገል ብቻ ነው፤ የመጥምቁ ዮሐንስ ድርሻም ይኸው ነው:: *እጅግ ደስ ይለዋል*፤ ደስታው፣ ራሱ ሚዜ በመሆኑ ሳይሆን፣ የሙሽራው በዚያ መገኘት ነው:: የዮሐንስም ደስታ የኢየሱስ ተልእኮ ሲሳካ መስማቱ ነበር::

3፥30 መጥምቁ ዮሐንስ የተላከው የመሲሑን መንገድ ለመጥረግ ስለ ነበር፣ እርሱ አገልጋይ እንጂ ዋና አለመሆኑን በድጋሚ ያረጋግጣል::

3፥31 *ከላይ የሚመጣው*፤ 'ኢየሱስ ከምድር ሳይሆን ከሰማይ ነው' የሚለው ሐሳብ ለዮሐንስ ጥልቅ ምስጢር ነበረው:: (ከ1 ቆሮ 15፥47 ጋር ያነጻጽሩ):: *ከምድር የሆነው*፤ ማንኛውንም ሰው የሚያመለክት የወል አገላለጽ ነው፤ እዚህ ላይ ግን የሚያመለክተው በተለይ መጥምቁ ዮሐንስን ነው:: የዚህ ቍጥር ሐሳብ ከቍጥር 13 ጋር የተያያዘ ነው::

3፥32 *ያየውንና የሰማውን*፤ ኢየሱስ ያስተማረው መለኮታዊ ዕውቀቱን መሠረት አድርጎ ነው:: *ማንም*፤ የተናገረውን የተቀበለ አንድም ሰው አልነበረም ማለት ሳይሆን (ቍ 33)፣ አብዛኛው ሕዝብ በጥቅሉ እምቢተኛ ነበር ለማለት ነው::

3፥33 *አረጋገጠ*፤ ማንም ሰው የክርስቶስን ምስክርነት ሲቀበል፣ ኢየሱስ ከሰማይ መውረዱንና እግዚአብሔርም ዓለምን ለማዳን በእርሱ ሆኖ መሥራቱን ያምናል፤ ልጁን እንደ ላከ በማመኑም እግዚአብሔር እውነተኛ እንደ ሆነ ያረጋግጣል::


3፥34 *ሳይሰፍር*፤ አንዳንዶች መንፈስ ቅዱስ በምልዓት የተሰጠው ለኢየሱስ ብቻ ነው ሲሉ፣ ሌሎች ግን መንፈስ ቅዱስ ያለ ገደብ ለክርስቲያኖች በክርስቶስ መስጠቱን ነው ይላሉ:: *እግዚአብሔር የላከው*፤ ኢየሱስን ማለቱ ነው::

3፥36 *አለው*፤ ዘላለማዊ ሕይወት ከሞት በኋላ ብቻ ሳይሆን በሕይወት እያሉም እውን የሚሆን ነገር ነው (የቍ 15 ማብ ይመ):: *የእግዚአብሔር ቍጣ*፤ እግዚአብሔር ክፉ የሆነውን ሁሉ እንደሚቃወም የሚያመለክት ጠንካራ አገላለጽ ነው:: 'ቍጣ' የሚለው ቃል በዮሐንስ ወንጌል በዚህ አገላለጽ የሚገኘው በዚሁ ቦታ ብቻ ነው (የሮሜ 1፥18 ማብ ይመ):: *በላዩ ይሆናል*፤ ኀጢአተኛ፣ የእግዚአብሔር ቍጣ ሲዘገይ፣ ያለ አንዳች ማስተሰረያ ሲቈይ ይበርዳል ብሎ መታለል የለበትም፤ እግዚአብሔር ርኵሰትን የሚጠላው ፈጽሞ ለዘለቄታው ነውና::

4፥1 *ፈሪሳውያን*፤ እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች ቀደም ሲል ዮሐንስን፣ በኋላም ኢየሱስን ለማጥመድ በጥብቅ ይከታተሉት ነበር (የ1፥24 ማብ ይመ)::

*4፥2፤* ኢየሱስ ሳይፈቅድ ሐዋርያት አላጠመቁም ነበር (3፥22)::

4፥3 *ይሁዳን ለቆ...ሄደ*፤ ኢየሱስ ይሁዳን ትቶ የሄደው ሥራው ባለመሳካቱ ሳይሆን፣ የሥራው መሳካት ተቃውሞ የሚያስነሣ መሆኑን በማወቁ (7፥1)፣ ለመጋፈጥም ጊዜው ስላልደረሰ ነው::



የሜድትራንያን ባሕር
ጼጤሌማይስ
ኢየሱስ በይሁዳና በሰማርያ
ገሊላ
ቅፍርናሆም
የገሊላ ባሕር
ጥብርያዶስ
ቃና
ናዝሬት
ታቦር ተራራ
የርሙክ ወንዝ
ናይን
የርዳኖስ ወንዝ
ቤትሻን
ቂሣርያ
በአዲስ ኪዳን ዘመን በይሁዳ ዋነኛ ወደብ
ሰማርያ
ፔላ
ሳሌም
ሄኖን
መጥምቁ ዮሐንስ በዚህ አካባቢ ያጠምቅ ነበር (ዮሐ 3:23)፡ ምናልባትም አገልግሎቱን ያካሄድ የነበረው እዚሁ አካባቢ ነው።
በያዕቆብ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ኢየሱስ ከሰማርያዋ ሴት ጋር ተነጋገረ(ዮሐ 4:5)።
ሰማርያ
ያቦቅ ወንዝ
የገሪዛን ተራራ
ሲካር
በውሃው ጉድጓድ አጠገብ በነበረችው የሰማርያ ሴት እንደተገለጸው ይህ ተራራ ለሰማርያ ሰዎች የአምልኮ ማዕከላቸው ነበር (ዮሐ 4:20-23)።
ይሁዳ
የርዳኖስ ወንዝ
ፔሪያ
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዋነኛ ከተማ ስትሆን በትንቢት እንደተነገረው ኢየሱስ በዚሁ ከተማ ተሰቀለ (ማቴ 16:21፤ማር10:33፤ ሉቃ 18:31)።
ከትንሣኤ በኋላ ኢየሱስ ወደ ኤማሁስ ይጓዙ ለነበሩ ሁለት ሰዎች ተገለጠ፤ ከእነርሱም ጋር በላ (ሉቃ 24:13)።
ኢያሪኮ
በዚህ ከተማ ኢየሱስ ዐይነ ሥውሩን ፈወሰ (ማቴ 20:29፤ እንዲሁም ዘኬዎስን ከዛፍ ላይ እንዲወርድ ጠራው (ሉቃ 19:1) ደጉ ሳምራዊው በመንገድ የወደቀውን ሰው የረዳው በዚሁ ጎዳና ላይ ነው (ሉቃ 10:30)።
ኤማሁስ
ኢየሩሳሌም
ቢታንያ
ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት አስነሣ (ዮሐ 11:43-44)፤በዚሁ ከተማ ኢየሱስ በለምጻሙ ስምዖን ቤት ሳለ ሽቱ ተቀባ (ማቴ 26:6)፡ ወደ አባቱ ያረገውም ከዚሁ ቦታ ነበር (ሉቃ 24:50-51)።
ቤተልሔም
የኢየሱስ የትውልድ ስፍራ (ማቴ 2:1፤ ሉቃ 2:4)
ሙት ባሕር
መቃሪየስ
የአርኖን ወንዝ
ማይልስ 5 0 10 20
ኪ.ሜ 5 0 10 20 30

4በሰማርያም በኩል ማለፍ ነበረበት:: 5ስለ
ዚህ በሰማርያ፣ ያዕቆብ ለልጁ ለዮሴፍ በሰጠው
ቦታ አጠገብ ወደ ነበረች፣ ሲካር ወደምትባል
ከተማ መጣ:: 6በዚያም የያዕቆብ የውሃ
ጒድጓድ ነበረ፤ ኢየሱስም ከጒዞው የተነሣ
ደክሞት ስለ ነበር በውሃው ጒድጓድ አጠ
ገብ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ከቀኑ ስድስት ሰዓት
አካባቢ ነበር::
7አንዲት ሳምራዊት ሴት ውሃ ለመቅዳት
ስትመጣ ኢየሱስ፣ "እባክሽ የምጠጣው ስጪኝ"
አላት፤ 8ደቀ መዛሙርቱ ምግብ ለመግዛት
ወደ ከተማ ሄደው ነበር::
9ሳምራዊቷም፣ "አንተ አይሁዳዊ ሆነህ፣
እኔን ሳምራዊቷን እንዴት ውሃ አጠጪኝ
ትላለህ?" አለችው፤ ይህን ማለቷ አይሁድ
ከሳምራውያን ጋር ስለማይተባበሩ ነው::[o]
10ኢየሱስም፣ "የእግዚአብሔርን ስጦታ ብታ
ውቂና ውሃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑን
ብትረጂ ኖሮ፣ አንቺው በጠየቅሽው፣ እር
ሱም የሕይወትን ውሃ በሰጠሽ ነበር" ሲል
መለሰላት::
11ሴትዮዋም እንዲህ አለችው፤ "ጌታዬ፣
መቅጃ የለህም፤ ጒድጓዱም ጥልቅ ነው፤ ታዲያ
ይህን የሕይወት ውሃ ከየት ታገኛለህ?
12ለመሆኑ አንተ፣ ይህን ጒድጓድ ከሰጠን፣
ከአባታችን ከያዕቆብ ትበልጣለህን? እርሱ
ራሱና ልጆቹ፣ እንስሳቱም ከዚሁ ጒድጓድ
ጠጥተዋል::"
13ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላት፤ "ከዚህ
ውሃ የሚጠጣ እንደ ገና ይጠማል፤ 14እኔ
ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ግን ከቶ አይጠ
ማም፤ እኔ የምሰጠው ውሃ በውስጡ የሚፈልቅ
የዘላለም ሕይወት ውሃ ምንጭ ይሆናል::"
15ሴትዮዋም፣ "ጌታዬ፤ እንዳልጠማና ውሃ
ለመቅዳት እንዳልመላለስ፣ እባክህ ይህን ውሃ
ስጠኝ" አለችው::
16እርሱም፣ "ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደ
ዚህ ተመለሽ" አላት::
17ሴትዮዋም፣ "ባል የለኝም" ብላ መለሰች::
ኢየሱስም፣ እንዲህ አላት፤ "ባል የለኝም
ማለትሽ ትክክል ነው፤ 18በእርግጥ አምስት
ባሎች ነበሩሽ፤ አሁን ከአንቺ ጋር ያለውም
ባልሽ ስላልሆነ፣ የተናገርሽው እውነት ነው::"
19ሴትዮዋም እንዲህ አለችው፤ "ጌታዬ፣
አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ፤ 20አባቶ
ቻችን በዚህ ተራራ ላይ ሰገዱ፤ እናንተ
አይሁድ ግን ሰው መስገድ ያለበት በኢየሩ
ሳሌም ነው ትላላችሁ" አለችው::
21ኢየሱስም እንዲህ አላት፤ "አንቺ ሴት፤
በዚህ ተራራም ሆነ በኢየሩሳሌም ለአብ የማ
ትሰግዱበት ጊዜ እንደሚመጣ እመኚኝ::
22እናንተ ሳምራውያን ለማታውቁት ትሰግዳ
ላችሁ፤ እኛ ግን ድነት ከአይሁድ ስለ ሆነ
ለምናውቀው እንሰግዳለን:: 23በእውነት የሚ
ሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግ
ዱበት ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም መጥቶአል፤
አብም እንደዚህ በእውነት የሚሰግዱለትን
ይፈልጋል:: 24እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤
የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰ
ግዱለት ይገባል::"

4፥4 ማቴ10፥5
4፥5 ዘፍ33፥19፤ ኢሱ24፥32
4፥7 ዘፍ24፥17፤ 1ነገ17፥10
4፥8 ቁ5:39
4፥9 ማቴ10፥5
4፥10 ኢሳ44፥3፤ 55፥1፤ ኤር2፥13፤ 17፥13፤ ዘካ14፥8፤ ዮሐ7፥37:38፤ ራእ7፥17፤21፥6፤ 22፥1:17
4፥12 ቁ6
4፥14 ኢሳ12፥3፤ 58፥11፤ማቴ25፥46፤ ዮሐ6፥35፤7፥38
4፥15 ዮሐ6፥34
4፥19 ማቴ21፥11
4፥20 ዘዳ11፥29፤ ኢሱ8፥33፤ሉቃ9፥53
4፥21 ሚል1፥11፤ ዮሐ5፥28፤16፥2፤ 1ጢሞ 2፥8
4፥22 2ነገ17፥28-41፤ኢሳ2፥3፤ ሮሜ3፥1:2፤9፥4:5፤ 15፥8:9
4፥23 ዮሐ5፥25፤ 16፥32፤ፊል3፥3
4፥24 ፊል3፥3

[o]9 *ወይም ሳምራውያን በተጠቀሙበት ሰሐን/ዕቃ አይጠቀሙም ነበር*

4፥4 *ሰማርያ*፤ ስሙ የሚያመለክተው ከተማዋን ብቻ ሳይሆን ክፍለ አገሩን ጭምር ነው:: አይሁድ ዮርዳኖስን ተሻግረው በምሥራቅ በኩል በማለፍ ሰማርያን ሳይረግጡ መጓዝን ያዘወትሩ ነበር (የማቴ 10፥5፤ የሉቃ 9፥52 ማብ ይመ):: *ማለፍ ነበረበት*፤ ከቦታው አቀማመጥ ሳይሆን ከኢየሱስ ተልእኮ አንጻር የተነገረ ነው::

4፥5 *ሲካር*፤ ሴኬም አጠገብ የምትገኝ አነስተኛ መንደር ነበረች፤ በሴኬም አካባቢ ያዕቆብ ትንሽ መሬት ገዝቶ ነበር (ዘፍ 33፥18-19)፤ ለዮሴፍ የሰጠውም ይህንኑ መሬት ነው (ዘፍ 48፥21-22)::

4፥6 *የያዕቆብ የውሃ ጒድጓድ*፤ ከዚህ ክፍል ውጪ በመ ጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ቦታ አልተጠቀሰም::

4፥7 *ውሃ ለመቅዳት*፤ ሰዎች ውሃ የሚቀዱት በጠራራ ፀሐይ ሳይሆን ጀምበር ስታቈለቍል ነበር (ዘፍ 24፥11 እና ማብ ይመ)::

4፥9 አይሁድ፣ ሳምራውያን ሁሉ ርኩሳን ናቸው ብለው ስለሚያምኑ፣ ሳምራዊ በነካው ዕቃ መጠጣት በሥርዐታቸው መሠረት የተከለከለ ነበር::

4፥10 *ስጦታ*፤ ይህ ቃል በግሪኩ ቋንቋ በዚህ ወንጌል ውስጥ የተጠቀሰው እዚህ ቦታ ብቻ ሲሆን፣ በክርስቶስ የሚገኘውን የእግዚአብሔር ጸጋ በሚገባ ያሳያል:: ኢየሱስ ሕይወትን ሰጥቶናል፤ ዋጋም አይከፈልበትም:: *የሕይወት ውሃ*፤ በ7፥38-39 መንፈስ ቅዱስ ነው ተብሎ ሐሳቡ ተተርጒሟል፤ በዚ ህ ላይ የሚያመለክተው ግን የዘላለምን ሕይወት ነው (ቍ 14)::

4፥11 *ጥልቅ*፤ በተጠቀሰው አካባቢ፣ አንድ መቶ ጫማ ያህል ጥልቀት ያለው የውሃ ጒድጓድ እንደ ነበር፣ ከአራተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ያሉ የክርስቲያኖች የጒዞ ጽሑፎች ያሳያሉ:: ይህ ጒድጓድ እ.ኤ.አ በ1935 ሲጠረግ 138 ጫማ የሚሆን ጥልቀት እንዳለው ታውቋል::

4፥12 *ከአባታችን ከያዕቆብ*፤ ሳለፈው ታሪክ ያላት ከፍተኛ አክብሮት የዛሬውን ትልቅ ዕድል እንዳታስተውል ጋርዷታል::

4፥14 *የሚፈልቅ*፤ አገላለጹ የውሃው አመጣጥ በኀይል መሆኑን ሲያሳይ፣ መዝለል የሚለውን ትርጒም ያዘለ ነው:: እዚህ ላይ ኢየሱስ የተናገረው ኀይልና ሙላት ስላለው ሕይወት ነው (ከ10፥10 ጋር ያነጻጽሩ)::

*4፥15*፤ ይህን ሐሳብ ከኒቆዲሞስ አለመረዳት ጋር ያነጻጽሩ (3፥4)፤ በሁለቱም ሰዎች ሁኔታ ሰፋ ላለ ትምህርት በር ተከፍቷል::

4፥18 *አምስት ባሎች*፤ አይሁድ በሥርዐታቸው፣ አንዲት ሴት ሁለት ጊዜ፣ ግፋ ቢልም ሦስት ጊዜ አግብታ መፍታት ትችላለች ብለው ያምኑ ነበር፤ ሳምራውያንም ተመሳሳይ ሥርዐ ትን የሚቀበሉ ከሆነ፣ ሴትዮዋ ከልክ በላይ ምግባረ ብልሹ ነበረች ማለት ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ በዚህ ጊዜ አብሯት ያለው ሰው ባሏ አልነበረም::

4፥19 *ነቢይ*፤ ምስጢርን በማወቁ ነው::

4፥20 *በዚህ ተራራ*፤ ሴትዮዋ የተከራከረችው የንግግሩ አዝማሚያ ደስ ስላላላት ሊሆን ይችላል:: አይሁድና ሳምራውያን ትክክለኛውን የማምለኪያ ቦታ በተመለከተ ይከራከሩ ነበር፤ ሳም ራውያን፣ 'ይህ ተራራ' (ገሪዛን) የተቀደሰ ነው ብለው ያምናሉ፤ አብርሃምና ያዕቆብ በዚህ አካባቢ መሠዊያ ሠርተው ነበር (ዘፍ 12፥7፤ 33፥20):: ሕዝቡም በዚህ ተራራ ላይ ተባርኮ ነበር (ዘዳ 11፥29፤ 27፥12):: በሳምራውያን ቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት፣ ሙሴ መሠዊያ እንዲሠራ የታዘዘው በጌባል ተራራ ሳይሆን በገሪዛን ተራራ ላይ ነው (ዘዳ 27፥4-6):: ሳምራውያን በ400 ዓ. ቅ.ክ አካባቢ በገሪዛን ተራራ ላይ ቤተ መቅደስ ሠርተው ነበር፤ አይሁድ ግን ይህን ቤተ መቅደስ በ128 ዓ.ቅ.ክ አወደሙት:: ስለዚህ እነዚህ ሁለቱ ድርጊቶች በሁለቱ ወገኖች መካከል የነበ ረውን አለመጣጣም አባብሰውታል::

4፥22 *ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ*፤ የሳምራውያን መጽሐፍ ቅዱስ አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት ብቻ የያዘ ነው:: እውነተኛውን አምላክ ያመልካሉ፤ ሙሉ ቃሉን አለመቀበላቸው ግን እግዚአ ብሔርን የሚያውቁት በጥቂቱ መሆኑን ያመለክታል:: *ድነት ከአይሁድ ስለ ሆነ*፤ መሲሑ ከአይሁድ ወገን መሆኑን ያመለ ክታል:: የመጀመሪያዎቹ የቃሉ መልእክተኞችም አይሁድ ነበሩ::

4፥24 *እግዚአብሔር መንፈስ ነው...በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል*፤ ትክክለኛው አምልኮ መንፈስ ከሆነው

[25]ሴትዮዋም፣ "ክርስቶስ የተባለ መሲሕ እን
ደሚመጣ ዐውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን
ነገር ይነግረናል" አለችው።
[26]ኢየሱስም፣ "የማነጋግርሽ እኮ እኔ እርሱ
ነኝ" ሲል ገልጦ ነገራት።

### ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው መጡ

[27]በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው
መጡ፤ ከሴት ጋር ሲነጋገር በማግኘታቸው
ተደነቁ፤ ሆኖም ግን፤ "ምን ፈለግህ?" ወይም፣
"ከእርሷ ጋር የምትነጋገረው ለምንድን ነው?"
ብሎ የጠየቀው ማንም አልነበረም።
[28]ሴትዮዋም እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ
ተመለሰች፤ ለሕዝቡም፣ [29]"ያደረግሁትን ሁሉ
የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እርሱ ክርስቶስ"
ይሆን እንዴ?" አለች፤ [30]እነርሱም ከከተማ
ወጥተው እርሱ ወዳለበት አመሩ።
[31]በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ፣ "ረቢ፣ እህል
ቅመስ እንጂ" አሉት።
[32]እርሱ ግን፣ "እናንተ የማታውቁት፣ የም
በላው ምግብ አለኝ" አላቸው።
[33]ደቀ መዛሙርቱም፣ "ሰው ምግብ አምጥ
ቶለት ይሆን እንዴ?" ተባባሉ።
[34]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "የእኔ ምግብ
የላከኝን ፈቃድ ማድረግና ሥራውን መፈ
ጸም ነው፤ [35]እናንተ፣ 'ከአራት ወር በኋላ
መከር ይደርሳል' ትሉ የለምን? እነሆ፣ አዝ
መራው ለመከር እንደ ደረሰ ቀና ብላችሁ
ማሳውን ተመልከቱ እላችኋለሁ። [36]አጫጁ
አሁንም ቢሆን እንኳ ደመወዙን የተቀበለ
ነው፤ ለዘላለም ሕይወት ይሆን ዘንድ አዝ
መራውን ይሰበስባል፤ ይህም ዘሪውና አጫጁ
በጋራ ደስ እንዲላቸው ነው። [37]ስለዚህ፣
'አንዱ ይዘራል፤ ሌላውም ያጭዳል' የተባለው
ምሳሌ እውነት ነው። [38]ያልደከማችሁበትን
እንድታጭዱ ላክኋችሁ፤ አድካሚውን ሥራ
ሌሎች ሠሩ፤ እናንተም የድካማቸውን ፍሬ
ሰበሰባችሁ።"

### ብዙ ሳምራውያን አመኑ

[39]ሴትዮዋ፣ "ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ" ብላ
ስለ መሰከረች፣ ከዚያች ከተማ ብዙ ሳምራ
ውያን በእርሱ አመኑ። [40]ስለዚህ፣ ሳምራውያኑ
ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ አብሮአቸው እንዲ
ቈይ አጥብቀው ለመኑት፤ እዚያም ሁለት
ቀን ቈየ። [41]ከቃሉም የተነሣ ሌሎች ብዙዎች
አመኑ።
[42]ሴትዮዋንም፣ "ከእንግዲህ የምናምነው
አንቺ ስለ ነገርሽን ብቻ አይደለም፤ እኛ ራሳ
ችን ሰምተነዋል፤ ይህ ሰው በእውነት የዓለም
አዳኝ እንደ ሆነ እናውቃለን" አሏት።

### ኢየሱስ የሹሙን ልጅ ፈወሰ

[43]ከሁለቱ ቀናት በኋላም ወደ ገሊላ ሄደ፤
[44]ነቢይ በገዛ አገሩ እንደማይከበር ኢየሱስ
ራሱ ተናግሮ ነበርና። [45]ገሊላ እንደ ደረሰም
የገሊላ ሰዎች በደስታ ተቀበሉት፤ ምክንያ
ቱም፣ እነርሱም በፋሲካ በዓል ኢየሩሳሌም
ስለ ነበሩና በዚያ ያደረገውን ሁሉ ስላዩ ነው።

4፥25 ማቴ1፥16፤ ዮሐ1፥41
4፥26 ዮሐ8፥24፤ 9፥35-37
4፥27 ቍ8
4፥29 ቍ17፡18፤ ማቴ12፥23፤ ዮሐ7፥26፡31
4፥31 ማቴ23፥7
4፥32 ኢዮ23፥12፤ ማቴ4፥4፤ዮሐ 6፥27
4፥34 ማቴ26፥39፤ ዮሐ19፥30
4፥35 ማቴ9፥37፤ ሉቃ10፥2
4፥36 ማቴ25፥46፤ ሮሜ1፥13
4፥37 ኢዮ31፥8፤ ሚክ6፥15
4፥39 ቍ5:29
4፥42 ሉቃ2፥11
4፥43 ቍ40
4፥44 ማቴ13፥57፤ሉቃ4፥24
4፥45 ዮሐ2፥23

"29 ወይም *መሲሕ*

ከእግዚአብሔር ባሕርይ ጋር የተያያዘ ነው፤ በዚህም ምክንያት የማምለኪያው ቦታ ወሳኝነት የለውም። በዮሐንስ ወንጌል፣ እውነት ከክርስቶስ ጋር የተሳሰረ ነው (14፥6 እና የ1፥14 ማብ ይመ)። ትክክለኛውን የክርስቲያን አምልኮ ለማስተዋልም ይህ እውነታ ዐቢይ ድርሻ አለው።

4፥25 *መሲሕ...ሁሉን ነገር ይነግረናል*፤ ይህ አነጋገርዋ፣ ሴትዮዋ ከዋናው ሐሳብ ለመሸሽ ስትል ያደረገችው የመጨረሻ ሙከራ ነበር። በእርሷ አመለካከት፣ ለእግዚአብሔር የመስገዱ ነገር ታላቅ ስለ ሆነ ጉዳዩን ማንሣት የመሲሑ ድርሻ እንጂ የእርሷ የኢየሱስ እንዳልሆነ ቈጥራለች። ሁሉንም ነገር ለመረዳት መሲሑ መምጣት ነበረበት (የ1፥25 ማብ ይመ)። ሳምራውያን የመሲሑን መምጣት ያምኑ ነበር፤ ከአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ውጪ ሌሎቹን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አለ መቀበላቸው፣ ስለ መሲሑ የሚያውቁት ነገር እጅግ አነስተኛ መሆኑን ያመለክታል፤ መሲሑንም የሚያስቡት ይልቁን በመምህርነቱ ነበር።

4፥26 *እኔ እርሱ ነኝ*፤ ኢየሱስ ከመከሰሱ በፊት መሲሕ መሆኑን በግልጽ የተናገረው በዚህ ቦታ ላይ ብቻ ነው (ይሁን እንጂ ማር 9፥41 ይመ)። ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን በግልጽ መናገሩ በይሁዳ የነበረውን ከመሲሑ ጋር የተያያዘ የፖለቲካ ስሜት በሰማርያ ባለመኖሩ ሳይሆን አይቀርም።

4፥27 *ተደነቁ*፤ የአይሁድ የሃይማኖት መምህራን ከሴት ጋር በአደባባይ ስለማይነጋገሩ ነበር።

4፥29 *ያደረግሁትን ሁሉ*፤ የተጋነነ አነጋገር ቢሆንም፣ በኢየሱስ ምን ያህል እንደ ተገረመች ያሳያል። *እርሱ ክርስቶስ ይሆን እንዴ?* ጥያቄዋ ጕጕቷን የሚገልጽ ቢሆንም፣ ከሰዎቹ አዎንታዊ መልስ የሚጠበቅ አልነበረም።

*4፥33*፤ ሴትዮዋ እንዳላስተዋለች ሁሉ (ቍ15)፣ ደቀ መዛሙርቱም አላስተዋሉም።

4፥34 *የእኔ ምግብ የላከኝን ፈቃድ ማድረግ...ነው*፤ ኢየሱስ በአባቱ ፈቃድ መሠረት እንደሚሠራና የላከውን የአባቱን ተግባር እንደሚያከናውን ዮሐንስ ብዙ ጊዜ ያመለክታል (ለምሳሌ:- 5፥30፤ 6፥38፤ 8፥26፤ 9፥4፤ 10፥37-38፤ 12፥49-50፤ 14፥31፤ 15፥10፤ 17፥4)።

4፥35 *ከአራት ወር በኋላ መከር ይደርሳል*፤ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፤ ይኸውም 'በአንድ ቀን ጀንበር፣ አይደርስም መከር' ከሚለው አባባል ጋር ይመሳሰላል። የተዘራ እህል እንዲታጨድና እንዲሰበሰብ ጊዜ ቢያስፈልገውም፣ ኢየሱስ ያመለከታቸው 'መከር' ግን የደረሰ ነበር።

4፥36 *ደመወዙን እየተቀበለ ነው*፤ ሥራው በሙሉ ወይም በከፊል ተከናውኖ ነበር፤ ሌሎችም በትጋት እየሠሩ ነው። ደቀ መዛሙርቱ መከሩ ገና አልደረሰም ብለው ማሰብ አልነበረባቸውም። ኢየሱስ የተናገረው በመስክ ላይ ስለ ነበረው መከር ሳይሆን፣ ስለ 'ዘላለም ሕይወት አዝመራ' ነው፤ መከሩ ጊዜ ስለማይሰጥ በጥድፊያ መሥራት አስፈላጊ ነበር። *በጋራ ደስ እንዲላቸው*፤ ታማኝ በሆኑ የክርስቶስ አገልጋዮች መካከል ፉክክር የለም፤ ዘሪውም ሆነ መከር ሰብሳቢው የአዝመራው ደስታ ተካፋይ ናቸውና።

*4፥37*፤ 1ቆሮ 3፥6-9 ይመ።

4፥38 *ሌሎች*፤ መጥምቁ ዮሐንስንና ረዳቶቹን ሊመለከት ይችላል፤ ሐዋርያትም የገነቡት በእነርሱ ሥራ ላይ ነው። ወይም ኢየሱስ እንዲህ ማለቱ ከእነዚህ አልፎ፣ የቀደሙትን ነቢያትንና ሌሎች መንፈሳውያን ሰዎችን ሊሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ የኢየሱስ ፍላጎት ሐዋርያት ዘሪዎችና መከር ሰብሳቢዎች እንዲሆኑ ነበር።

4፥42 *የዓለም መድኃኒት*፤ ይህ አገላለጽ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኘው በዚህ ቍጥርና በ1 ዮሐ 4፥14 ላይ ብቻ ነው፤ 1) ኢየሱስ አስተማሪ ብቻ ሳይሆን አዳኝም መሆኑን፣ 2) አዳኝነቱም መላውን ዓለም የሚያጠቃልል መሆኑን ያመለክታል (የዮሐ 3፥16 ማብ ይመ)።

4፥44 *ነቢይ በገዛ አገሩ እንደማይከበር*፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሄደ፤ ሰውን ሁሉ ለማዳን መጥቶአልና (ከ1፥29 ጋር ያነጻጽሩ)።

4፥45 *በደስታ ተቀበሉት*፤ የገሊላ ሰዎች የፈለጉት ታምራቱን ብቻ ስለ ሆነ፣ አቀባበላቸው ከእምነት የመነጨ አልነበረም፤ የተቀበሉት ሊያድናቸው የሚችለውን መሲሕ ሳይሆን፣ ታምር እየሠራ የሚያስደንቃቸውን ሰው ብቻ ነበር።

46ኢየሱስም ውሃውን የወይን ጠጅ ወዳደ
ረገበት፣ በገሊላ ወደምትገኘው ወደ ቃና ዳግ
መኛ መጣ፤ በቅፍርናሆምም ልጁ የታመ
መበት አንድ የቤተ መንግሥት ሹም ነበረ፤
47ይህም ሰው ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ
መምጣቱን በሰማ ጊዜ፣ ወደ እርሱ ሄደና
በሞት አፋፍ ላይ የነበረውን ልጁን መጥቶ
እንዲፈውስለት ለመነው::
48ኢየሱስም፣ "መቼውንም እናንተ ምልክቶ
ችንና ድንቅ ነገሮችን ካላያችሁ አታምኑም"
አለው::
49ሹሙም፣ "ጌታዬ፤ ልጄ ከመሞቱ በፊት
እባክህ ድረስልኝ" አለው::
50ኢየሱስም፣ "ልጅህ በሕይወት ይኖራልና
ሂድ" አለው::
ሰውዬውም ኢየሱስ የተናገረውን ቃል
አምኖ ሄደ፤ 51በመንገድ ላይ እንዳለም፣ አገል
ጋዮቹ አግኝተውት ልጁ በሕይወት መኖሩን
ነገሩት:: 52እርሱም ልጁ በስንት ሰዓት እንደ
ተሻለው ሲጠይቃቸው፣ "ትኩሳቱ የለቀቀው
ትናንት በሰባት ሰዓት ላይ ነው" አሉት::
53አባትየውም ሰዓቱ ኢየሱስ፣ "ልጅህ በሕ
ይወት ይኖራል" ያለበት ሰዓት መሆኑን ተገ
ነዘበ፤ እርሱና ቤተ ሰቡም ሁሉ አመኑ::
54ይህም፣ ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ መጥቶ
ያደረገው ሁለተኛው ታምራዊ ምልክት ነው::

### በቤተ ሳይዳ የተደረገው ፈውስ

5 ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበረ፤ ኢየሱስም
ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ:: 2በኢየሩሳሌም፣
በበጎች በር አጠገብ፣ አምስት ባለ መጠለያ
መመላለሻዎች የነበሯት፣ በአራማይክ ቋንቋ
ቤተ ሳይዳ[w] የተባለች አንዲት መጠመቂያ
አለች:: 3በእነዚህም መመላለሻዎች ውስጥ
ብዙ አካለ ስንኩላን፣ ዐይነ ስውሮች፣ አንካሶችና
ሽባዎች [የውሃውን መንቀሳቀስ እየተጠባበቁ፣
ይተኙ ነበር:: 4ዐልፎ ዐልፎ የጌታ መልአክ
ወርዶ ውሃውን በሚያናውጥበት ጊዜ፣ ቀድሞ
ወደ መጠመቂያዪቱ የገባ ካደረበት ማንኛ
ውም በሽታ ይፈወስ ነበር::][f] 5በዚያም ለሠላሳ
ስምንት ዓመት ሕመምተኛ ሆኖ የኖረ አንድ
ሰው ነበር:: 6ኢየሱስም ይህን ሰው ተኝቶ
ባገኘው ጊዜ፣ ለብዙ ጊዜ በዚህ ሁኔታ እንደ
ነበር ዐውቆ "ልትድን ትፈልጋለህን?" አለው::
7ሕመምተኛውም መለሰ፣ "ጌታዬ፣ ውሃው
በሚናወጥበት ጊዜ ወደ መጠመቂያዪቱ የሚ
ያወርደኝ ሰው የለኝም፤ ለመግባትም ስሞክር
ሌላው ይቀድመኛል" አለው::
8ኢየሱስም፣ "ተነሥ! መተኛህን ተሸከመህ
ሂድ" አለው:: 9ሰውዬውም ወዲያው ተፈወሰ፤
መተኛውንም ተሸክሞ ሄደ::
ይህም የሆነው በሰንበት ቀን ነበር:: 10አይ
ሁድም የተፈወሰውን ሰው፣ "ሰንበት ስለ
ሆነ መተኛህን እንድትሸከም ሕጉ አይፈቀ
ድልህም" አሉት::

4፥46 ዮሐ2፥1-11
4፥47 ቁ3:54
4፥48 ዳን4፥2:3፤ ዮሐ2፥11፤ሐሥ2፥43፤14፥3፤ሮሜ15፥19፤2ቆሮ12፥12፤ ዕብ2፥4
4፥53 ሐሥ11፥14
4፥54 ቁ48፤ ዮሐ 2፥11
5፥2 ነህ3፥1፤ 12፥39፤ዮሐ19፥13: 17:20፤20፥16፤ ሐሥ21፥40፤22፥2፤ 26፥14
5፥8 ማቴ9፥5:6
5፥9ማቴ12፥1-14፤ ዮሐ9፥14
5፥10 ቁ16፤ነህ 13፥15-22፤ኤር17፥21፤ማቴ12፥2

[w]2 አንዳንድ ቅጆች ቤተ ዛታ ሌሎች ቅጆች ቤተ ሳይዳ ይላሉ
[f]4 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ከቍ 3 የመጨረሻ ክፍል አንሥቶ እስከ ቍ 4 ድረስ ያለውን ክፍል አይጨምሩም

4፥46 *የቤተ መንግሥት ሹም፤* ከሄድሮስ የግቢ መኰንኖች አንዱ መሆን አለበት::

4፥48 *መቼውንም እናንተ ምልክቶችንና ድንቅ ነገሮችን ካላያችሁ አታምኑም፤* ይህን ያለው በተለይ መኰንኑን ሳይሆን፣ በአጠቃላይ የገሊላን ሰዎች ነው::

4፥50 *ልጅህ በሕይወት ይኖራል፤* የነቢይነት መልእክት ብቻ ሳይሆን፣ ኀይል ያለው ቃል ነው:: ኢየሱስ ይህን ቃል ሲናገር መልካም አጋጣሚ እንደሚመጣ መተንበዩ አይደለም፤ ነገር ግን ልጁ በዚያኑ ጊዜ የተፈወሰ መሆኑን መግለጹ ነበር (ቍ 51 እና 53 ይመ):: *አምኖ ሄደ፤* የዚህ ሹም ወደ ቤቱ መመለስ፣ ኢየሱስ ልጁን እንደሚፈውስለት ማመኑን ብቻ ሳይሆን፣ ታዛዥነቱንና የእምነቱን ጥንካሬ ያሳያል::

*4፥51፤* የቦታ ርቀት የጌታን የመፈወስ ኀይል አይወስነውም::

4፥53 *አመኑ፤* ከዚህ ወንጌል ዓላማ (20፥31) ጋር ያነጻጽሩ::

4፥54 *ሁለተኛው ታምራዊ ምልክት፤* በርግጥ እንደዚህ ያሉ ምልክቶች ከዚህ በፊት ነበሩ (2፥23፤ 3፥2)፤ ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ ከመጣ በኋላ ግን ታምር ሲያደርግ ይህ ሁለተኛው ጊዜ በመሆኑ ነው::

5፥1 *ከዚህ በኋላ፤* ጊዜው ምን ያህል እንደሆነ አይገልጽም፤ (ከ6፥1 እና ከ7፥1 ጋር ያነጻጽሩ):: *የአይሁድ በዓል፤* ምናልባት ወንድ አይሁዳዊ ሁሉ ቤተ መቅደሱ አለበት ቦታ ድረስ በመሄድ እንዲያከብራቸው ከተወሰኑት ከፋሲካ፣ ከጰንጠቆስጤ ወይም ከዳስ በዓል መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል:: በኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን ውስጥ የነበሩትን የፋሲካ በዓላት ቍጥር ለማወቅና የጌታም አገልግሎት ለምን ያህል ዘመን እንደ ነበር ለመረዳት፣ ይህ በዓል የትኛው እንደሆነ መለየቱ ጠቃሚ ነው:: ዮሐንስ ቢያንስ ሦስት የተለያዩ ፋሲካዎችን በግልጽ ይጠቅሳል፤ የመጀመሪያው በ2፥13:23 (የ2፥13 ማብ ይመ)፣ ሁለተኛው በ6፥4 ላይ ተጽፎ የሚገኘው ሲሆን፣ ሦስተኛው ብዙ ጊዜ ተጠቅሶአል (ለምሳሌ በ11፥55፤ በ12፥1):: ሦስቱን የፋሲካ በዓላት ማሳለፉ ከታወቀ፣ የኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን ከሁለት ተኩል እስከ ሦስት ዓመት ይደርሳል ማለት ነው:: በ5፥1 ላይ የተጠቀሰው በዓል አራተኛው ፋሲካ ከሆነ፣ ወይም አራተኛው ፋሲካ ማለፉን የሚያመለክት ከሆነ፣ የኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን ከሦስት እስከ አራት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ መሆኑን ያሳያል::

5፥2 *አለች፤* 'ነበረች' ሳይሆን 'አለች' የተባለበት ምክንያት ይህ መጽሐፍ በተጻፈበት ጊዜ ኩሬው ይገኝ ነበር ማለት ነው፤ ይህም ሁኔታ ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ከኢየሩሳሌም መጥፋት በፊት መሆኑን ያሳያል:: ይሁን እንጂ የተጻፈበትን ዘመን በትክክል አያመለክትም:: *ቤተ ሳይዳ፤* የጥንት ጽሑፎች የተለያዩ ስሞችን ይጠቅሳሉ፤ ከሙት ባሕር ጥቅልል የብራና ጽሑፎች አንዱ ግን ትክክለኛው ስም ቤተ ዛታ ነው ይላል:: ቦታው በአሁኑ ጊዜ ቅድስት ሐና ቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ (ኢየሩሳሌም) ያሉት መንታ ኩሬዎች የሚገኙበት ቦታ እንደ ሆነ ይታመናል:: በአራቱ ማዕዘናት አንዳንድ ዓምዶች፣ በሁለቱ ኩሬዎች መካከል አንድ ዓምድ ሳይተከል አልቀረም::

*5፥3-4፤* ቍ 3 በከፊልና ቍ 4 በጥንት ቅጂዎች ሳይሆን፣ በኋለኞች ቅጂዎች የተገኘ ነው::

5፥5 *ሕመምተኛ፤* ዮሐንስ የሕመሙን ዓይነት አልገለጸም፤ ነገር ግን የሰውነትን በድን መሆን ሊያመለክት ይችላል፤ መለስተኛ ነው ከተባለም ሽባነት ቢሆን ነው::

5፥6 *ልትድን ትፈልጋለህ?* ሰውዬው ኢየሱስን እንዲያድነው ባይጠይቀውም፣ ይህ ጥያቄ አስፈላጊ ነበር:: ምክንያቱም በዚያ ጊዜ የነበረ ለማኝ ቢፈወስ በቀላሉ የሚያገኘውን ገቢ ስለሚያጣ፣ ወይም ሰውዬው የመዳን ተስፋው ስለ ተሟጠጠበት ሊሆን ይችላል::

5፥7 *ውሃው በሚናወጥበት ጊዜ፤* በሽተኛው ኢየሱስ አዳኝ ሊሆን ይችላል ብሎ ስላልገመተ ልቡን የጣለው ያድናል ተብሎ በሚታመነው ውሃ ላይ ነበር::

5፥9 *ሰውዬውም...ተፈወሰ፤* አንድ ሰው ከበሽታ ለመፈወስ አስቀድሞ በኢየሱስ ማመን ያስፈልገዋል (ለምሳሌ ማር 5፥34):: በዚህ ላይ ግን በሽተኛው ሌላው ቀርቶ ኢየሱስ ማን እንደ ሆነ እንኳ አያውቅም ነበር (ቍ 13):: ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ የሚያድነው እምነት ያለውን ሰው ነው፤ ሆኖም የጌታ ምሕረት የእምነተ ቢስነትንም ድንበር ሲጥስ ይታያል::

5፥10 *መተኛህን እንድትሸከም ሕጉ አይፈቅድልህም፤* በሰንበት ቀን ምንም ዓይነት ሸክም እንዳይንቀሳቀስ የከለከለው

11እርሱ ግን፣ "ያ የፈወሰኝ ሰው፣ 'መተ
ኛህን ተሸክመህ ሂድ' ብሎኛል" ሲል መለሰላ
ቸው::
12እነርሱም፣ "'መተኛህን ተሸክመህ ሂድ'
ያለህ እርሱ ማነው?" ብለው ጠየቁት::
13ኢየሱስ ፈቀቅ ብሎ ወደ ሕዝብ መካከል
ገብቶ ስለ ነበር፣ ሰውዬው ማን እንደ ፈወሰው
አላወቀም::
14ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ያን ሰው በቤተ
መቅደስ አግኝቶ፣ "እነሆ፣ ተፈውሰሃል፤ ከእ
ንግዲህ ግን ኀጢአት አትሥራ፤ ያለዚያ ከዚህ
የባሰ ይደርስብሃል" አለው:: 15ሰውዬውም
የፈወሰው ኢየሱስ መሆኑን ሄዶ ለአይሁድ
ነገራቸው::

## ወልድ ሕይወትን ይሰጣል

16አይሁድም፣ በሰንበት ቀን እነዚህን ድርጊ
ቶች በመፈጸሙ፣ ኢየሱስን ያሳድዱት ነበር::
17ኢየሱስም፣ "አባቴ እስካሁን እየሠራ ነው፤
እኔም ደግሞ እሠራለሁ" አላቸው:: 18እንግ
ዲህ አይሁድ፣ ኢየሱስ ሰንበትን ስለ ሻረ
ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን አባቱ በማድረግ፣
ራሱን ከእግዚአብሔር እኩል በማድረጉ፣ ሊገድ
ሉት አጥብቀው ይፈልጉት ነበር::
19ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እውነት እላችኋለሁ፤ አብ ሲሠራ ያየውን
ብቻ እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ
አይችልም፤ አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ
ደግሞ ያደርጋልና፤ 20አብ ወልድን ስለሚወድ
የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል፤ ትደነቁም
ዘንድ ከእነዚህም የሚበልጥ ነገር ያሳየዋል::
21ምክንያቱም አብ ሙታንን እንደሚያስነሣ፣
ሕይወትንም እንደሚሰጥ፣ ወልድም ደግሞ
ለሚፈቅደው ሁሉ ሕይወትን ይሰጣል:: 22አብ
በማንም ላይ አይፈርድም፤ ነገር ግን ፍርድን
ሁሉ ለወልድ አሳልፎ ሰጥቶታል፤ 23ይኸውም፣
ሁሉ አብን እንደሚያከብሩ ወልድን ያከብሩት
ዘንድ ነው፤ ወልድን የማያከብር፣ የላከውን
አብንም አያከብርም::
24"እውነት እላችኋለሁ፤ ቃሌን የሚሰማ፣
በላከኝም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤
ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ
አይመጣም:: 25እውነት እላችኋለሁ፤ ሙታን
የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ጊዜ
ይመጣል፤ አሁንም መጥቶአል፤ የሚሰሙትም
በሕይወት ይኖራሉ:: 26አብ በራሱ ሕይወት
እንዳለው ሁሉ፣ ወልድም በራሱ ሕይወት
እንዲኖረው ሰጥቶታልና፤ 27ወልድ የሰው ልጅ
ስለ ሆነም እንዲፈርድ ሥልጣን ሰጥቶታል::
28"በዚህ አትደነቁ፤ መቃብር ውስጥ ያሉ
ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል፤
29መልካም የሠሩ ለሕይወት ትንሣኤ፣ ክፉ
የሠሩ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ:: 30እኔ
ብቻዬን ከራሴ ምንም ማድረግ አልችልም፤

5፥14 ማር2፥5፤ ዮሐ8፥11
5፥15 ዮሐ1፥19
5፥17 ሉቃ2፥49፤ ዮሐ9፥4፤14፥10
5፥18 ማቴ12፥14፤ ዮሐ10፥30:33፤19፥7
5፥19 ቊ30፤ ዮሐ 14፥24
5፥20 ዮሐ3፥35፤ 14፥12
5፥21 ዮሐ11፥25 ሮሜ4፥17፤8፥11፤ 2ቆሮ1፥9፤ዕብ11፥19
5፥22 ቊ27፤ ዘፍ18፥25፤መሳ11፥27፤ ዮሐ9፥39፤ ሐሥ10፥42
5፥23 ሉቃ10፥16፤ 1ዮሐ2፥23
5፥24 ማቴ10፥40፤ 25፥46፤ዮሐ3፥15:17 13፥18፤1ዮሐ3፥14
5፥25 ዮሐ4፥23፤ 8፥43:47፤16፥32
5፥26 ዘዳ30፥20፤ ኢዮ10፥12፤33፥4፤ መዝ36፥9፤ዮሐ1፥4
5፥27 ቊ22
5፥28 ዮሐ4፥21፤ 16፥2
5፥29 ማቴ25፥46
5፥30 ቊ19፤ማቴ 26፥39፤ኢሳ28፥6፤ ዮሐ8፥16

የሙሴ ሕግ ሳይሆን፣ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የአይሁድ የሕግ አተረጓጐም ነው:: ሰንበትን በመጠበቅ ረገድ ጥብቅ ሕግ አላቸው፤ ይሁን እንጂ የአሪት ሕግ መምህራን ደንቡን እንዳመቻቸው የሚጠመዝዙበትም መንገድ ነበራቸው (ከማቴ 23፥4 ጋር ያነጻጽሩ)::

5፥12 *ያለህ እርሱ ማነው?* አይሁድ በሰንበት የተጠከናወነውን ድርጊት የሚከለክለውን የእግዚአብሔርን ሕግ ሥልጣን፣ ድርጊቱን ከፈቀደው 'ተራ ሰው' ከሚሉት ከኢየሱስ ጋር ያነጻጽሩ ነበር::

5፥14 *ከዚህ የባሰ*፤ በኀጢአት ምክንያት የሚደርሰው ዘላለማዊ ቅጣት ከማንኛውም ዓይነት ሕመም እጅግ የከፋ ነው::

5፥16 *በመፈጸሙ*፤ ይህ የሚያሳየው ተደጋጋሚ ተግባር መሆኑን ነው፤ አይሁድም ይህንኑ ያስተዋሉ ይመስላል:: *ያሳድዱት ነበር*፤ ዮሐንስ እዚህ ላይ የሚያመለክተው፣ ኢየሱስ እንዲህ ያሉትን ታምራት ቢያደርግም፣ የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች አጥብቀው መቃወም መጀመራቸውን ነው::

5፥17 *አባቴ እስካሁን እየሰራ ነው፤* ኢየሱስ ለሚያከናውነው ተግባር ማረጋገጫ አድርጎ የሚያቀርበው ከአባቱ ጋር ያለውን የጠበቀ ግንኙነት ነው:: አይሁድ በዘልማድ እግዚአብሔርን 'አባታችን' ወይም በጸሎት ጊዜ 'በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ' ቢሉም፣ በቅርበት ደረጃ 'አባቴ' ለማለት አይደፍሩም:: ኢየሱስ ሰንበት እንዴት መከበር እንዳለበት በተግባር በማሳየት አስተ ምሯል፤ እግዚአብሔር ቸር ተግባሩን በሰንበት ቀን መፈጸምን አላቋረጠም፤ ኢየሱስም ያደረገው ይህንኑ ነበር::

5፥18 *እግዚአብሔርን አባቱ*፤ ልዩ የሆነውን የአባትና የልጅን ግንኙነት ያመለክታል፤ አይሁድ እግዚአብሔር፣ 'የሁሉም አባት ነው' የሚለውን ሐሳብ አልተቃወሙም:: ነገር ግን ኢየሱስ ከሌላው ጋር ሳይቈጠር በተለየ ግንኙነት 'አባቴ ነው' የሚለውንና ከዚህም አገላለጽ የተነሣ ኢየሱስን ከአብ ጋር እኩል የሚያደርገውን መሠረተ ሐሳብ በጥብቅ ይቃወማሉ::

5፥19 *አይችልም*፤ ዘመን ከመቈጠሩ በፊትም ሆነ በኋላ፣ ወልድ ከአብ ተለይቶ አንድም ነገር በግሉ አላደረገም፤ አያደርግምም::

5፥20 *አብ ወልድን ስለሚወድ*፤ ስለዚህም አብ ዕቅዱንና ዓላማውን ለወልድ/አሳየው፤ ወልድም ትእዛዙን ፈጸመ:: *ከእነዚህም የሚበልጥ፤* በወልድ ሥልጣን የሚፈጸመውን ትንሣኤ ሙታንንና ፍርድን ያመለክታል (ከቊ 21-30 ይመ)::

5፥21 *አብ ሙታንን እንደሚያስነሣ*፤ አይሁድ ስለ ሙታን ትንሣኤ ያላቸው እምነት ጽኑ ነበር፤ እንዲህ ያለውንም ሥልጣን ለማንም አልሰጠም ብለው ያምናሉ:: ተቃዋሚ የሆኑት አይሁድ ለአብ ብቻ የተሰጠ ነው ብለው የሚያምኑትን ይህን ሥልጣን፣ ኢየሱስ 'የእኔም ሥልጣን ነው' ማለቱን ሊቀበሉ አልቻሉም:: *ወልድም...ሕይወትን ይሰጣል*፤ በዚህ ምድር ላይ አሁኑኑ የተትረፈረፈ ሕይወት መኖሩን ያመለክታል፤ ምናልባትም የሙታንን ትንሣኤ ሊያመለክት ይችላል (11፥25-26 ይመ)::

5፥22 *ፍርድን ሁሉ ለወልድ አሳልፎ ሰጥቶታል*፤ አይሁድ የዓለም ፈራጅ አብ ብቻ ነው ብለው ስለሚያምኑ፣ ይህ ትምህርት ኑፋቄ መስሎ ታይቷቸዋል::

5፥24 *በላከኝም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤* እምነትና ሕይወት የተያያዙ ናቸው (ከ20፥31 ጋር ያነጻጽሩ):: *የዘላለም ሕይወት አለው፤* አለኝታነቱ ከአሁን ጀምሮ የሚገኝ ነው (የ3፥15 ማብ ይመ):: *ተሻገረ*፤ ቈራጥ እርምጃ በመውሰዱ ከእንግዲህ ወዲህ እማኝ የሙታን ወገን አይደለም::

5፥25 *ይመጣል፤ አሁንም መጥቶአል*፤ ተጠቃሽነቱ ወደ ፊት እውን ለሚሆነው የሙታን ትንሣኤ ብቻ ሳይሆን፣ ክርስቶስ አሁንም በምድር ላይ ሕይወትን እንደሚሰጥ ያሳያል፤ በመንፈስ ሙታን የሆኑትም እርሱን ሲሰሙ ሕይወት ያገኛሉ::

5፥26 *በራሱ ሕይወት እንዳለው፤* ይህ አባባል ግልጽ ሊሆን የሚችለው ከብሉይ ኪዳን አንጻር ሲታይ ነው፤ ምክንያቱም ሕይወት የአብ ስጦታ እንደ ሆነ ተገልጿል (ዘዳ 30፥20፤ ኢዮ 10፥12፤ 33፥4፤ መዝ 16፥11፤ 27፥1፤ 36፥9):: የአብ ሕይወት የወልድም ነው (ከ1ዮሐ 5፥11 ጋር በማነጻጸር፣ ሕይወት ለሰዎችም የተሰጠ መሆኑን ያስተውሉ)::

5፥27 *የሰው ልጅ*፤ የ1፥51 ማብ ይመ:: በብሉይ ኪዳን የመሲሑ ምልክቶች አንዱ 'ልጅ' መሆኑ ነው:: *እንዲፈርድ ሥልጣን*፤ ለወልድ፣ ከአብ የተሰጠ ሥልጣን ነው::

5፥28-29፤ የሙታን ትንሣኤ ወደ ፊት መኖሩን የሚያሳዩ ጥቅሶች ናቸው::

5፥29 *መልካም የሠሩ...ክፉ የሠሩ...ይወጣሉ፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እንደሚገኘው 'ፍርድ' የሚለው ሐሳብ ሁልጊዜ የሚታየው ከሥራ አንጻር ነው፤ ድነት የሚሰጠው ግን የእግዚአብሔርን ስጦታ በእምነት ለሚቀበሉ ሁሉ ነው (ከቊ 24 ጋር ያነጻጽሩ)::

5፥30 *እኔ...ከራሴ ምንም ማድረግ አልችልም*፤ ኢየሱስ በአባቱ ፈቃድ እንደሚሠራ አበክሮ ያሳያል (የቊ 19 ማብ ይመ)::

የምፈርደው የምሰማውን ብቻ ነው፤ የላከኝን
እንጂ የራሴን ፈቃድ ስለማልሻም ፍርዴ ትክ
ክል ነው።

### ስለ ኢየሱስ የሚናገሩ ምስክርነቶች

31 “እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር፣ ምስክርነቴ
ተቀባይነት አይኖረውም። 32 ስለ እኔ የሚመሰክር
ሌላ አለ፤ እርሱ ስለ እኔ የሚሰጠውም ምስ
ክርነት እውነት እንደ ሆነ ዐውቃለሁ።
33 “ወደ ዮሐንስ ልካችሁ ነበር፤ እርሱም ስለ
እውነት መስክሮአል፤ 34 እኔ የሰው ምስክርነት
የምቀበል አይደለሁም፤ ይህን የምናገረው ግን
እናንተ እንድትድኑ ነው። 35 ዮሐንስ እየነደደ
ብርሃን የሚሰጥ መብራት ነበረ፤ እናንተም
ለጥቂት ጊዜ በብርሃኑ ደስ ልትሰኙ ወደዳችሁ።
36 “እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክርነት የላቀ
ምስክር አለኝ፤ እንድፈጽመው አብ የሰጠኝ፣
እኔም የምሠራው ሥራ አብ እንደ ላከኝ
ይመሰክራል። 37 የላከኝ አብ ራሱ ስለ እኔ
መስክሮአል፤ እናንተም ከቶ ድምፁን አልሰ
ማችሁም፤ መልኩንም አላያችሁም፤ 38 የላከ
ውንም ስላላመናችሁ ቃሉ በእናንተ አይኖርም።
39 በእነርሱ የዘላለም ሕይወትን የምታገኙ
እየመሰላችሁ፣ መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፤*
እነዚሁ መጻሕፍት ስለ እኔ የሚመሰክሩ
ናቸው፤ 40 እናንተ ግን፣ ሕይወት እንዲኖራ
ችሁ ወደ እኔ መምጣት አትፈልጉም።

5፥31 ዮሐ8፥14
5፥32 ቊ37፤ ዮሐ 8፥18
5፥33 ዮሐ1፥7
5፥34 ሐሥ16፥30፡31፤ኤፌ2፥8፤ ቲቶ3፥5፤1ዮሐ5፥9
5፥35 ዳን12፥3፤ 2ጴጥ1፥19
5፥36 ዮሐ3፥17፤ 14፥11፤15፥24፤ 1ዮሐ 5፥9
5፥37 ዘዳ4፥12፤ ዮሐ1፥18፤8፥18፤ 1ጢሞ1፥17
5፥38 ኢሳ26፥10፤ ዮሐ3፥17፤1ዮሐ 1፥10፤2፥14
5፥39 ማቴ25፥46፤ ሉቃ 24፥27፡44፤ ሮሜ 2፥17፡18፤ ሐሥ13፥27
5፥40 ዮሐ6፥44
5፥41 ቊ44
5፥44 ሮሜ2፥29
5፥45 ዮሐ9፥28፤ ሮሜ2፥17
5፥46 ዘፍ3፥15፤ ሉቃ24፥27፡44፤ ሐሥ26፥22
5፥47 ሉቃ16፥29፡31
6፥2 ዮሐ2፥11
6፥3 ቊ15
6፥4 ዮሐ11፥55

41 “እኔ ከሰው ክብር አልቀበልም፤ 42 ነገር
ግን እናንተን ዐውቃችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርም
ፍቅር በልባችሁ እንደሌለ ዐውቃለሁ።
43 እኔ በአባቴ ስም መጥቼ አልተቀበላች
ሁኝም፤ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ ግን ትቀ
በሉታላችሁ። 44 እናንተ እርስ በርሳችሁ ክብር
የምትሰጣጡ፣ ነገር ግን ከአንዱ አምላክ*
የሚመጣውን ክብር የማትፈልጉ ከሆነ፣ እን
ዴት ልታምኑ ትችላላችሁ?
45 “ከሳሻችሁ ተስፋ የጣላችሁበት ሙሴ
እንጂ፣ እኔ በአብ ፊት የምከሳችሁ አይም
ሰላችሁ፤ 46 ሙሴን ብታምኑ ኖሮ፣ እኔን
ባመናችሁ ነበር፤ ምክንያቱም እርሱ የጻፈው
ስለ እኔ ነው። 47 እርሱ የጻፈውን ካላመናችሁ፣
እኔ የምናገረውን እንዴት ታምናላችሁ?”

### ኢየሱስ አምስት ሺህ ሕዝብ መገበ

6፥1-13 ተጓ ምብ - ማቴ 14፥13-21፤ ማር 6፥32-44፤ ሉቃ 9፥10-17

6 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ጥብርያዶስ የተባለ
ውን የገሊላ ባሕር ተሻግሮ ራቅ ወዳለው
የባሕሩ ዳርቻ ሄደ። 2 ብዙ ሰዎችም በሽተኞ
ችን በመፈወስ ያደረጋቸውን ታምራዊ ምልክ
ቶች ስላዩ ተከተሉት። 3 ከዚያም ኢየሱስ
ወደ ተራራ ወጥቶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር
ተቀመጠ። 4 የአይሁድ የፋሲካ በዓልም
ተቃርቦ ነበር።

*39 *ወይም መጻሕፍትን መርምሩ*
*44 አንዳንድ የጥንት ቅጆች

ከአብ በሰማው ብቻ ስለሚፈርድ፣ ፍርዱ አይዛነፍም።

*5፥31-47፤* ይህ ክፍል የመጥምቁ ዮሐንስን (ቊ 33)፣ የኢየሱስን *ሥራዎች* (ቊ 36)፣ የእግዚአብሔር አብን (ቊ 37)፣ የቅዱሳት *መጻሕፍትን* (ቊ39)፣ የሙሴን (ቊ 46) ምስክርነት *ያረጋግጣል* (የ1፥7 *ማብ ይመ*)።

*5፥31፤* ኢየሱስ ስለ ራሱ የሰጠው ምስክርነት እግዚአብሔር ስለ እርሱ በገለጠው መንገድ ሁሉ መደገፍ አለበት፤ ይህ ባይሆን ኖሮ ምስክርነቱ ተቀባይነት ባላገኘ ነበር።

5፥32 *ሌላ፤* አብን *ያመለክታል፤* አይሁድ ግን ይህን ምስክርነት ሳይቀበሉት ይችላሉ። *አንዳንዶች ደግሞ ቃሉ የሚያመለክተው መጥምቁ ዮሐንስን ነው ይላሉ።*

5፥33 *ወደ ዮሐንስ ልካችሁ ነበር፤* ከአይሁድ *መሪዎች* ወደ *መጥምቁ* ዮሐንስ የተላኩትን *መልእክተኞች የሚያመለክት* ነው (1፥19)። *መስክሮአል፤* ከአብ ምስክርነት ጋር ባይስተካከልም የዮሐንስ ምስክርነት አስፈላጊ ነበር። አይሁድ የዮሐንስን ምስክርነት ቢያምኑ ኖሮ፣ በክርስቶስ አምነው በዳኑ ነበር።

5፥35 *ዮሐንስ...ነበር፤* በኀላፊ ጊዜ *መጠቀሱ*፣ ዮሐንስ *መሞቱን ወይም መታሰሩን ያመለክታል፤* የዮሐንስም ብርሃንነት *ዘላለማዊ እንዳልሆነ ያሳያል፤ ይሁን እንጂ ዮሐንስ ተልእኮውን ተወጥቷል።* *እየነደደ ብርሃን የሚሰጥ፤* ዮሐንስ በብዙ *መከራ* ውስጥ በማለፍ ብርሃን ይሰጥ እንደ ነበር *ያሳያል።* *ለጥቂት ጊዜ፤* የአይሁድ *መሪዎች* የዮሐንስን ምስክርነት *አላስተዋሉም፤ ላቀረበው ጥሪ ያደረጉት ምላሽ ቢኖር ጊዜያዊና የይምሰል ነበር።*

5፥36 *ሥራ፤* የኢየሱስ *ታምራት፣* ማንነቱንና *መለኮታዊ ተልእኮውን ይመሰክራሉ* (10፥25)።

5፥37 *አብ ራሱ...መስክሮአል...ድምፁን፤* ምናልባት በቅዱሳት *መጻሕፍት* አማካይነት የሚሰማውን የእግዚአብሔርን *ድምፅ ሊሆን ይችላል* (ቊ 33-39)። ኢየሱስ ሲጠመቅ፣ የአብ *ድምፅ ተሰምቷል* (ማቴ 3፥17)። *መልኩንም አላያችሁም፤* የኢየሱስን ማንነት ባለማስተዋላቸው *መንፈሳዊ* ዐይናቸው ማየት እንደ ተሳነው ለማመልከት *ሊሆን ይችላል።*

5፥38 *ስላላመናችሁ፤* አይሁድ በኢየሱስ አለማመናቸው፣ እግዚአብሔር የተናገረውን እንዳላስተዋሉ *ያሳያል።*

5፥39 *ትመረምራላችሁ፤* የአይሁድ *መሪዎች* ቅዱሳት *መጻሕፍትን የሚያጠኑት* ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ገብተው ነበር (የማቴ 5፥18-21 *ማብ ይመ*)፤ ይሁን እንጂ *መጻሕፍቱ* ከሁሉም አብልጠው የመሰከሩለትን አላወቁትም።

5፥41 *ከሰው ክብር፤* ኢየሱስ የሰውን ምስክርነት እንዳልተቀበለ ሁሉ (ቊ 34)፣ ከሰው *የሚመጣውንም* ምስጋና አልተቀበለም።

5፥42 *የእግዚአብሔርም ፍቅር፤* የእግዚአብሔር ፍቅር ለእነርሱ፣ ወይም የእነርሱ ፍቅር ለእግዚአብሔር ማለት ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ሁለተኛው ሳይሆን አይቀርም፤ በመሠረቱ ሰዎች ለእግዚአብሔር ፍቅር የሚኖራቸው፣ ቀድሞውኑ እግዚአብሔር ስለ ወደዳቸው ነው (1ዮሐ 4፥19)።

5፥43-44፤ አይሁድ በሚያደርጉት ነገር ከሰው ክብርን ይጠብቃሉ፤ ለራስ ፍላጎትና ከሰው ለሚመጣ ምስጋና ያሳዩት ጕጕት፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣውን እንዳልተቀበሉና በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን ክብር እንዳላገኙ ያሳያል።

5፥45 *ከሳሻችሁ ...ሙሴ እንጂ፤* አይሁድ ሕግን ካመጣላቸው ከሙሴ ጋር ባላቸው ቅርበት ስለሚኩራሩ፣ በእግዚአብሔር ፊት ሙሴ ራሱ እንደሚከሳቸው ኢየሱስ መናገሩ ያልጠበቁት ዱብ ዕዳ ነበር።

5፥46 *የጻፈው ስለ እኔ ነው፤* የብሉይ ኪዳን *መጻሕፍት* በትክክል ከተነበቡ ወደ ክርስቶስ እንደሚያመለክቱ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች *ያረጋግጣሉ* (ከሉቃ 24፥25-27፡ 44 *ጋር ያነጻጽሩ*)፤ ኢየሱስም የሙሴ *መጻሕፍት* (ለምሳሌ የዘፍ 49፥10፤ የዘፀ 12፥21፤ የዘሌ 16፥5፤ የዘኍ 24፥17፤ የዘዳ 18፥15) ወደ እርሱ እንደሚያመለክቱ በግልጽ ተናግሯል።

5፥47 *እርሱ የጻፈውን፤* አምስቱን የኦሪት *መጻሕፍት* (ዘፍ-ዘዳ) ሙሴ መጻፉን ኢየሱስ ተናግሯል።

*6፥1-15፤* ከትንሣኤ ሌላ በአራቱም ወንጌሎች ተጽፎ የሚገኘው አንዱ *ታምር*፣ ኢየሱስ 5000 ሰዎችን መመገቡ ነው። ኢየሱስ የሰዎችን ፍላጎት የሚያረካ መሆኑን ከማሳየቱም በላይ፣ ራሱ የሕይወት እንጀራ ለመሆኑ ይህ *ታምር* ምስክር ነው (ቊ 35)።

6፥1 *ከዚህ በኋላ፤* 5፥1 እና *ማብ ይመ*። *ጥብርያዶስ... ባሕር፤* ምናልባት በሮም ገዥዎች የሚታወቅበት ስም ሲሆን፣ ስሙ የተገኘው በንጉሡ ነገሥቱ ስም ከተሰየመችው ከጥብርያዶስ ከተማ ነው፤ በአካባቢውም የሚጠራው የገሊላ ባሕር ተብሎ ነበር፤ ከዚህ ቀደም ግን ጌንሳሬጥ ይባል ነበር። ከተማዋ በ20 ዓመተ ምሕረት አካባቢ ብትቈረቈርም፣ በኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን ጠቀሜታዋ ጕልህ አልነበረም።

6፥2 *ታምራዊ ምልክቶች፤* የ2፥11 *ማብ ይመ*።

6፥4 *ፋሲካ፤* የ2፥13 *ማብ ይመ*።

⁵ኢየሱስም ቀና ብሎ ሲመለከት ብዙ ሕዝብ
ወደ እርሱ ሲመጣ አየ፤ ፊልጶስንም፣ “እነዚህ
ሰዎች እንዲበሉ እንጀራ ከየት እንግዛ?” አለው።
[6]ይህን የጠየቀው ሊፈትነው እንጂ ራሱ ሊያ
ደርግ ያሰበውን ያውቅ ነበር።
[7]ፊልጶስም፣ “እያንዳንዱ ሰው ትንሽ ትንሽ
እንዲቃመስ ለማድረግ፣ የሁለት መቶ ዲናር[7]
እንጀራ እንኳ አይበቃም” ሲል መለሰ።
[8]ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፣ የስምዖን ጴጥ
ሮስ ወንድም እንድርያስም፣ እንዲህ አለ፤
[9]“አምስት ትንንሽ የገብስ እንጀራና ሁለት
ትንንሽ ዓሣ የያዘ አንድ ልጅ እዚህ አለ፤
ይህ ግን ለዚህ ሁሉ ሕዝብ እንዴት ይዳረ
ሳል?”።
[10]ኢየሱስም፣ “ሰዎቹ እንዲቀመጡ አድርጉ”
አለ። በዚያ ቦታ ብዙ ሣር ነበረ፤ አምስት
ሺህ ያህል ወንዶችም ተቀመጡ። [11]ኢየሱስ
አምስቱን እንጀራ አንሥቶ አመሰገነ፤ ለተቀ
መጡትም የሚፈልጉትን ያህል ዐደለ፤ ዓሣ
ውንም እንዲሁ።
[12]ሁሉም በልተው ከጠገቡ በኋላ፣ ደቀ
መዛሙርቱን፣ “ከተረፈው ቍርስራሽ ምንም
እንዳይባክን ሰብስቡ” አላቸው። [13]እነርሱም፣
ከተበላው አምስት የገብስ እንጀራ የተረፈውን
ቍርስራሽ ሰብስበው ዐሥራ ሁለት መሶብ
ሞሉ።

6፥5 ዮሐ1፥43
6፥8 ዮሐ1፥40
6፥9 2ነገ4፥43
6፥11 ቍ23፤ ማቴ 14፥19
6፥14 ዘዳ18፥15፡18፤ማቴ11፥3፤ 21፥11፤ዮሐ2፥11
6፥15 ማቴ14፥23፤ ማር6፥46፤ ዮሐ18፥36
6፥19 ኢዮ9፥8
6፥20 ማቴ14፥27
6፥22 ቍ2፡15-21
6፥23 ቍ1፡11

[14]ሰዎቹም ኢየሱስ ያደረገውን ታምራዊ
ምልክት ካዩ በኋላ፣ “ወደ ዓለም የሚመጣው
ነቢይ በእርግጥ ይህ ነው” አሉ። [15]ኢየሱስም
ሰዎቹ መጥተው በግድ ሊያነግሡት እንዳ
ሰቡ ዐውቆ እንደ ገና ብቻውን ወደ ተራራ
ገለል አለ።

## ኢየሱስ በውሃ ላይ እየተራመደ ሄደ

6፥16-21 ተጓ ምብ - ማቴ 14፥22-33፤ ማር 6፥47-51

[16]በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ባሕር
ወረዱ፤ [17]በጀልባውም ተሳፍረው ወደ ቅፍርና
ሆም ለመሻገር ተነሡ። ጊዜው መሽቶ ነበር፤
ኢየሱስም ወደ እነርሱ ገና አልመጣም ነበር።
[18]ኀይለኛ ነፋስ ይነፍስ ስለ ነበር ባሕሩ ተና
ወጠ። [19]አምስት ወይም ስድስት ኪሎ ሜትር[m]
ያህል እንደ ቀዘፉ፣ ኢየሱስ በውሃ ላይ እየተ
ራመደ ወደ ጀልባዋ ሲመጣ አይተው ደነገጡ።
[20]እርሱ ግን፣ “እኔ ነኝ፤ አትፍሩ” አላቸው።
[21]እነርሱም እንዲሳፈር ፈለጉ፤ ጀልባዋም ወዲ
ያውኑ ወደሚሄዱበት ዳርቻ ደረሰች።
[22]በማግሥቱ በባሕሩ ማዶ የቀሩት ሰዎች
በዚያ አንዲት ጀልባ ብቻ እንደ ነበረች ተረዱ፤
ኢየሱስ እንዳልተሳፈረና ደቀ መዛሙርቱ
ብቻቸውን እንደ ሄዱም ዐወቁ። [23]ከዚያም
በኋላ፣ ሌሎች ጀልባዎች ከጥብርያዶስ፣

[7]7 ወይም የስምንት ወር ደመወዝ
[m]19 በግሪኩ ሃያ አምስት ወይም ሠላሳ ምዕራፍ ቀዘፉ ይላል

6፥5 *ፊልጶስ፤* የመጣው ከቤተ ሳይዳ አቅራቢያ ስለ ሆነ (1፥44)፣ እርሱን መጠየቅ ተገቢ ነበር።

6፥9 *የገብስ እንጀራ፤* በቀላል ዋጋ የሚገኝ የድኻ ምግብ ነበር።

6፥10 *አምስት ሺህ ያህል፤* የወንዶቹ ቍጥር ብቻ ነው፤ የሴቶቹና የልጆቹ ቍጥር አልተጠቀሰም (ማቴ 14፥21)።

6፥12 *ቍርስራሽ...ሰብስቡ፤* የማር 6፥43 ማብ ይመ።

6፥13 *የተረፋቸውን...አሥራ ሁለት መሶብ ሞሉ፤* በልተው ከጠገቡ በኋላ የተረፈ ምግብ ማለት ነው።


6፥14 *ምልክት፤* ወደ ኢየሱስና እርሱ ወደሚሰጠው የዘላለም ሕይወት (ቍ 27) ያመለክታል፤ እነርሱ ግን በዘዳ 18፥15 ላይ እንደ ተጠቀሰው እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ብቻ መስላቸው (1፥21 እና ማብ ይመ)። እግዚአብሔር በምድረ በዳ ውስጥ በሙሴ አማካይነት ለሕዝቡ ምግብና ውሃ ሰጥቷቸው ነበር፤ በኢየሱስ ዘመን የነበሩት አይሁድም የሚመጣው ነቢይ ከሙሴ የበለጠ ያደርጋል ብለው አልገመቱም ነበር።

6፥15 *በግድ ሊያነግሡት፤* በዓለም ወግ መሠረት ንጉሥ መሆን፣ የሰይጣን ፈተና ነው በማለት ኢየሱስ አልተቀበለውም (ማቴ 4፥8-10፤ የዮሐ 18፥36 ማብ ይመ)።

6፥19 *አምስት ወይም ስድስት ኪሎ ሜትር ያህል፤* ማርቆስ ‘በባሕር መካከል ነበሩ’ ይላል (ማር 6፥47)። *ደነገጡ፤* ምትሐት መስሏቸው ነበር (ማቴ 14፥26)።

6፥21 *ወዲያውኑ ወደሚሄዱበት ዳርቻ ደረሰች፤* አንዳንዶች ይህም ራሱ ሌላ ታምር ነው ይላሉ። ያም ሆነ ይህ ጀልባዋ በደህና የደረሰችው በኢየሱስ ኀይል መሆኑ የሚታወቅ ነው።

*6፥22-24፤* ሕዝቡ፣ ኢየሱስ የት እንደ ደረሰ በግልጽ



ሕዝቡ ጌታ የባረከውን እንጀራ ወደ በላበት
ስፍራ መጡ:: [24]ሰዎቹም፣ ኢየሱስ ወይም ደቀ
መዛሙርቱ በዚያ አለመኖራቸውን እንዳወቁ፣
ኢየሱስን ፍለጋ በጀልባዎቹ ወደ ቅፍርናሆም
ሄዱ::

## ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ

[25]ከባሕሩ ማዶ ባገኙትም ጊዜ፣ "ረቢ፤ መቼ
ወደዚህ መጣህ?" አሉት::
[26]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እውነት እላችኋለሁ የምትፈልጉኝ እንጀራ
ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ እንጂ፣ ታምራዊ
ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም:: [27]ለሚጠፋ
እንጀራ አትሥሩ፤ ነገር ግን የሰው ልጅ
ለሚሰጣችሁ ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር
ምግብ ሥሩ፤ ለዚህም እግዚአብሔር አብ ማረ
ጋገጫ ማኅተሙን በእርሱ ላይ አትሞአልና::"
[28]እነርሱም፣ "ታዲያ የእግዚአብሔርን ሥራ
ለመሥራት ምን ማድረግ አለብን?" አሉት::
[29]ኢየሱስም፣ "እርሱ በላከው ታምኑ ዘንድ፣
ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው" ሲል መለሰላቸው::
[30]ስለዚህ እንዲህ ብለው ጠየቁት፤ "አይተን
እንድናምንህ ምን ታምራዊ ምልክት ታደር
ጋለህ? ምንስ ትሠራለህ? [31]'ይበሉ ዘንድ
ከሰማይ እንጀራን ሰጣቸው' ተብሎ እንደ
ተጻፈ፣ አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ::"
[32]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት
እላችኋለሁ፤ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ
አይደለም፤ እውነተኛውን እንጀራ ከሰማይ
የሚሰጣችሁ ግን አባቴ ነው፤
[33]የእግዚአብሔር እንጀራ እርሱ ከሰማይ የሚ

6፥25 ማቴ23፥7
6፥26 ቁ-24:30፤ ዮሐ2፥11
6፥27 ቁ-54፤ ኢሳ55፥2፤ማቴ8፥20፤ 25፥46፤ሮሜ4፥11፤ 1ቆሮ9፥2፤2ቆሮ1፥22፤ ኤፌ1፥13፤4፥30፤ 2ጢሞ2፥19፤ራእ7፥3
6፥29 ዮሐ3፥17፤ 1ዮሐ3፥23
6፥30 ማቴ12፥38፤ ዮሐ2፥11
6፥31 ዘፀ16፥4:15፤ ዘኍ11፥7-9፤ነህ9፥15 ፤መዝ78፥24፤105፥40
6፥33 ቁ-50፤ ዮሐ3፥13:31
6፥34 ዮሐ4፥15
6፥35 ቁ-48:51፤ዘፀ 3፥14፤ ዮሐ3፥15፤4፥ 14፤8፥12፤10፥7:11፤ 11፥25፤14፥6፤15፥1
6፥37 ቁ-39፤ ዮሐ17፥2:6:9:24
6፥38 ማቴ26፥39፤ ዮሐ3፥13:31፤3፥17
6፥39 ቁ-40:44: 54፤ኢሳ27፥3፤ኤር 23፥4፤ዮሐ10፥28፤ 17፥12፤18፥9
6፥40 ማቴ25፥46፤ ዮሐ12፥45
6፥42 ቁ-38:62፤ ሉቃ4፥22፤ ዮሐ7፥27:28
6፥44 ቁ-65፤ኤር 31፥3፤ዮሐ12፥32
6፥45 ኢሳ54፥13፤ ኤር31፥33:34፤1ቆሮ 2፥13፤1ተሰ4፥9፤ዕብ 8፥10:11፤10፥16፤ 1ዮሐ2፥27

ወርድ፣ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና::"
[34]እነርሱም፣ "ጌታ፣ እንግዲያውስ ይህን
እንጀራ ሁልጊዜ ስጠን" አሉት::
[35]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "የሕይወት
እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይ
ራብም፤ በእኔም የሚያምን ፈጽሞ አይጠማም::
[36]ነገር ግን እንደ ነገርኋችሁ፣ አይታችሁኝም
እንኳ አታምኑም:: [37]አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ
እኔ ይመጣል፤ ወደ እኔ የሚመጣውንም ከቶ
ወደ ውጭ አላወጣውም፤ [38]ከሰማይ የወረድሁት
የራሴን ፈቃድ ለማድረግ ሳይሆን፣ የላከኝን
የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም ነውና፤ [39]የላከኝም
ፈቃድ፣ ከሰጠኝ ሁሉ አንድ እንኳ ሳይጠፋብኝ
በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣ ነው:: [40]የአባቴ
ፈቃድ ወልድን አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ
የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ነው፤ እኔም
በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ::"
[41]አይሁድም፣ "ከሰማይ የወረደ እንጀራ
እኔ ነኝ" በማለቱ ያጕረመርሙበት ጀመር::
[42]ደግሞም፣ "ይህ አባቱንና እናቱን የምናው
ቃቸው፣ የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ አይደለምን?
ታዲያ አሁን እንዴት፣ 'ከሰማይ ወረድሁ
ይላል' " አሉ::
[43]ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ "እርስ
በርሳችሁ አታጕረምርሙ፤ [44]የላከኝ አብ ካልሳ
በው በቀር ማንም ወደ እኔ መምጣት አይ
ችልም፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ::
[45]በነቢያትም፣ 'ሁሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ
ይሆናሉ' ተብሎ ተጽፎአል፤ አብን የሚሰማና
ከእርሱም የሚማር ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል::

---

ማወቅ አልቻሉም:: እንደ ገናም ሊያገኙት ወደዱ፤ ይገኛል ብለውም በገመቱት ስፍራ በቅፍርናሆም ፈለጉት::

6፥27 *የዘላለም ሕይወት*፤ ይህ ሕይወት የሚገኘው ከሰው በጎ ሥራ የተነሣ ሳይሆን፣ በክርስቶስ በማመን ነው (ቁ 28-29 እና የ3፥15 ማብ ይመ):: *የሰው ልጅ*፤ የማር 8፥31 ማብ ይመ::

6፥28 *ምን ማድረግ አለብን?* የዘላለም ሕይወት የክርስቶስ ስጦታ መሆኑን ዘንግተው በበጎ ሥራ የሚገኝ መሰላቸው::

6፥29 *የእግዚአብሔር ሥራ*፤ እግዚአብሔር ከሰዎች የሚ ፈልገው በጎ ሥራ፣ የዘላለምን ሕይወት በሚሰጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ ነው::

6፥30 *ምንስ ትሠራለህ?* እነርሱ የፈለጉት በሙሴ አማካይነት ከሰማይ ከወረደው መና የላቀ ታምር ኢየሱስ እንዲ ያሳያቸው ነበር::

6፥31 *መና*፤ በአይሁድ ዘንድ፣ መሲሑ ሲመጣ እንደ ገና መና ያወርድልናል የሚል ተስፋ ነበር:: የተሰበሰበው ሕዝብ ኢየሱስ ከሙሴ ያነሰ ተግባር አከናውኗል ብሎ ሳያምን አልቀረም፤ ኢየሱስ 5000 ሰዎችን መግቧል፤ ሙሴ ግን የመገበው መላውን ሕዝብ ነበር፤ ኢየሱስ የመገባቸው አንድ ቀን ብቻ ነው፤ ሙሴ ግን 40 ዓመት ሙሉ መግቧል፤ ኢየሱስ የሰጠው የተለመደውን እንጀራ ሲሆን፣ ሙሴ የሰጠው ከሰማይ የወረደ መና ነበር::

*6፥32፤* ኢየሱስ፣ በምድረ በዳ መናውን ለሕዝቡ ያወረደ ላቸው ሙሴ ሳይሆን እግዚአብሔር መሆኑን በማመልከት አረ ማቸው፤ አሁንም ቢሆን እውነተኛውን መና (ወልድ የሚሰጠ ውን ሕይወት) የሚሰጥ አብ ነው::

6፥33 *የእግዚአብሔር እንጀራ*፤ ኢየሱስ ርእስ ጕዳዩን ከመና እጅግ ወደ ላቀ ደረጃ አሸጋገረው::

6፥34 *ይህን እንጀራ*፤ ከውሃው ጕድጓድ አጠገብ ከነበረችው ሴት ጋር እንደ ተከሠተው ሁሉ፣ እዚህም ላይ አለ መግባባት ተፈጥሮ ሊሆን ይችላል፤ 4፥15 እና ኒቆዲሞስን (3፥4) ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ:: ሐሳባቸው ምድራዊ ጥቅም ላይ ያተኰረ ነበር::

6፥35 *የሕይወት እንጀራ*፤ አንድም 'ሕያው እንጀራ' አሊያም 'ሕይወት የሚሰጥ እንጀራ' ወይም ሁለቱንም ሊሆን ይችላል:: በቍጥር 33 በውስጠ ታዋቂነት የቀረበው ይህ ሐሳብ፣ እዚህ ላይ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት ግልጽ ሆኖ ቀርቧል፤ በድጋሚም በቁ 41:48:51 ላይ ተጠቅሷል:: *እኔ ነኝ፤* ኢየሱስ የራሱን ማንነት ለመግለጽ ከተጠቀመባቸው ሰባት መግለጫዎች የመጀመሪያው 'እኔ ነኝ' የሚለው ነው (8፥12፤ 9፥5፤ 10፥7: 9:11:14፤ 11፥25፤ 14፥6፤ 15፥1:5 ይመ):: ቃላቱ በግሪክ ቋንቋ ክብደት ያላቸው ከመሆናቸውም በላይ የዘፀ 3፥14 ሐሳብን ያን ጸባርቃሉ::

*6፥36፤* ከ20፥29 ጋር ያነጻጽሩ::

*6፥37፤* በድነት ረገድ ቀዳሚውን ቦታ የሚይዘው የእግዚ አብሔር ሥራ እንጂ (ቁ 44፤ 10፥29፤ 17፥6፤ 18፥9 ይመ)፣ የሰው ተግባር አይደለም (ቁ-28):: የክርስቶስ ምሕረት ጸንቶ የሚኖር ነው (ቁ-31-40፤ 10፥28፤ 17፥9:12:15:19፤ 18፥9 ይመ)::

6፥38 *ከሰማይ የወረድሁት*፤ ይህ የኢየሱስን መለኮትነት የሚገልጽ አባባል፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስድስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል (ቁ 33:38:41: 50-51:58):: *የላከኝን ፈቃድ ለመፈጸም፤* የ4፥34 ማብ ይመ::

6፥39 *አንድ እንኳ ሳይጠፋብኝ፤* እውነተኛ አማኝ እስከ ዘለቄታው የሚቆመው ከክርስቶስ ብርቱ ጥበቃ የተነሣ ነው (ፊል 1፥6 ይመ):: *በመጨረሻው ቀን*፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድን የተወሰነ ቀን የሚመለከት ይህ አገላለጽ የሚገኘው በዮሐንስ ወንጌል ብቻ ነው (ቁ 40:44:54 ይመ)::

6፥40 *የዘላለም ሕይወት*፤ የ3፥15 ማብ ይመ:: *በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ፤* ክርስቶስ የሚሰጠውን ሕይወት ሞት አያሸንፈውም::

6፥41 *አይሁድ*፤ የ1፥19 ማብ ይመ::

6፥44 *ካልሳበው*፤ ሰዎች ወደ ክርስቶስ የሚመጡት ሙሉ በሙሉ በራሳቸው አነሳሽነት ሳይሆን አብ ሲስባቸው ነው::

6፥45 *ነቢያት*፤ ጥቅሱ የሚገኝበትን የብሉይ ኪዳን ክፍል የሚያመለክት ነው:: *ከእርሱ የሚማር ሁሉ...ይመጣል*፤ ወደ

46ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሆነው በቀር አብን ያየ
ማንም የለም፤ አብን ያየው እርሱ ብቻ ነው።
47እውነት እላችኋለሁ፤ የሚያምን ሁሉ የዘላለም
ሕይወት አለው። 48የሕይወት እንጀራ እኔ
ነኝ። 49አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ፤
ይሁን እንጂ ሞቱ። 50ነገር ግን ሰው እን
ዳይሞት ይበላው ዘንድ ከሰማይ የሚወርድ
እንጀራ ይህ ነው። 51ከሰማይ የወረደ ሕያው
እንጀራ እኔ ነኝ፤ ማንም ሰው ከዚህ እንጀራ
ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ ይህም እንጀራ፣ ለዓ
ለም ሕይወት እንዲሆን የምሰጠው ሥጋዬ ነው።”
52አይሁድም፣ “እንበላ ዘንድ ይህ ሰው
ሥጋውን እንዴት ሊሰጠን ይችላል?” እያሉ
እርስ በርሳቸው አጥብቀው ይከራከሩ ጀመር።
53ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እውነት
እላችኋለሁ፤ የሰውን ልጅ ሥጋውን ካልበላች
ሁና ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት
የላችሁም። 54ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜንም የሚጠጣ
የዘላለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው
ቀን አስነሣዋለሁ፤ 55ሥጋዬ እውነተኛ ምግብ፣
ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና፤ 56ሥጋዬን
የሚበላ፣ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤
እኔም በእርሱ እኖራለሁ። 57ሕያው አብ እንደ
ላከኝ፣ እኔም ከእርሱ የተነሣ በሕይወት
እንደምኖር፣ የሚበላኝም እንዲሁ ከእኔ የተነሣ
በሕይወት ይኖራል። 58ከሰማይ የወረደ እን
ጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በሉ፤ ሞቱም፤
ይህን እንጀራ የሚበላ ግን ለዘላለም ይኖራል።”
59ይህን የተናገረው በቅፍርናሆም፣ በምኵራብ
እያስተማረ ሳለ ነበር።

**ብዙ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን መከተል ተዉ**

60ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ይህን ሲሰሙ፣
“ይህ የሚያስጨንቅ ቃል ነው፤ ማንስ ሊቀ
በለው ይችላል?” አሉ።
61ደቀ መዛሙርቱም በዚህ ነገር ማጒረ
ምረማቸውን ኢየሱስ በገዛ ራሱ ተረድቶ፣
እንዲህ አላቸው፤ “ይህ ዕንቅፋት ይሆንባች
ኋልን? 62ታዲያ፣ የሰው ልጅ ቀድሞ ወደ
ነበረበት ሲወጣ ብታዩ ምን ልትሉ ነው?
63መንፈስ ሕይወትን ይሰጣል፤ ሥጋ ግን
ምንም አይጠቅምም። እኔ የነገርኋችሁ ቃል
መንፈስም ሕይወትም ነው፤ 64ይሁን እንጂ
ከእናንተ የማያምኑ አንዳንዶች አሉ።” ይህም፣
ኢየሱስ እነማን እንዳላመኑና ማን አሳልፎ
እንደሚሰጠው ቀድሞውኑ ያውቅ ስለ ነበር ነው።
65ቀጥሎም፣ “‘ከአብ ካልተሰጠው በቀር፣
ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም’ ያልኋችሁ
ለዚህ ነው” አለ።
66ከዚህም በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች
ወደ ኋላ ተመለሱ፤ ከዚያም ወዲያ አልተከተ
ሉትም።
67ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን፣ “እናንተም
ደግሞ መሄድ ትፈልጋላችሁ?” አላቸው።
68ስምዖን ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤
“ጌታ ሆይ፤ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ
የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤ 69አንተ አንድያ
የእግዚአብሔር ቅዱስ እንደ ሆንህ አምነናል፤
ዐውቀናልም።”
70ኢየሱስም መለሰ፣ “ዐሥራ ሁለታችሁንም
የመረጥኋችሁ እኔ አይደለሁምን? ነገር ግን

6፥46 ዮሐ1፥18፤ 5፥37፤7፥29
6፥47 ማቴ25፥46
6፥48 ቊ35፡51
6፥49 ቊ31፡58
6፥50 ቊ33
6፥51 ቊ35፡41፡ 48፡58፤ዕብ10፥10
6፥52 ዮሐ1፥19፤ 7፥43፤9፥16፤10፥19
6፥53 ማቴ8፥20፤ 26፥26፡28
6፥54 ቊ39
6፥56 ዮሐ15፥4-7፤ 1ዮሐ2፥24፤3፥24፤ 4፥15
6፥57 ዮሐ3፥17
6፥58 ቊ49-51፤ ዮሐ3፥36፤5፥24
6፥60 ቊ52፡66
6፥61 ማቴ13፥57
6፥62 ማቴ8፥20፤ ማር16፥19፤ ዮሐ3፥13፤17፥5
6፥63 2ቆሮ3፥6
6፥64 ማቴ10፥4፤ ዮሐ2፥25
6፥65 ቊ37፡44፤ ማቴ13፥11
6፥66 ቊ60
6፥67 ማቴ10፥2
6፥68 ቊ63፤ ማቴ16፥16
6፥69 ማር1፥24፤ 8፥29፤ ሉቃ9፥20
6፥70 ዮሐ13፥27፤ 15፥16፡19፤17፥12

ድነት የሚደርሱት ከእግዚአብሔር የተማሩት ብቻ ናቸው፤ ከእርሱ የተማሩትም ሁሉ ይድናሉ።

6፥49 *ሞቱ፤* የኢየሱስ ተቃዋሚዎች ሐሳባቸው ያተኰረው መንፈሳዊ ሕይወትን በማይሰጥና በማይ ደግፍ ነገር ላይ ነው (ከቊ 31 ጋር ያነጻጽሩ)።

6፥50 *እንዳይሞት ይበላው ዘንድ፤* የኢየሱስ ስጦታ ከመናው ጋር ተነጻጽሯል፤ ኢየሱስ የሚሰጠው ሕይወት የዘላለም ሕይወት ነው።

6፥51 *ከዚህ እንጀራ ቢበላ፤* የአንድን ሰው ሕይወት ጠብቆ የሚያቈየው ኢየሱስ እንደ ሆነ የቃሉ አገባብ ያሳያል። *የምሰጠው ሥጋዬ፤* ስቅለቱን ማመልከቱ ነው፤ ኢየሱስ የዘላለምን ሕይወት የሚያወርሰው ከፍተኛ መሥዋዕትነትን ከፍሎ ነው። *ዓለም፤* የ4፥42 ማብ ይመ።

6፥53-58 ኢየሱስ በማያወላዳ ቃሉ፣ “የሰው ልጅን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ፣ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም” ያለው (ቊ 53)፣ በቀጥታ የጌታን እራት ለማመልከት አልነበረም። የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ብቸኛው መንገድ ቅዱስ ቍርባንን መቀበል ነው ብሎም በግልጽ አላስተማረም፤ ወይም ክርስቶስንና የጸጋውን ትሩፋት በዚሁ ሥርዐት አማካይነት ብቻ ማግኘት ይቻላል አላለም። በዚህም ንግግሩም የምስክሮች ቃል ውጤት ለሆነው እምነት አጽንዖትን ይሰጣል (ቊ 35፡40፡ 47፡51 ይመ)። ‘ሥጋ… ደም’ የሚለው ሐረግም ወደ ተሰቀለውና የሕይወት ምንጭ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ያመለክታል። ለድነት የሚያበቃው እምነት፣ በኢየሱስ መሥዋዕትነት ላይ እንዲመ ሠረት እግዚአብሔር የፈቀደው ነው፤ ሥርዐቶች ግን ለድነት አያበቁም።

6፥54 *በመጨረሻው ቀን፤* የቊ 39 ማብ ይመ።

6፥58 *ከሰማይ የወረደ እንጀራ፤* በቊ 49 እንደ ተመለከተው የመና ጠቀሜታ/ውሱን ሆኖ፣ ክርስቶስ ከሚሰጠው ሰማያዊ ምግብ ጋር ተነጻጽሯል። ኢየሱስ ከሰማይ ስለ መምጣቱ ወይም ከሰማይ የወረደ መና ስለ መሆኑ በዚሁ ምዕራፍ ላይ ደጋግሞ ተወስቷል።

6፥60 *የሚያስጨንቅ፤* ሊያስተውሉት ሳይሆን ሊቀበሉት የሚያስቸግር ንግግር ነበር፤ የሰው ልጅን ሥጋ መብላት፣ ደሙንም መጠጣት የሚለው የኢየሱስ ንግግር ለብዙኃኑ አይሁድ አድ ማጮቹ ያለ ጥርጥር የሚያስደነግጥ ነበር (የቊ 53-58 ማብ ይመ)።

6፥62 *የሰው ልጅ፤* የማር 8፥31፤ የሉቃ 6፥5፤ 19፥10 ማብ ይመ። *ቀድሞ ወደ ነበረበት፤* ኢየሱስ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በሰማይ የነበረ መሆኑን ያመለክታል። ሲወጣ፤ ኢየሱስ ስለ ከበረባቸው ሁኔታዎች ማለትም ከስቅለት ጀምሮ በተከታታይ ስለ ተፈጸሙት ድርጊቶች ሊሆን ይችላል (የ7፥39 ማብ ይመ)።

*6፥63፤* ከ3፥5፡6፡8 ጋር ያነጻጽሩ። *መንፈስም ሕይወትም ነው፤* መንፈስ ቅዱስ ለሰው ሕይወትን ለመስጠት የሚሠራው በቃሉ አማካይነት መሆኑ ያስታውቃል።

*6፥65፤* ለድነት ወደ ክርስቶስ መምጣት በሰው ጥረት የሚሆን አይደለም (ቊ 37፡39፡44-45 ይመ)።

6፥66 *ከዚህም በኋላ፤* ‘ከዚህም የተነሣ’፣ ወይም ከላይ የወረደው ሐረግ እንዳለ ማለት ሊሆን ይችላል። *ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ፤* ኢየሱስ፣ ደቀ መዝሙር መሆን ምን ማለት እንደ ሆነ በግልጽ አስተምሯል፤ ብዙዎች ግን እርሱ ባስተማራቸው መሠ ረት ሕይወትን ለመቀበል ዝግጁዎች አልነበሩም።

*6፥68፤* ተመሳሳይ በሆኑት ሦስቱ ወንጌሎች (የማቴዎስ፣ የማ ርቆስና የሉቃስ ወንጌሎች) ውስጥ እንደሚታየው ሁሉ፣ ጴጥሮስ እዚህም ላይ ሌሎቹን ደቀ መዝሙርት ወክሎ ሲናገር ይታያል። *የዘላለም ሕይወት ቃል፤* አጠቃላይ አገላለጽ ነው፤ ጴጥሮስ ግን የተናገረው በዘልማድ የያዘውን ሳይሆን፣ በልቡ ውስጥ የሠረጸውን የኢየሱስን ትምህርት ነው፤ በቊ.63 ላይ የተገለጸውንም እውነት አስተውሏል።

6፥69 *አምነናል፤ ዐውቀናልም፤* ግሶቹ የቅርብ ኀላፊ ጊዜን የሚያመለክቱ በመሆናቸው፣ ‘እስከ ዛሬ ድረስ ወዳለው እምነትና ዕውቀት አድማስ ደርሰናል’ የሚለውን ሐሳብ ያስተላልፋሉ። *አንድያ የእግዚአብሔር ቅዱስ፤* በማር 1፥24 እና በሉቃ 4፥34 እንደሚታወቀው አባባሉ ኢየሱስን የሚያመለክት ነው (ሐሥ

ከእናንተ አንዱ ዲያብሎስ ነው" አላቸው።
71የአስቆሮቱ የስምዖን ልጅ ይሁዳ፣ ከዐሥራ
ሁለቱ አንዱ ቢሆንም፣ ኋላ አሳልፎ ስለሚሰጠው
ስለ እርሱ መናገሩ ነበር።

## ኢየሱስ የዳስ በዓል ወደሚከበርበት ሄደ

7 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ፣ በዚያ የነበሩት
አይሁድ ሊገድሉት ስለ ፈለጉ፣ በይሁዳ
አውራጃ መዘዋወር ትቶ በገሊላ ተዘዋወረ።
2የአይሁድ የዳስ በዓል በተቃረበ ጊዜ ግን፣
3የኢየሱስ ወንድሞች እንዲህ አሉት፤ "ደቀ
መዛሙርትህም ደግሞ የምታደርገውን ታም
ራት እንዲያዩ፣ ከዚህ ወደ ይሁዳ ሂድ፤
4ራሱን ሊገልጥ እየፈለገ በስውር የሚሠራ
ማንም የለምና። አንተም እነዚህን ነገሮች
የምታደርግ ከሆነ፣ ራስህን ለዓለም ግለጥ።"
5የገዛ ወንድሞቹ እንኳ አላመኑበትም ነበር።
6ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "ለእኔ ትክ
ክለኛው ጊዜ ገና አልደረሰም፤ ለእናንተ ግን
ማንኛውም ጊዜ ምቹ ነው። 7ዓለም እናንተን
ሊጠላ አይችልም፤ እኔ ግን፣ አድራጎቱ ክፉ
መሆኑን ስለምመሰክርበት ይጠላኛል። 8እናንተ
ወደ በዓሉ ሂዱ፤ ለእኔ ትክክለኛው ጊዜ
ስላልደረሰ[ሠ] ወደ በዓሉ አልሄድም።" 9ይህን
ብሎአቸው በገሊላ ቈየ።
10ይሁን እንጂ፣ ወንድሞቹ ወደ በዓሉ ከሄዱ
በኋላ፣ እርሱም በግልጥ ሳይሆን በስውር
ወደ በዓሉ ሄደ። 11በበዓሉም ላይ አይሁድ፣

6፥71 ማቴ10፥4፤ 26፥14
7፥1 ቍ19፥25፤ ማቴ12፥14፤ ዮሐ1፥19
7፥2 ዘሌ23፥34፤ ዘዳ16፥16
7፥3 ማቴ12፥46
7፥5 መዝ69፥8፤ ማር3፥21
7፥6 ማቴ26፥18
7፥7 ዮሐ3፥19፡20፤ 15፥18፡19
7፥8 ቍ6፤ ማቴ26፥18
7፥11 ዮሐ11፥56
7፥12 ቍ40፡43
7፥13 ዮሐ9፥22፤ 12፥42፤19፥38፤ 20፥19
7፥14 ቍ28፤ ማቴ26፥55
7፥15 ማቴ13፥54፤ ዮሐ1፥19፤ ሐሥ26፥24
7፥16 ዮሐ14፥24
7፥17 መዝ25፥14
7፥18 ዮሐ5፥41፤ 8፥50፡54
7፥19 ቍ1፤ዘዳ 32፥46፤ማቴ12፥14፤ ዮሐ1፥17

"ያ ሰው የት አለ?" እያሉ ይፈልጉት ነበር።
12ስለ እርሱ በሕዝቡ መካከል ብዙ ጕም
ጕምታ ነበር። አንዳንዶች፣ "ደግ ሰው ነው"
አሉ።
ሌሎች ግን፣ "የለም፤ ሕዝቡን የሚያስት
ነው" አሉ። 13ይሁን እንጂ አይሁድን ከመፍራት
የተነሣ ስለ እርሱ በግልጽ የተናገረ ማንም
አልነበረም።

## ኢየሱስ በበዓሉ ላይ ተገኝቶ አስተማረ

14በበዓሉም አጋማሽ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅ
ደስ ወጥቶ ያስተምር ጀመር። 15አይሁድም
በመደነቅ፣ "ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን
እንዴት ሊያውቅ ቻለ?" አሉ።
16ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ "የማ
ስተምረው ትምህርት ከራሴ ሳይሆን፣ ከላከኝ
የመጣ ነው። 17ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ
ለማድረግ ቢፈልግ፣ የእኔ ትምህርት ከእግዚ
አብሔር ወይም ከራሴ የመጣ መሆኑን ለይቶ
ያውቃል፤ 18ከራሱ የሚናገር፣ ያን የሚያደ
ርገው ለራሱ ክብርን ስለሚሻ ነው፤ ስለ
ላከው ክብር የሚሠራ ግን እርሱ እውነተኛ
ነው፤ ሐሰትም አይገኝበትም። 19ሙሴ ሕግን
አልሰጣችሁምን? ነገር ግን አንዳችሁም ሕጉን
አልጠበቃችሁም። ለምን ልትገድሉኝ ትፈ
ልጋላችሁ?"

[ሠ]8 አንዳንድ ቅጆች ገና ስላልደረሰ ይላሉ

2፥27)።

6፥70 *ዲያብሎስ* ይሁዳን ማለቱ ነው (ቍ. 71)፤ በሰይጣን መንፈስ በመገፋፋት ኢየሱስን ተቃውሟልና።

6፥71 *አስቆሮቱ፤* 'ቄርዮት ከተባለ ስፍራ የመጣ ሰው' ማለት ነው፤ ቦታው በይሁዳ አውራጃ የሚገኝ ነበር (ኢሱ 15፥25)። አባትየው ወይም ልጁ ከዚያ መምጣታቸውን ሊያመለክት ይችላል (ከ12፥4 ጋር ያነጻጽሩ) ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል ከገሊላ ምድር ውጭ የሆነው ይሁዳ ብቻ ይመስላል።

7፥1-8፥59 ዮሐንስ፣ በወንጌሉ ከም 7 እስከ 8፣ በኢየሱስ ላይ የተነሣውን ከፍተኛ ተቃውሞና ሕይወቱን ለማጥፋት በተደጋጋሚ ስለ ተደረገው ሙከራ ጽፏል (7፥1፡13፡19፡25፡30፡32፡44፤ 8፥37፡40፡59)። ሐዋርያው፣ መሲሕነትን አስመልክቶ የተነሡትን ዐበይት ክርክሮች አንድ ላይ አቀናጅቶ በዚህ ክፍል ላይ መልስ ሰጥቶባቸዋል።

7፥1 *ከዚህ በኋላ፤* በ5፥1 እና በ6፥1 ላይ እንደሚታየው በዚህም ላይ ጊዜው ምን ያህል እንደ ሆነ አይታወቅም፤ ቢሆንም 6፥4 የፋሲካን በዓል ሲያመለክት፣ 7፥2 ደግሞ የአይሁድን የዳስ በዓል የሚያመለክት በመሆኑ፣ በሁለቱ በዓላት መካከል ያለውን የጊዜ ርቀት ስድስት ወር ያህል ያደርሰዋል።

7፥2 *የዳስ በዓል፤* አይሁድ በዓመት ውስጥ ከሚያከብሯቸው በዓላት መካከል ታላቁ ሲሆን፣ የመከር መሰብሰቢያ ማክተሚያ ወቅትንና አባቶቻቸው በምድረ በዳ ይጓዙና በድንኳን ይኖሩ በነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን በጎነት በማስታወስ የሚከበር ነው (ዘሌ 23፥33-43፤ ዘዳ 16፥13-15 ይመ፤ ከዘካ 14፥16-19 ጋር ያነጻጽሩ)። ስሙም በዓሉን የሚያከብረው ሕዝብ ለሰባት ቀን ከሚሰነብትበት የቅጠል ዳስ የተወረሰ ነው። የፋሲካ በዓል በተከበረ በስድስተኛው ወር አካባቢ ይከበራል።

7፥3 *ወንድሞች (የኢየሱስ)፤* የሉቃ 8፥19 ማብ ይመ።

7፥4፤ ወንድሞቹ ሌሎች ሰዎች ያላስተዋሉትን የኢየሱስን ታምራት በመገንዘባቸው ይሁን፣ ወይም መሲሕነት ሁሉ በኢየሩሳሌም ውስጥ መጽደቅ አለበት ማለታቸው ይሁን ግልጽ አይደለም፤ በኢየሱስ ስላላመኑ ምክራቸው ከልብ የመነጨ አልነበረም (ቍ. 5)።

7፥6 *ትክክለኛው ጊዜ፤* ኢየሱስ የሚሠራው ሁሉ በእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው (የ2፥4 ማብ ይመ)።

7፥7 *ዓለም፤* እግዚአብሔርን የሚቃወሙትን ሰዎች ወይም ከእግዚአብሔር ዓላማ አንጻር በተቃውሞ የተሰለፈውን የሰው ሥርዐት ሊያመለክት ይችላል (የ1፥9 ማብ ይመ)። ወንድሞቹ ከዓለም ጋር አንድ ስለ ሆኑ የዓለም ጥላቻ አያሰጋቸውም፤ ኢየሱስ ግን ዓለምን ይወቅስ ስለ ነበር ዓለም ጠላው።

7፥8 *ስላልደረሰ፤* ወንድሞቹ ባላሰቡት መሠረት ወደ አንድ ቅዱስ ስፍራ በዘልማድ እንደሚጓዝ ምእመን ተነሥቶ መሄድን ኢየሱስ አልፈቀደም እንጂ፣ ወደ በዓሉ የመሄዱን ሁኔታ አልተቃወመም፤ የሚሄደውም በተወሰነው 'ትክክለኛ ጊዜ' (ቍ. 6) ከእግዚአብሔር የተላከበትን የነቢይነት መልእክት ለሕዝብ ለማቅረብ ነው።

7፥10 *በግልጥ ሳይሆን፤* በአደባባይ እንዲወጣ ወንድሞቹ ያቀረቡትን ሐሳብ የሚቃወም ነው (ቍ. 4)።

7፥12 *ጕምጕምታ፤* በግልጽ መናገር የሚያስከትለው መዘዝ ስለ ነበር ነው (ከቍ. 13 ጋር ያነጻጽሩ)።

7፥14 *በበዓሉ አጋማሽ፤* የተሰበሰበው ሕዝብ ብዛት ከፍተኛ ቍጥር ላይ ሲደርስ ማለት ነው፤ በዚህ ጊዜ በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ማስተማሩ፣ ትምህርቱ ለብዙኃን እንዲደርስ ያመቻል።

7፥15 *አይሁድም፤* በቍ. 12 'ሕዝቡ' ተብለው ከተጠቀሱት ብዙኃን አይሁድ ሌላ ማለት ነው (የ1፥19 ማብ ይመ)። *ሳይማር፤* ኢየሱስን ማንም መምህር (ረቢ) ስላላስተማረው ነው።

7፥16 *ከራሴ ሳይሆን፤* 'መምህሩ' የላከው አባቱ ነበር (የ4፥34 ማብ ይመ)።

7፥17 *የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ቢፈልግ፤* ስለ ሕይወት ያለውን አጠቃላይ አቋም ይሳያል፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም የተዘጋጀ ሰው የኢየሱስን ትምህርት ተቀብሎ ያምንበታል (ከ6፥29 ጋር ያነጻጽሩ)። *ለይቶ ያውቃል፤* ያስተውላል ማለት ነው።

7፥18 *እውነተኛ፤* ኢየሱስ የራሱን ክብር ፈላጊ አለመሆኑን ማስተዋል አለባቸው። በዚህ ወንጌል ውስጥ ከእግዚአብሔር አብ በቀር 'እውነተኛ' የተባለ የለም (3፥33፤ 8፥26)። በዚህ ክፍል ደግሞ ኢየሱስ 'እውነተኛ' ተብሏል። ዮሐንስ እንደ ገና ጌታ ኢየሱስን ከእግዚአብሔር አብ ጋር አስተካክሎ ሲያቀርበው እናያለን።

[20]ሕዝቡም፣ “አንት ጋኔን ያደረብህ! ደግሞ
አንተን ማን ሊገድል ይፈልጋል?” አሉት።
[21]ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “አንድ
ሥራ ብሠራ፣ ሁላችሁም ተገረማችሁ። [22]ግዝ
ረት የመጣው ከአባቶች እንጂ ከሙሴ አይ
ደለም፤ ሆኖም ሙሴ ግዝረትን ስለ ሰጣችሁ
በሰንበት እንኳ ሕፃን ትገርዛላችሁ። [23]የሙሴ
ሕግ እንዳይሻር ሕፃን በሰንበት የሚገረዝ ከሆነ፣
የሰውን ሁለንተና በሰንበት ስለ ፈወስሁ ለምን
በእኔ ላይ ትቈጣላችሁ? [24]የሰውን ፊት በማ
የት መፍረድ ትታችሁ ቅን ፍርድ ፍረዱ።”

## ኢየሱስ፣ እርሱ ክርስቶስ ስለ መሆኑ

[25]በዚህ ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበሩ አንዳንድ
ሰዎች እንዲህ አሉ፤ “ሊገድሉት የሚፈልጉት
ሰው ይህ አይደለምን? [26]ይኸው እርሱ በአደ
ባባይ ይናገራል፤ አንድም ቃል አይናገሩትም፤
ክርስቶስ[a] ነው ብለው ባለ ሥልጣኖቹም
ተቀብለውት ይሆን? [27]ይህ ሰው ግን ከየት
እንደ ሆነ እኛ እናውቃለን፤ ክርስቶስ ሲመጣ
እኮ ከየት እንደ ሆነ ማንም አያውቅም።”
[28]ኢየሱስ በቤተ መቅደስ አደባባይ ሲያስ
ተምር ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ፤
“አዎን፣ እኔን ታውቁኛላችሁ፤ ከየት እንደ
ሆንሁም ታውቃላችሁ። እኔ እዚህ ያለሁት
በግዛ ራሴ አይደለም፤ ነገር ግን የላከኝ እርሱ
እውነተኛ ነው። እናንተ አታውቁትም፤ [29]እኔ
ግን ከእርሱ ዘንድ ስለ ሆንሁ፣ እርሱም ስለ
ላከኝ ዐውቀዋለሁ።”
[30]ስለዚህ ሊይዙት ፈለጉ፤ ነገር ግን ጊዜው
ገና ስላልደረሰ ማንም እጁን አላሳረፈበትም፤
[31]ሆኖም ከሕዝቡ ብዙዎች በእርሱ አምነው፣
“ታዲያ፣ ክርስቶስ ሲመጣ ይህ ሰው ከሚ
ሠራቸው ታምራዊ ምልክቶች የበለጠ ያደር
ጋል?” አሉ።
[32]ፈሪሳውያን፣ ሕዝቡ ስለ እርሱ በጕም
ጕምታ የሚነጋገረውን ሰሙ፤ የካህናት አለ
ቆችና ፈሪሳውያንም እንዲይዙት የቤተ
መቅደስ ጠባቂዎችን ላኩባቸው።
[33]ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ “ከእናንተ ጋር
የምቈየው ጥቂት ጊዜ ነው፤ ከዚያም ወደ
ላከኝ እሄዳለሁ፤ [34]ትፈልጉኛላችሁ፤ ግን አታ
ገኙኝም፤ ወዳለሁበትም ልትመጡ አትችሉም።”
[35]አይሁድም እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባ
ባሉ፤ “ይህ ሰው፣ ልናገኘው የማንችለው ወዴት
ለመሄድ ቢያስብ ነው? በግሪኮች መካከል
ተበታትነው ወደሚኖሩት ወገኖቻችን ሄዶ
ግሪኮችን ሊያስተምር ፈልጎ ይሆን? [36]‘ትፈ
ልጉኛላችሁ፤ ግን አታገኙኝም፤’ ደግሞም፣
‘እኔ ወዳለሁበት ልትመጡ አትችሉም’ ሲል ምን
ማለቱ ይሆን?”
[37]የበዓሉ መጨረሻ በሆነው በታላቁ ቀን፣
ኢየሱስ ቆሞ ከፍ ባለ ድምፅ እንዲህ አለ፤

[a]26 ወይም *መሲሑ፤* እንዲሁም ቍ 27፡31፡41 እና 42 ይመ

7፥20 ማር3፥22
7፥21 ቍ23፤ ዮሐ5፥2-9
7፥22 ዘፍ17፥10-14፤ዘሌ12፥3
7፥24 1ሳሙ16፥7፤ ኢሳ11፥3፡4፤ ዮሐ8፥15፤2ቆሮ10፥7
7፥25 ቍ1፤ ማቴ 12፥14
7፥26 ቍ48፤ ዮሐ4፥29
7፥27 ማቴ13፥55፤ ሉቃ4፥22፤ዮሐ6፥42
7፥28 ቍ14፤ ዮሐ8፥14፡26፡42
7፥29 ማቴ11፥17፤ ዮሐ3፥17
7፥30 ቍ32፡44፤ ማቴ26፥18፤ ዮሐ10፥39
7፥31 ዮሐ2፥11፤ 8፥30፤10፥42፤ 11፥45፤12፥11፡42
7፥33 ዮሐ12፥35፤ 13፥33፤16፥5፡10፡ 16፡17፡28
7፥34 ቍ36፤ ዮሐ8፥21፤13፥33
7፥35 ዮሐ12፥20፤ ሐሥ17፥4፤18፥4፤ ያዕ1፥1
7፥36 ቍ34
7፥37 ዘሌ23፥36፤ ኢሳ55፥1፤ራእ22፥17

7፥19 *ሕግ፤* አይሁድ የኦሪትን ሕግ ለመቀበል የተመረጡ በመሆናቸው ይኵራራሉ (ከሮሜ 2፥17 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይሁን እንጂ፣ ይህን ያህል የተኵራሩበትን ሕግ ሁላቸውም ያፈረሱት መሆናቸውን ኢየሱስ ይነግራቸዋል።

7፥20 *ሕዝቡ፤* ምናልባት በቍ 1 ላይ ኢየሱስን ለመግደል ከሞከሩትና በቍ 25 ላይ ስለዚሁ የግድያ ሤራ ከሚያውቁት ‘አይሁድ’ ሌላ፣ በዓሉን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም የመጡትን ሰዎች ሊያመለክት ይችላል። *ጋኔን ያደረብህ፤* የዚህ ዓይነቱ የስድብ ቃል በዚሁ በዮሐንስ ወንጌል በሌላ ቦታ ተመልክቷል (ለምሳሌ 8፥48-52፤ 10፥20-21 ይመ፤ ከማቴ 12፥24-32፤ ከማር 3፥22-30 ጋር ያነጻጽሩ)።

7፥21 *አንድ ሥራ፤* ስለ ሰንበት የተነሣው ክርክር እንደ ሚያሳየው፣ ሽባውን ሰው የማዳኑን ታምር (5፥1-9) የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

7፥22 *ግዝረት፤* እስራኤላውያን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ መሆናቸውን የሚገልጹበት ሥርዐት ነው፤ ሥርዐቱም የሚመለከተው ወንዶችን ብቻ ነው። ሙሴ በሰጠው ሕግ ላይ የግዝረት አስፈላጊነት ታክሏል (ዘፀ 12፥44፡48፤ ዘሌ 12፥3)። ነገር ግን ይህ ሥርዐት የተሰጠው ለሙሴ ሳይሆን ቀደም ብሎ ለአብርሃም ነበር (ዘፍ 17፥9-14)። ሥራ በማይሠራበት የሰንበት ቀን ላይ ቢውልም እንኳ፣ በዘሌ 12፥3 የተጻፈውን መሠረት በማድረግ ስምንት ቀን ከሞላ መፈጸም አለበት ብለው አይሁድ ያምናሉ። ክርክሩን በአግባቡ ለማስተዋል ይህን ልዩ ሁኔታ መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው (ቍ 23)። ኢየሱስ፣ ሰንበት አይከበርም ወይም የአይሁድ ሕግ ሸክም ነው ማለቱ ሳይሆን፣ ተቃዋሚዎቹ ሰንበት ምን ማለት እንደ ሆነ አለመረዳታቸውን ለማስገንዘብ ነበር። ስለ ግዝረት የተሰጠው ሕግ የሚያሳየው፣ በሰንበት ቀን ሥራ ሊከናወን እንደሚችል ብቻ ሳይሆን፣ አስፈላጊ ከሆነ መሥራት እንደሚገባም ነው፤ በጎ ሥራም ከዚህ ተለይቶ ሊታይ አይችልም።

7፥25 *በኢየሩሳሌም የነበሩ…ሰዎች፤* በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ዓይነት አገላለጽ የሚገኘው በዚህ ክፍልና በማር 1፥5 ላይ ብቻ ነው። ምናልባትም ኢየሩሳሌም ውስጥ በተቃውሞ የተነሣውን ሕዝብ ያመለክታል (የቍ 20 ማብ ይመ)፤ ሕዝቡ ^ኢየሱስ ላይ ባያሤርም ሤራው መኖሩን ያውቅ ነበር።

7፥26 *ባለ ሥልጣኖቹ ተቀብለውት ይሆን?* በግሪኩ ው አቀማመጥ አሉታዊ መልስን የሚጠብቅ ነው። *ክርስቶስ፤* የ1፥25 ማብ ይመ።

7፥27 *ከየት እንደ ሆነ ማንም አያውቅም፤* አንዳንድ አይሁድ፣ የመሲሑ አመጣጥ ከየት እንደ ሆነ ብሉይ ኪዳን ያመለክታል ብለው ያምናሉ (ከቍ 42፤ ከማቴ 2፥4-6 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ሌሎቹ ግን አያመለክትም ይላሉ፤ ምክንያቱም መሲሕ እንዲሁ ሳይታሰብ በድንገት እንደሚመጣ በብዙኃኑ ዘንድ ይታመን ነበር።

7፥28 *እኔን ታውቁኛላችሁ፤* በአንድ በኩል ኢየሱስ ከናዝሬት እንደ መጣ ያውቃሉ፤ በሌላ በኩል ግን ኢየሱስን ሆነ አብን በጥልቀት ስለማያውቁ የምጸት አነጋገር ነው (8፥19)። ኢየሱስ በአባቱ ፈቃድ እንደሚመላለስ እንደ ገና በማመልከት (ከ4፥34 ጋር ያነጻጽሩ)፣ እርሱ እግዚአብሔርን በትክክል እንደሚያውቅ፣ እነርሱ ግን እንደማያውቁ ግልጽ አደረገ፤ እነርሱ ባይገነዘቡትም፣ አመጣጡም ሆነ ተልእኮው ከእግዚአብሔር ነው።

7፥30 *ሊይዙት ፈለጉ፤* ጊዜው እስካልደረሰ ድረስ፣ ተቃዋሚዎቹ ኢየሱስን ለመያዝ ኀይል አልነበራቸውም (የ2፥4 ማብ ይመ)።

7፥31 *ሕዝቡ፤* በዓሉን ለማክበር የመጡትን ያመለክታል (የቍ 20 ማብ ይመ)። ብዙዎቹም ከታምራቱ የተነሣ አምነዋል (ከ6፥26 ጋር ያነጻጽሩ)።

7፥32 *ፈሪሳውያን፤* የማቴ3፥7፤ የማር2፥16፤ የሉቃ5፥17 ማብ ይመ። *የካህናት አለቆች፤* በጊዜው ያስተዳድር የነበረው የካህናት አለቃ አንድ ብቻ ነው፤ ይሁን እንጂ የሮም ገዥዎች ብዙዎቹን የካህናት አለቆች ከሥልጣን አውርደውአቸው ስለ ነበር፣ በዚህ ስፍራ በቀድሞ ማዕረጋቸው ‘የካህናት አለቆች’ የተባሉት ለወጉ ያህል ነበር።

7፥33 *ከዚያም…እሄዳለሁ፤* ኢየሱስ የንግግሩን ርእስ በረቀቀ መንገድ ከታምራቱ ወደ ሞቱ ለወጠው (ቍ 34)።

7፥35 *በግሪኮች መካከል ተበታትነው፤* ከምርኮ ዘመን ጀምሮ ብዙ አይሁድ ከመካከለኛው ምሥራቅ ተሰደው በአያሌ የሮም ግዛት ከተሞች (በግሪክ አገር) ይኖሩ ነበር።

7፥37 *የበዓሉ መጨረሻ… ቀን፤* ሰባተኛው ወይም ስምንተኛው ቀን ሊሆን ይችላል። ይህ በዓል ሰባት ቀን ሙሉ ይከበራል (ዘሌዋ 23፥34፤ ዘዳ 16፥13፡15)፤ ስምንተኛው ቀን ግን ‘የመደምደሚያ ጉባኤ’ ነው (ዘሌ 23፥36)፤ የማር 14፥12 ማብ ይመ። *ቆሞ ከፍ ባለ ድምፅ…አለ፤* ብዙውን ጊዜ መምህራን

'ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤
38በእኔ የሚያምን፣ መጽሐፍ እንዳለ[e] የሕይወት
ውሃ ምንጭ ከውስጡ ይፈልቃል።" 39ይህን
ያለው በእርሱ የሚያምኑ ስለሚቀበሉት መንፈስ
ነበር፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ገና ስላልከበረ
መንፈስ አልተሰጠም ነበር።
40ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ቃሉን ሰምተው፣
"ይህ ሰው በእርግጥ ነቢዩ ነው" አሉ።
41ሌሎችም፣ "እርሱ ክርስቶስ ነው" አሉ።
ሌሎች ደግሞ እንዲህ አሉ፤ "ክርስቶስ ከገ
ሊላ እንዴት ሊመጣ ይችላል? 42መጽሐፍ፣
ክርስቶስ ከዳዊት ዘር[f]፣ ዳዊትም ከኖረበት
ከቤተ ልሔም እንደሚመጣ ይናገር የለምን?"
43ስለዚህም በኢየሱስ ምክንያት በሕዝቡ መካ
ከል መለያየት ሆነ፤ 44አንዳንዶቹም ሊይዙት
ፈለጉ፤ ነገር ግን ማንም እጁን አላሳረፈበትም።

## የአይሁድ መሪዎች አለማመን

45በመጨረሻም የቤተ መቅደስ ጠባቂዎቹ፣
ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ፈሪሳውያን ተመ
ልሰው ሄዱ፤ እነርሱም ጠባቂዎቹን፣ "ለምን
አላመጣችሁትም?" አሏቸው።
46ጠባቂዎቹም፣ "እንደዚህ ሰው፣ ከቶ ማንም
ተናግሮ አያውቅም" ሲሉ መለሱ።
47ፈሪሳውያንም እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ "እና
ንተም ተታላችኋል ማለት ነው? 48ለመሆኑ
ከባለሥልጣኖችና ከፈሪሳውያን በእርሱ ያመነ
አለ? 49ሕጉን የማያውቅ ይህ ሕዝብ ግን
የተረገመ ነው።"
50ከዚህ ቀደም ወደ ኢየሱስ ሄዶ የነበ
ረውና ከእነርሱ አንዱ የሆነው ኒቆዲሞስ እንዲህ
አላቸው፤ 51"ሕጋችን፣ አስቀድሞ አንድን ሰው
ሳይሰማና ምን እንዳደረገ ሳይረዳ ይፈርድበ
ታልን?"
52እነርሱም፣ "አንተም ደግሞ ከገሊላ ነህን?
ነቢይ ከገሊላ እንደማይነሣ መርምር፤ ትደር
ስበታለህ" ብለው መለሱለት።
53ከዚህ በኋላ ሁሉም ወደየቤታቸው ሄዱ።

## በምንዝር የተያዘች ሴት

8 ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ሄደ። 2በማ
ለዳም በቤተ መቅደስ አደባባይ እንደ
ገና ታየ፤ ሕዝቡም በዙሪያው ተሰበሰበ፤ ሊያስ
ተምራቸውም ተቀመጠ። 3የኦሪት ሕግ መምህ
ራንና ፈሪሳውያን በምንዝር የተያዘች ሴት
አመጡ፤ በሕዝቡም ፊት አቁመዋት፣ 4ኢየ
ሱስን እንዲህ አሉት፤ "መምህር ሆይ፣ ይህች
ሴት ስታመነዝር ተያዘች፤ 5ሙሴም፣ እንደዚች
ያሉ ሴቶች በድንጋይ እንዲወገሩ በሕጉ አዞ
ናል፤ አንተስ ምን ትላለህ?" 6ይህን ጥያቄ
ያቀረቡለት፣ እርሱን የሚከሱበት ምክንያት
ለማግኘት ሲፈትኑት ነው።

[e]37:38 *ወይም ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣ፤ 38በእኔ የሚያምን ይጠጣ*
[f]42 *ወይም ከዳዊት ቤተ ሰብ*

7፥38 ዮሐ3፥15፤ 4፥10፡14፤ኢሳ58፥11
7፥39 ኢዩ2፥28፤ ዮሐ1፥33፤12፥23፤ 20፥22፤ሐሥ2፥17፡ 33፤13፥31፡32
7፥40 ማቴ21፥11
7፥41 ቍ52፤ ዮሐ1፥46
7፥42 ማቴ1፥1፤ 2፥5፡6፤ሉቃ2፥4፤ ሚክ5፥2
7፥43 ዮሐ6፥52፤ 9፥16፤10፥19
7፥44 ቍ30
7፥46 ማቴ7፥28
7፥47 ቍ12
7፥48 ዮሐ12፥42
7፥50 ዮሐ3፥1፤ 19፥39
7፥52 ቍ41
8፥1 ማቴ21፥1
8፥2 ቍ20፤ ማቴ 26፥55
8፥5 ዘሌ20፥10፤ ዘዳ22፥22፤ ኢዮ31፥11
8፥6 ማቴ12፥10፤ 22፥15፡18

ተቀምጠው ያስተምሩ ነበር፤ ኢየሱስ ግን ቆሞ በመናገሩ አድማጮቹ ለመልእክቱ ልዩ ትኵረት ሰጡ።

7፥38 *የሕይወት ውሃ፤* የ4፥10 ማብ ይመ።

7፥39 *መንፈስ፤* በቍ 38 ላይ፣ 'የሕይወት ውሃ' ያለውን ያብራራል። *አልተሰጠም ነበር፤* መንፈስ ቅዱስ በጰንጠቆስጤ (በበዓለ ኀምሳ ዕለት) በተሰጠው መልክ አልወረደም ነበር ማለት ነው (ሐሥ2 ይመ)። *ስላልከበረ፤* እዚህ ቦታ ላይ ስቅለቱ፣ ትንሣኤውንና ዕርገቱን ያመለክታል (የ13፥31 ማብ ይመ)። መንፈስ ቅዱስ በሙላት እንዲሠራ የኢየሱስ የማዳን ሥራ አስቀድሞ መከናወን ነበረበት።

7፥40 *ሕዝቡ፤ ቍ 20* ላይ 'ሕዝብ' ከተባለው ጋር አንድ ነው (የቍ 20 ማብ ይመ)።

7፥42 *ቤተ ልሔም፤* መሲሑ ከየት እንደሚመጣ የተለያዩ ሐሳቦች ተሰንዝረው ነበር (ከቍ 27 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ከእነዚህም አንዱ ቤተ ልሔም ነው።

7፥43 *መለያየት ሆነ፤* ዮሐንስ፣ ኢየሱስን በተመለከተ በሕዝቡ መካከል ሦስት ጊዜ መከፋፈል እንደ ነበር ይገልጻል፤ ይኸውም በዚህ ክፍል ስለ ማን ነቱ፣ በ9፥16 ስለ ሥልጣኑ፣ በ10፥19 ስለ ሕማማቱ ነበር።

7፥46 *ጠባቂዎቹ፤* ኢየሱስን አለመያዛቸው መዘዝ እንደሚያመጣባቸው ያውቃሉ፤ ሆኖም የሕዝቡን ተቃውሞ በፈሪሳውያን ፊት እንደ ምክንያት አላቀረቡም፤ በኢየሱስ ትምህርት ተመስጠው ስለ ነበርም ሊያደናቅፉት አልፈለጉም።

7፥47 *ፈሪሳውያንም...መለሱ፤* መልሳቸው እጅግ፣ ሳይጠበሳጩ እንዳልቀሩ ያሳያል፤ እንደተለመደው ከሆነ፣ የካህናት አለቆች ጠባቂዎቹን መገሠጽ ነበረባቸው።

7፥49 *ይህ ሕዝብ፤* በዓሉን ለማክበር የመጣውን ሕዝብ የሚያመለክት ነው (የቍ 20 ማብ ይመ)። *የማያውቅ (ሕጉን)፤* ፈሪሳውያን፣ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል አለማወቁን አጋንነዋል (ከቍ 42 ጋር ያነጻጽሩ)። ፈሪሳውያን በእጅጉ የሚጨነቁለትን ጥቃቅኑን ሥርዐት፣ ተራው አይሁዳዊ ሥራዬ ብሎ አይጨነቅበትም። በጕልበቱ የሚተዳደረው ብዙኃኑ ሙያተኛ 'የአባቶች ልማድ' ታላቅ ሸክም ስለሚሆንበት፣ ግምት አይሰጠውም ነበር።

*7፥50-51፤* እዚህ ላይ የሚያስገርም ነገር ይታያል፤ ፈሪሳውያን፣ በኀላፊነት ላይ የሚገኝ ማንም የሸንጎ አባል በኢየሱስ አላመነም ሲሉ (ቍ 48-49)፣ የአይሁድ አለቃ የነበረው ኒቆዲሞስ ግን (3፥1) ስለ ጌታ መሰከረ። በሕጉ መሠረት እንዲመላለስ ሕዝቡን ይገፋፉ እንጂ፣ ራሳቸው ሕጉን መጠበቅ እንደ ተሳናቸው ኒቆዲሞስ አመልክቷል።

7፥52 *ነቢይ ከገሊላ እንደማይነሣ፤* 1፥46 ይመ። ተቈጥተውና ስሕተትም ላይ ወድቀው ነበር፤ ዮናስ የመጣው ከገሊላ ነበርና፤ ሌሎች ነቢያትም እንደዚሁ ከዚያው ሳይመጡ አልቀረም። ከሁሉም በላይ ግን፣ እግዚአብሔር ነቢያትን ከፈቀደው ቦታ ማስነሣት እንደሚችል ፈሪሳውያን አላስተዋሉም።

*7፥53-8፥11፤* በዚህ ክፍል የሚገኘው ታሪክ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ በጥንቱ ቅጂ ያልሰፈረ ሊሆን ይችላል። ታሪኩ የሚገኝባቸው ሌሎች ቅጂዎች መዝግበውት የሚገኘው በሌላ ቦታ ነው (ለምሳሌ ከሉቃ 21፥38 ቀጥሎ)፤ ይሁን እንጂ ታሪኩ እውነተኛ መሆኑ አያጠራጥርም።

*7፥53፤* ይህ ቍጥር (ከ8፥1 ጋር ሲታይ)፣ ታሪኩ ከመጀመሪያውኑ ከሌላ ታሪክ ጋር ተያይዞ እንደ ነበር ያስገነዝባል፤ በቍ 45-52 በተገለጸው የአይሁድ ሸንጎ ላይ ኢየሱስ አልነበረምና።

8፥1 *ደብረ ዘይት፤* የማር 11፥1 ማብ ይመ።

8፥3 *የኦሪት ሕግ መምህራን፤* የማቴ 2፥4፤ የሉቃ 5፥17 ማብ ይመ። *በምንዝር የተያዘች ሴት፤* ይህን ኀጢአት አንድ ሰው ብቻውን ሊፈጽመው ስለማይችል፣ ሴትዮዋ ብቻ ለፍርድ ለምን ቀረበች? የሚለው ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም። ክሱ የተቀናጀው ኢየሱስን ለመፈተን ተብሎ ነው (ቍ6)፤ ሰውዬውም ሆን ተብሎ እንዲያመልጥ ሳይደረግ አይቀርም። ከሳሾቿ፣ ሴትዮዋን እስር ቤት አቆይተው ስለ ሁኔታው ኢየሱስን ማነጋገር ሲችሉ፣ አደባባይ እንድትወጣ ማድረጋቸው ሊያዋርዷት ፍላጎት እንደ ነበራቸውም ያሳያል።

8፥4 *ስታመነዝር ተያዘች፤* የአይሁድ ሕግ የዓይን ምስክር የሚፈልግ በመሆኑ፣ እንደ ሁኔታው የሚቀያየር መረጃ በቂ ሊሆን አይችልም።

8፥5 *እንደዚች ያሉ ሴቶች በድንጋይ እንዲወገሩ፤* ይህን ሲሉ፣ ሕጉን በመጠኑ ለውጠዋል፤ ሴቲቱ የታጨች ድንግል ካልሆነች በቀር፣ እንደዚህ ላለው አጋጣሚ የሞት ቅጣት አልተደነገገም (ዘዳ 22፥23-24)። ሕጉ ሴትዮዋ ብቻ ሳትሆን ሁለቱም ጥፋተኞች በድንጋይ ተወግረው እንዲሞቱ ያዛል (ዘሌ 20፥10፤ ዘዳ 22፥22)።

8፥6 *ይህን ጥያቄ ያቀረቡለት፣ እርሱን የሚከሱበት ምክንያት ለማግኘት ሲፈትኑት ነው፤* አይሁድ የሞት ፍርድ

ኢየሱስ ግን ጎንበስ ብሎ በጣቱ በምድር
ላይ ይጽፍ ጀመር። [7]በጥያቄ ሲወተውቱት
ቀና ብሎ፣ "ከእናንተ ኀጢአት የሌለበት እርሱ
አስቀድሞ ድንጋይ ይወርውርባት" አላቸው።
[8]እንደ ገናም ጎንበስ ብሎ በምድር ላይ ጻፈ።
[9]ይህን እንደ ሰሙ፣ ከሽማግሌዎች ጀምሮ
አንድ በአንድ ወጡ፤ ሴትዮዋም እዚያው
ፊቱ እንደ ቆመች ኢየሱስ ብቻውን ቀረ።
[10]ኢየሱስም ቀና ብሎ፣ "አንቺ ሴት፣ ሰዎቹ
የት ሄዱ? የፈረደብሽ የለምን?" አላት።
[11]እርሷም፣ "ጌታ ሆይ፤ አንድም የለም"
አለች።
ኢየሱስም፣ "እኔም አልፈርድብሽም፤ በይ
ሂጂ፤ ከእንግዲህ ግን ኀጢአት አትሥሪ"
አላት።*

## የኢየሱስ ምስክርነት እውነት መሆኑ

[12]ኢየሱስ እንደ ገና ለሰዎቹ፣ "እኔ የዓለም
ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝም የሕይወት ብርሃን
ይሆንለታል እንጂ ከቶ በጨለማ አይመላ
ለስም" አላቸው።
[13]ፈሪሳውያንም፣ "አንተ ስለ ራስህ ስለምት
መሰክር፣ ምስክርነትህ ተቀባይነት የለውም"
አሉት።
[14]ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ "እኔ
ስለ ራሴ ብመሰክር ከየት እንደ መጣሁና
ወዴት እንደምሄድ ስለማውቅ ምስክርነቴ
እውነት ነው፤ እናንተ ግን ከየት እንደ መጣሁ
ወይም ወዴት እንደምሄድ የምታውቁት ነገር
የለም። [15]እናንተ እንደ ሰው አስተሳሰብ ትፈር
ዳላችሁ፤ እኔ በማንም አልፈርድም፤ [16]ብፈር
ድም፣ ከላከኝ ከአብ ጋር እንጂ ብቻዬን
ስላልሆንሁ ፍርዴ ትክክል ነው።
[17]የሁለት ሰዎች ምስክርነት ተቀባይነት
እንዳለው በሕጋችሁ ተጽፎአል። [18]ስለ ራሴ
የምመሰክር አንዱ እኔ ነኝ፤ ሌላውም ምስክሬ
የላከኝ አብ ነው።"
[19]ከዚያም፣ "አባትህ የት ነው?" አሉት።
ኢየሱስም፣ "አባቴንም እኔንም አታውቁም፤
እኔን ብታውቁኝ ኖሮ፣ አባቴንም ባወቃችሁ
ነበር" ሲል መለሰላቸው። [20]ኢየሱስ ይህን
የተናገረው በቤተ መቅደሱ ግቢ፣ በግምጃ
ቤት አጠገብ ሲያስተምር ነበር፤ ይሁን እንጂ
ጊዜው ገና ስላልደረሰ ማንም አልያዘውም።
[21]ኢየሱስም እንደ ገና፣ "እኔ እሄዳለሁ፤
እናንተም ትፈልጉኛላችሁ፤ በኀጢአታችሁም
ትሞታላችሁ፤ እኔ ወደምሄድበት ግን ልት
መጡ አትችሉም" አላቸው።
[22]አይሁድም፣ "'እኔ ወደምሄድበት ልት
መጡ አትችሉም' ያለው ራሱን ሊገድል
ይሆን?" አሉ።
[23]እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ "እናንተ
ከታች ናችሁ፤ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ
ዓለም ናችሁ፤ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም።
[24]በኀጢአታችሁ እንደምትሞቱ ነግሬአችኋ
ለሁ፤ እኔ እርሱ ነኝ[ፐ] ስላችሁ እኔ እርሱ እንደ
ሆንሁ ካላመናችሁ፣ በኀጢአታችሁ ትሞታላችሁ።"

8፥7 ዘዳ17፥7፤ ሕዝ 16፥40፤ ሮሜ2፥1፡22
8፥11 ዮሐ3፥17፤ 5፥14
8፥12 ምሳ4፥18፤ ማቴ5፥14፤ዮሐ1፥4፤ 6፥35
8፥15 ዮሐ3፥17፤ 7፥24
8፥16 ዮሐ5፥30
8፥17 ማቴ18፥16
8፥18 ዮሐ5፥37
8፥19 ዮሐ16፥3፤ 1ዮሐ2፥23
8፥20 ማቴ26፥18፡ 55፤ማር12፥41
8፥21 ሕዝ3፥18፤ ዮሐ7፥34፤13፥33
8፥23 ዮሐ3፥31፤ 17፥14
8፥24 ዮሐ4፥26፤ 13፥19

[ሠ]52 ሁለት የጥንት ቅጆች ነቢዩ ይላሉ
[ፐ]24 ወይም ያ ያልሁት እርሱ እኔ ነኝ፤ እንዲሁም ቍ28 ይመ

*ብዙ የጥንት ቅጆች ይህ ክፍል (7፥53-8፥11) የላቸውም፤ ወይም በሌላ ስፍራ ወይም በሌሎች ወንጌሎች ያስገቡታል።

እንዲፈርዱ ሮማውያን አይፈቅዱላቸውም (18፥31)፤ ስለዚህ ሴትዮዋ በድንጋይ እንድትወገር ኢየሱስ ቢፈቅድላቸው ኖሮ በሮ ማውያን ዘንድ ያስጠይቀው ነበር፤ መወገር የለባትም ቢል ደግሞ የሙሴን ሕግ ጥሶአል ተብሎ ይከሰስ ነበር። *ይጽፍ ጀመር*፤ ኢየሱስ መሬት ላይ ምን እንደ ጻፈ በትክክል ማወቅ ባይቻልም ክሳቸውን አለመቀበሉን ሊያመለክት ይችላል።

8፥7 *አስቀድሞ (ይወርውርባት)*፤ የኢየሱስ መልስ አሳፍሮ አቸዋል፤ ምክንያቱም 'ድንጋይ ይወርውርባት' በማለቱ፣ የአሪትን ሕግ አልጠበቀም ተብሎ ሊከሰስ አይችልም፤ ሴትዮዋ ተወግራለች ተብሎ እንዳይከሰስም በድንጋይ ለመውገር ብቃት ያለው ሰው አልተገኘም። *ኀጢአት የሌለበት*፤ አጠቃላይ ሐሳቡ፣ 'ይህን ኀጢአት ያልፈጸመ' ማለት ብቻ ሳይሆን፣ 'ምንም ዓይ ነት ኀጢአት ያላደረገ' ማለት ነው።

8፥9 *...ወጡ፤* ከእነርሱ 'ኀጢአት የሌለበት' አልነበረምና (ቍ 7)። *ከሽማግሌዎች ጀምሮ*፤ የነገሩ ጠንሳሾችና መሪዎች እንደ መሆናቸው፣ ለመግባትም ሆነ ለመውጣት ቅድሚያ ስለሚ ሰጣቸው፣ እንዲሁም መልሱ የሚመለከተው እነርሱኑ በመሆኑ አስቀድመው ወጡ፤ ይሁን እንጂ በዚያ የነበሩት ሰዎች ሁሉም ኅሊናቸው ወቅሷቸዋል ወይም ፍርሃት ገብቷቸዋል። በመጨ ረሻም ኢየሱስና ሴትዮዋ ብቻ ቀሩ።

8፥10 *አንቺ ሴት*፤ የተግሣጽ አጠራር አይደለም (አገባቡን ከ19፥26 ጋር ያነጻጽሩ)።

8፥11 *እኔም አልፈርድብሽም*፤ ወደ ንስሐና ወደ ድኅነት የሚያደርስ ንግግር ነው። *በይ ሂጂ፤ ከእንግዲህ ግን ኀጢአት አትሥሪ፤* ሴትዮዋ ቀድሞ የፈጸመችውን በደል ኢየሱስ ችላ ብሏል ማለት አይደለም።

8፥12 *እኔ...ነኝ፤* የ6፥35 ማብ ይመ። *ብርሃን*፤ 1፥4 እና ማብ፤ 9፥5፤ 12፥46 ይመ። እንዲሁም 1ዮሐ1፥5 'እግዚአብሔር ብርሃን ነው' ይላል፤ የኢየሱስ ተከታዮችም ከእርሱ የተገኘውን ብርሃን የሚያንጸባርቁ እንደ መሆናቸው መጠን፣ 'የዓለም ብርሃን' ተብለዋል (ማቴ 5፥14፤ ከፊል 2፥15 ጋር ያነጻጽሩ)። *ጨለማ*፤ የዚህ ዓለምና የሰይጣን ሥራ ማለት ነው። *የሕይወት ብርሃን*፤ 'እግዚአብሔር ብርሃን ነው' (1ዮሐ 1፥5)፤ የእሳት ዐምድ ለእስራኤላውያን በጕዞአቸው ብርሃን እንደ ሆነላቸው ሁሉ (ዘፀ13፥21፤ ነህ9፥12 ይመ)፣ ከእግዚአብሔር የተላከው ኢየሱስም የሕይወት መንገድ ብርሃን ነው።

8፥13 *ፈሪሳውያን*፤ የማቴ 3፥7፤ የማር 2፥16፤ የሉቃ 5፥17 ማብ ይመ።

*8፥14፤* ኢየሱስ ሲመልስ ሁለት ጕዳዮችን ግልጽ አድርጓል፦ ሀ) እርሱ ራሱ ምስክርነት ለመስጠት ብቁ መሆኑንና፣ ፈሪሳውያን ግን አለመሆናቸውን፤ ለ) እርሱ ከየት እንደ ሆነና ወዴት እን ደሚሄድ ማወቁን፣ እነርሱ ግን አንዱንም አለማወቃቸውን (ለሁለተኛው ሐሳብ በቍ16-18 የተጻፈውን ማብ ይመ)።

*8፥15፤* የፈሪሳውያን ፍርድ ውሱንና ምድራዊ ነበረ፤ ኢየሱስ፣ እነርሱ ፍርድን ፈርደሃል ባሉት መንገድ ፈጽሞ አልፈ ረደም፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እነርሱ በተረዱት መንገድ ሳይሆን፣ በትክክለኛው መንገድ ፈርዷል (ቍ 26)።

*8፥16-18፤* ሁለተኛው የኢየሱስ ሐሳብ የሕግ ድጋፍ ያለው ነው፤ አባቱ ከእርሱ ጋር ስላለ፣ የአባቱና የእርሱ ምስክርነት ሕጉ የሚጠይቀውን ያሟላል (ዘዳ 17፥6፤ 19፥15)።

8፥16 *ከላከኝ አብ*፤ ኢየሱስ አባቱ የሰጠውን ተልእኮ ምን ጊዜም አይዘነጋም (የ4፥34 ማብ ይመ)።

8፥19 *እኔንስ ብታውቁኝ ኖሮ*፤ ቃል (ኢየሱስ) ከእግዚ አብሔር ጋር እንደ ነበረ፣ ራሱም እግዚአብሔር እንደ ሆነ (1፥1)፣ እግዚአብሔርንም እንደሚያሳይ (1፥18)፣ ዮሐንስ ግል ጽ አድርጓል፤ ኢየሱስም፣ አብ በወልድ በኩል ብቻ እንደሚታወቅ እዚህ ላይ አበክሮ አሳይቷል።

8፥20 *ጊዜው*፤ የ2፥4 ማብ ይመ።

*8፥23፤* ሞትና ሕይወት ብቻ ሳይሆኑ፣ ሌሎችም ነገሮች ሰዎችን ለይተው ይመድቧቸዋል (ለምሳሌ ቍ47፤ 3፥31፤ 15፥19፤ 1ኛ ዮሐ 3፥10)። *ከ...፤* እዚህ ላይ የሚያመለክተው መገኛን ነው። ኢየሱስ በእርግጥ በዓለም ውስጥ ነበረ፤ ግን ከዓ ለም አልነበረም፤ እነርሱ ግን የሰይጣን ግዛት ከሆነው 'ከዚህ ዓለም' ናቸው (1ዮሐ 5፥19)።

8፥24 *እኔ...ነኝ*፤ እግዚአብሔር አብ ቀደም ሲል ስለ ራሱ

25እነርሱም፣ “ለመሆኑ፣ አንተ ማን ነህ?”
አሉት::
ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ “እስካ
ሁን የነገርኋችሁ እኔ እርሱ ነኝ፤ 26በእናንተ
ላይ ብዙ የምናገረውና ብዙ የምፈርደው
ነገር አለኝ፤ ዳሩ ግን የላከኝ ታማኝ ነው፤
ከእርሱም የሰማሁትን ለዓለም እናገራለሁ::”
27እነርሱም ስለ አብ እየነገራቸው እንደ
ነበር አላስተዋሉም:: 28ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ
አለ፤ “የሰው ልጅን ከፍ ከፍ ባደረጋችሁት
ጊዜ፣ ያ ያልሁት እርሱ እኔ እንደ ሆንሁና
አብ ያስተማረኝን እንደምናገር፣ በራሴም
ፈቃድ ምንም እንደማላደርግ ታውቃላችሁ፤
29የላከኝ እርሱ ከእኔ ጋር ነው፤ ምንጊዜም
የሚያስደስተውን ስለማደርግ ብቻዬን አልተ
ወኝም::” 30ይህንም እንደ ተናገረ ብዙዎች
በእርሱ አመኑ::

## የአብርሃም ልጆች

31ኢየሱስም በእርሱ ያመኑትን አይሁድ
እንዲህ አላቸው፤ “በትምህርቴ ብትጸኑ እና
ንተ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ 32እው
ነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም ነጻ ያወጣችኋል::”
33እነርሱም መልሰው፣ “እኛ የአብርሃም
ልጆች ነን[ሀ]፤ ለማንም ባሪያዎች ሆነን አና
ውቅም፤ ታዲያ፣ ‘ነጻ ትወጣላችሁ’ እንዴት
ትለናለህ?” አሉት::
34ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“እውነት እላችኋለሁ፤ ኀጢአት የሚያደርግ
የኀጢአት ባሪያ ነው፤ 35ባሪያ ለዘለቄታ በቤተ
ሰቡ ውስጥ አይኖርም፤ ልጅ ግን ምን ጊዜም
በቤት ይኖራል:: 36እንግዲህ ወልድ ነጻ ካወጣ
ችሁ፣ በእውነት ነጻ ትሆናላችሁ:: 37የአብርሃም
ልጆች መሆናችሁን ዐውቃለሁ፤ ነገር ግን
ቃሌን ስለማትቀበሉ ልትገድሉኝ ቈርጣችሁ
ተነሥታችኋል:: 38እኔ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን
እናገራለሁ፤ እናንተም ከአባታችሁ የሰማች
ሁትን ታደርጋላችሁ::”[ሐ]
39እነርሱም፣ “አባታችንስ አብርሃም ነው”
ብለው መለሱለት::
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “የአብርሃም
ልጆችስ ብትሆኑ[ሠ]፣ አብርሃም የሠራውን
ትሠሩ ነበር:: 40ከእግዚአብሔር ሰምቼ እውነቱን
የነገርኋችሁን እኔን ለመግደል ቈርጣችሁ
ተነሥታችኋል፤ አብርሃም ግን እንዲህ አላደ
ረገም:: 41እናንተ የምታደርጉት አባታችሁ
የሚያደርገውን ነው::”
እነርሱም፣ “እኛስ በዝሙት የተወለድን
አይደለንም፤ አባታችንም አንዱ እግዚአብሔር ብቻ
ነው” ሲሉ መለሱለት::

## የዲያብሎስ ልጆች

42ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እግዚአብሔር
አባታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ እኔ ከእግዚአብሔር
ወጥቼ መጥቻለሁና፣ በወደዳችሁኝ ነበር፤
እርሱ ላከኝ እንጂ በገዛ ራሴ አልመጣሁም::
43የምናገረውን ለምን አታስተውሉም? ምክን
ያቱም ቃሌን መስማት ስለማትችሉ ነው::
44እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ናችሁ፤
የአባታችሁንም ፍላጎት ለመፈጸም ትሻላችሁ::
እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበር፤ በእርሱ
ዘንድ እውነት ስለሌለ በእውነት አልጸናም፤
እርሱ ሐሰተኛ፣ የሐሰትም አባት በመሆኑ ሐሰ
ትን ሲናገር፣ የሚናገረው ከራሱ አፍልቆ
ነው፤ 45እኔ ግን እውነት ስለምናገር አታ
ምኑኝም:: 46ከእናንተ ስለ ኀጢአት በማስረጃ
ሊከሰኝ የሚችል አለን? እውነት የምናገር
ከሆነ፣ ለምን አታምኑኝም? 47ከእግዚአብሔር
የሆነ እግዚአብሔር የሚለውን ይሰማል፤ እናንተ
ግን ከእግዚአብሔር ስላልሆናችሁ አትሰሙም::”

8፥26 ዮሐ3፥32፤ 7፥28፤15፥15
8፥28 ዮሐ12፥32፤ 14፥24
8፥29 ቍ16፤ ኢሳ50፥5፤ዮሐ4፥34፤ 5፥30፤6፥38፤16፥32
8፥30 ዮሐ7፥31
8፥31 ዮሐ15፥7፤ 2ዮሐ9
8፥32 ቍ36፤ ሮሜ8፥2፤ 2ቆሮ 3፥17፤ገላ5፥1፡13
8፥33 ቍ37፡39፤ ሉቃ3፥8
8፥34 ሮሜ6፥16
8፥35 ገላ4፥30
8፥36 ቍ32
8፥37 ቍ39፡40
8፥38 ቍ41፡44፤ ዮሐ5፥19፡30፤ 14፥10፡24
8፥39 ቍ37፤ ሉቃ3፥8
8፥40 ቍ26፤ ማቴ12፥14
8፥41 ቍ38፡44፤ ኢሳ63፥16፤64፥8
8፥42 ዮሐ3፥17፤ 7፥28፤13፥3፤ 1ዮሐ5፥1
8፥44 ቍ38፥41፤ ዘፍ3፥4፤4፥9፤2ዜና 18፥21፤መዝ5፥6፤ 12፥2፤1ዮሐ3፥8
8፥45 ዮሐ18፥37
8፥47 ዮሐ18፥37፤ 1ዮሐ4፥6

[ሀ]33 በግሪኩ *ዘር* ይላል፤ ቍ 37 ይመ
[ሐ]38 ወይም *ስለዚህ ከአባታችሁ የሰማችሁትን አድርጉ*
[ሠ]39 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *የአብርሃም ልጆች ከሆናችሁ* ይላሉ

የተናገረውን ታላቅ ቃል፣ ኢየሱስም የራሱ አድርጎታል (ቍ 58፤ ዘፀ 3፥14 ይመ፤ እንደዚሁም የ6፥35 ማብ ይመ):: *ካላመናችሁ!* የ1፥7 ማብ ይመ::

8፥28 *ከፍ ከፍ (ባደረጋችሁት ጊዜ)*፤ ብዙውን ጊዜ ይህ አባባል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ‘ባከበራችሁት ጊዜ’ የሚለውን ሐሳብ ይይዛል፤ ዮሐንስ ግን እዚህ ያስገባው ስቅለትን ለማመ ልከት ነው (3፥14):: *የሰው ልጅ*፤ የ1፥51 ማብ ይመ::

8፥30 *አመኑ!* ከ20፥31 ጋር ያነጻጽሩ::

8፥31 *ያመኑትን*፤ ከአንገት በላይ የሆነ እምነት ያላቸውን ለማለት ይመስላል፤ እውነተኛ አማኞች እንዳልሆኑ አነጋገራቸው ያሳያል (ቍ 33 እና 37 ይመ)::

8፥32 *እውነት*፤ ከኢየሱስ ማንነት ጋር የተያያዘና (ቍ 36፤ 14፥6) ወደ ድነት የሚመራ እንጂ ፍልስፍናዊ እውነት አይደለም:: *ነጻ*፤ አርነት መውጣት የሚያስፈልገው ከድንቁርና ሳይሆን ከኀጢአት ነው (ቁ 36 ይመ)::

8፥33 *ባሪያዎች ሆነን አናውቅም!* በሮማውያን ቅኝ አገዛዝ ሥር ሆነው ይህን ማለታቸው የሚያስደንቅ ነው::

8፥34 *የኀጢአት ባሪያ*፤ በራሱ ኀይል ነጻ መውጣት አይቻለውም::

8፥37 *ልትገድሉኝ ቈርጣችሁ ተነሥታችኋል*፤ የም 7 መግቢያ (7፥1-8፥59 ማብ ይመ)::

*8፥38!* ‘እኔ...እንተም’፣ ‘ያየሁትን...የሰማችሁትን’፣ ‘አባቴ...አባታችሁ’ የሚለውን ንጽጽር ያስተውሉ:: ኢየሱስ፣ አባታቸው ማን እንደ ሆነ ወዲያው ባይነግራቸውም (ቁ 44)፣ አባታቸው እነርሱ እንደሚሉት እግዚአብሔር ወይም አብርሃም እንዳልሆነ እዚሁ ጥቅስ ላይ ግልጽ አድርጓል:: አይሁድ እንደ መሆናቸው በሥጋ የአብርሃም ልጆች ናቸው፤ ነገር ግን ባለ ማመናቸው ምክንያት በመንፈስ ልጆቹ ሊባሉ አልቻሉም::

*8፥39-41!* የማን ልጅ እንደ ሆኑ ተግባራቸው ይመሰክርባቸዋል::

8፥41 *በዝሙት የተወለድን*፤ ኢየሱስን ከድንግል አልተወ ለድህም ለማለት የሰነዘሩት የሽሙጥ አነጋገር ሊሆን ይችላል::

8፥43 *የምናገረውን*፤ የአገላለጹን ስልት ለማለት ነው:: *ቃሌን*፤ አይሁድ ቀድሞውኑ ልባቸው በራሳቸው ሐሳብ ተዘግቶ ስለ ነበር፣ ኢየሱስ የተናገረውን ፍሬ ነገር በትክክል አላዳ መጡም::

8፥44 *የአባታችሁ የዲያብሎስ*፤ አይሁድ ከዲያብሎስ ጋር ያላቸው ኅብረት እዚህ ላይ በግልጽ ተነግሯል፤ ‘እግዚአብሔር የሁሉም አባት ነው’ የሚለው ሐሳብ ሙሉ በሙሉ ትክክል እንዳልሆነ ኢየሱስ በግልጽ አስታወቀ፤ ምክንያቱም አባትነቱ ቃሉን ለሚቀ በሉና ለሚያከብሩት ብቻ ነው:: *ትሻላችሁ!* ቍርጥ ሐሳባቸው ምን እንደ ሆነ ያመለክታል፤ በመሠረቱ ጉድለታቸው ዕውቀት ማጣት ሳይሆን መንፈሳዊ ችግር ነበርና:: ለሰይጣን ያደሩ በመሆናቸው ነፍስ ለማጥፋት አቆብቁበው ነበር፤ (ቍ 37)፤ ውሉ አድሮም ነፍስ የማጥፋቱ ዕቅዳቸው ሊሳካላቸው ችሏል (ቍ 28):: *እውነት*፤ ሰይጣንና ተከታዮቹ ከእውነት ጋር ግንኙነት የላቸውም (14፥6 ይመ)::

8፥46 *ስለ ኀጢአት በማስረጃ ሊከሰኝ የሚችል አለን?* ዋናው ነገር አይሁድ ጥያቄውን መመለስ አለመቻላቸው ሳይሆን፣ ኢየሱስ ይህን ጥያቄ ማቅረቡ ነበር፤ ይህም ኢየሱስ ፍጹምና ንጹሕ ሕሊና እንዳለው ያሳያል::

## ኢየሱስ ስለ ራሱ የተናገረው

48አይሁድም መልሰው፣ “አንተ ሳምራዊ ነህ፤
ደግሞም ጋኔን አድሮብሃል ማለታችን ትክክል
አይደለምን?” አሉት።

49ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“እኔስ አባቴን አከብረዋለሁ እንጂ ጋኔን
አላደረብኝም፤ እናንተ ግን ታዋርዱኛላችሁ።
50እኔ የራሴን ክብር አልፈልግም፤ የሚፈልግ
ግን አለ፤ ፈራጁም እርሱ ነው። 51እውነት
እላችኋለሁ፤ ማንም ቃሌን ቢጠብቅ፣ ሞትን
ፈጽሞ አያይም።”

52አይሁድም እንዲህ አሉት፤ “ጋኔን እንዳ
ለብህ አሁን ዐወቅን፤ አብርሃም ሞተ፤ ነቢያ
ትም እንዲሁ፤ አንተ ግን ማንም ቃልህን
ቢጠብቅ ሞትን ፈጽሞ እንደማይ ቀምስ
ትናገራለህ። 53አንተ ከአባታችን ከአብርሃም
ትበልጣለህን? እርሱ ሞተ፤ ነቢያቱም እን
ዲሁ፤ ለመሆኑ አንተ ማን ነኝ ልትል ነው?”

54ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እኔ
ራሴን ባከብር፣ ክብሬ ከንቱ ነው፤ የሚያ
ከብረኝ ግን እናንተ አምላካችን የምትሉት
አባቴ ነው። 55እናንተ ባታውቁትም እኔ
ዐውቀዋለሁ፤ አላውቀውም ብል፣ እኔም
እንደ እናንተው ሐሰተኛ እሆናለሁ። እኔ
ግን ዐውቀዋለሁ፤ ቃሉንም እጠብቃለሁ።
56አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ለማየት ተስፋ
በማድረግ ተደሰተ፤ አየም፤ ሐሤትም አደረገ።”

57አይሁድም፣ “ገና አምሳ ዓመት ያልሞ
ላህ፣ አንተ አብርሃምን አይተሃል!” አሉት።

58ኢየሱስም፣ “እውነት እላችኋለሁ፤ አብር
ሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ” አላቸው።
59በዚህን ጊዜ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤

8፥48 ቍ52፤ ማቴ10፥5፤ማር3፥22
8፥50 ቍ54፤ ዮሐ5፥41
8፥51 ዮሐ11፥26
8፥52 ቍ48፤ ማር3፥22
8፥53 ቍ39፤ ዮሐ4፥12
8፥54 ቍ50፤ ዮሐ16፥14፤17፥1፡5
8፥55 ቍ19፤ ዮሐ7፥28፡29፤15፥10
8፥56 ቍ37፡39፤ ዘፍ18፥18፤ ማቴ13፥17
8፥58 ዘፀ3፥14፤ 6፥3፤ዮሐ1፥2
8፥59 ዘፀ17፥4፤ ዘሌ24፥16፤1ሳሙ 30፥6፤ዮሐ10፥31፤ 11፥8፤12፥36
9፥2 ቍ34፤ ዘፀ20፥5፤ኢዮ21፥19፤ ሕዝ18፥20፤ማቴ 23፥7፤ሉቃ13፥2፤ ሐሥ28፥4
9፥3 ዮሐ11፥4
9፥4 ዮሐ11፥9፤ 12፥35
9፥5 ዮሐ1፥4
9፥6 ማር7፥33፤ 8፥23
9፥7 ቍ11፤2ነገ 5፥10፤ኢሳ35፥5፤ ሉቃ13፥4፤ ዮሐ 11፥37
9፥8 ሐሥ3፥2፡10
9፥11 ቍ7

ኢየሱስ ግን ተሰወረባቸው፤ ከቤተ መቅደስም
ወጥቶ ሄደ።

## ኢየሱስ ዐይነ ስውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ፈወሰ

9በመንገድ ሲያልፍም ከተወለደ ጀምሮ
ዐይነ ስውር የሆነ ሰው አየ። 2ደቀ
መዛሙርቱም፣ “ረቢ፤ ይህ ሰው ዐይነ ስውር
ሆኖ እንዲወለድ ኀጢአት የሠራ ማን ነው?
እርሱ ራሱ ወይስ ወላጆቹ?” ብለው ጠየቁት።

3ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እርሱ
ወይም ወላጆቹ ኀጢአት አልሠሩም፤ ይህ
የሆነው ግን የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ ሕይወት
እንዲገለጥ ነው። 4ቀን ሳለ፣ የላከኝን ሥራ
መሥራት አለብኝ፤ ማንም ሊሠራ የማይ
ችልበት ሌሊት ይመጣል፤ 5በዓለም ሳለሁ
የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ።”

6ይህን ካለ በኋላ፣ በምድር ላይ እንትፍ
ብሎ በምራቁ ጭቃ አበጀ፤ የሰውዬውንም
ዐይን ቀባና፣ 7“ሄደህ በሰሊሆም መጠመቂያ
ታጠብ” አለው፤ ሰሊሆም ማለት ‘የተላከ’
ማለት ነው። ሰውዬውም ሄዶ ታጠበ፤ እያየም
ተመልሶ መጣ።

8ጎረቤቶቹና ከዚህ ቀደም ብሎ ሲለምን
ያዩት ሰዎች፣ “ይህ ሰው ተቀምጦ ሲለምን
የነበረው አይደለምን?” አሉ። 9አንዳንዶ
ቹም፣ “በእርግጥ እርሱ ነው” አሉ።

ሌሎችም፣ “ይመስለዋል እንጂ እርሱ
አይደለም” አሉ።

እርሱ ግን፣ “እኔው ነኝ” አለ።

10እነርሱም፣ “ታዲያ ዐይኖችህ እንዴት
ተከፈቱ?” ሲሉ ጠየቁት።

---

8፥47 *እግዚአብሔር የሚለውን ይሰማል*፤ 10፥3-4፤ 1ዮሐ 4፥6 ይመ።

8፥48 *አይሁድ*፤ የ1፥19 ማብ ይመ። *ሳምራዊ*፤ የአይሁድን ሕግ በማክበር ረገድ፣ እንደ ሳምራውያን ጥንቃቄ ይጎድለዋል ብለው በማመናቸው ሊሆን ይችላል፤ ምናልባትም ‘ከሳምራዊ የተወለድህ’ ለማለት ይሆናል። *ጋኔን አድሮብሃል*፤ 10፥20 እና የ7፥20 ማብ ይመ።

8፥51 *ቃሌን*፤ አምነው ቢቀበሉት፣ ከሞት ነጻ የሚያወጣውን ጠቅላላውን የኢየሱስን ትምህርት ማለት ነው። *ሞትን ፈጽሞ አያይም*፤ አማኝ ጊዜያዊ የሥጋ ሞት ቢሞትም፣ ዘላለማዊ የመንፈስ ሞት የለበትም (5፥24)።

8፥53 አንተ…ትበልጣለህን? ጥያቄው የታለመው አሉታዊ መልስ ለማግኘት ነበር። ኢየሱስ ከሙሴ የላቀ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ከአብርሃምም ስለሚበልጥ (6፥30-35 እና ማብ ይመ)፣ ጥያቄአቸው ሳያስቡት ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ውስጥ ከተታቸው።

8፥56 *ቀኔን*፤ በክርስቶስ የሥጋ ዘመን የተፈጸመውን ሁሉ ይመለከታል። ኢየሱስ ይህን ያለው አንድ የተወሰነን ቀን ለማመልከት አይመስልም፤ ነገር ግን በክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ዕቅድ በመፈጸሙ፣ የሰው ዘር ሁሉ በረከት የሚያገኝበትን ቀን አብርሃም አሻግሮ በማየቱ ተደሰተ ማለቱ ነበር (ዘፍ 18፥18)። *አየም*፤ በእምነት ዓይን፣ ከሩቅ ተመለከተ ማለት ነው።

8፥57 ገና *አምሳ ዓመት ያልሞላህ*፤ ስለ ኢየሱስ ዕድሜ የሰጡት ግምት ከፍ ያለ ነው፤ አገልግሎቱን ሲጀምር ሠላሳ ዓመቱ ነበርና።

8፥58 *እኔ፣ እኔ ነኝ*፤ እግዚአብሔር ስለ ራሱ በዘፀ 3፥14 በአጽንዖት የተናገረውን ታላቅ ቃል፣ ኢየሱስም የራሱ አድርጎታል (ቍ 24 እና 28 ይመ፤ እንዲሁም የ6፥35 ማብ ይመ)። ኢየሱስ ‘ነኝ’ አለ እንጂ ‘ነበርሁ’ አላለም፤ ይኸውም ዘላለማዊነቱንና ከአብ ጋር አንድ መሆኑን ለመግለጽ ነው (1፥1 ይመ)። ደረጃ በደረጃ እያደገ በመጣው በዚህ ንግግሩ ‘የዓለም ብርሃን ነኝ’ (ቍ12) በማለት የጀመረውን ሐሳብ ይደመድማል።

8፥59 *ሊወግሩት*፤ ኢየሱስ ስለ ራሱ ማንነት የገለጸውን ሐሳብ፣ አይሁድ የሚያስቀሥፍ ስድብ ነው በማለት በድንጋይ ከመውገር ሌላ ትርጕም አላገኙለትም (ዘሌ 24፥16)።

9፥1-12 ኢየሱስ ከሌሎቹ ታምራት ይልቅ በተደጋጋሚ ያደረገው ታምር ዐይነ ስውሩን ማብራት ነው። ዐይነ ስውራንን ማብራት የመሲሑ ተግባር እንደ ሆነ ትንቢት ተነግሯል (ኢሳ 29፥18፤ 35፥5፤ 42፥7)። ስለዚህ ኢየሱስ መሲሑ እንደ ሆነ እነዚህ ታምራት ተጨማሪ ማስረጃዎች ናቸው (20፥31)።

9፥2 …*ኀጢአት የሠራ ማነው?* የአይሁድ መምህራን፣ ‘ኀጢአት ከሌለ ሞት የለም፤ በደል ካልተገኘም መሠቃየት አይኖርም’ የሚል እምነት ነበራቸው። አንድ ሕፃን በማኅፀን ውስጥ ሳለ ኀጢአት ሊሠራ ይችላል፤ ወይም ከመፀነሱ በፊት ነፍሱ ኀጢአት ሠርታ ይሆናል እስከ ማለት ደርሰው ነበር። በአንድ ሕዝብ ላይ የተወሰነ አሠቃቂ ቅጣት የሚደርሰውም ከወላጆቹ መተላለፍ የተነሣ ብቻ ነው ብለው ያምናሉ። የሚቀጥለው ቍጥር (ቍ 3) እንደሚያሳየው ኢየሱስ እንደዚህ ያለውን እምነት ውድቅ አድርጓል።

9፥4 *አለብን (እኛ)*፤ ኢየሱስ ብቻ አይደለም፤ አባቱን ወይም ደቀ መዛሙርቱን ጭምር ሊሆን ይችላል።

9፥5 *የዓለም ብርሃን*፤ የ8፥12 ማብ ይመ።

*9፥6*፤ ኢየሱስ የሚፈውሰው በተለያየ መንገድ ነው፤ እያንዳንዱ የጌታ አሠራርም የሚሰጠው ትምህርት አለው።

9፥7 *ሰሊሆም*፤ ጥንትም የታወቀ ስም ነው (የነህ 3፥15 ማብ እና ኢሳ 8፥6 ይመ)። ኢየሩሳሌም ከተመሠረተችበት ኰኮረብታ በስተደቡብ ጫፍ ይገኝ የነበረና ከተፈለፈለ ቋጥኝ የተሠራ ኵሬ ሲሆን፣ ንጉሥ ሕዝቅያስ ለከተማው ውሃ አገልግሎት ካሠራው የዋናው ውሃ መስመር አንዱ ክፍል ነበር።

9፥8 *ሲለምን*፤ ቀደም ሲል ሲለምን እንደ ነበረ አልተጠቀሰም፤ ነገር ግን በዚያን ጊዜ አንድ ዐይነ ስውር ለመኖር

11እርሱም፣ “ኢየሱስ የሚሉት ሰው ጭቃ
አድርጎ ዐይኔን ቀባኝ፤ ወደ ሰሊሆም ሂጄ
እንድታጠብም ነገረኝ፤ ሂጄ ታጠብሁ፤ ማየ
ትም ቻልሁ” ሲል መለሰ።
12እነርሱም፣ “ታዲያ፣ ያ ሰው የት አለ?”
አሉት።
እርሱም፣ “እኔ አላውቅም” አለ።

### ፈሪሳውያን ሰውየው እንዴት እንደ ተፈወሰ ማጣራት ቀጠሉ

13እነርሱም ዐይነ ስውር የነበረውን ሰው
ወደ ፈሪሳውያን ወሰዱት። 14ኢየሱስ ጭቃ
የሠራበት፣ የሰውዬውንም ዐይን የከፈተበት
ቀን ሰንበት ነበር። 15ስለዚህ ፈሪሳውያንም
እንዴት ማየት እንደ ቻለ ጠየቁት። ሰውዬ
ውም፣ “እርሱ ዐይኔን ጭቃ ቀባኝ፤ እኔም
ታጠብሁ፤ ይኸው አያለሁ” አላቸው።
16ከፈሪሳውያንም አንዳንዶቹ፣ “ይህ ሰው
ሰንበትን ስለማያከብር፣ ከእግዚአብሔር አይደ
ለም” አሉ።
ሌሎች ግን፣ “ኀጢአተኛ፣ እንዲህ ያሉትን
ታምራዊ ምልክቶች እንዴት ሊያደርግ ይች
ላል?” አሉ። በመካከላቸውም አለመስማማት
ተፈጠረ።
17ስለዚህ፣ ዐይነ ስውር ወደ ነበረው ሰው
ተመልሰው፣ “ዐይንህን ስለ ከፈተው ሰው፣
እንግዲህ አንተ ምን ትላለህ?” አሉት።
ሰውየውም፣ “እርሱ ነቢይ ነው” አለ።
18አይሁድ ወደ ወላጆቹ ልከው እስኪያስጠ
ሯቸው ድረስ፣ ሰውየው ዐይነ ስውር እንደ
ነበረና እንዳየ አላመኑም ነበር። 19እነርሱም፣
“ዐይነ ስውር ሆኖ ተወልዶአል የምትሉት
ልጃችሁ ይህ ነውን? ታዲያ አሁን እንዴት
ሊያይ ቻለ?” አሏቸው።
20ወላጆቹም እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ “ልጃ
ችን መሆኑንና ዐይነ ስውር ሆኖ መወለዱን
እናውቃለን፤ 21አሁን ግን እንዴት ማየት
እንደ ቻለና ዐይኖቹን ማን እንደ ከፈተለት
እኛ አናውቅም። ሙሉ ሰው ስለ ሆነ፣ ስለ
ራሱ መናገር ይችላልና እርሱን ጠይቁት።”

9፥14 ማቴ12፥1-14፤ዮሐ5፥9
9፥15 ቍ10
9፥16 ማቴ12፥2፤ ዮሐ2፥11፤6፥52
9፥17 ማቴ21፥11
9፥18 ዮሐ1፥19
9፥22 ቍ34፤ ሉቃ6፥22፤ዮሐ7፥13 12፥42፤16፥2
9፥23 ቍ21
9፥24 ቍ16፤ ኢያ7፥19
9፥27 ቍ15
9፥28 ዮሐ5፥45
9፥29 ዮሐ8፥14
9፥31 ዘፍ18፥23-32፤መዝ34፥15፡16፤ 66፥18፤145፥19፡20፤ ምሳ15፥29፤ ኢሳ1፥15፤59፥1፡2፤ ዮሐ 15፥7፤ 1ዮሐ5፥14-15፤ ያዕ5፥16-18
9፥33 ቍ16፤ ዮሐ3፥2
9፥34 ቍ2፡22፡35፤ ኢሳ66፥5

22ኢየሱስን፣ ክርስቶስ– ነው ብሎ የመሰከረ
ሁሉ ከምኵራብ እንዲባረር አይሁድ አስቀ
ድመው ወስነው ስለ ነበር፣ ወላጆቹ ይህን
ያሉት አይሁድን ፈርተው ነው። 23ስለዚህ
ወላጆቹ፣ “ሙሉ ሰው ስለ ሆነ እርሱን ጠይቁት”
አሉ።
24ዐይነ ስውር የነበረውንም ሰው ዳግመኛ
ጠርተው፣ “አንተ ሰው፤ እግዚአብሔርን አክብር–፤
ይህ ሰው ኀጢአተኛ መሆኑን እኛ እናው
ቃለን” አሉት።
25እርሱም፣ “ኀጢአተኛ መሆኑን እኔ አላ
ውቅም፤ ነገር ግን ዐይነ ስውር እንደ ነበርሁ፤
አሁን ግን እንደማይ ይህን አንድ ነገር ዐው
ቃለሁ” አለ።
26እነርሱም፣ “ምን አደረገልህ? እንዴትስ
ዐይንህን ከፈተ?” ብለው ጠየቁት።
27እርሱም፣ “አስቀድሜ ነገርኋችሁ፤ አላዳ
መጣችሁኝም፤ ለምን እንደ ገና መስማት
ፈለጋችሁ? እናንተም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ
ልትሆኑ ትሻላችሁ?” አለ።
28ከዚህ በኋላ በእርሱ ላይ የስድብ ናዳ
በማውረድ እንዲህ አሉት፤ “የዚህ ሰው
ደቀ መዝሙር አንተ ነህ፤ እኛስ የሙሴ
ደቀ መዛሙርት ነን! 29እግዚአብሔር ሙሴን
እንደ ተናገረው እናውቃለን፤ ይህ ሰው ግን
ከየት እንደ መጣ እንኳ አናውቅም።”
30ሰውየውም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“እናንተ ከየት እንደ መጣ አለማወቃችሁ
የሚያስደንቅ ነው፤ ይሁን እንጂ እርሱ
ዐይኖቼን ከፈተልኝ። 31እግዚአብሔር፣ የሚፈራ
ውንና ፈቃዱን የሚያደርገውን እንጂ፣
ኀጢአተኞችን እንደማይሰማ እናውቃለን፤
32ዐይነ ስውር ሆኖ የተወለደን ሰው ዐይን
የከፈተ አለ ሲባል፣ ዓለም ከተ ፈጠረ ጀምሮ
ማንም ሰምቶ አያውቅም። 33ይህ ሰው ከእ
ግዚአብሔር ባይሆን ኖሮ ይህን ማድረግ
ባልቻለ ነበር።”
34እነርሱም፣ “ሁለንተናህ በኀጢአት ተነክሮ

–22 ወይም መሲሑ
–24 እውነት ለመናገር የሚደረግ መሐላ ነው ኢሱ (7፥19 ይመ)

ከልመና በቀር ሌላ አማራጭ አልነበረውም።

9፥13 *ፈሪሳውያን*፤ የማቴ 3፥7፤ የማር 2፥16፤ የሉቃ 5፥17 ማብ ይመ።

9፥14 *ሰንበት*፤ ከ5፥16 እና ከዚያ ቀጥሎ ካለው ሐሳብ ጋር ያነጻጽሩ።

9፥16 *አንዳንዶቹ...ሌሎች*፤ በመጀመሪያው ቡድን ያሉ ሰዎች ሆን ብለው ልባቸውን ስለ ዘጉ፣ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ሊሆን ይችላል የሚለውን ሐሳብ ሊቀበሉ አልፈለጉም፤ በሁለተኛው ያሉት ግን፣ ‘ታምራዊ ምልክቶችን’ መሠረት አድርገው የተነሡ በመሆናቸው፣ ኀጢአተኛ ነው የሚል ግምት አልነበራቸውም (ከቍ 31-33 ጋር ያነጻጽሩ)።

9፥17 *እንግዲህ አንተ ምን ትላለህ?* መንገድ ላይ ተቀምጦ ለሚለ ምን ዐይነ ስውር እንደዚህ ያለ ጥያቄ መሰንዘራቸው የሚያስደንቅ ነው፤ ጥያቄአቸው ግራ የተጋቡ መሆናቸውን ያመለክታል። *ነቢይ!* ምናል ባት ሰውዬው የሚያውቀው ከፍተኛ ማዕረግ፣ ‘ነቢይ’ የሚለው ብቻ ይሆናል። ይህ ሰው ስለ ኢየሱስ ያለው አመለካከት እድገት እያሳየ መጥቷል፤ ‘ሰው’ ከሚለው (ቍ 11)፣ ‘ነቢይ’ ወደሚለው (ቍ 17)፤ ‘ደቀ መዛሙርት ሊኖሩት የሚችል’ ከሚለው (ቍ27)፣ ‘ከእግዚአብሔር የሆነ’ ወደሚልና (ቍ33) ‘ሊመለክ ወደሚገባው’ (ቍ38) ወደሚለው ተሸጋግሯል።

9፥18 *አይሁድ*፤ የ1፥19 ማብ ይመ። በወልጋዳ አመለካከታቸው ምክንያት ከታምራቱ ትምህርት ከመቅሰም ይልቅ ታምሩን ዋጋ ቢስ ለማድረግ ተፍጨርጭረዋል።

9፥21 *ሙሉ ሰው ስለ ሆነ*፤ ወላጆቹ ምስክርነት ያልሰጡበት ብዙ ምክንያት ነበራቸው፤ ልጃቸው ራሱን የቻለ መሆኑን መናገራቸው፣ በነገሩ ውስጥ እንዳይገቡ መፍራታቸውን ያሳያል።

9፥22 *ከምኵራብ እንዲባረር*፤ ውግዘት ከጥንት ከዕዝራ ዘመን ጀምሮ ተጠቅሷል (ዕዝ 10፥8)፤ በአዲስ ኪዳን ዘመን ግን የውግዘቱ ሁኔታ እንዴት እንደ ነበር የሚገልጽ ማስረጃ አልተገኘም። ምኵራብ የአይሁድ ማኅበራዊ ሕይወት ማዕከል ነበር፤ በዚህም ምክንያት ውግዘት አንድን ሰው ከአያሌ ማኅበራዊ ሕይወት ያስወግደዋል፤ በኋለኛው ዘመን ግን በአንዳንድ መልኩ ከአምልኮ አያስወግድም ነበር።

9፥24 *እኛ!* ቃሉ በግሪክ ማንነታቸውን ለማጕላት እንደተጠቀሙበት ያሳያል።

9፥27 *እናንተም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ...!* ሰውዬው ራሱን እንደ ደቀ መዝሙር የቈጠረ ይመስላል።

*9፥30-33!* ትምህርት ከሌለው ሰው ይህን የመሰለ ብቃት ያለው ሐሳብ ተሰንዝሯል።

የተወለድህ፣ አንተ እኛን ለማስተማር እንዴት
ትደፍራለህ?" ሲሉ መለሱለት፤ አባረሩትም።

## መንፈሳዊ ዕውርነት

35ኢየሱስም ሰውየውን እንዳባረሩት ሰማ፤
ባገኘውም ጊዜ፣ "በሰው ልጅ *ታምናለህን?"
አለው።
36ሰውየውም፣ "ጌታዬ፤ አምንበት ዘንድ
እርሱ ማን ነው?" ሲል ጠየቀው።
37ኢየሱስም፣ "አይተኸዋል፤ አሁንም ከአንተ
ጋር የሚነጋገረው እርሱ ነው" አለው።
38ሰውየውም፣ "ጌታ ሆይ፤ አምናለሁ"
አለ፤ ሰገደለትም።
39ኢየሱስም፣ "ዕውሮች እንዲያዩ፣ የሚ
ያዩም እንዲታወሩ፣ ለፍርድ ወደዚህ ዓለም
መጥቻለሁ" አለ።
40ከእርሱ ጋር ከነበሩት ፈሪሳውያን አንዳን
ዶቹ ይህን ሰምተው፣ "ምን ማለትህ ነው?
ታዲያ እኛም ዕውሮች መሆናችን ነው?"
አሉት።
41ኢየሱስም፣ "ዕውሮችስ ብትሆኑ ኀጢአት
ባልሆነባችሁ ነበር፤ አሁን ግን እናያለን
ስለምትሉ፣ ኀጢአታችሁ እንዳለ ይኖራል"
አላቸው።

## እረኛና መንጋው

10 "እውነት እላችኋለሁ፤ ወደ በጎች
ጕረኖ በበሩ ሳይሆን፣ በሌላ በኩል
ዘሎ የሚገባ ሌባና ነጣቂ ነው፤ 2በበሩ የሚ
ገባ ግን እርሱ የበጎቹ እረኛ ነው፤ 3በር ጠባ
ቂው በሩን ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን
ይሰማሉ። የራሱንም በጎች በየስማቸው እየጠራ
ያወጣቸዋል። 4የራሱ የሆኑትንም ሁሉ ካወጣ
በኋላ ፊት ፊታቸው ይሄዳል፤ በጎቹም ድምፁን
ስለሚያውቁ ይከተሉታል። 5እንግዳ የሆነውን
ግን ድምፁን ስለማያውቁ ከእርሱ ይሸሻሉ
እንጂ ፈጽሞ አይከተሉትም።" 6ኢየሱስ ይህን
ምሳሌ ነገራቸው፤ እነርሱ ግን ምን እንደ ነገራ
ቸው አላስተዋሉም።
7ስለዚህ ኢየሱስ ዳግም እንዲህ አላቸው፤
"እውነት እላችኋለሁ፤ የበጎች በር እኔ ነኝ።
8ከእኔ በፊት የመጡት ሁሉ ሌቦችና ቀማ
ኞች ነበሩ፤ በጎቹ ግን አልሰሟቸውም። 9በሩ
እኔ ነኝ፤ በእኔ በኩል የሚገባ ሁሉ ይድናል[c]፤
ይገባል፤ ይወጣልም፤ መሰማሪያም ያገኛል።
10ሌባው ሊሰርቅ፣ ሊገድልና ሊያጠፋ ብቻ
ይመጣል፤ እኔ ግን ሕይወት እንዲኖራቸውና
እንዲትረፈረፍላቸው መጥቻለሁ።"
11"መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም እረኛ
ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል፤ 12ተቀ
ጣሪው እረኛ ግን በጎቹ የእርሱ ስላልሆኑ፣
ተኵላ ሲመጣ ጥሎአቸው ይሸሻል፤ ተኵላ
ውም በጎቹን ይነጥቃል፤ ይበትናቸዋልም።
13የሚሸሸውም ተቀጣሪ ስለ ሆነና ለበጎቹ ደንታ
ስለሌለው ነው።
14"መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ በጎቼን ዐውቃ
ለሁ፤ እነርሱም ያውቁኛል፤ 15ይህም አብ እኔን
እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው

9፥35 ማቴ8፥20፤ ዮሐ3፥15
9፥36 ሮሜ10፥14
9፥37 ዮሐ4፥26
9፥38 ማቴ28፥9
9፥39 ማቴ13፥13፤ ሉቃ4፥18፤ዮሐ3፥19፤ 5፥22፤12፥47
9፥40 ሮሜ2፥19
9፥41 ዮሐ15፥22፡24
10፥1 ቍ8፡10
10፥2 ቍ11፡14፤ ማር6፥34
10፥3 ቍ4፡5፡14፡ 16፡27
10፥4 ቍ3
10፥6 ማር9፥32፤ ዮሐ16፥25
10፥7 ቍ9፤ዮሐ6፥35
10፥8 ቍ1፤ኤር 23፥1፡2፤ሕዝ34፥2
10፥10 መዝ65፥ 11፤ዮሐ1፥4፤3፥15፡ 16፤5፥40፤20፥31፤ ሮሜ5፥17
10፥11 ቍ14፡15፡ 17፡18፤መዝ23፥1፤ ኢሳ40፥11፤ ሕዝ34፥11-16፡23፤ ማቴ2፥6፤ሉቃ12፥32 ዮሐ6፥35፤15፥13፤ ዕብ13፥20፤ 1ጴጥ2፥25፤5፥4፤ 1ዮሐ3፥16፤ራእ7፥17
10፥12 ዘካ11፥16፡ 17
10፥14 ቍ11፡27፤ ዘፀ33፥12
10፥15 ቍ11፡17፡ 18፤ማቴ11፥27

*አንዳንድ የጥንት ቅጆች 'የእግዚአብሔር ልጅ' ይላሉ።
[c]9 ወይም *በደኅና ይጠበቃል*

9፥31 *እግዚአብሔር...ኀጢአተኞችን እንደማይሰማ፤* ፈሪሳውያን በቍ 16 ላይ ከሰነዘሩት አስተያየት ጋር ያነጻጽሩ።

9፥34 አባረሩት፤ 'ከጉባኤአቸው አስወገዱት' ወይም 'አወገዙት' ማለት ሊሆን ይችላል (የቍ 22 ማብ ይመ)።

9፥35 *ባገኘውም ጊዜ፤* ኢየሱስ ሰውዬውን ሊያገኘው ፈልጎ እንደ ነበር ይገልጻል። *የሰው ልጅ፤* የ1፥51፤ ማብ ይመ።

*9፥36፤* በዚህ ጊዜ ሰውዬው መልካም ያደረገለትን ሰው ሐሳብ ለመቀበል ዝግጁ ነበር።

9፥38 አምናለሁ፤ 20፥31 እና የ1፥7 ማብ ይመ። *ጌታ ሆይ...ሰገደለትም፤* ሰውዬው ለኢየሱስ የሰጠው ክብር ለእግዚአብሔር የሚገባውን ነው።

*9፥39፤* በቍ 35-38 ውስጥ የተመለከተው ንግግር ፈሪሳውያኑ በተገኙበት የተደረገ አይመስልም፤ በቍ 39-41 ላይ የሰፈረውም ንግግር ከጥቂት ጊዜ በኋላ የተደረገ ሳይሆን አይቀርም። *ለፍርድ፤* በመሠረቱ ኢየሱስ ለፍርድ አልመጣም (3፥17፤ 12፥47)፤ አመጣጡ ግን ሰዎችን እንዳቀባበላቸው ይመድባቸዋል፤ ይህም ሁኔታ የሚያስከትለው ፍርድ አለ፤ ስጦታውንም ያልተቀበሉት መጨረሻቸው በመንፈስ እንደ ታወሩ መቅረት ነው።

9፥40 *ምን ማለትህ ነው?* በእምነት ረገድ ማንም ደፍሮ 'ዕውር' ይለናል ብለው ስላልገመቱ በጣም መገረማቸውን ያሳያል።

9፥41 ፈሪሳውያን እናያለን ማለታቸው፣ በመንፈስ ፈጽሞ መታወራቸውንና የጐደላቸውን አለማወቃቸውን ያሳያል፤ ዐይን አለን ቢሉም ሥራቸው መታወራቸውን ያረጋግጣል።

10፥1-30፤ በብሉይ ኪዳን ውስጥ (እንዲሁም ጥንት በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ)፣ እንደ ተነገረው 'እረኛ' ሲባል የተከበረ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠባቂ ማለት ነው፤ ሐሳቡ በዚሁ መንፈስ መታየት አለበት። እግዚአብሔር ራሱ፣ 'የእስራኤል እረኛ' ተብሎ ይጠራ ነበር (መዝ 80፥1 ይመ፤ ከመዝ 23፥1 ከኢሳ 40፥10-11፤ ከሕዝ 34፥11-16 ጋር ያነጻጽሩ)። የተሰጣቸውን ሥልጣን ላላከበሩትም እንጂ፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል 'እረኞች' ከፍተኛ ኀላፊነት ሰጥቶ ነበር። እግዚአብሔር ሐሰተኞች እረኞችን በማውገዝ (ኢሳ56፥9-12፤ ሕዝ34)፣ በጎቹን በሚገባ የሚጠብቅን እውነተኛውን እረኛ፣ መሲሑን እንደሚልክ ቃል ገብቶ ነበር (ሕዝ 34፥23)።

10፥1 *የበጎች ጕረኖ፤* አንድ በር ብቻ ያለው፣ ዙሪያውንም የታጠረና ጣራ የሌለው ስፍራ ነው፤ ቅጥሩ በጎቹ እንዳይባዝኑና አውሬ እንዳይበላቸው ይከለክላል።

10፥3 *በር ጠባቂው፤* ትልቅ መንጋ የሚመስግበትን በረት የሚጠብቅ መሆን አለበት። *የራሱንም በጎች፤* እረኛው የጠራው የራሱን እንጂ፣ ማንኛውንም በግ አይደለም።

10፥4 *በፊት በፊታቸው ይሄዳል፤* በእስራኤልና በአካባቢዋ እረኛ በጎቹን ይመራቸዋል እንጂ አይነዳቸውም፤ በጎቹም ድምፁን ስለሚያውቁ ይከተሉታል።

10፥7 *እኔ ነኝ፤* የ6፥35 ማብ ይመ።

10፥8 *ከእኔ በፊት...ሁሉ፤* የብሉይ ኪዳንን እውነተኞች ነቢያት ሳይሆን እንደ ፈሪሳውያንና እንደ ካህናት አለቆች ያሉትን 'ሐሰተኞች እረኞች' ለማለት ነው፤ የዚህን ምዕራፍ መግቢያ (የቍ 1-30) ማብ ይመ።

10፥9 *በሩ፤* ወደ ድነት የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ ነው፤ በዚያ የገባም ሙሉ ዋስትና አለው፤ እንደ ልብ ወጥቶ የሚያስ ፈልገውን ሁሉ የሚያገኝበት መሰማሪያም በዚያ አለለት።

10፥10 *ሌባው፤* ስራቂው ራሱን ይወዳል፤ ዝንባሌውም ሁሉ ወደ ራሱ ጥቅም ያደላ ነው። የክርስቶስ ፍቅር ግን፣ የተሟላ ሕይወት እንዲያገኙ በሚያስችላቸው፣ በበጎቹ ላይ ነው (የ1፥4 ማብ ይመ)።

10፥11 *እኔ ነኝ፤* የ6፥35 ማብ ይመ። *ሕይወቱን...አሳልፎ ይሰጣል፤* በእስራኤልና በአካባቢዋ እረኛ ለበጎቹ ሲል ሕይወቱን ለአደጋ እስከማጋለጥ ይደርስ ነበር (ዘፍ 31፥39፤ 1ሳሙ17፥34-37 ይመ)፤ ይሁን እንጂ ሊያጋጥመው የሚችለውን አደጋ አልፎ በሕይወት እንደሚቈይ ተስፋ ያደርጋል። ኢየሱስ ግን መልካም እረኛ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ እንደሚሰጥ ያረጋግጣል።

10፥12 *ተቀጣሪው (እረኛ)፤* እንዲህ ያለው እረኛ የሚያ ስበው ስለ ደመወዙ እንጂ ስለ በጎቹ አይደለም፤ ምንደኛ በመሆኑም ነጣቂ አውሬ ሲመጣ፣ በጎቹን ትቶ ይሸሻል (ቍ 13)።

10፥14 *በጎቼን ዐውቃለሁ፤* እነርሱም ያውቁኛል፤ ጌታ የራሱ የሆኑትን ያውቃል (2ጢሞ 2፥19)፤ በጎቹም ያወቃቸውንና

ነው። ሕይወቴንም ስለ በጎቼ አሳልፌ እሰጣ
ለሁ። 16ከዚህ ጒረኖ ያልሆኑ ሌሎች በጎች
አሉኝ፤ እነርሱንም ማምጣት አለብኝ። እነር
ሱም ድምፄን ይሰማሉ፤ አንድ መንጋም፣ ይሆ
ናሉ፤ እረኛውም አንድ። 17መልሼ ለማንሣት
ሕይወቴን አሳልፌ ስለምሰጥ አባቴ ይወደ
ኛል። 18ሕይወቴን በራሴ ፈቃድ አሳልፌ
እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም፤
አሳልፌ ለመስጠትም ሆነ ለማንሣት ሥል
ጣን አለኝ፤ ይህን ትእዛዝ የተቀበልሁትም
ከአባቴ ነው።"
19ከዚህም ቃል የተነሣ በአይሁድ መካከል
እንደ ገና መለያየት ተፈጠረ። 20ብዙዎቹም፣
"ጋኔን ያደረበት እብድ ነው፤ ለምን ትሰሙ
ታላችሁ?" አሉ።
21ሌሎች ግን፣ "ይህ ጋኔን ያደረበት ሰው
ንግግር አይደለም፤ ጋኔን የዐይነ ስውርን ዐይን
መክፈት ይችላልን?" አሉ።

## የአይሁድ አለማመን

22በኢየሩሳሌምም የቤተ መቅደስ መታደስ
በዓል[^] ሆነ፤ ጊዜውም ክረምት ነበረ፤ 23ኢየሱ
ስም በቤተ መቅደስ ግቢ፣ በሰሎሞን መመ
ላለሻ ያልፍ ነበር፤ 24አይሁድም ከበውት፣
"እስከ መቼ ልባችንን አንጠልጥለህ ታቈየ
ናለህ? አንተ ክርስቶስ[#] ከሆንህ በግልጽ ንገ
ረን" አሉት።
25ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ "እኔ
ነግሬአችሁ ነበር፤ እናንተ ግን አታምኑም፤
በአባቴ ስም የማደርጋቸው ታምራትም ስለ እኔ
ይናገራሉ፤ 26እናንተ ግን በጎቼ ስላልሆናችሁ
አታምኑም፤ 27በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔ ዐው
ቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ይከተሉኛል፤ 28እኔ የዘላ
ለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠፉም፤
ከእጄም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም።
29እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል[+]፤
ከአባቴም እጅ ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም።
30እኔና አብ አንድ ነን።"
31አይሁድ ሊወግሩት እንደ ገና ድንጋይ
አነሡ፤ 32ኢየሱስ ግን፣ "ከአብ የሆኑ ብዙ
ታላላቅ ታምራትን አሳየኋችሁ፤ ታዲያ ከእ
ነዚህ ስለ የትኛው ትወግሩኛላችሁ?" አላቸው።
33አይሁድም፣ "የምንወግርህ፣ ተራ ሰው ሆነህ
ሳለህ፣ ራስህን አምላክ በማድረግ፣ የስድብ
ቃል ስለ ተናገርህ ነው እንጂ ከእነዚህ ስለ
የትኛውም አይደለም" ብለው መለሱለት።
34ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ "በሕ
ጋችሁ፣ 'እናንተ አማልክት ናችሁ አልሁ'
ተብሎ አልተጻፈምን? 35የእግዚአብሔር ቃል

10+16 ኢሳ56+8፤ ሕዝ34+23፡37+24፤ ዮሐ11+52፡17+20፡21፤ሐሥ10+34፡35፤ ኤፌ2+11-19
10+17 ቍ11፡15፡18
10+18 ማቴ26+53፤ዮሐ15+10፤ፊል 2+8፤ዕብ5+8
10+19 ዮሐ6+52
10+20 ማር3+21፡22፤ንግ9+11፤ኤር29+26
10+21 ዘፀ4+11፤ ማቴ4+24፤ ዮሐ9+32፡33
10+23 ሐሥ3+11፤5+12
10+24 ዮሐ1+19፤ 16+25፡29፤ሉቃ22+67
10+25 ዮሐ4+26፤ 5+36፤8+58፤14+11
10+26 ዮሐ8+47
10+27 ቍ4፡14
10+28 ኢሳ66+22 ፤ማቴ25+46፤ዮሐ6+39
10+29 ዮሐ14+28፤17+2፡6፡24
10+30 ዘዳ6+4፤ ዮሐ17+21-23
10+31 ዮሐ8+59
10+33 ዘሌ24+16፤ማቴ26+63-66፤ ዮሐ5+18
10+34 መዝ82+6፤ ዮሐ8+17፤12+34፤15+25፤ሮሜ3+19፤1ቆሮ 14+21 10+35 ዕብ4+12፤ማቴ5+18

^22 "ሁኑካ" ማለት ነው #24 ወይም *መሲሑ*
+29 ብዙ የጥንት ቅጆች *አባቴ የሰጠኝ ከሁሉ ይበልጣል* ይላሉ

ራሱን የገለጠላቸውን እረኛ ያውቁታል።

10+15 *ሕይወቴንም...አሳልፌ እሰጣለሁ፤* ቊ. 11 እና ማብ እንዲሁም 15+13 ይመ።

10+16 *ሌሎች በጎች፤* እንዲህ የተባሉት ገና ወደ እርሱ ያልመጡ ቢሆኑም በመሠረቱ የክርስቶስ ናቸው። 'ከዚህ ጒረኖ ያልሆኑ' ሲል፤ ከአይሁድ ወገን ውጭ የሆኑትን ማለት ነው፤ ወደ ፊት በዓለም ዙሪያ የምትስፋፋውም ቤተ ክርስቲያን እዚህ ላይ በጨረፍታ ትታያለች። *አንድ መንጋ፤* የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ እረኛ አንድ ነው፤ (17+20-23 ይመ)።

*10+17-18፤* ክርስቶስ ለሕዝቡ ይሞታል የሚለው ሐሳብ በዚህ የወንጌል ክፍል ውስጥ ተናኝቷል። የአብ ፍቅርና ዕቅድ፣ ለልጁም የሰጠው ሥልጣን ተያይዘው ቀርበዋል። ክርስቶስ በታዛዥነት መሥዋዕት መሆንን ፈቀደ እንጂ የእርሱን ሕይወት ለማሳለፍ ማንም ኀይል አልነበረውም።

10+19 *መለያየት ተፈጠረ፤* 7+43 እና 9+16 ይመ።

10+20 *ጋኔን ያደረበት፤* የ7+20 ማብ ይመ።

10+21፤ ከ9+16 ጋር ያነጻጽሩ።

10+22 *የቤተ መቅደስ መታደስ በዓል፤* አንጦያኮስ ኤጲፋንስ የተባለ ሰው ለጣዖት ሠውቶበት የአይሁድን ቤተ መቅደስ ካረከሰ በኋላ፣ ይሁዳ መቃቢስ ከቅ.ክ. በታኅሣሥ 165 ዓመት ያነጻበት መታሰቢያ በዓል ነው። ይህም አይሁድ በመጨረሻ የተቀዳጁት ታላቅ ድል ነበር። *ክረምትም ነበር፤* የአይሁድን ዘመን አቈጣጠር ለማያውቁ ሰዎች እገዛ ለማድረግ የሰፈረ ሐሳብ ነው።

10+23 *በሰሎሞን መመላለሻ፤* ሐሥ 3+11 እና 5+12 ይመ። በአንድ ፊት ግድግዳ ያለው በሌላ ፊት ግን በዐምዶች ተደግፎ ባለ ጣራ ሆኖ የተሠራ መግቢያ መውጫ ነበር። መመላለሻው በሰሎሞን ዘመን የተሠራ ነው የሚለው ግምት ትክክል አይደለም።

10+24 *ክርስቶስ፤* የ1+25 ማብ ይመ፤ ከ20+31 ጋር ያነጻጽሩ። በዚህ ክፍል የቀረበው ጥያቄ ወሳኝ ነበር፤ ስለ መሲሑ አመጣጥ በጊዜው የተለያየ ሐሳብ ተነዝቶ ስለ ነበር፣ ይህን ጥያቄ መመለስ ቀላል አልነበረም።

10+25 *ነግሬአችሁ ነበር፤* ኢየሱስ መሲሕነቱን ከሳምራዊቷ ሴት በስተቀር ለማንም በግልጽ አልተናገረም (4+26)። እዚህ ላይ የትምህርቱ ዋና ሐሳብ መሲሕነቱን በግልጽ እንደሚያመለክት መንገሩ ሊሆን ይችላል፤ ወይም በ8+58 ላይ የተናገረው ሐሳቡን ግልጽ አድርጎታል ማለቱም ሊሆን ይችላል፤ ወይም ታምራቱን ጨምሮ የሕይወቱን አካሄድ በሙሉ፣ ይኸውም በአብ ስም ያደረገውን ሁሉ እንደ ማስረጃ ማመልከቱ ሊሆን ይችላል። *ስም (በአባቴ)፤* የ2+23 ማብ ይመ)።

10+26 *በጎቼ ስላልሆናችሁ፤* የእርሱ በጎች እንዳይሆኑ የከለከላቸው ደንዳና ልባቸው ነው።

10+27 *ድምፄ፤* ከቊ. 3-5 ካለው ጋር ያነጻጽሩ። *ዐውቃቸዋለሁ፤* ከቊ. 14 ጋር ያነጻጽሩ። *ይከተሉኛል፤* ከቊ. 4-5 ካለው ጋር ያነጻጽሩ።

10+28 **የዘላለም ሕይወት፤** የክርስቶስ ስጦታ ነው (የ3+15 ማብ ይመ)። *ከቶ አይጠፉም፤* የግሪኩ አገላለጽ በጎች ሊጠፉ ይችላሉ የሚለውን ሐሳብ ፈጽሞ አያመለክትም፤ የበጎቹ ደኅንነት ማንም እንዲነጥቃቸው በማይፈቅደው እረኛ ኀይል ይጠበቃል።

10+29 *አባቴ፤* የ5+17 ማብ ይመ። *አይችልም፤* በጎቹን ከማንኛውም ጠላት በአስተማማኝ ሁኔታ ለመጠበቅ የአብ ክንድ ኀያል ነው።

10+30 *አንድ፤* ሁለቱ በባሕርይ አንድ ሲሆኑ በአካል የተለያዩ ናቸው። ይህ ታላቅ ምስጢር ኢየሱስን 'እኔ ነኝ' እንዲል አስችሎታል (8+24፡ 28፡58፤ የ6+35 ማብ፤ 17+21-22 ይመ)።

10+31 *አይሁድ፤* የ1+19 ማብ ይመ። *ሊወግሩት፤* የኢየሱስን ንግግር እግዚአብሔርን እንደ ማቃለል በመቊጠር፣ የሕጉን ሥርዐት ሳይከተሉ፣ በጕልበታቸው ሕጉን ለመፈጸም (ዘሌ 24+16) ተነሣሡ።

10+32 *ታላላቅ ታምራት፤* የኢየሱስን ታምራት የሚያከትቱ ቢሆንም፣ የግሪኩ አገላለጽ በአጠቃላይ ውብና ክቡር የሆኑትን ተግባራት ያመለክታል (የቊ. 38 ማብ ይመ)፤ ስለዚህ 'መልካም ሥራዎች' ማለትም ይሆናል (ለምሳሌ ማቴ 5+16፤ 1ጢሞ 5+10፡ 25፤ 6+18)።

10+33 *የስድብ ቃል፤* የአይሁድ መሪዎች የኢየሱስን ንግግር ዓላማ በሚገባ ተረድተዋል፤ ይሁን እንጂ የተዛባ አመለካከታቸውና አለማመናቸው የተናገረውን እውነት እንዳይቀበሉ አግዶአቸዋል።

10+34 *በሕጋችሁ፤* 'ሕግ' ሲባል አበክሮ የሚያሳየው አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት ሲሆን፣ ብዙ ጊዜ ግን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በሙሉ ያመለክታል። *አማልክት ናችሁ፤* ኢየሱስ በመዝ 82+6 ላይ ያሉትን ቃላት ሲጠቅስ ገዥዎችን (ወይም

የመጠሪያቸውን ‘አማልክት’ካላቸውና፣ መጽሐፍም
ሊሻር የማይቻል ከሆነ፣ [36]ታዲያ፣ ‘የእግዚ
አብሔር ልጅ ነኝ’ ስላልሁ፣ አብ ለራሱ ለይቶ
የቀደሰውንና ወደ ዓለም የላከውን፣ ተሳድ
በሃል ብላችሁ ለምን ትወነጅሉኛላችሁ? [37]አባቴ
የሚያደርገውን ባላደርግ አትመኑኝ፤ [38]የማደ
ርገው ከሆነ ግን እኔን ባታምኑኝ እንኳ፣
አብ በእኔ እንዳለ እኔም በአብ እንዳለሁ
ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ታምራቱን እመኑ።”
[39]እንደ ገናም ሊይዙት ሞከሩ፤ እርሱ ግን ከእ
ጃቸው አመለጠ።

[40]ከዚያም ኢየሱስ፣ ቀደም ሲል ዮሐንስ
ያጠምቅበት ወደ ነበረበት፣ ወደ ዮርዳኖስ
ማዶ ተመለሰ፤ በዚያም ሰነበተ፤ [41]ብዙ ሰዎ
ችም ወደ እርሱ መጡ። እነርሱም፣ “ዮሐ
ንስ አንድም ታምራዊ ምልክት አላደረገም፣
ነገር ግን ስለዚህ ሰው የተናገረው ሁሉ እው
ነት ነበረ” አሉ። [42]በዚያም ስፍራ ብዙዎች
በኢየሱስ አመኑ።

## የአልዓዛር መሞት

11 በማርያምና በእኅቷ በማርታ መንደር
በቢታንያ ይኖር የነበረው አልዓዛር
ታሞ ነበር።

[2]ይህች ወንድሟ አልዓዛር የታመመባት
ማርያም፣ በጌታ ላይ ሽቱ አፍስሳ እግሩን
በጠጕሯ ያበሰችው ነበረች። [3]እኅትማማቾ
ቹም፣ “ጌታ ሆይ፤ የምትወደው ሰው ታሞአል”
ብለው መልእክት ላኩበት።

[4]ኢየሱስ ይህን በሰማ ጊዜ፣ “ይህ ሕመም
የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ
ለእግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት የሚያ

10፥36 ኤር1፥5፤ ዮሐ3፥17፤ 5፥17፡ 18፤6፥69
10፥37 ቍ25
10፥38 ዮሐ14፥10፡ 11፡20፤17፥21
10፥39 ሉቃ4፥30፤ ዮሐ7፥30፤8፥59
10፥40 ዮሐ1፥28
10፥41 ዮሐ1፥26፡27፡ 30፡34፤ 2፥11
10፥42 ዮሐ7፥31
11፥1 ማቴ21፥17፤ ሉቃ10፥38
11፥2 ማር14፥3፤ ሉቃ7፥38፤ዮሐ12፥3
11፥3 ቍ5፡36
11፥4 ቍ40
11፥7 ዮሐ10፥40
11፥8 ማቴ23፥7፤ ዮሐ8፥59፤10፥31
11፥9 ዮሐ9፥4፤ 12፥35
11፥11 ቍ3፤ ማቴ9፥24
11፥13 ማቴ9፥24
11፥16 ማቴ10፥3፤ ዮሐ14፥5፤20፥24-28፤21፥2፤ሐሥ1፥13

ደርስ አይደለም” አለ። [5]ኢየሱስም ማርታን፣
እኅቷንና አልዓዛርን ይወዳቸው ነበር። [6]ሆኖም
አልዓዛር መታመሙን በሰማ ጊዜ በነበረበት
ስፍራ ሁለት ቀን ቈየ።

[7]ከዚህም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን፣ “ወደ
ይሁዳ እንመለስ” አላቸው።

[8]እነርሱም፣ “መምህር ሆይ፤ ከጥቂት ጊዜ
በፊት አይሁድ በድንጋይ ሊወግሩህ እየፈለጉህ
ነበር፤ እንደ ገና ወደዚያ ትሄዳለህን?” አሉት።

[9]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ቀኑ
ዐሥራ ሁለት ሰዓት ብርሃን አይደለምን?
ከዚህ ዓለም ብርሃን የተነሣ ስለሚያይ በቀን
የሚመላለስ አይሰናከልም፤ [10]የሚሰናከለው
ግን በሌሊት የሚመላለስ ነው፤ ብርሃን የለው
ምና።”

[11]ይህን ከነገራቸው በኋላ፣ “ወዳጃችን አልዓ
ዛር ተኝቶአል፤ እኔም ከእንቅልፉ ላስነሣው
እሄዳለሁ” አላቸው።

[12]ደቀ መዛሙርቱም፣ “ጌታ ሆይ፤ ተኝቶ
ከሆነስ ይድናል” አሉት። [13]ኢየሱስ ይህን
የነገራቸው ስለ ሞቱ ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱ
ግን እንቅልፍ ስለ መተኛቱ የተናገረ መሰላ
ቸው።

[14]ስለዚህም በግልጽ እንዲህ አላቸው፤
“አልዓዛር ሞቶአል፤ [15]ታምኑ ዘንድ፣ በዚያ
ባለመኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፤ አሁን
ግን ወደ እርሱ እንሂድ።”

[16]ከዚያም ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ
ለተቀሩት ደቀ መዛሙርት፣ “እኛም ሄደን
ከእርሱ ጋር እንሙት” አላቸው።

ሌሎች መሪዎችን ወይም አለቆችን) ለማመልከት ሲሆን፣ ተግባራ ቸውን ለማከናወን በመለኮት የተቀቡ መሆናቸውን ለማሳየት ነበር (ዘፀ22፥28፤ ዘዳ 1፥17፤ 16፥18፤ 2ዜና 19፥6 ይመ)።

10፥35 *መጻሕፍትም ሊሻሩ የማይቻል ከሆነ፤* ብሉይ ኪዳን ሙሉ ሥልጣን ያለውና ሊታመን የሚገባው መሆኑን ኢየሱስ ይመሰክራል።

*10፥36፤* ሰዎች፣ ‘አማልክት ናችሁ’ እስከ መባል ከደረሱ (መዝ 82፥6)፣ አብ ለራሱ የለየውና የላከው የቱን ያህል አብልጦ ይባል!

10፥37 *አባቴ የሚያደርገውን፤* እግዚአብሔር ራሱ የሚያደርገውን የርኅራኄ ሥራ ለማለት ነው።

10፥38 *ታምራቱን፤* ቀጥታ ትርጕሙ ‘ሥራዎች’ ማለት ነው፤ ታምራቱ ከኢየሱስ ሥራዎች አንዱ ክፍል ናቸው፤ ቀድሞውኑ ኢየሱስ ይህን የገለጸው፣ ሰዎቹ ለማስተዋል ባለ መብቃታቸው ሳይሆን፣ የሕይወቱን አርዓያነት ለማሳየት ነው (የቍ 32 ማብ ይመ)።

10፥39 *ሊይዙት ሞከሩ፤* ፍርድ ፊት ለማቅረብ ይሁን ወይም በድንጋይ ለመውገር፣ እዚህ ላይ ግልጽ አይደለም። *አመለጠ፤* በምን ምክንያት ሊይዙት እንዳልቻሉ ዮሐንስ አላመለከተም፤ የተወሰነው ጊዜ ከመድረሱ በፊት ግን ኢየሱስ ሕይወቱ ሊያልፍ እንደማይችል ዮሐንስ አብዛኛውን ጊዜ በግልጽ አስረድቷል (የ2፥4 ማብ እና ሉቃ 4፥30 ይመ)።

10፥41 *ዮሐንስ...የተናገረው ሁሉ፤* መጥምቁ ዮሐንስ የመሰከረውን ሁሉ ማለት ነው (1፥7 እና ማብ ይመ)።

11፥1 *አልዓዛር፤* ይህ ስም በዮሐንስ ወንጌል የተጠቀሰው በም 11 እና 12 ብቻ ነው። ተመሳሳይ ስም፣ በሉቃ 16፥19-31 በተመለከተው ምሳሌ ይገኛል። እኅቶቹ ግን በሉቃ 10፥38-42 ተጠቅሰዋል።

11፥2 *ሽቱ አፍስሳ፤* 12፥3 ይመ።

11፥3 *የምትወደው ሰው፤* ጌታ፣ አልዓዛርን ምን ያህል ይወደው እንደ ነበር ያመለክታል።

*11፥4፤* ከ9፥3 ጋር ያነጻጽሩ። *ይህ ሕመም...ለሞት የሚያደርስ አይደለም፤* ኢየሱስ እንዲህ ማለቱ የአልዓዛርን መነሣት አስቀድሞ መናገሩ ነው (ቍ 44)፤ የአልዓዛርን መሞት አውቆ ነበርና (ቍ 14)። ቍ 17 እና 39 ላይ፣ ‘አራት ቀን’ የተባለው ሲታሰብ አልዓዛር የሞተው መልእክተኞቹ ከተነሡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደሆነ ያመለክታል፤ ይኸውም አንዱ ቀን መልእክቱን ማድረሻ፣ ሁለቱ ቀናት ደግሞ ኢየሱስ ሁኔታውን ከሰማ በኋላ ከነበረበት ስፍራ የቈየበት ሲሆን (ቍ 6፤ 10፥40) ሌላው አንድ ቀን ደግሞ ኢየሱስ ወደ ቢታንያ የተጓዘበት ነው። ይሁን እና በቍ 17 ላይ የተጻፈውን ማብ ይመ። ክብር፤ የ7፥39፤ የ12፥41፤ የ13፥31 ማብ ይመ። እዚህ ላይ አልዓዛር በታምር ከሞት በመነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ ይከብራል፤ ታምሩም በአንድ በኩል የእግዚአብሔር ክብር በኢየሱስ መገለጡን ሲያሳይ (ቍ 40፤ እግዚአብሔር ብቻውን ሙታንን ያስነሣልና 5፥21 ይመ)፣ በሌላም በኩል አይሁድ በጠላትነት እንዲነሣሡበት አድርጓል ቍ 46-53)።

11፥6 *በነበረበት ስፍራ...ቈየ፤* ማርያምና ማርታ እንዳሰቡት ሳይሆን፣ አባቱ እንደ መራው ኢየሱስ ከቦታ ቦታ ይዘዋወር ነበር (ከ2፥3-4 ጋር ያነጻጽሩ)።

11፥8 *አይሁድ፤* የ1፥19 ማብ ይመ። *ሊወግሩህ እየፈለጉህ፤* የ10፥31 ማብ ይመ፤ ወደ ይሁዳ ምድር መሄዱ በእርግጥ አደጋ ያስከትል ነበር።

11፥9 *ቀኑ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ብርሃን አይደለምን?፤* በአብ ፈቃድ መመላለሱን እንደ ቀን ብርሃን ቈጥሮታል።

11፥11 *ተኝቶአል፤* ክርስቲያኖችም ሆኑ ሌላው ዓለም ሞትን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ስም ለበስ አባባል ነው።

11፥15 *ታምኑ ዘንድ፤* ከ20፥31 ጋር ያነጻጽሩ።

11፥16 *ዲዲሞስ...ቶማስ፤* ‘ቶማስ’ የሚለው ስም የተገኘበት የዕብራይስጡ ቃልና ‘ዲዲሞስ’ የሚለው የግሪኩ ቃል ትርጕማቸው ‘መንታ’ ማለት ነው፤ ብዙውን ጊዜ ቶማስን የምናውቀው በተጠራጣሪነቱ ነው (20፥24-28) ይሁን እንጂ ትጕህና

## ኢየሱስ የአልዓዛርን እኅቶች ማጽናናቱ

17ኢየሱስ ሲደርስ አልዓዛር ከተቀበረ አራት
ቀን ሆኖት ነበር፡፡ 18ቢታንያ ከኢየሩ
ሳሌም ዐሥራ አምስት ምዕራፍ[ሀ] ያህል ትርቅ
ነበር፡፡ 19ብዙዎች አይሁድም ማርታንና
ማርያምን ስለ ወንድማቸው ሞት ሊያጽናኗ
ቸው መጥተው ነበር፤ 20ማርታ የኢየሱስን
መምጣት ሰምታ ልትቀበለው ወጣች፤ ማርያም
ግን በቤት ቀርታ ነበር፡፡
21ማርታም ኢየሱስን እንዲህ አለችው፤
"ጌታ ሆይ፤ አንተ በዚህ ብትሆን ኖሮ፣
ወንድሜ ባልሞተ ነበር፡፡ 22አሁንም ቢሆን
የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚሰጥህ
ዐውቃለሁ፡፡"
23ኢየሱስም፣ "ወንድምሽ ይነሣል" አላት፡፡
24ማርታም፣ "በመጨረሻው ቀን፣ በትንሣኤ
እንደሚነሣ ዐውቃለሁ" አለችው፡፡
25ኢየሱስም እንዲህ አላት፤ "ትንሣኤና ሕይ
ወት እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳ
በሕይወት ይኖራል፤ 26በእኔ የሚኖር፣ የሚ
ያምንብኝም ከቶ አይሞትም፤ ይህን ታምኛ
ለሽን?"
27እርሷም፣ "አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ ወደ
ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ[+] የእግዚአብሔር ልጅ
መሆንህን አምናለሁ" አለችው፡፡
28ይህን ካለች በኋላ፣ ተመልሳ እኅቷን
ማርያምን ለብቻዋም ጠርታ፣ "መምህሩ መጥ
ቷል፤ ይፈልግሻልም" አለቻት፡፡ 29ማርያምም
ይህን እንደ ሰማች፣ ፈጥና ተነሥታ ወደ
እርሱ ሄደች፡፡ 30በዚህ ጊዜ ኢየሱስ፣ ማርታ
እርሱን በተቀበለችበት ቦታ ነበር እንጂ፣
ገና ወደ መንደር አልገባም ነበር፡፡ 31ማርያምን
ሲያጽናኑ በቤት ውስጥ የነበሩ አይሁድም፣
ብድግ ብላ መውጣቷን ሲያዩ፣ ወደ መቃብሩ
ሄዳ የምታለቅስ መስሎአቸው ተከተሏት፡፡
32ማርያምም ኢየሱስ ወደ ነበረበት ቦታ
ደርሳ እንዳየችው፣ እግሩ ላይ ተደፍታ፣ "ጌታ
ሆይ፤ አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ፣ ወንድሜ
ባልሞተ ነበር" አለችው፡፡
33ኢየሱስም እርሷ ስታለቅስ፣ ተከትለዋትም
የመጡት አይሁድም ሲያለቅሱ ባየ ጊዜ መን
ፈሱ በሐዘን ታወከ፤ 34"የት ነው ያኖራችሁት?"
ሲል ጠየቀ፡፡
እነርሱም፣ "ጌታ ሆይ፤ መጥተህ እይ"
አሉት፡፡
35ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ፡፡
36አይሁድም፣ "እንዴት ይወደው እንደ
ነበር አያችሁ!" አሉ፡፡
37ከእነርሱ አንዳንዶቹ ግን፣ "የዐይነ ስውሩን
ዐይን የከፈተ፣ ይህም ሰው እንዳይሞት ማድ
ረግ አይችልም ነበር?" አሉ፡፡

## ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣቱ

38ኢየሱስ ልቡ ዳግመኛ በኀዘን ተነክቶ
ወደ መቃብሩ መጣ፤ መቃብሩም በድንጋይ
የተገጠመ ዋሻ ነበር፤ 39እርሱም፣ "ድንጋዩን
አንሡት" አለ፡፡
የሟቹም እኅት ማርታ፣ "ጌታ ሆይ፤ አሁንማ
አራት ቀን ስለ ቈየ ይሸታል" አለችው፡፡
40ኢየሱስም፣ "ብታምኚስ የእግዚአብሔርን
ክብር ታያለሽ ብዬ አልነገርሁሽም?" አላት፡፡
41ስለዚህ ድንጋዩን አነሡ፡፡ ኢየሱስም ወደ
ላይ ተመልክቶ እንዲህ አለ፤ "አባት ሆይ፤
ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ 42ሁልጊዜም
እንደምትሰማኝ ዐውቃለሁ፤ ይህን መናገሬ
ግን በዚህ የቆሙ ሰዎች አንተ እንደላክኸኝ
ያምኑ ዘንድ ነው፡፡"

[ሀ]18 ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ነው
[+]27 ወይም መሲሕ

11፥17 ቍ6፡39
11፥18 ቍ1፤ ማቴ21፥17
11፥19 ቍ31፤ ኢዮ2፥11
11፥20 ሉቃ10፥38-42
11፥21 ቍ32፡37
11፥22 ቍ41፡42
11፥24 ዳን12፥2፤ ዮሐ5፥28፡29፤6፥39፡40፤ሐሥ24፥15
11፥25 ዮሐ1፥4፤ 3፥15፤6፥35
11፥26 ማቴ25፥46፤ዮሐ3፥15
11፥27 ማቴ4፥3፤ ሉቃ2፥11፤ዮሐ6፥14
11፥28 ማቴ26፥18፤ዮሐ13፥13
11፥30 ቍ20
11፥31 ቍ19
11፥32 ቍ21
11፥33 ቍ38፤ ዮሐ12፥27
11፥35ሉቃ19፥41
11፥36 ቍ3
11፥37 ቍ21፡32፤ ዮሐ9፥6፡7
11፥38 ቍ33፤ ማቴ27፥60፤ ሉቃ24፥2፤ዮሐ20፥1
11፥39 ቍ17
11፥40 ቍ4፡23-25
11፥41 ማቴ11፥25፤ዮሐ17፥1
11፥42 ዮሐ3፥17፤ 12፥30

ደፋር ሰውም ነበር፡፡

11፥17 *አራት ቀን*፤ የቍ 4 ማብ ይመ፡፡ ብዙ አይሁድ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ወደ ሕይወት ሊመለስ ስለሚችል፣ ነፍሱ ከአስከሬኑ አጠገብ እስከ ሦስት ቀን ትቈያለች ብለው ያምናሉ፡፡ ይህ ሐሳብ በእነዚህ ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ከሆነ፣ አልዓዛር ሊመለስ ይችላል ተብሎ ተስፋ በማይደረግበት ሁኔታ ሞቶ ነበር ማለት ነው፡፡

11፥18 *ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል*፤ ዮሐንስ ለትክክለኛ አገላለጽ ምን ያህል ጥንቃቄ እንደ ነበረው ያሳያል፡፡

11፥19 *ሊያጽናኗቸው*፤ በአይሁድ ልማድ፣ ለሦስት ቀናት እጅግ ከባድ ሐዘን፣ ለሚቀጥሉት አራት ቀናት መለስ ያለ ሐዘን፣ ሠላሳው ቀን እስከሚያበቃ ድረስ ቀለል ያለ ሐዘን እንዲደረግ ይፈቀዳል፤ ወዳጆችም ሐዘን የደረሰበትን ቤተ ሰብ ማጽናናት ይጠበቅባቸዋል፡፡

11፥20 *ልትቀበለው ወጣች*፤ ታላቂቱ እርሷ በመሆኗ ሳይሆን አይቀርም፤ በቤቷ ተቀብላዋለችና (ሉቃ 10፥38)፡፡

*11፥21፤* በቍ 32 ይህንኑ ሐሳብ ማርያም በድጋሚ ትናገ ራለች፤ እኅትማማቾቹ የኢየሱስን መምጣት ሲጠባበቁ፣ ይህንኑ ሐሳብ ደጋግመው ሳያነሡት አልቀረም፡፡

11፥22 *የምትለምነውን ሁሉ፤* የአልዓዛር ሬሳ በመበስበስ ላይ ቢሆንም፣ ማርታ በዚያኑ ቀን ወንድሟ በቅጽበት ሊነሣ እንደሚችል ተስፋ እንዳላት ይህ አስተያየቷ ያመለክታል፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና፡፡

11፥25 *እኔ ነኝ፤* የ6፥35 ማብ ይመ፡፡ *ሕይወት*፤ የ1፥4 ማብ ይመ፡፡ ኢየሱስ ሕይወትና ትንሣኤ ከመስጠቱ ይልቅ፣ 'እኔ ነኝ' በማለት መለኮትነቱን ገልጿል፡፡ በአንድ በኩል ሕይወትና ትንሣኤ በእርሱ እንደሚገለጡ ያሳያል፤ በሌላ በኩል ከባሕርዩ የተነሣ ሞት እንደማይገዛው ያመለክታል፡፡ እርሱም ራሱ ሕይወት ነው (ከ14፥6፤ ከሐሥ 3፥15፤ ከዕብ 7፥16 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ *በእኔ የሚያምን... በሕይወት ይኖራል*፤ የ1፥7 ማብ ይመ፡፡ ኢየሱስ ሕይወትን መስጠት ብቻ ሳይሆን፣ ለሚታመንበት ሁሉ ሞት እንዳይነ ግሥበት ድልን ይሰጠዋል (ከ1ቆሮ 15፥54-57 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡

11፥27 *አምናለሁ፤* ማርታ የምትታወቀው በሉቃ 10፥40-41 ላይ በታየው ድክመቷ ነው፤ ይህ አስደናቂ ገለጻዋ ግን እምነት ያላት ሴት መሆኗን ያሳያል፡፡

11፥28 *መምህሩ፤* በዚያን ጊዜ 'ረቢዎች' ሴቶችን አያስተ ምሩም ነበር (ከ4፥27 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ ኢየሱስ ግን አዘውትሮ ያስተምራቸው ነበር፤ ስለዚህ አንዲት ሴት በዚያ ስያሜ ስትጠራ ያልተለመደ ነው፡፡

11፥31 *ሄዳ የምታለቅስ*፤ በመቃብር ላይ ማልቀስ የተለ መደ ስለ ነበር፣ በዚያ የተሰበሰቡት አይሁድ፣ ማርያም ወደ መቃብሩ ሄዳ ልታለቅስ መስሏቸው እስከ መቃብሩ ቦታ ተከ ተሏት፤ የኢየሱስም ታምር በብዙ ሕዝብ ዘንድ ሊታወቅ ቻለ፡፡

*11፥32፤* ከቍ 21 ጋር ያነጻጽሩ፡፡

11፥33 *ስታለቅስ...ሲያለቅሱ፤* ሁለቱም የሚያመለክቱት በዋይታ የሚገለጸውን ሐዘን ነው፡፡

11፥35 *እንባውን አፈሰሰ*፤ የግሪኩ ቃንቋ የሚያመለ ክተው፣ 'እንባውን አፈሰሰ' ሲባል በቍ 33 ላይ እንደተገለጸው በዋይታ ማዘንን ሳይሆን፣ በጸጥታ ማልቀስን ነው፤ ይህም በእንባ ብቻ የሚገለጽ ሐዘን ማለት ነው፡፡

*11፥36፤* ከቍ 5 ጋር ያነጻጽሩ፡፡

*11፥37፤* የአንዳንዶቹ አመለካከት እንደ ማርታና (ቍ 21) እንደ ማርያም (ቍ 32) ቢመስልም፣ ይህን ለማለት የበቁት የዐይነ ስውሩን ዐይን መክፈት መሠረት በማድረግ ነበር፡፡

43 ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ በታላቅ ድምፅ፣
“አልዓዛር፣ ና ውጣ!” ብሎ ተጣራ:: 44 የሞ
ተውም ሰው እጅና እግሩ በቀጭን ስስ ጨርቅ
እንደ ተጠቀለለ፣ ፊቱም በሻሽ እንደተጠ
መጠመ ወጣ::
ኢየሱስም “መግነዙን ፍቱለትና ይሂድ”
አላቸው::

**ኢየሱስን ለመግደል የተደረገ ሤራ**

45 ስለዚህ ወደ ማርያም ከመጡት፣ ኢየሱስ
ያደረገውን ካዩት አይሁድ ብዙዎች በእርሱ
አመኑ:: 46 አንዳንዶቹ ግን ሄደው ኢየሱስ
ያደረገውን ለፈሪሳውያን ተናገሩ፤ 47 ከዚያም
የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን የአይሁድን
ሸንጎ ስብሰባ ጠሩ::
እነርሱም እንዲህ አሉ፤ “ይህ ሰው ብዙ
ታምራዊ ምልክቶችን እያደረገ ስለ ሆነ ምን
ብናደርግ ይሻላል? 48 እንዲሁ ብንተወው ሰው
ሁሉ በእርሱ ያምናል፤ ሮማውያንም መጥተው
ስፍራችንንና* ሕዝባችንን ይወስዱብናል::”
49 ከመካከላቸውም አንዱ፣ በዚያ ዓመት ሊቀ
ካህናት የነበረው ቀያፋ እንዲህ ሲል ተና
ገረ፤ “እናንተ እኮ ምንም አታውቁም! 50 ሕዝቡ
ሁሉ ከሚጠፋ ስለ ሕዝቡ አንድ ሰው ቢሞት
የሚሻል መሆኑን አታስተውሉም::”
51 ይህን ያለው ከራሱ አልነበረም፤ ነገር ግን
በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት እንደ መሆኑ፣
ኢየሱስ ለአይሁድ ሕዝብ እንደሚሞት ትንቢት
መናገሩ ነበር፤ 52 ለዚያም ሕዝብ ብቻ ሳይ
ሆን፣ የተበተኑትን የእግዚአብሔርን ልጆች በአ
ንድነት ለመሰብሰብ ነው:: 53 ከዚያን ቀን
ጀምሮም ሊገድሉት አሤሩ::
54 ስለዚህ ኢየሱስ ከዚያ ወዲያ በአይሁድ
መካከል በይፋ አልተመላለሰም፤ ነገር ግን
በምድረ በዳ አጠገብ ወደምትገኝ ኤፍሬም
ወደ ተባለች መንደር ገለል አለ፤ በዚያም
ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሰነበተ::
55 የአይሁድ ፋሲካ እንደ ተቃረበም፣ በዓሉ
ከመድረሱ በፊት የመንጻት ሥርዐት ለማ
ድረግ ብዙዎች ከአገር ቤት ወደ ኢየሩ
ሳሌም ወጡ:: 56 ኢየሱስንም ይፈልጉት ነበር፤
በቤተ መቅደስም ቆመው፣ “ምን ይመስላ
ችኋል? ለበዓሉ አይመጣ ይሆን?” ተባባሉ::
57 የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ግን ኢየሱስን
ይይዙት ዘንድ የት እንዳለ የሚያውቅ ሰው
እንዲጠቍም ትእዛዝ ሰጥተው ነበር::

**ኢየሱስ በቢታንያ ሽቱ መቀባቱ**

12፥1-8 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥6-13፤ ማር 14፥3-9፤ ሉቃ 7፥37-39

12 የፋሲካ በዓል ስድስት ቀን ሲቀረው
ኢየሱስ፣ ከሞት ያስነሣው አልዓዛር
ወደሚኖርበት፣ ወደ ቢታንያ መጣ:: 2 በዚ
ያም ለኢየሱስ ሲባል ራት ተዘጋጀ:: ማርታ
ስታገለግል፣ አልዓዛር ከእርሱ ጋር በማእድ
ከተቀመጡት አንዱ ነበር:: 3 ማርያምም ዋጋው

11፥43 ሉቃ7፥14
11፥44 ዮሐ19፥40፤ 20፥7
11፥45 ቍ19፤ ዘፀ14፥31፤ዮሐ2፥23፤ 7፥31
11፥47 ቍ57፤ ማቴ5፥22፤26፥3፤ ዮሐ2፥11
11፥49 ቍ51፤ማቴ 26፥3፤ዮሐ18፥13:14
11፥50 ዮሐ18፥14
11፥52 ኢሳ49፥6፤ ዮሐ10፥16
11፥53ማቴ12፥14
11፥54 ዮሐ7፥1
11፥55 ዘፀ12፥13: 23:27፤2ዜና30፥17: 18፤ማቴ26፥1:2፤ ማር14፥1፤ዮሐ13፥1
11፥56 ዮሐ7፥11
12፥1 ማቴ21፥17፤ ዮሐ11፥55
12፥2 ሉቃ10፥38-42

*48 ወይም *መቅደሳችንን*

11፥39 *አራት ቀን*፤ የቍ 4 እና 17 ማብ ይመ::

11፥40 *ክብር*፤ የቍ 4 ማብ ይመ::

11፥44 *በቀጭን ስስ ጨርቅ*፤ እንደ ፋሻ ያለ ጨርቅ ነው፤ አንዳንድ ጊዜ ሬሳ እንደ ደበላ ባለ ጨርቅ ይጠቀለል ነበር (የ19፥40 ማብ ይመ):: *ሻሽ*፤ ከመግነዙ የተለየ እራፊ ጨርቅ ነው::

11፥45 *ከ…አይሁድ ብዙዎች በእርሱ አመኑ*፤ ምናልባትም ከዚህ ቀደም ይቃወሙት ከነበሩት አይሁድ መካከል፣ ከዚህ ታምር የተነሣ ጥቂቶቹ በዚህ ጊዜ አምነውበት ይሆናል (የ1፥19 ማብ ይመ):: ከቍ 20፥31 ጋር ያነጻጽሩ)::

11፥46 *ፈሪሳውያን*፤ የማቴ 3፥7፤ የማር 2፥16፤ የሉቃ 5፥17ማብ ይመ::

11፥47 *የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን*፤ ፈሪሳውያን የኢየሱስ አገልግሎት ዋና ተቃዋሚዎች እንደ ነበሩ በአራቱም ወንጌሎች ተገልጿል፤ የፖለቲካ ሥልጣን ግን አልነበራቸውም:: ለኢየሱስ መሰቀል ዋና ምክንያት የሆኑት የካህናት አለቆች በወቅቱ በተጠራው የአይሁድ ሸንጎ ስብሰባ ተሳታፊዎች ነበሩ (የማር 14፥55 ማብ ይመ):: የታምራታዊ ምልክቶቹን እውነታ አልካዱም (የ2፥11 ማብ ይመ)፤ ነገር ግን እምነት ስላልነበራቸው የታምራቱን ምንነት አልተረዱም::

11፥48 *ስፍራችንን*፤ አይሁድ አንዳንድ ጊዜ ኢየሩሳሌምን ለማመልከት ይህን መጠሪያ ቢጠቀሙበትም፣ እዚህ ላይ ግን ቤተ መቅደሱን ማለታቸው ሊሆን ይችላል (ሐሥ 6፥13-14፤ 21፥28 ይመ)::

11፥49 *በዚያ ዓመት ሊቀ ካህናት የነበረው*፤ በዚያን ዘመን ሊቀ ካህናት የነበረ ማለት ነው፤ ሊቀ ካህናትነቱም የአንድ ዓመት ሥልጣን ሳይሆን የዕድሜ ልክ ነበር:: *ቀያፋ*፤ ከ18-36 ዓ.ም የነበረው ሊቀ ካህናት ሳይሆን አይቀርም:: እርሱም በ15 ዓ.ም ከሊቀ ካህናትነቱ በሮማውያን የተሻረው የሐና አማች ነበር (18፥13):: *ምንም አታውቁም*፤ የሰዱቃውያንን ልቅ ባሕርይ የሚያመለክት አባባል ነው፤ (ሊቀ ካህናቱ ቀያፋ ሰዱቃዊ ነበረ):: ታሪክ ጸሓፊው ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን (ዩሰፋስ)፣ “ሰዱቃውያን ከአቻዎቻቸው ጋር በሚገናኙበት ወቅት ስድ እንደ ሆኑ ሁሉ፣ ከባዕዳንም ጋር እንደዚያው ናቸው ይላል”:: ስለ ሰዱቃውያን የማቴ 2፥4፤ 3፥7፤ የማር 12፥18፤ የሉቃ 20፥27፤ የሐሥ 4፥1 ማብ ይመ::

11፥50 *የሚሻል*፤ ቀያፋን ያስጨንቅ የነበረው ከበደል ንጹሕ የመሆን ወይም ያለመሆን ጉዳይ ሳይሆን፣ የፖለቲካው አዝማሚያ ነው:: አንድ ሰው በደል ባይኖርበትም፣ መላው ሕዝብ ከሚጠፋ አንድ ሰው ቢጠፋ እንደሚሻል ያምን ነበር:: እንዳለውም አይሁድ ኢየሱስን ሰቀሉ፤ ይሁን እንጂ በ70 ዓ.ም. ሕዝቡም ጠፋ፤ ኢየሩሳሌምም ወደመች::

11፥51 *ሊቀ ካህናት እንደ መሆኑ*፤ ቀያፋ አንድ ተራ ሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ የተሾመ ካህን ስለ ነበር፣ ትንቢት እንዲናገር ያደረገው እግዚአብሔር ነው:: *ትንቢት መናገሩ ነበር*፤ ንግግሩ ሁሉ ከገመተው በላይ ትክክል ነበር:: ትንቢት በቅዱሳት መጻሕፍት ከመለኮት የተገለጠውን እውነት እንዲታወቅ ማድረግ ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የቀያፋ ንግግር ሊተረጐም የሚችለው የኢየሱስ ሞት ለሕዝቡ የሚበጀው የፖለቲካን መሰናክል በማስወገድ ረገድ ሳይሆን፣ የሚያምኑበትን ሰዎች ኀጢአት በማስወገድ ነው::

11፥52 *የተበተኑትን የእግዚአብሔርን ልጆች*፤ የኢየሱስ ሞት ቤዛነት ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ሕዝብ ነው (ከ1፥29፤ 3፥16፤ 4፥42፤ 10፥16 ጋር ያነጻጽሩ)::

11፥54 *ገለል አለ*፤ ኢየሱስ ‘ጊዜው’ ከመድረሱ በፊት ባይሞትም (የ2፥4 ማብ ይመ)፣ ጠላቶቹን ለመጋፈጥ አልተጣደፈም፤ ስለዚህ የተቃዋሚዎቹን አዝማሚያ በማስተዋል ዘወር አለ፤ ለሰው ልጆች ሲል የሚሞተውም ጠላቶቹ በወሰኑት ጊዜ ሳይሆን፣ ራሱ በወሰነው ጊዜ ነው:: *ኤፍሬም*፤ ምናልባት ‘አፍራህ’ በመባል የምትታወቀዋ ከሆነች፣ ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ሃያ አራት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ነበረች::

11፥55 *ፋሲካ*፤ የ2፥13፤ የ5፥1 ማብ ይመ:: *የመንጻት ሥርዐት*፤ ይህ ሥርዐት በዓላትን ለማክበር፣ በተለይም እንደ ፋሲካ ላለው አስፈላጊ ነበር፤ ሳይነጹ ምንም ዓይነት በዓል ማክበር አይቻልም ነበርና (ከ18፥28 ጋር ያነጽጽሩ፤ የ2፥6 ማብ ይመ)::

11፥56 *አይመጣ ይሆን?*፤ የጥያቄው አሰነዛዘር፣ ‘የለም፤ አይመጣም’ የሚለውን መልስ የሚጋብዝ ነው::

*12፥1-11*፤ አራቱም ወንጌሎች ኢየሱስን ሽቱ ስለ ቀባች ሴት ይተርካሉ፤ የዮሐንስ ትረካ በማቴ 26፥6-13 እና በማር 14፥3-9 የተተረከውን ይመስላል፤ በሉቃ 7፥36-50 የተተረከው

ውድ የሆነ፣ ግማሽ ሊትር[a] ንጹሕ የናርዶስ
ሽቱ አምጥታ በኢየሱስ እግር ላይ አፈሰ
ሰች፤ እግሩንም በጠጕሯ አበሰች፤ ቤቱንም
የሽቱው መዓዛ ሞላው።

4ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፣ ኋላ አሳልፎ
የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ግን በመቃወም
እንዲህ አለ፤ 5"ይህ ሽቱ በሦስት መቶ ዲናር
ተሸጦ ገንዘቡ ለድኾች ለምን አልተሰጠም?"
6ይህን የተናገረው የገንዘብ ከረጢት ያዥ
በመሆኑ፣ ከሚቀመጠው ለራሱ የሚጠቀም
ሌባ ስለ ነበር እንጂ ለድኾች ተቈርቋሮ
አልነበረም።

7ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "ይህ ሽቱ ለቀ
ብሬ ቀን የታሰበ ስለ ሆነ እንድታቈየው
ተዋት፤ 8ድኾች ምንጊዜም ከእናንተ ጋር
ናቸው፤ እኔን ግን ሁል ጊዜ አታገኙኝም።"

9በዚህ ጊዜ ብዙ አይሁድ ኢየሱስ በዚያ
መኖሩን ዐውቀው መጡ፤ የመጡትም ኢየ
ሱስን ብለው ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ ከሙታን
ያስነሣውን አልዓዛርንም ለማየት ነበር።
10ስለዚህ የካህናት አለቆች አልዓዛርን ጭምር
ለመግደል ተማከሩ፤ 11ይህም በእርሱ ምክን
ያት ብዙ አይሁድ ወደ ኢየሱስ እየሄዱ
ያምኑበት ስለ ነበር ነው።

## ኢየሱስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ

12፥12-15 ተጓ ምብ - ማቴ 21፥4-9፤ ማር 11፥7-10፤
ሉቃ 19፥35-38

12በማግሥቱም ለበዓሉ የመጣው ብዙ ሕዝብ
ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እየመጣ መሆኑን
ሰሙ፤ 13የዘንባባም ዝንጣፊ ይዘው ሊቀበ
ሉት ወጡ፤ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው
እንዲህ አሉ፤
"ሆሣዕና![b]
"በጌታ ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው!"
"የእስራኤል ንጉሥ ቡሩክ ነው!"
14ኢየሱስም የአህያ ውርንጫላ አግኝቶ
ተቀመጠበት፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤

15"የጽዮን ልጅ ሆይ፤ አትፍሪ፤
እነሆ፤ ንጉሥሽ በአህያ ግልገል ተቀምጦ
ይመጣል።"

16ደቀ መዛሙርቱ ይህን ሁሉ በመጀመሪያ
አላስተዋሉም፤ ስለ እርሱ የተጻፉትንና ለእ
ርሱም የተደረጉትን ልብ ያሉት ኢየሱስ
ከከበረ በኋላ ነበር።

17አልዓዛርን ከመቃብር ጠርቶ ከሙታን
ባስነሣበት ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች
መነሣቱን ይመሰክሩ ነበር። 18ብዙ ሰዎችም
ይህን ታምራዊ ምልክት ማድረጉን ስለ
ሰሙ ሊቀበሉት ወጡ። 19ስለዚህም ፈሪሳ
ውያን እርስ በርሳቸው፣ "እንግዲህ ምን
ማድረግ ይቻላል? አያችሁ! ዓለሙ ሁሉ
ግልብጦ ብሎ ተከትሎታል" ተባባሉ።

## ኢየሱስ ስለ ሞቱ አስቀድሞ ተናገረ

20ለአምልኮ ወደ በዓሉ ከወጡት መካከል
የግሪክ ሰዎችም ነበሩ። 21እነርሱም በገሊላ
ከምትገኘው ከቤተ ሳይዳ ወደ ሆነው ሰው፣
ወደ ፊልጶስ መጥተው፣ "ጌታው፤ እባክህን፣
ኢየሱስን ለማየት እንፈልጋለን" አሉት።
22ፊልጶስም ለእንድርያስ ሊነግረው ሄደ፤
እንድርያስና ፊልጶስም ለኢየሱስ ነገሩት።
23ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"የሰው ልጅ የሚከብርበት ሰዓቱ ደርሶአል፤
24እውነት እላችኋለሁ፤ የስንዴ ቅንጣት መሬት

12፥3 ማር14፥3፤ ዮሐ11፥2
12፥4 ማቴ10፥4
12፥6 ዮሐ13፥29
12፥7 ዮሐ19፥40
12፥8 ዘዳ15፥11
12፥9ዮሐ11፥43፡44
12፥11 ቍ17፡18፤ ዮሐ11፥45፤7፥31
12፥13 ዘሌ23፥40፤ መዝ118፥25፡26፤ ዮሐ1፥49
12፥15 ዘካ9፥9
12፥16 ቍ23፤ ማር9፥32፤ዮሐ2፥22፤ 7፥39
12፥17 ዮሐ11፥42
12፥18 ቍ11፤ ሉቃ19፥37
12፥19 ዮሐ11፥ 47፡48
12፥20 ዮሐ7፥35፤ ሐሥ11፥20
12፥21ማቴ11፥21
12፥23ማቴ26፥18፤ ዮሐ13፥32፤17፥1
12፥24 1ቆሮ15፥36

[a]3 በግሪኩ ሊትራ ይላል
[b]13 በዕብራይስጡ ሆሳዕና ማለት ሲሆን የምስጋና ድምፅ ነው

ግን ከሁሉም ለየት ያለ ነው።

12፥1 *ቢታንያ፤* የማቴ 21፥17 ማብ ይመ።

12፥3 *ናርዶስ፤* የዕፅ ወይም ከዕፁ የሚቀመም ሽቱ ስም ነው። የሽቱው ዋጋ እጅግ ከፍተኛ ስለ ሆነ የማርያም አድራጎት የቱን ያህል ከልቧ እንደ ነበር ያሳያል፤ ሽቱውን በራሱ ላይ ሳይሆን በእግሩ ላይ ማፍሰሷ፣ የክብሯ ምልክት በሆነውም ጠጕሯ እግሩን ማበሷ ያልተለመደ ተግባር ከመሆኑም በላይ ትሕትናዋን ያመለክታል (የ1፥27፤ የ13፥5 ማብ ይመ)።

12፥4 *የአስቆሮቱ ይሁዳ፤* የ6፥71 ማብ ይመ።

12፥6 *ሌባ፤* ይሁዳ አታላይ እንደ ነበር በግልጽ የምና ይበት ክፍል ነው። ገንዘብ ያዥ መሆኑ ግን እንደ ታማኝ ተቈጥሮ እንደ ነበር ያመለክታል።

12፥7 *እንድታቆየው፤* ምናልባት 'ለቀብሬ እንዲሆን ታስ ቀምጠው' ማለቱ ይሆናል። ብዙውን ጊዜ ሽቱ ከደስታ ጋር የተያያዘ ቢሆንም፣ ለቀብርም ያገለግላል (19፥39-40 ይመ)። ማርያም ሳይታወቃት የፈጸመችውን፣ ኢየሱስ ከቀብሩ ጋር አገናኘው።

12፥9 *አይሁድ፤* የ1፥19 ማብ ይመ።

*12፥10፤* የአይሁድ አለቆች ቀደም ሲል 'አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል' አሉ (11፥50)፤ አሁን ደግሞ ሌላ ሰው እንዲገደል ፈለጉ። ይህም የኀጢአትን ዕድገት ያስገነዝባል።

12፥12 *ብዙ ሕዝብ፤* ከየገጠሩ ለፋሲካ በዓል የመጡትን ምእመናን ያመልክታል። ከነዚህም መካከል ብዙዎቹ ኢየሱስን በገሊላ አይተውትና ሰምተውት ስለ ነበር መሲሕነቱን በገሃድ ለመናገር ዕድሉን ተጠቅመውበታል።

12፥13 *የዘንባባ ዝንጣፊ፤* የድል በዓል ሲከበር ይያዝ ነበር። ዮሐንስ በራእዩ ብዙዎች በሰማይ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው አይቶአል (ራእ 7፥9)። *ሆሣዕና፤* የማቴ 21፥9 ማብ ይመ። *ስም፤* የ2፥23 ማብ ይመ። *የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው!* ይህ፣ ዳዊት በመዝ 118፥26 የተናገረው ሳይሆን፣ ሕዝቡ ያስማው ተጨማሪ ቃል ነው፤ ተጽፎ የሚገኘውም በዚሁ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው። ዮሐንስ የኢየሱስን ንጉሥነት አጕልቶ ያሳያል፤ ሕማ ማቱንም ሲተርክ በብዙ ቦታ ይጠቅሳል።

12፥14 *ውርንጫላ፤* የዘካ 9፥9፤ የማቴ 21፥2፡7፤ የማር 11፥2፤ የሉቃ 19፥30 ማብ ይመ።

*12፥16፤* ይህ የ16፥13 ትርጒም አንዱ ምሳሌ ነው። *ከበረ፤* የቍ41፤ የ11፥4፤ የ13፥31 ማብ ይመ። ሐዋርያት የትንቢቱን ትርጒምና ፍጻሜውን ለማስተዋል የበቁት ጌታ ከተሰቀለ፣ መንፈስ ቅዱስም ከወረደ በኋላ ነው።

12፥19 *ፈሪሳውያን፤* የማቴ 3፥7፤ የማር 2፥16፤ የሉቃ 5፥17 ማብ ይመ።

12፥20 *የግሪክ ሰዎች፤* ምናልባት ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረባቸው ሆነው፣ በአንድ አምላክ ብቻ በማመንንና በግብረገብ ትምህርቱ ምክንያት የአይሁድ ሃይማኖት የማረካቸው፣ በሌላ በኩል ግን የአይሁድ ብሔራዊ ስሜትና እንደ ግዝረት ያለው የሃይማኖት ሥርዐት ያራቃቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በየምኩ ራቡ እየተገኙ ያምልኩ እንጂ የአይሁድን እምነት ሙሉ በሙሉ አልተቀበሉም ነበር።

12፥21 *ፊልጶስ፤* ግሪኮቹ ወደ ፊልጶስ የመጡት ስሙ የግሪክ በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም። *ለማየት፤* ለመጠየቅ፣ ለማነጋገር ማለት ነው። ከቍጥር 22 በኋላ ዮሐንስ ስለ እነዚህ ግሪኮች አልጻፈም (ቢሆንም የቍ 32 ማብ ይመ)። ዮሐንስ እዚህ ላይ ቁም ነገር አድርጎ የቈጠረው ከኢየሱስ ጋር ያደረጉትን ንግግር ሳይሆን፣ ወደ ኢየሱስ መምጣታቸውን ነው። ኢየሱስ ለዓ ለም ሁሉ ቤዛ ለመሆን መጥቶአል፤ የእነዚህም አሕዛብ እርሱ ወደሚገኝበት ስፍራ መምጣት፣ በመቃረብ ላይ ያለው የመስቀል ሞቱ ምን ያህል ታላቅና አስፈላጊ እንደ ሆነ ያሳያል።

12፥23 *የሚከብርበት፤* ኢየሱስ በፍጹም መታዘዝ ሕይወ ቱን በመስቀል ላይ በመስጠት፣ በትንሣኤውና በዕርገቱ ከፍ ከፍ የሚልበት ጊዜ ነው (የቍ 41፤ የ11፥4፤ የ13፥31 ማብ ይመ)።

ላይ ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤
ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች። 25ሕይ
ወቱን የሚወድ ያጣታል፤ በዚህ ዓለም ሕይወቱን
የሚጠላ ግን ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል።
26የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፤ እኔም ባለ
ሁብት አገልጋዬም በዚያ ይሆናል፤ የሚያገ
ለግለኝንም አባቴ ያከብረዋል።
27"አሁንስ ነፍሴ ተጨነቀች፤ ምን ልበል?
አባት ሆይ፤ ከዚች ሰዓት ታድነኝ? የለም፤
ይሁን የመጣሁት ለዚህች ሰዓት ነውና።
28አባት ሆይ፤ ስምህን አክብረው።"
ከዚያም፣ "አክብሬዋለሁ፤ ደግሞም አከብ
ረዋለሁ" የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ።
29በዚያ የነበሩት፣ ድምፁን የሰሙት አያሌ
ሰዎች፣ "ነጐድጓድ ነው" አሉ፤ ሌሎች ደግሞ፣
"መልአክ ተናገረው" አሉ።
30ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "ይህ ድምፅ የመ
ጣው ስለ እኔ ሳይሆን ስለ እናንተ ነው፤
31ይህ ዓለም የሚፈረድበት ጊዜ አሁን ነው፤
የዚህም ዓለም ገዥ አሁን ወደ ውጭ ይጣ
ላል። 32እኔ ግን ከምድር ከፍ ከፍ ባልሁ ጊዜ
ሰውን ሁሉ ወደ ራሴ እስባለሁ።" 33ይህን
የተናገረው በምን ዐይነት ሞት እንደሚሞት
ለማመልከት ነበር።
34ሕዝቡም፣ "እኛስ ክርስቶስ[*] ለዘላለም
እንደሚኖር ከሕግ ሰምተናል፤ ታዲያ፣ 'የሰው
ልጅ ከፍ ከፍ ማለት አለበት' እንዴት ትላ
ለህ? ይህስ 'የሰው ልጅ' ማን ነው?" አሉት።

12፥25 ማቴ10፥39፤ 25፥46፤ማር8፥35፤ ሉቃ14፥26፤ 17፥33
12፥26 ዮሐ14፥3፤ 17፥24፤2ቆሮ5፥8፤ ፊል1፥23፤1ተሰ4፥17
12፥27 ቊ23፤ማቴ 11፥25፤26፥38፡39፤ ዮሐ11፥33፡38፤13፥21
12፥28 ማቴ3፥17
12፥30 ዘፀ19፥9፤ ዮሐ11፥42
12፥31 ዮሐ14፥30፤ 16፥11፤2ቆሮ4፥4፤ ኤፌ2፥2፤1ዮሐ4፥4፤ 5፥19
12፥32 ቊ34፤ ኢሳ1፥10፤ዮሐ3፥14፤ 6፥44፤8፥28
12፥33 ዮሐ18፥32፤ 21፥19
12፥34 መዝ110፥4፤ ኢሳ9፥7፤ሕዝ37፥25፤ ዳን7፥14፤ማቴ8፥20፤ ዮሐ3፥14፤10፥34
12፥35 ቊ46፤ ኤፌ5፥8፤1ዮሐ1፥6፤ 2፥11
12፥36 ቊ46፤ ሉቃ16፥8፤ዮሐ8፥59
12፥37 ዮሐ2፥11
12፥38 ኢሳ53፥1፤ ሮሜ10፥16
12፥40 ኢሳ6፥10፤ ማቴ13፥13፡15
12፥41 ኢሳ6፥1-4፤ ሉቃ24፥27

35ኢየሱስም እንዲህ ሲል ተናገራቸው፤
"ከእንግዲህ ለጥቂት ጊዜ ብርሃን አለላችሁ፤
ጨለማ ሳይመጣባችሁ፣ ብርሃን ሳለላችሁ
ተመላለሱ፤ በጨለማ የሚመላለስ ወዴት
እንደሚሄድ አያውቅም። 36የብርሃን ልጆች
እንድትሆኑ ብርሃን ሳለላችሁ በዚህ ብርሃን
እመኑ።" ኢየሱስ ይህን ተናግሮ እንደ ጨረሰ
ተለያቸው፤ ተሰወረባቸውም።

### አይሁድ ባለማመን መጽናታቸው

37ኢየሱስ እነዚህን ታምራዊ ምልክቶች ሁሉ
በፊታቸው ቢያደርግም እንኳ፣ አሁንም
አላመኑበትም፤ 38ይኸውም ነቢዩ ኢሳይያስ፣

"ጌታ ሆይ፤ ምስክርነታችንን ማን አመነ?
የጌታ ክንድስ ለማን ተገለጠ?" ያለው ቃል
እንዲፈጸም ነው።

39ስለዚህ ማመን አልቻሉም፤ ይህም ኢሳ
ይያስ በሌላ ቦታ እንዲህ ሲል እንደ ተናገረው
ነው፤

40"ዐይናቸውን አሳውሯል፤
ልባቸውንም አደንድኖአል፤
ስለዚህ በዐይናቸው አያዩም፤
በልባቸውም አያስተውሉም፤
እንዳልፈውሳቸውም አይመለሱም።"

41ኢሳይያስ ይህን ያለው የኢየሱስን ክብር
ስላየ ነው፤ ስለ እርሱም ተናገረ። 42ይህም

[*]34 ወይም መሲሕ

***ሰዓቱ ደርሶአል***፤ ነገሮች ሁሉ እየተገባደዱ ኢየሱስ ለሞት አልፎ ወደሚሰጥበት ሰዓት ደረሰ ማለት ነው (የ2፥4 ማብ ይመ)።

12፥24 ***ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች፤*** በመሞት ሕይወትን ማግኘት፣ በዕፅዋት ዓለም እውን ሆኖ ይታያል። አንድ ተክል እንዲገኝ ከተፈለገ ዘሩ በዘርነቱ መሞት አለበት።

12፥25 ***ሕይወቱን የሚጠላ...ይጠብቃታል***፤ ይህ ጒልቶ የሚታየው በኢየሱስ መስቀል ላይ ነው። ስለ ግል ሕይወት መጨነቅና በዚህ ዓለም በሚገኘው ብልጽግና ላይ ማተኰር ግን ከሁሉ የሚበልጠውን ከማየት ይጋርዳል (ከማቴ 16፥24-25፤ ከማር8፥34-35፤ ከሉቃ 9፥23-24 ጋር ያነጻጽሩ)። ***የዘላለም ሕይወት***፤ የ3፥15 ማብ ይመ።

12፥27 ***ተጨነቀች***፤ ይህ የዮሐንስ አገላለጽ በሌሎቹ ወንጌሎች ከተገለጸው የጌቴሴማኒ ሕማማት ጋር በአቻነት ይታያል። ***ከዚች ሰዓት***፤ ኢየሱስ ስለ ሰው ልጆች ኀጢአት፣ መሥዋዕት ሆኖ (2ኛ ቆሮ 5፥21) የመቅረቡ ሁኔታ እየታሰበው ሳለ፣ ከዚህ ሞት እንዲያድነው አብን ለመለመን ፈልጎ ነበር፤ ይሁን እንጂ የመጣው ለዚሁ መሥዋዕትነት ስለ ሆነ መጸለዩን ተወ።

12፥28 ***አባት ሆይ፤ ስምህን አክብረው***፤ ይህን የጸለየው ከሞት ለመዳን ፈልጎ ሳይሆን፣ አብ እንዲከበር ነበር። ከሰማይ የተሰማውም ድምፅ ይህንኑ አረጋግጦአል። ***ስም***፤ የ2፥23 ማብ ይመ።

12፥31 ***ይህ ዓለም (የሚፈረድበት)***፤ 'መስቀል' እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ላይ የወሰነውን ፍርድ ያመለክታል። የዚህ ዓለም ገዥ፤ ሰይጣንን ለማለት ነው (ከ16፥11 ጋር ያነጻጽሩ)። ለሰይጣን፣ መስቀል ድል የሚያደርግበት መንገድ ይምሰለው እንጂ፣ እንደ እውነቱ ከሆነ መሸነፊያው ነበር፤ ይህ ነው የማይ ባል መልካምነት ከመስቀሉ መንጭቶአልና።

12፥32 ***ከፍ ከፍ***፤ የ3፥14 ማብ ይመ፤ መስቀል ኢየሱስ እጅግ ከፍ ብሎ የከበረበት ምልክት ነው (የቊ 41፤ የ13፥31 ማብ ይመ)። ***ሰውን ሁሉ***፤ ዜግነት፣ መልክ፣ ጾታ፣ ወይም ሀብት ሳይል፣ ኢየሱስ ማንኛውንም ሰው ወደ ራሱ ይጠራል። በዚህ በዓል ላይ ከአሕዛብ ወገን የሆኑት ግሪኮች መገኘታቸውም ይህንኑ ሐሳብ የሚያረጋግጥ ነው (ቊ 20)።

12፥34 ***ከሕግ***፤ እዚህ ላይ ሕግ ሲል በአጠቃላይ ብሉይ ኪዳንን ማለቱ ሊሆን ይችላል (የ10፥34 ማብ ይመ)። ግንኙነቱ ግን በተለይ ከመዝ 89፥36፤ 110፥4፤ ከኢሳ 9፥7፤ ከዳን 7፥14 ጋር ነው። ***ክርስቶስ***፤ የ1፥25 ማብ ይመ። ***የሰው ልጅ***፤ በወንጌሎቹ ውስጥ ኢየሱስ ራሱን በዚህ ስም ከመጥራቱ ሌላ፣ ሌሎች ሰዎች ይህን ስም ሲጠቀሙበት የምናገኘው እዚህ ላይ ብቻ ነው። እዚህም ላይ ቢሆን የተጠቀሰው የኢየሱስ የራሱ አባባል ነው (የማር 8፥31 ማብ ይመ)።

12፥35-36 ***ብርሃን፤*** "በዚህ ብርሃን እመኑ" የሚለው ጥሪ ኢየሱስ ራሱ ብርሃን መሆኑን ያሳያል (የ1፥4፤ የ8፥12 ማብ ይመ)።

12፥37 ***አሁንም አላመኑበትም***፤ እግዚአብሔር መሲሑን ሲልክ፣ ከጥንት ዘመን አንሥቶ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት እስራኤላውያን በቅን ልቡና መቀበል፣ የሠራቸውንም ታምራት ታላቅነት ማስተዋል ነበረባቸው።

12፥39 ***ማመን አልቻሉም***፤ ሰዎቹ የራሳቸውን ውሳኔ ለማድረግ ዕድል አልነበራቸውም ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ሆን ብለው እግዚአብሔርን እምቢ ብለዋል፤ የክፋትንም መንገድ መርጠዋል ማለት ነው። እግዚአብሔርም ለእምቢተኝነታቸው አጸፋ፣ ዐይን የሚያሳውርና ልቡና የሚያደነድን ፍርድ እንዳመጣባቸው ቊ 40 ላይ እናያለን (ሮሜ1፥28 ይመ)። ቢሆንም ብዙ የአይሁድ አለቆች ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን አምነዋል (ቊ 42)።

12፥40፤ እነዚህ በኢሳይያስ 6፥10 ላይ የሚገኙትን ቃላት ራሱ ኢየሱስ (ማቴ 13፥14-15፤ ማር 4፥12፤ ሉቃ 8፥10)፣ እንዲሁም ጳውሎስ (ሐሥ 28፥26-27) ጠቅሰዋል።

12፥41 ***የኢየሱስን ክብር ስለ አየ***፤ ቀደም ሲል ኢሳይያስ የተናገረው ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው (ኢሳ 6፥3)። ዮሐንስ የተናገረው ደግሞ ስለ ኢየሱስ ክብር ነበር፤ ይኸውም ኢየሱስና እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆኑ፣ መሠረታዊ ልዩነትም እንደ ሌላቸው በመመስከር ነው። እዚህ ላይ ክብር ሲባል ረቀቅ ያለ ሐሳብ አለው፤ ክብር 'ግርማን' ሊያመለክት ይችላል። ዮሐንስም ዐቢይ ቁም ነገር አድርጎ የቈጠራቸው:- የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት፣ ትንሣኤውና ልዕልናው ክብሩን የሚያሳዩ ናቸው። ኢሳ 53፥1 እና 6፥10 እንደሚያመለክቱት፣ ኢሳይያስ ቀድሞውኑ ክርስቶስ ተቀባይነትን እንደማያገኝ ተንብዮአል፤ ይኸውም በአንድ በኩል ስለ ታወረ ዓይንና ስለ ደነደነ ልብ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ስለ ፈውስ ሲናገር፣ በሁለቱም አገላለጽ የተናገረው ስለ መሲሑ ነው። ይህ መስቀሉ ነው፤ ክብሩም ነው። መስቀሉ

ቢሆን፣ ከአለቆች መካከል እንኳ ሳይቀር
ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤ ይሁን እንጂ ፈሪሳ
ውያን ከምኩራብ እንዳያስወጧቸው ስለ ፈሩ
ማመናቸውን አይገልጡም ነበር፤ [43]ይህም
የሆነው በእግዚአብሔር ከመመስገን ይልቅ በሰው
መመስገንን ስለ ወደዱ ነው።
[44]ከዚያም ኢየሱስ ድምፁን ከፍ አድርጎ
እንዲህ አለ፤ "ማንም በእኔ ቢያምን በእኔ ብቻ
ሳይሆን በላከኝም ማመኑ ነው፤ [45]እኔንም
የሚያይ የላከኝን ያያል። [46]በእኔ የሚያምን
በጨለማ እንዳይኖር ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም
መጥቻለሁ።
[47]"ቃሌን ሰምቶ በማይፈጽመው ላይ የም
ፈርደው እኔ አይደለሁም፤ ዓለምን ላድን
እንጂ በዓለም ላይ ልፈርድ አልመጣሁምና።
[48]በማይቀበለኝና ቃሌን በሚያቃልል ላይ
የሚፈርድበት አለ፤ የተናገርሁት ቃል ራሱ
በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል፤ ምክንያቱም
[49]እኔ ከራሴ አልተናገርሁም፤ ነገር ግን
የላከኝ አብ ምን እንደምናገርና እንዴት
እንደምናገር አዘዘኝ። [50]የእርሱ ትእዛዝ ወደ
ዘላለም ሕይወት እንደሚያደርስ ዐውቃለሁ፤
ስለዚህም የምለው ሁሉ አብ እንድናገረው
የነገረኝን ብቻ ነው።

## ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠቡ

13 ጊዜው ልክ ከፋሲካ በዓል በፊት
ነበረ፤ ኢየሱስም ይህን ዓለም ትቶ ወደ
አብ የሚሄድበት ጊዜ እንደ ደረሰ ዐወቀ።
በዓለም የነበሩትን፣ የራሱ የሆኑትን ወደዳ
ቸው፤ በፍጹም ፍቅሩም ወደዳቸው።[a]
[2]እራትም ቀርቦ ሳለ፣ ኢየሱስን አሳልፎ
እን ዲሰጥ ዲያብሎስ የስምዖንን ልጅ የአስቆሮቱን ይሁዳ ልብ አነሣሥቶ ነበር። [3]ኢየ
ሱስም፣ አብ ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር
እንዳደረገለት፣ ከእግዚአብሔር እንደ ተላከና
ወደ እግዚአብሔርም እንደሚመለስ ዐውቆ፣
[4]ከእራት ተነሣ፤ መጐናጸፊያውን አስቀመጠ፤
ወገቡንም በፎጣ ታጠቀ። [5]ከዚያም በመታጠቢ
ያው ውሃ ጨምሮ የደቀ መዛሙርቱን
እግር እያጠበ በታጠቀው ፎጣ ያብስ ጀመር።
[6]ወደ ስምዖን ጴጥሮስም መጣ፤ ጴጥሮስም፣
"ጌታ ሆይ፤ አንተ እግሬን ታጥባለህ?" አለው።
[7]ኢየሱስም መልሶ፣ "የማደርገውን አሁን
አታውቅም፤ በኋላ ግን ታስተውላለህ" አለው።
[8]ጴጥሮስም፣ "የለም፤ እግሬን ከቶ አታጥ
ብም" አለው።
ኢየሱስም፣ "ካላጠብሁህማ ከእኔ ጋር ዕድል
ፈንታ የለህም" አለው።
[9]ስምዖን ጴጥሮስም፣ "ጌታ ሆይ፤ እንግዲ
ያውስ እግሬን ብቻ ሳይሆን እጄንም ራሴ
ንም እጠበኝ" አለው።
[10]ኢየሱስም፣ "ገላውን የታጠበ ሰው የሚያ
ስፈልገው እግሩን ብቻ መታጠብ ነው፤ የቀረው

[a]1 ወይም እስከ መጨረሻው

12+42 ቊ11፤ ዮሐ7+13፡48፤9+22
12+43 1ሳሙ15+30፤ ሮሜ2+29
12+44 ማቴ10+40፤ ዮሐ5+24
12+45 ዮሐ14+9
12+46 ዮሐ1+4
12+47 ዮሐ3+17
12+48 ዮሐ5+45
12+49 ዮሐ14+31
12+50 ማቴ25+46፤ ዮሐ14+24
13+1 ማቴ26+18፤ ዮሐ11+55፤16+28
13+2 ማቴ10+4
13+3 ማቴ28+18፤ ዮሐ8+42፤16+27፡28፡30፤17+8
13+4 ማቴ20+28
13+5 ሉቃ7+44
13+7 ቊ12
13+10 ቊ18፤ ዮሐ15+3

ከትንሣኤውና ከልዕልናው ጋር ሲታይ፣ ሥቃይንና ፈውስን፣ መናቅንና ድል ማድረግን፣ ውርደትንና ክብርን ያመለክታል።

12+42 *ከአለቆች...ብዙዎች...አመኑ፤* ዮሐንስ፤ ስለዚህ ጉዳይ ብርሃን የሌለው ጭጋጋማ ሥዕል አያቀርብም፤ የአይሁድ አለቆች ውግዘት እንዳይደርስባቸው በመፍራት እምነታቸውን በድብቅ ይያዙት እንጂ (የ9+22 ማብ ይመ)፣ ብዙዎቹ በጌታ አምነዋል (የ1+7 ማብ ይመ)።

12+44 *ድምፁን ከፍ አድርጎ፤* ቃሉ ከፍ ባለ ድምፅ ከመነገሩ የተነሣ አጽንዖት አግኝቶአል። *በእኔ ቢያምን፤* ዮሐንስ የኢየሱስን ይፋ አገልግሎት ትረካ የሚደመድመው ሰዎች እምነት እንዲኖራቸው በማሳሰብ ነው። ኢየሱስ ይህን ቃል መቼ እንደ ተናገረ ዮሐንስ አይገልጽም፤ *በላከኝ፤* የኢየሱስ ተልእኮ፣ እንዲሁም የአብና የወልድ አንድነት፣ ተጀምሮ እስከሚጨረስ ድረስ በዚህ ወንጌል ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶታል።

12+46 *ብርሃን፤* የ1+4፤ 8+12 ማብ ይመ። *ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤* የኢየሱስን ቅድመ ዓለም ህልውናና እንዲሁም ተልእኮውን ያመለክታል።

12+47 *ልፈርድ፤* ኢየሱስ የመጣው በዓለም ላይ ለመፍረድ አይደለም፤ ይሁን እንጂ ፍርድ የድነት ሌላው ገጽታ ነው። ፀሓይ የምትወጣው ብርሃን ለመስጠት ነው፤ ብርሃን ስትሰጥ ግን ጥላ መኖሩ አይቀርም።

12+49 *አብ ምን እንደምናገር...አዘዘኝ፤* ኢየሱስ የሚናገረውን የሰሙ ሰዎች ከፍተኛ ኀላፊነት አለባቸው፤ 'ቃሉ' (ቊ48) አብ የሰጠው ትእዛዝ ነውና። እንግዲህ ይህን ቃል አል ቀበልም ማለት እግዚአብሔርን አልቀበልም ማለት ይሆናል።

12+50 *የዘላለም ሕይወት፤* የ3+15 ማብ ይመ። *ስለዚህም፤* ኢየሱስ የተናገረው ሁሉ የአብን ፈቃድ በመፈጸም ነው፤ ይህም የኢየሱስ ይፋ አገልግሎት የተደመደመበት ድንቅ አገላለጽ ነው።

*13+1-17+26፤* ዮሐንስ የፋሲካ እራት ስለ ተዘጋጀበት ስለ ላይኛው ክፍል (ደርብ) ከሌሎቹ ወንጌላውያን ይልቅ ሰፋ ያለ ገለጻ ሰጥቶ ሳለ፣ ስለ ጌታ እራት ሥርዐት ሳያነሣ ማለፉ ግን የሚያስደንቅ ነው። ይሁን እንጂ ጌታ በዚያች ሌሊት ለሐዋርያቱ ምን እንዳላቸው ብዙውን ሐሳብ የምናገኘው ከዮሐንስ ወንጌል ነው። በዚያች ሌሊት ካስተማራቸው ትምህርት አንዱ ያተኰረው ፍቅርን በተመለከተ ነበር። 'ፍቅር' ወይም 'መውደድ' የሚለው ቃል ከም 1-12 ባለው ክፍል 6 ጊዜ ብቻ ሲጠቀስ፣ ከም 13-17 ግን ብዙ ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል።

13+1 *የፋሲካ በዓል፤* የ2+13፤ የ5+1 ማብ ይመ። *ጊዜ፤* የ2+4 ማብ ይመ።

13+2 *እራት፤* አንዳንዶች ይህ ከፋሲካ በዓል በፊት በማኅበር የሚበላ ግብዣ ነው ብለው ያምናሉ። በሌሎቹ ሦስት ወንጌሎች ላይ በግልጽ እንደተጻፈው ግን የጌታ እራትና የፋሲካ እራት አንድ ላይሆኑ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ ይህ እራት ራሱ የፋሲካ እራት ሊሆን ይችላል፤ ይህም ከሆነ፣ የሦስቱ ወንጌሎችና የዮሐንስ ትረካ ተመሳሳይነት ይኖራቸዋል። *ዲያብሎስ፤* ቊ 27 ይመ። *የአስቆሮቱ ይሁዳ፤* የ6+71 ማብ ይመ።

13+3 *አብ ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር እንዳደረገለት፤* ዮሐንስ እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ዕቅድ እንደ ተፈጸመና ኢየሱስም ሁኔታውን እንደተቈጣጠረ እንደገና በአጽንዖት ያሳያል።

13+5 *የደቀ መዛሙርቱን እግር እያጠበ፤* እግር ማጠብ አንድ የቤት አገልጋይ የሚያከናውነው ዝቅተኛ ሥራ ነው (የ1+27 ማብ ይመ)። በዚህ ወቅት አገልጋይ አልነበረም፤ አገልጋይ ልሁን ያለም የለም። ኢየሱስ ይህን ያደረገው፣ ወዲያው እንደ ደረሱ ሳይሆን፣ በእራት ላይ እያሉ ነበር። እግር ማጠቡ አንድ ትምህርት ለማስተላለፍ ሆን ተብሎ የተደረገ ነው፤ ይኸውም ትሕትናን ለማስተማር ነበር። እንዲሁም በመስቀል ላይ እውን ለመሆን የተቃረበውን ከእኔነት የተላቀቀውን የአገልግሎት መርሕ ቁልጭ አድርጎ አሳይቶአል። ይህን ሁኔታ የሚገልጸው ዮሐንስ ብቻ ነው፤ ይሁን እንጂ በደቀ መዛሙርቱ መካከል ማን ታላቅ እንደሚሆን በመካከላቸው ተነሥቶ ለነበረው ክርክር ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በመገሠጽ፣ 'እኔ በመካከላችሁ አሁን የምገኘው እንደ አገልጋይ ሆኜ ነው' ብሎአል (ሉቃ 22+27)። የኢየሱስ የአገልግሎት ሕይወት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው በመስቀል ላይ ነው።

13+8 *የለም፤* እግር መታጠቡን በግልጽ የተቃወመ ማንም ባይኖርም፣ ጴጥሮስ ከግል ጠባዩ የተነሣ ሲከላከል እናያለን። ኢየሱስ ይህን ዝቅተኛ ሥራ እንዳይሠራ ጴጥሮስ መቃወሙ ትሕትናውን ሲያሳይ፣ መመሪያ ለመስጠት መሞከሩ፣ ግን ዐውቃለሁ ባይነቱን ያመለክታል። *ካላጠብሁህማ፤* የኢየሱስ መልስ ከእግር ማጠቡ ድርጊት በላይ መሆኑን ያመለክታል፤ ይኸውም ጴጥሮስ በመንፈስ መንጻት አለበት ማለት ነው። አካላዊ ንጽሕና ከኀጢአት የመንጻት ምሳሌ ነው፤ መተላለፍ ሲኖር፣ መንጻት ለክርስቲያኖች አስፈላጊ ነውና (የ 1ዮሐ 1+9 ማብ ይመ)።

13+9 *እጄንም ራሴንም፤* የጴጥሮስ መልስ ከልብ ነበር፤

አካሉ ግን ንጹሕ ነው:: ሁላችሁም ባትሆኑ፣
እናንተ ንጹሓን ናችሁ” አለው:: 11“ሁላችሁም
ንጹሓን አይደላችሁም” ያለው አሳልፎ የሚ
ሰጠው ማን እንደ ሆነ ያውቅ ስለ ነበር ነው::
12እግራቸውን አጥቦ ካበቃ በኋላም፣ ልብ
ሱን ለብሶ ተመልሶ በቦታው ተቀመጠ፤ እን
ዲህም አላቸው፤ “ያደረግሁላችሁን ታስተውላላ
ችሁን? 13እናንተ፣ ‘መምህርና ጌታ’ ትሉኛላችሁ፤
ትክክል ነው፤ እንደምትሉኝ እንዲሁ ነኝና::
14እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ሆኜ
ሳለሁ እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናንተም እንደዚሁ
እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ
ይገባችኋል። 15እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናን
ተም እንደዚሁ እንድታደርጉ ምሳሌ ትቼላች
ኋለሁ:: 16እውነት እላችኋለሁ፤ አገልጋይ ከጌ
ታው፣ መልእክተኛም ከላከው አይበልጥም::
17እንግዲህ እነዚህን ነገሮች ዐውቃችሁ ብትፈ
ጽሙ ትባረካላችሁ::

## አልፎ እንደሚሰጥ ኢየሱስ መናገሩ

18“ስለ ሁላችሁ መናገሬ አይደለም፤ የመ
ረጥኋቸውን ዐውቃለሁ፤ ነገር ግን፣ ‘እንጀ
ራዬን አብሮኝ የቈረሰ ተረከዙን አነሣብኝ’
የሚለው የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም ነው::
19“ሲፈጸም እኔ እንደ ሆንሁ ታምኑ ዘንድ፣
ይህ ከመሆኑ በፊት አሁን ነገርኋችሁ::
20እውነት እላችኋለሁ፤ እኔ የላክሁትን የሚ
ቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔን የተቀበለም
የላከኝን ይቀበላል::”

13፥11 ማቴ10፥4
13፥13ማቴ26፥18፤ 28፥18፤ሉቃ1፥43፤ 2፥11፤ዮሐ11፥28፤ 6፥46፤11፥1፤ሐሥ 10፥36፤ሮሜ10፥9፡ 12፤14፥9፤1ቆሮ12፥3 ፤ፊል2፥11፤ቈላ 2፥6
13፥14 1ጴጥ5፥5
13፥15ማቴ11፥29፤ 1ጢሞ4፥12
13፥16ማቴ10፥24፤ ሉቃ6፥40፤ ዮሐ 15፥20
13፥17 ማቴ7፥24፡ 25፤ሉቃ11፥28፤ ያዕ1፥25
13፥18 ቍ10፤ መዝ41፥9፤ ማቴ1፥22፤26፥23፤ ዮሐ6፥70፤15፥16፡19
13፥19 ዮሐ4፥26፤ 8፥24፤14፥29፤16፥4
13፥20ማቴ10፥40
13፥21ማቴ26፥21፤ ዮሐ12፥27
13፥23ዮሐ19፥26፤ 20፥2፤21፥7፡20
13፥25ማቴ26፥22፤ ዮሐ21፥20
13፥26 ማቴ10፥4
13፥27 ሉቃ22፥3
13፥29 ቍ1፤ዮሐ 12፥5፡6
13፥30 ሉቃ22፥53

21ይህን ካለ በኋላም ኢየሱስ በመንፈሱ
ታውኮ፣ “እውነት እላችኋለሁ፤ ከእናንተ አንዱ
እኔን አሳልፎ ይሰጣል” ሲል በግልጽ ተናገረ።
22ደቀ መዛሙርቱም ማንን ማለቱ እንደ
ሆነ ግራ ተጋብተው እርስ በርሳቸው ተያዩ::
23ከእነርሱ አንዱ፣ ኢየሱስ ይወደው የነበረ
ደቀ መዝሙር ወደ ኢየሱስ ደረት ተጠ
ግቶ ተቀምጦ ነበር:: 24ስምዖን ጴጥሮስም
ይህን ደቀ መዝሙር በምልክት ጠቅሶ “ማንን
ማለቱ እንደ ሆነ ጠይቀው” አለው::
25እርሱም ወደ ኢየሱስ ደረት ደገፍ ብሎ፣
“ጌታ ሆይ፤ ማን ይሆን?” ብሎ ጠየቀው::
26ኢየሱስም፣ “ይህን ቍራሽ እንጀራ ከወጭቱ
አጥቅሼ የምሰጠው እርሱ ነው” አለው፤ ከዚ
ያም ቍራሹን እንጀራ አጥቅሶ ለስምዖን
ልጅ ለአስቆሮቱ ይሁዳ ሰጠው:: 27ይሁዳም
ቍራሹን እንጀራ እንደ ተቀበለ ወዲያው
ሰይጣን ገባበት::
ኢየሱስም፣ “የምታደርገውን ቶሎ አድርግ”
አለው፤ 28ይሁን እንጂ ኢየሱስ ለምን እንዲህ
እንዳለው ማንም አላወቀም ነበር:: 29ይሁዳ
ገንዘብ ያዥ ስለ ነበረ፣ አንዳንዶቹ ለበዓሉ
የሚያስፈልግ ነገር እንዲገዛ ወይም ለድኾች
እንዲሰጥ ኢየሱስ የተናገረው መሰላቸው::
30ይሁዳም ያን ቍራሽ እንጀራ እንደ ተቀበለ
ወጥቶ ሄደ፤ ሌሊትም ነበረ::

ግን አሁንም ለኢየሱስ ትእዛዝ በመስጠት ላይ ይገኛል::

13፥10 *እግሩን ብቻ መታጠብ*፡ በዚያን ጊዜ አንድ ሰው ወደ ግብዣ ከመሄዱ በፊት ገላውን የመታጠብ ልማድ ነበር፤ ሰውዬው ግብዣው ስፍራ እንደ ደረሰም መታጠብ የሚያስፈልገው በመንገድ ላይ የጐደፈውን እግሩን ብቻ ነው::

13፥11 *ያውቅ ስለ ነበር*፡ ኢየሱስ ሁኔታው ሁሉ ከሥልጣኑ ሥር እንደ ነበር፣ ዮሐንስ እንደ ገና በአጽንዖት ያሳያል::

13፥13 *መምህር፣ ጌታም*፡ የሚያስተምር ሰው በተለምዶ ‘መምህር’ ይባላል፤ ‘ጌታ’ የሚለው መጠሪያ የሚሰጠው እጅግ ከፍተኛ ሥልጣን ለያዘ ሰው ነው:: ኢየሱስ ሁለቱንም መጠሪያ ተቀብሎአል::

*13፥14-15፤* አንዳንድ ክርስቲያኖች የእግር መተጣጠብ ሥርዐት ዘወትር ይከናወን ዘንድ ክርስቶስ ደንግጎአል ይላሉ፤ ብዙዎች ክርስቲያኖች ግን እዚህ ላይ የታየው የክርስቶስ አድራጎት የትሕትና አገልግሎት ምሳሌ ነው ይላሉ::

13፥14 *እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ* ክርስቲያኖች እጅግ ዝቅተኛ የሆነውን አገልግሎት እርስ በርስ ያበረክቱ ዘንድ ፈቃደኛ መሆን ይገባቸዋል::

*13፥16፤* ኢየሱስ ብዙ ጊዜ የተናገረው ይህ አባባል፣ በመጠነኛ የአገላለጽ ልዩነት በ15፥20፤ በማቴ 10፥24፤ በሉቃ 6፥40 ላይ ተጽፎ ይገኛል (ከሉቃ 22፥27 ጋር ያነጻጽሩ)::

13፥18 *ስለ ሁላችሁ መናገሬ አይደለም*፡ እዚህ ላይ ኢየሱስ አልፎ ስለ መስጠቱ አስቀድሞ የሚናገረውን ያመለክታል (ቍ21):: *እንጀራዬን አብሮኝ የቈረሰ*፡ እንጀራን በአንድነት መቍረስ የጠበቀ ኅብረት ምልክት ነው (መዝ 41፥9 ይመ):: *ተረከዙን አነሣብኝ፤* በቅሎ ለመራገጥ እግሩን ከሚያነሣው ሁኔታ ወይም አንድ ሰው አቧራን ከእግሩ ለማራገፍ ከሚያደርገው ድርጊት የመጣ አባባል ሊሆን ይችላል (ሉቃ 9፥5 እና 10፥11)::

13፥19 *እኔ እንደ ሆንሁ፤* በ8፥58 ላይ እንደ ተመለከተው በአጽንዖት መልክ የተነገረ አገላለጽ ነው (የ8፥58 ማብ ይመ):: *ታምኑ ዘንድ*፡ 20፥31 ይመ:: ኢየሱስ አስቀድሞ ይህን የተናገረው፣ ለራሱ ብሎ ሳይሆን ለደቀ መዛሙርቱ ሲል ነው::

13፥20 *እኔ የላኩትን...እኔን...የላከኝን*፡ በዚህ ወንጌል ውስጥ ከፍተኛውን ስፍራ የያዘው የኢየሱስ ተልእኮ ሲሆን፣ እዚህ ላይ ደግሞ የደቀ መዛሙርቱ ተልእኮ ከእርሱ ተልእኮ ጋር ተያይዞ እናያለን (ከ20፥21 ጋር ያነጻጽሩ)::

13፥21 *ታውኮ፤* 11፥33 ይመ:: እንደሚከደው ቀደም ሲል ቢያውቅም፣ ወዳጁ የነበረው ሰው ድርጊት ኢየሱስን አሳዝኖታል።

13፥22 *ግራ ተጋብተው፤* የደቀ መዛሙርቱ መደናገጥ ይሁዳ ከሊቀ ካህናቱ ጋር ቀደም ሲል ያደረገውን ስምምነት እንዳላወቁ ያሳያል። ይሁዳ ይህን ያደርጋል ብሎ የጠረጠረ ማንም አልነበረም (ቍ28)፤ እነርሱም የኢየሱስ አልፎ የመስጠት ጉዳይ ያለ ውዴታ የሚከሰት ነው ብለው ሳያስቡ አልቀረም (ማር 14፥19 ይመ)::

13፥23 *ኢየሱስ ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር*፡ ይህ ሰው ብዙውን ጊዜ፣ የዚህ ወንጌል ጸሓፊ የሆነው ሐዋርያው ዮሐንስ ነው ተብሎ ይገመታል (19፥26፤ 20፥2፤ 21፥7፡20 ይመ):: የቃሉ አገላለጽ ኢየሱስ ሌሎቹን ደቀ መዛሙርት አይወዳቸውም ነበር ማለት ሳይሆን፣ ለዚህ ሐዋርያ ግን የተለየ ፍቅር እንደ ነበረው ያመለክታል:: *ተቀምጦ*፡ በአይሁድ ልማድ ሰዎች ወደ ማዕድ ሲቀርቡ፣ በግራ ጐናቸው ጋደም ብለው ክንዳቸውን እመከዳ ላይ ደገፍ በማድረግ ራሳቸውን ወደ ገበታ ያዘነብላሉ::

13፥26 *...እንጀራ ከወጭቱ አጥቅሼ የምሰጠው*፡ ይሁዳ የተቀመጠው ኢየሱስ አጠገብ እንደ ነበር አያጠራጥርም፤ ምናልባትም የተቀመጠበት ቦታ የክብር ስፍራ ሊሆን ይችላል:: ዮሐንስ ስለዚች ወሳኝ ወቅት ሲጽፍ የይሁዳን ስም የጠቀሰው ከነአባቱ ነው (የ6፥71 ማብ ይመ)::

13፥27 *ቍራሹን እንጀራ እንደ ተቀበለ*፡ በዚያችው ወሳኝ ወቅት ጌታ ቍራሹን አጥቅሶ ለይሁዳ የሰጠው ለአክብሮት ከሆነ፣ ይሁዳ ይህን የመጨረሻውን የንስሓ ዕድል አልተጠቀመበትም ማለት ነው:: *ሰይጣን*፡ ይህ ስም በዮሐንስ ወንጌል ተጽፎ የሚገኘው እዚህ ላይ ብቻ ነው (ከቍ 2 ጋር ያነጻጽሩ):: *ቶሎ አድርግ*፡ ኢየሱስ አሁንም ሁኔታውን ከሥልጣኑ ሥር እንደ ሆነ ቃሉ ያሳያል:: ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጠው በተቃዋሚዎቹ ውሳኔ ሳይሆን፣ በራሱ ፈቃድ ነው::

13፥29 *በዓሉ፤* ቍ 1 እና የቍ 2 ማብ ይመ:: *ድኾች*፤ 12፥5 ይመ::

13፥30 *ሌሊት*፡ ዮሐንስ፣ በብርሃንና በጨለማ መካከል ያለውን ቅራኔ አጠንክሮ ከማሳየቱ አንጻር ስንመለከተው፣ ‘ሌሊት’

### ጴጥሮስ እንደሚክደው ኢየሱስ መናገሩ

13፥37-38 ተጓ ምብ – ማቴ 26፥33-35፤ ማር 14፥29-31፤
ሉቃ 22፥33-34

31ይሁዳ ከወጣ በኋላ፣ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤
“አሁን የሰው ልጅ ከበረ፤ በእርሱም እግዚ
አብሔር ከበረ:: 32እንግዲህ እግዚአብሔር በእርሱ
ከከበረ[ሀ]፣ እግዚአብሔር ልጁን በራሱ ዘንድ ያከ
ብረዋል፤ ወዲያውም ያከብረዋል::
33“ልጆቼ ሆይ፤ ከእናንተ ጋር የምቈየው
ለጥቂት ጊዜ ነው፤ እናንተም ትፈልጉኛላችሁ፤
ለአይሁድ፣ ‘እኔ ወደምሄድበት ልትመጡ
አትችሉም’ እንዳልኋቸው፣ አሁንም ለእናንተ
ይህንኑ እላችኋለሁ::
34“አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ ይኸውም
እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ነው፤ እንግዲህ
እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ
በርሳችሁ ተዋደዱ:: 35እርስ በርሳችሁ ብት
ዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት
እንደ ሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ::”
36ስምዖን ጴጥሮስ፣ “ጌታ ሆይ፤ የምትሄ
ደው ወዴት ነው?” አለው::
ኢየሱስም፣ “ወደምሄድበት አሁን ልትከ
ተለኝ አትችልም፤ ኋላ ግን ትከተለኛለህ” ሲል
መለሰለት::
37ጴጥሮስም፣ ጌታ ሆይ፤ አሁን ልከተልህ
የማልችለው ለምንድን ነው? ስለ አንተ ሕይ
ወቴንም ቢሆን አሳልፌ እሰጣለሁ አለው::
38ኢየሱስም፣ እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ሕይ
ወትህን በእርግጥ ለእኔ አሳልፈህ ትሰጣለህን?
እውነት እልሃለሁ፤ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ
ትክደኛለህ::”

### ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አበረታታ

14 “ልባችሁ አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር
እመኑ[ለ]፤ በእኔም ደግሞ እመኑ:: 2በአ
ባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ይህ ባይሆንማ
ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤ የምሄደውም ስፍራ
ላዘጋጅላችሁ ነው:: 3ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላ
ችሁ በኋላ፣ እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ
ጋር እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመ
ጣለሁ:: 4እኔ ወደምሄድበትም ስፍራ የሚያ
ደርሰውን መንገድ ታውቃላችሁ::”

### ወደ አብ የሚያደርሰው መንገድ

5ቶማስም፣ “ጌታ ሆይ፤ ወዴት እንደምትሄድ
አናውቅም፤ ታዲያ፣ መንገዱን እንዴት ማወቅ
እንችላለን?” አለው::
6ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “መንገዱ እኔ
ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ
በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ
የለም:: 7እኔን ብታውቁኝ ኖሮ አባቴንም
ባወቃችሁት ነበር::[መ] ከአሁን ጀምሮ ግን
ታውቁታላችሁ፤ አይታችሁታልም::”
8ፊልጶስም፣ “ጌታ ሆይ፤ አብን አሳየንና
ይበቃናል” አለው::
9ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “አንተ ፊልጶስ!
ይህን ያህል ጊዜ ከእናንተ ጋር ስኖር አታ
ውቀኝምን? እኔን ያየ አብን እየቶአል፤ እን
ዴትስ፣ ‘አብን አሳየን’ ትላለህ? 10እኔ በአብ
እንዳለሁ፣ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን?
የምነግራችሁ ቃል ከራሴ አይደለም፤ ነገር
ግን ሥራውን የሚሠራው በእኔ የሚኖረው
አብ ነው:: 11እኔ በአብ እንዳለሁ አብም
በእኔ እንዳለ ስነግራችሁ እመኑኝ፤ ሌላው
ቢቀር ስለ ድንቅ ሥራዎቹ እንኳ እመኑ::
12እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚያምን እኔ

13፥31 ማቴ8፥20፤ ዮሐ7፥39፤12፥23፤ 14፥13፤17፥4፤ 1ጴጥ4፥11
13፥32 ዮሐ17፥1
13፥33 ዮሐ7፥33: 34
13፥34 ዘሌ19፥18፤ ዮሐ15፥12፤ኤፌ5፥2፤ 1ተሰ4፥9፤1ጴጥ1፥22፤ 1ዮሐ2፥7-11፤ 3፥11፤4፥10:11
13፥35 1ዮሐ3፥14፤ 4፥20
13፥36 ቍ33፤ ዮሐ14፥2፤16፥5፤ 21፥18:19፤ 2ጴጥ1፥14
13፥38 ዮሐ18፥27
14፥1 ቍ27፤ መዝ4፥5፤ዮሐ3፥15
14፥2 ዮሐ13፥33: 36፤16፥5
14፥3 ቍ18:28፤ ማቴ16፥27፤ ዮሐ 12፥26
14፥5 ዮሐ11፥16
14፥6 ዮሐ1፥4:14፤ 6፥35፤10፥9፤ሐሥ 4፥12፤ኤፌ2፥18፤ ዕብ10፥20
14፥7 ዮሐ1፥18፤ 1ዮሐ2፥23
14፥8 ዮሐ1፥43
14፥9 ኢሳ9፥6፤ ዮሐ1፥14፤12፥45፤ 2ቆሮ4፥4፤ፊል2፥6፤ ቈላ1፥15፤ዕብ1፥3
14፥10 ቍ11:20: 24፤ዮሐ10፥38፤ 17፥21
14፥11 ዮሐ5፥36፤ 10፥38
14፥12 ማቴ21፥21፤ ሉቃ10፥17

[ሀ]32 አያሌ የጥንት ቅጆች እግዚአብሔር በእርሱ ከከበረ የሚለው ሐረግ የላቸውም
[ለ]1 ወይም እናንተ በእግዚአብሔር ታምናላችሁ
[መ]7 አንዳንድ የጥንት ቅጆች በእርግጥ እኔን ብታውቁ አባቴንም ታውቃላችሁ ይላሉ

የሚለው ቃል ወቅትን ለማሳየት ብቻ የገባ ሳይሆን፣ በተለይ የይሁዳ ነፍስ ወደ ጨለማ መግባቷን የሚያመለክት ይመስላል::

13፥31 *የሰው ልጅ፤* የማር 8፥31 ማብ ይመ:: *ከበረ፤* ቍ 32 እና የ7፥39 ማብ ይመ:: እዚህ ላይ ‘ከበረ’ የሚለው ሐሳብ የኢየሱስን በመስቀል ላይ መሠዋትና መስቀሉ ያስገኘውን ክቡር የሆነውን ድነት ያመለክታል:: *በእርሱም እግዚአብሔር ከበረ፤* የአብ ክብር ከወልድ ክብር ጋር የተያያዘ ነው::

13፥34 *አዲስ ትእዛዝ፤* በመሠረቱ ጥንትም የነበረ ትእዛዝ ነው (ዘሌ 19፥18)፤ ሆኖም ለደቀ መዛሙርቱ አዲስና ልዩ ትርጒም አለው:: ክርስቶስ ለእነርሱ ካሳየው ታላቅ ፍቅር የተነሣ እርስ በርስ መዋደዳቸው የእርሱ ለመሆናቸው መለዮ ነበርና (ከማቴ 22፥37-39፤ ከማር 12፥30-31፤ ከሉቃ 10፥27 ጋር ያነጻ ጽሩ):: *እኔ እንደ ወደድኋችሁ፤* የመዋደዳችን መለኪያ ክርስቶስ ለእኛ ያሳየው ፍቅር ነው::

13፥35 *ብትዋደዱ፤* ፍቅር የክርስቶስ ተከታዮች መለዮ ነው (ከ1ዮሐ 3፥23፤ 4፥7-8: 11-12: 19-21 ጋር ያነጻጽሩ)::

13፥36 *የምትሄደው ወዴት ነው?* ኢየሱስ ስለ ፍቅር የተናገረውን ቃል ልብ በማለት ፈንታ ጌታው ከእርሱ የመለየቱ ነገር ጴጥሮስን ያስጨነቀው ይመስላል::

13፥37 *ሕይወቴንም...እሰጣለሁ፤* የጴጥሮስ አባባል በ10፥11 ስለ መልካሙ እረኛ የተገለጠው ዓይነት ነው:: ጴጥሮስ በዚህ ጊዜ ሕይወቱን ስለ ኢየሱስ አሳልፎ እንደሚሰጥ ሲገልጽ፣ ትምክህቱ በራሱ ብቻ ይሁን እንጂ ከልቡ ነበር፤ የተፈጸመው ግን እንደ ፎከረው ሳይሆን ተቃራኒው ነው::

13፥38 *ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ፤* በአራቱም ወንጌሎች ጴጥሮስ እንደሚክድ አስቀድሞ ተነግሮአል (ማቴ26፥33-35፤ ማር14፥29-31፤ ሉቃ22፥31-34)::

14፥1 *...አይጨነቅ፤* ሐዋርያት ከጥቂት ጊዜ በፊት የሚያስደነግጥ ነገር ሰምተው ነበር (13፥33:36):: *እመኑ፤* ለታወከ ልብ እምነት መድኀኒቱ ነው::

14፥2 *በአባቴ ቤት፤* መንግሥተ ሰማያት ማለት ነው:: *መኖሪያ፤* ቀጥታ ትርጒሙ ‘መኖሪያ ቦታ’ ማለት ሲሆን፣ ዘለቄታ ያለው መሆኑን ያመለክታል::

14፥3 *ዳግመኛ እመጣለሁ፤* ኢየሱስ በተለያየ መንገድ ሊገለጥ ይችላል፤ እዚህ ላይ ግን ዳግም ምጽአቱን ያመለክታል::

14፥4 *መንገድ፤* ቍ 6 ይመ::

14፥5 *ቶማስ፤* እውነተኛ ሰው ስለ ነበር፣ ነገሩ እንዳል ገባው ለጌታ በግልጽ ተናገረ (የ11፥16 ማብ ይመ)::

14፥6 *እኔ ነኝ፤* የ6፥35 ማብ ይመ:: *መንገድ፤* ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ ማለት ሲሆን፣ ኢየሱስ አሉ ከሚባሉት ከብዙ የሃይማኖት መንገዶች አንዱ ሳይሆን፣ ብቸኛ መንገድ መሆኑን ያሳያል (ከሐሥ4፥12፤ ከዕብ 10፥19-20 ጋር ያነጻጽሩ):: በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ጊዜ የክርስትና እምነት ራሱ፣ ‘መንገድ’ ተብሎ ይጠራ ነበር (ለምሳሌ ሐሥ 9፥2፤ 19፥9: 23):: *እውነት፤* በዚህ ወንጌል ውስጥ ዓይነተኛ የሆነ ቃል ነው (የ1፥4 ማብ ይመ):: *ሕይወት፤* የ1፥4 ማብ ይመ:: የቍ6 ሐሳብ ‘እውነትና ሕይወት በመሆኔ፣ ወደ አብ የሚያደርስ መንገድ እኔ ነኝ’ ማለት ነው::

14፥7 *እኔን...አባቴንም፤* ኢየሱስ በአባቱና በእርሱ መካከል ያለውን ጽኑ ግንኙነት በድጋሚ ያረጋግጣል፤ በዚህም ሐዋርያት የአብን ማንነት በትክክል እንዲረዱ አድርጎአቸዋል (ከ1፥18 ጋር ያነጻጽሩ)::

14፥10 *ከራሴ አይደለም፤* የኢየሱስ ትምህርት ከሰው የተገኘ አልነበረም፤ ቃሉና ሥራውም አይለያዩም::

14፥11 *እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ...*

የማደርገውን ሥራ ይሠራል፤ እንዲያውም እኔ
ወደ አብ ስለምሄድ፣ ከእነዚህም የሚበልጥ
ያደርጋል። 13አብ በወልድ እንዲከብር፣ በስሜ
የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ፤ 14ማንኛ
ውንም ነገር በስሜ ብትለምኑኝ፣ እኔ አደ
ርገዋለሁ።

## ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ተስፋ

15"ብትወዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ።
16እኔ አብን እለምናለሁ፤ እርሱም ከእናንተ
ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣ
ችኋል፤
17እርሱም የእውነት መንፈስ ነው፤ ዓለም
ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው አይ
ችልም። እናንተ ግን፣ አብሮአችሁ ስለሚኖ
ርና በውስጣችሁ ስለሚሆን° ታውቁታላችሁ።
18ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤
ወደ እናንተ እመጣለሁ። 19ከጥቂት ጊዜ
በኋላ፣ ዓለም ከቶ አያየኝም፤ እናንተ ግን
ታዩኛላችሁ። እኔ ሕያው ስለ ሆንሁ እናንተም
ሕያዋን ትሆናላችሁ። 20እኔ በአባቴ እንዳለሁ፣
እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፣ እኔም ደግሞ
በእናንተ እንዳለሁ በዚያ ቀን ትረዳላችሁ።
21የሚወደኝ ትእዛዜን ተቀብሎ የሚጠብቅ
ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል፤ እኔም
እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጥለታለሁ።"
22ከዚያም የአስቆሮቱ ያልሆነው ይሁዳ፣
"ጌታ ሆይ፣ ታዲያ፣ ለዓለም ሳይሆን ራስህን
ለእኛ የምትገልጠው እንዴት ነው?" አለው።
23ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "የሚወደኝ
ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤
ወደ እርሱ እንመጣለን፤ ከእርሱም ጋር እን
ኖራለን። 24የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም።
ይህ የምትሰሙት ቃል የላከኝ የአብ ነው
እንጂ የእኔ አይደለም።
25"አሁን ከእናንተ ጋር እያለሁ ይህን ሁሉ
ነግሬአችኋለሁ፤ 26አብ በስሜ የሚልከው አጽ
ናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስ
ተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባ
ችኋል። 27ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜን
እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደ
ሚሰጣችሁ አይደለም። ልባችሁ አይጨነቅ፤
አይፍራም።

14+13 ማቴ7+7
14+15 ቁ21:23፤ መዝ103+18፤ ዮሐ 15+10፤ 1ዮሐ2+3-5፤3+22:24፤ 5+3፤2ዮሐ 6፤ ራእ12+17፤14:12
14+16 ቁ26፤ ዮሐ 15+26፤16+7
14+17ዮሐ15+26፤ 16+13፤1ቆሮ2+14፤ 1ዮሐ4+6፤5+6
14+18 ቁ3:28፤ 1ነገ6+13፤ ማቴ16+27
14+19 ዮሐ6+57፤ 7+33:34፤16+16
14+20 ቁ10:11፤ ዮሐ10+38፤16+23: 26፤17+21፤ ሮሜ8+10
14+21 ቁ15፤ዘጸ 7+13፤ዮሐ16+27፤ 1ዮሐ2+5
14+22 ሉቃ6+16፤ ሐሥ1+13፤10+41
14+23 ቁ15፤ ሮሜ8+10
14+24 ቁ10፤ዘጸ 18+18፤ዮሐ5+19፤ 7+16፤8+28፤ 12+49:50
14+26 ቁ16፤ ሐሥ2+33፤ዮሐ2+22፤15+26፤16+7:13፤ 1ዮሐ2+20:27
14+27 ቁ1፤ዘኁ6+26፤መዝ85+8፤ሚል2+6፤ ሉቃ2+14፤24+36፤ ዮሐ16+33፤ ፊል4+7፤ቈላ3+15
14+28 ቁ2-4:18፤ማቴ16+27፤ዮሐ5+18፤10+29

°17 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *በውስጣችሁ ስላለ* ይላሉ

*እምነቱ*፤ የሚያድን እምነት በክርስቶስ መታመን ሲሆን፣ ትክክለኛ በሆነ ትምህርት ላይ መመሥረት አለበት፤ እምነትም፣ አብና ወልድ አንድ መሆናቸውን ማመንን ያጠቃልላል።

14+12 *ከእነዚህም የሚበልጥ፤* ታምራዊ ድርጊቶች ማለት ነው (ቁ 11)። ይህ የሚሆነው ኢየሱስ ወደ አብ ከሄደ በኋላ ነው፤ እነዚህ ሥራዎች ሊከናወኑ የሚችሉትም እርሱ ከአብ ዘንድ በሚልከው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል አማካይነት በመሆኑ ነው (15+26፤ ከ14+16-17 ጋር ያነጻጽሩ)።

14+13 *በስሜ፤* የኢየሱስን ስም እንዲሁ በመጥራት ብቻ የሚደረግ ጸሎት ሳይሆን፣ ከባለ ስሙ ማንነት ጋር የሚጣጣም ጸሎት ማለት ነው (የ2+23 ማብ *ይመ*)። ይህም፣ ኢየሱስ የጀመረውን ሥራ እንዲቀጥል የሚያደርግና እርሱ ራሱ መልስ የሚሰጥበት ጸሎት ነው (በተጨማሪ ቁ 14 *ይመ*)።

14+15 *ብትወዱኝ ትእዛዜን*፤ ፍቅርም እንደ እምነት ከመታዘዝ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም (ያዕ 2+14-26)።

14+16 *እርሱም (አብም)...ይሰጣችኋል*፤ የአብ ስጦታ ስለ ሆነው ስለ መንፈስ ቅዱስ ከሚናገሩት ዐበይት ተከታታይ ክፍሎች ይህ የመጀመሪያው ነው (ቁ 26፤ 15+26፤ 16+7-15)። *ሌላ፤* ከኢየሱስ ሌላ ማለት ነው። *አጽናኝ፤* ወይም 'ረዳት' ማለት ነው። ቃሉ የሕግ ቃል ሲሆን፣ የሕግ አማካሪ ከሚለው ሐሳብ ሰፋ ያለ ትርጒም የያዘ ነው (1ዮሐ 2+1)። ሕግን በተመለከተ ችግር ያጋጠመውን ሰው የሚያማክርን ረዳት ያመለክታል፤ መንፈስ ቅዱስም ከክርስቶስ ወገኖች ጋር ምንጊዜም ይቆማል።

14+17 *የእውነት መንፈስ*፤ መንፈስ ቅዱስ በባሕርይና በተግባር ሲታይ መለዮው 'እውነት' ነው፤ ሰዎችንም ወደ እግዚ አብሔር እውነት ይመራል። ወልድ እውነት እንደ ሆነ ሁሉ (14+6)፣ አብም እውነት ነው (4+23-24፤ ከመዝ 31+5፤ ከኢሳ 65+16 ጋር ያነጻጽሩ)፤ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ እውነት ነው። *ዓለም*፤ ለእግዚአብሔር መንፈስ ዋጋ የማይሰጥ ሥርዐት ነው (ከ1ቆሮ 2+14 ጋር ያነጻጽሩ)። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ጋር ነበረ፤ በእነርሱም ውስጥ ይኖራል። አንዳንዶች፣ 'በእነርሱ ውስጥ ይኖራል' የሚለውን ሐሳብ፣ በጰንጠቆስጤ ቀን የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ያመለክታል ብለው ያምናሉ (ሐሥ 2፤ ከሮሜ 8+9 ጋር ያነጻጽሩ)።

14+18 *ወደ እናንተ እመጣለሁ፤* ቃሉ ከመንፈስ ቅዱስ መምጣት ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ ኢየሱስ ራሱን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መግለጹን ያሳያል፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ መገለጡን እንዲሁም ዳግም ምጽአቱን ያመለክታል (ቁ 3:19:28፤ 16+22)።

14+19 *ዓለም...እናንተ ግን*፤ መስቀል ዓለምን ለሁለት ከፍሎታል፤ ይኸውም ከስቅለት ጀምሮ፣ ባለማመኑ ኢየሱስን የማያየው ዓለም በአንድ በኩል ሲመደብ፣ ኢየሱስን በእምነት የሚያዩት ደቀ መዛሙርት ደግሞ በሌላ በኩል ሆነዋል። *እኔ ሕያው ስለ ሆንሁ እናንተም ሕያዋን ትሆናላችሁ፤* የክርስ ቲያን ሕይወት ምንጊዜም በክርስቶስ ሕይወት ላይ የተመሠረተ ነው (ከ1+4፤ ከ3+15 ጋር ያነጻጽሩ)።

14+20 *በዚያን ቀን ትረዳላችሁ፤* ትንሣኤው፣ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ አስተሳሰባቸውን ይለውጣል፤ መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ ሲወርድ፣ ጌታ በግርማ ሞገሱ በአብ ዘንድ እንዳለና እነርሱም በእርሱ ዘንድ እንዳሉ ይረዳሉ።

14+21 *የሚወደኝ...የሚጠብቅ*፤ ለክርስቶስ ያለን ፍቅር እውን የሚሆነው ትእዛዙን ስንጠብቅ ነው (የቁ15 ማብ *ይመ*)። *አባቴ ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤* ወልድ ትእዛዙን የሚጠብቀውን እንደሚወድ ሁሉ፣ አብም የወልድን ትእዛዝ የሚጠብቀውን ይወዳል።

14+22 *ለምንድን ነው?* ይኸኛውም ደቀ መዝሙር ሆነ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት በሕዝብ ዘንድ የመሲሕ ተግባር ነው ተብሎ የሚታወቀውን፣ ኢየሱስ እንዲያከናውን ይጠባበቁ ነበር። በዚህም ምክንያት ለዓለም ሳይሆን ለደቀ መዛሙርቱ ብቻ ራሱን ይገልጣል የሚለውን ሐሳብ መረዳት ቀላል አልነበረም።

14+23 *የሚወደኝ...ይጠብቃል፤...ይወደዋል*፤ በዚህም ቦታ ፍቅርና መታዘዝ የማይነጣጠሉ መሆናቸው ተገልጦአል (ከቁ 15 እና 21 ጋር ያነጻጽሩ)።

14+24፤ አሁንም በዚህ ቦታ በኢየሱስ ቃልና በአብ ቃል መካከል ያለው የጠበቀ ግንኙነት ትኩረት ተሰጥቶበታል (ቁ 10፤ 7+16 *ይመ*)።

14+26 *አጽናኙ፤* የቁ 16 ማብ *ይመ*። *አብ...የሚልከው፤* መንፈስ ቅዱስን አብም ወልድም ይልኩታል (15+26)። *በስሜ፤* የቁ 13፤ 2+23 ማብ *ይመ*። *መንፈስ ቅዱስ*፤ በዚህ ወንጌል ውስጥ፣ በዚህ ቦታና በ1+33 ብቻ የተጠቀሰ ቢሆንም፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተለመደው አጠራሩ ይህ ነው፤ ይህም ስም ያተ ኰረው በኀይሉ ወይም በታላቅነቱ ላይ ሳይሆን፣ በቅዱስነቱ ላይ ብቻ ነው። *እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል*፤ ለቤተ ክርስቲያን ሕያውነት፣ እንዲሁም ለአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መጻፍ የመንፈስ ቅዱስ መላክ እጅግ አስፈላጊ ነበር።

14+27 *ሰላምን...ሰላሜን*፤ ይህ የተለመደ የዕብራውያን ሰላምታ አቀራረብ ነው (20+19: 21:26)፤ እዚህ ላይ ግን ኢየ ሱስ የተጠቀመበት በተለየ ሁኔታ ነው። ቃሉ በኢየሱስ የማዳን ሥራ አማካይነት ደቀ መዛሙርቱ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ኅብረት የሚያገኙትን የተሟላ የውስጥ ሰላምና የመንፈስ ዕረፍት ያመለክታል። የቃሉ መደጋገም የሚያሳየው እውነተኛ ሰላም የእርሱ ስጦታ መሆኑን ነው። *ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም፤*

[28]"'እሄዳለሁ፤ ተመልሼም ወደ እናንተ
እመጣለሁ' ማለቴን ሰምታችኋል፤ ብትወዱኝስ
አብ ከእኔ ስለሚበልጥ ወደ አብ በመሄ
ዴደስ ባላችሁ ነበር፤ [29]የተናገርሁት ሲፈ
ጸም እንድታምኑ፣ ከመሆኑ በፊት አሁን
ነግሬአችኋለሁ። [30]የዚህ ዓለም ገዥ ስለ
ሚመጣ ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር
ብዙ አልነጋገርም። እርሱም በእኔ ላይ
ሥልጣን የለውም፤ [31]ነገር ግን እኔ አብን
እንደም ወድ፣ አባቴ ያዘዘኝንም እንደ
ማደርግ ዓለም እንዲያውቅ ነው።
"ተነሡ፤ ከዚህ እንሂድ።"

## የወይን ግንድና ቅርንጫፎቹ

**15** "እውነተኛው የወይን ተክል እኔ ነኝ፤
አትክልተኛውም አባቴ ነው። [2]እርሱም
በእኔ ያለውን፣ የማያፈራውን ቅርንጫፍ ሁሉ
ቈርጦ ይጥለዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውን ቅርን
ጫፍ ሁሉ ግን የበለጠ እንዲያፈራ ይገርዘ
ዋል።* [3]ከነገርኋችሁ ቃል የተነሣ እናንተ
አሁን ንጹሓን ናችሁ። [4]በእኔ ኑሩ፤ እኔም
በእናንተ እኖራለሁ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ
ካልሆነ በቀር ብቻውን ፍሬ ሊያፈራ አይ
ችልም፤ እናንተም በእኔ ካልኖራችሁ ፍሬ
ልታፈሩ አትችሉም።
[5]"እኔ የወይን ተክል ነኝ፤ እናንተም ቅር
ንጫፎች ናችሁ። ማንም በእኔ ቢኖር እኔም
በእርሱ ብኖር፣ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል፤

14፥29 ዮሐ13፥19፤ 16፥4
14፥30 ዮሐ12፥31
14፥31 ዮሐ10፥18፤ 12፥49
15፥1 መዝ80፥8-11፤ ኢሳ5፥1-7፤ዮሐ6፥35
15፥2 ቁ6፤መዝ 92፥14፤ማቴ3፥8፥10፤ 7፥20፤ገላ5፥22፤ ኤፌ5፥9፤ፊል1፥11
15፥3 ዮሐ13፥10፤ 17፥17፤ኤፌ5፥26
15፥4 ዮሐ6፥56
15፥5 ቁ16
15፥6 ቁ2፤ ሕዝ15፥4፤ማቴ3፥10
15፥7 ቁ4፤ ማቴ7፥7፤ዮሐ6፥56
15፥8 ማቴ9፥8፤ ዮሐ8፥31
15፥9 ዮሐ17፥23፤ 24፡26
15፥10 ዮሐ14፥15
15፥11 ዮሐ3፥29
15፥12 ቁ17፤ ዮሐ13፥34
15፥13 ዘፍ44፥33፤ ዮሐ10፥11፤ ሮሜ 5፥7፡8
15፥14 ኢዮ16፥20፤ ምሳ18፥24፤ ማቴ12፥50፤ሉቃ12፥4
15፥15 ዮሐ8፥26
15፥16 ቁ5፥19፤ ማቴ7፥7፤ዮሐ13፥18

ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና።
[6]በእኔ የማይኖር ተጥሎ እንደሚደርቅ ቅርን
ጫፍ ነው፤ እንዲህ ያሉት ቅርንጫፎች
ተለቅመው ወደ እሳት ይጣላሉ፤ ይቃጠላ
ሉም። [7]በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ
ቢኖሩ፣ የምትፈልጉትን ማንኛውንም ነገር
ለምኑ፤ ይሰጣችኋልም። [8]ብዙ ፍሬ በማፍራት
ደቀ መዛሙርቴ መሆናችሁን ብትገልጡ፣
በዚህ አባቴ ይከብራል።
[9]"አብ እንደ ወደደኝ ሁሉ እኔም ወደ
ድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ። [10]እኔ የአባቴን ትእ
ዛዝ ጠብቄ በፍቅሩ እንደምኖር፣ እናንተም
ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ።
[11]ደስታዬ በእናንተ እንዲሆንና ደስታችሁም
ሙሉ እንዲሆን ይህን ነግሬአችኋለሁ። [12]ትእ
ዛዜ ይህች ናት፤ እኔ እንደ ወደድኋችሁ
እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። [13]ስለ
ወዳጆቹ ሕይወቱን አሳልፎ ከመስጠት የሚ
በልጥ ፍቅር ማንም የለውም፤ [14]የማዛችሁን
ብትፈጽሙ ወዳጆቼ ናችሁ። [15]ከእንግዲህ
አገልጋዮች አልላችሁም፤ አገልጋይ ጌታው
የሚሠራውን አያውቅምና፤ ነገር ግን ከአባቴ
የሰማሁትን ሁሉ ስለ ገለጽሁላችሁ ወዳጆች
ብያችኋለሁ። [16]እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ
አልመረጣችሁኝም፤ እንድትሄዱና ፍሬ እንድ
ታፈሩ ፍሬያችሁም እንዲኖር ሾምኋችሁ።

*2 *ይገርዘዋል* የሚለው የግሪኩ ቃል *ያጠራዋል* የሚል ትርጒም አለው

የዓለም ሰላምታ መለዋወጥ ከናፍቆትና ከምኞት መግለጫ አያል
ፍም፤ የኢየሱስ ሰላም ግን እውንና የሚያረካ ነው። *አይጨነቅ፤* የቍ 1 ማብ ይመ።

14፥28 *ማለቴን ሰምታችኋል፤* ከቍ 3 ጋር ያነጻጽሩ። *አብ ከእኔ ስለሚበልጥ፤* ኢየሱስ ሥጋ በመልበሱ መሠረታዊ የሆነውን የአጻኝነት የሥራ ድርሻ ራሱን ዝቅ በማድረግ መቀበሉን ያሳያል። ይህን ሐሳብ መረዳት የሚቻለው በአብና በወልድ መካከል ካለው አንድነት አንጻር ነው (10፥30)።

14፥30 *የዚህ ዓለም ገዥ፤* የ12፥31 ማብ ይመ። *በእኔ ላይ ሥልጣን የለውም፤* የሰው ዘር ከጥንቱ በኀጢአት የወደቀ ስለ ሆነ፣ ከሰይጣን ሥልጣን ሥር ነው፤ ክርስቶስ ግን ከኀጢአት ነጻ ስለ ሆነ፣ ሰይጣን በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውም።

14፥31 *አባቴም ያዘዘኝንም እንደማደርግ፤* ኢየሱስ፣ ታዛዥነት አስፈላጊ መሆኑን ለተከታዮቹ አበክሮ አስገንዝቦአል (ቍ 15፡ 21፡ 23)፤ እርአያም ሆኖአቸዋል። ይህንም ተናግሮ ተልእኮውን ለመፈጸም አመራ (ምዕ 18-19)።

15፥1 *እኔ ነኝ፤* የ6፥35 ማብ ይመ። *እውነተኛው የወይን ተክል፤* በብሉይ ኪዳን ውስጥ የወይን ተክል ብዙውን ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ ምሳሌ ነው (ለምሳሌ መዝ 80፥8-16፤ ኢሳ 5፥1-7፤ ኤር 2፥21)። ይህ ተምሳሌት አብዛኛውን ጊዜ የእስራኤልን ጕድለት የሚገልጽ ነው፤ ሆኖም ኢየሱስ 'እውነተኛው የወይን ተክል' ነው።

15፥2 *ቆርጦ ይጥለዋል፤* የሚያመለክተው የፍርድን ቀን ነው (የቍ6 ማብ ይመ)። *ይገርዘዋል፤* አትክልትን መግረዝ ብዙ ፍሬ ያስገኛል። ይህም በአዲስ ኪዳን የመልካም ፍሬ ምሳሌ የሆነውን የቅድስናን ሕይወት ያመለክታል (ማቴ3፥8፤7፥16-20)፤ መልካም ባህርይንም ሊያመለክት ይችላል (ገላ 5፥22-23፤ ኤፌ 5፥9፤ ፊል 1፥11)።

15፥3 *ንጹሓን፤* የመግረዝ ውጤት ነው (የቍ 2 ማብ ይመ)። *ቃል፤* የኢየሱስን ትምህርት ሁሉ ያካትታል።

15፥4 *በእኔ ኑሩ፤* እምነት ከኢየሱስ ጋር ባለው አንድነትና ግንኙነት ካልሆነ በቀር፣ በራሱ ፍሬ ሊያፈራ አይችልም፤ ከወይን ግንድ የተገነጠለ ቅርንጫፍ ሕይወት የለውምና።

15፥5 *እኔ የወይን ተክል ነኝ፤* የቍ 1 ማብ ይመ። ድግግሙ አጽንዖትን ያሳያል። *ማንም በእኔ ቢኖር እኔም በእርሱ፤* ከክርስቶስ ጋር ሕያው የሆነ ኅብረት ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው፤ ይህን የመሰለ ኅብረት ከሌለ ምንም መሥራት አይቻልም።

15፥6 *ወደ እሳት ይጣላሉ፤ ይቃጠላሉም፤* ተፈርዶባቸው ማለት ነው (የቍ 2 ማብ ይመ)። በ6፥39፤ 10፥27-28 ላይ በሰፈረው ሐሳብ መሠረት ሲታዩ፣ እነዚህ ቅርንጫፎች ምናልባት እውነተኛውን እማኝ አይወክሉም። እውነተኛ ድነት ፍሬያማ በሆነ ሕይወት ይረጋገጣል (ቍ 10፤ የቍ 2 እና 4 ማብ ይመ፤ እንዲሁም የዕብ 6፥9 ማብ ይመ)።

15፥7 *ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፤* የክርስቶስን ቃል ካላወቁና ካላመኑ በትክክል መጸለይ አይቻልም። *የምትፈልጉትን ማንኛውንም ነገር ለምኑ፤* 14፥13 እና ማብ ይመ።

15፥8 *አባቴ ይከብራል፤* አብ በወልድ ሥራ ይከብራል (13፥31-32) በደቀ መዛሙርቱም ፍሬያማነት ይከብራል (ማቴ 7፥20፤ ሉቃ 6፥43-45)።

15፥10 *የአባቴን ትእዛዝ ጠብቄ…እንደምኖር…ትእዛዜን ብትጠብቁ፤* እዚህም ላይ የመታዘዝ አስፈላጊነት ይታያል (ከ14፥15፡21፡23 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የክርስቶስም ምሳሌነት ቀርቦአል (ከ14፥31 ጋር ያነጻጽሩ)። *በፍቅሩ…በፍቅሬ፤* ቍ12 እና 14 ይመ፤ መታዘዝና ፍቅር አይነጣጠሉም (1ዮሐ 2፥5፤ 5፥2-3)።

15፥11 *ደስታዬ፤* ከዚህ ቃል ቀደም ሲል በዚህ ወንጌል በ3፥29 ላይ ተጠቅሶ ይገኛል፤ ጌታ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የመጨረሻውን እራት በበላበት ምሽት ከተናገራቸውም ፍሬ ነገሮች አንዱ ነበር (16፥20-22፡24፤ 17፥13)። የክርስትና መንገድ ሐዘን የተሞላበት ጕዞ አይደለም፤ ምክንያቱም ኢየሱስ የተከታዮቹ ደስታ የተሟላ እንዲሆን ይፈልጋል።

15፥13፤ የክርስቶስ ፍቅር በቃላት ብቻ የተነገረ ሳይሆን ሕይወቱን በመሠዋት የተገለጸ ነው።

15፥15 *አገልጋዮች…ወዳጆች፤* ብዙውን ጊዜ አገልጋይ የጌታውን ዓላማ ሳያውቅ ትእዛዙን የሚያከናውን ነው። ኢየሱስ ግን ወዳጆቹን የምሥጢሩ ተካፋዮች አድርጎአቸዋል። *…ሁሉ ስለ ገለጽሁላችሁ፤* ከ16፥12 እንደምንረዳው፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ የአብን ፈቃድ በሚችሉት መጠን እንዲያውቁ ቢያደርግም፣ ዕቅዱ ሁሉ ለእነርሱ ግልጽ የመሆኑ ጕዳይ ገና የሚቀረው ነገር ነበረው። መንፈስ ቅዱስ ግልጽ ያልሆነውን ነገር ጊዜው ሲደርስ እንዲታወቅ ያደርጋል።

15፥16 *እኔ መረጥኋችሁ…ፍሬ እንድታፈሩ…የምትለምኑትን፤* ደቀ መዛሙርት መምህራቸውን መርጠው መከተል

ስለዚህም አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ
ይሰጣችኋል። 17እርስ በርሳችሁ እንድትዋ
ደዱ፣ ትእዛዜ ይህቺ ናት።

### ዓለም ደቀ መዛሙርትን መጥላቱ

18"ዓለም ቢጠላችሁ፣ ከእናንተ በፊት እኔን
እንደ ጠላኝ ዕወቁ። 19ከዓለም ብትሆኑ ኖሮ፣
ዓለም የራሱ እንደሆኑት አድርጎ በወደዳ
ችሁ ነበር፤ ከዓለም ለይቼ ስለ መረጥኋችሁ
የዓለም አይደላችሁም፤ ዓለም የሚጠላችሁም
ስለዚሁ ነው። 20'አገልጋይ ከጌታው አይበልጥም'
ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስታውሱ። እኔን
አሳደውኝ ከሆነ፣ እናንተንም ያሳድዷችኋል፤
ቃሌን ጠብቀው ከሆነም ቃላችሁን ይጠብ
ቃሉ። 21የላከኝን ስለማያውቁ፣ በስሜ ምክ
ንያት ይህን ያደርጉባችኋል። 22መጥቼ ባል
ነግራቸው ኖሮ ኀጢአት ባልሆነባቸው ነበር፤
አሁን ግን ለኀጢአታቸው የሚሰጡት ምክን
ያት የላቸውም። 23እኔን የሚጠላ፣ አባቴንም
ይጠላል። 24ሌላ ሰው ያላደረገውን በመካከላቸው
ባላደርግ ኖሮ፣ ኀጢአት ባልሆነባቸው ነበር፤
አሁን ግን እነዚህን ታምራት አይተዋል፤ ሆኖም
እኔንም አባቴንም ጠልተዋል። 25ይህም፣
'ያለ ምክንያት ጠሉኝ' ተብሎ በሕጋቸው
የተጻፈው ቃል እንዲፈጸም ነው።
26"እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ፣ ከአብ
የሚወጣው አጽናኙ የእውነት መንፈስ በመጣ
ጊዜ፣ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል። 27እና

15፥17 ቍ12
15፥18 ኢሳ66፥5፤ ዮሐ7፥7፤1ዮሐ3፥13
15፥19 ቍ16፤ ዮሐ17፥14
15፥20ዮሐ13፥16፤ 2ጢሞ3፥12
15፥21 ኢሳ66፥5፤ ማቴ5፥10:11፤ 10፥22፤ሉቃ6፥22፤ ዮሐ16፥3፤ሐሥ5፥41 ፤1ጴጥ4፥14፤ራእ2፥3
15፥22 ሕዝ2፥5፤ 3፥7፤ዮሐ9፥41፤ሮሜ 1፥20፤2፥1
15፥24 ዮሐ5፥36፤ 9፥41
15፥25መዝ35፥19፤ 69፥4፤109፥3፤ ዮሐ10፥34
15፥26 ዮሐ14፥16 :17:26፤16፥7፤ 1ዮሐ 5፥7
15፥27 ሉቃ1፥2፤ 24፥48፤ዮሐ21፥24፤ 1ዮሐ1፥2፤4፥14
16፥1 ማቴ11፥6፤ ዮሐ15፥18-27
16፥2 ዮሐ9፥22፤ 12፥42፤ ኢሳ66፥5፤ ሐሥ26፥9:10፤ ራእ 6፥9
16፥3 ዮሐ15፥21፤ 17፥25፤1ዮሐ3፥1
16፥4 ዮሐ5፥27፤ 13፥19፤14፥29፤
16፥5 ቍ10:17:28፤ ዮሐ7፥33፤13፥36፤

ንተም ደግሞ፣ ከመጀመሪያው ከእኔ ጋር ስለ
ነበራችሁ፣ ትመሰክራላችሁ።

16 "ይህን ሁሉ የነገርኋችሁ እንዳትሰ
ናከሉ ነው። 2ከምኵራብ ያስወጧ
ችኋል፤ እንዲያውም የሚገድላችሁ ሁሉ
እግዚአብሔርን እንዳገለገለ የሚቈጥርበት ጊዜ
ይመጣል። 3ይህን ሁሉ የሚያደርጉባችሁ፣
አብን ወይም እኔን ስላላወቁ ነው። 4አስ
ቀድሜ ይህን የነገርኋችሁ ጊዜው ሲደርስ
እንድታስታውሱ ነው፤ ከእናንተ ጋር ስለ
ነበርሁ፣ ይህን ከመጀመሪያው አልነገርኋች
ሁም።

### የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

5"እንግዲህ ወደ ላከኝ እሄዳለሁ፤ ይሁን
እንጂ ከእናንተ፣ 'የምትሄደው የት ነው?'
ብሎ የሚጠይቀኝ የለም። 6ይህን በመና
ገሬም ልባችሁ በሐዘን ተሞልቶአል፤ 7ነገር
ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፤ መሄዴ ይበጃ
ችኋል። እኔ ካልሄድሁ አጽናኙ ወደ እና
ንተ አይመጣም፤ ከሄድሁ ግን እርሱን ወደ
እናንተ እልካለሁ፤ 8በሚመጣበትም ጊዜ
ዓለምን ስለ ኀጢአት[ˣ]፣ ስለ ጽድቅና ስለ
ፍርድ ይወቅሳል። 9ስለ ኀጢአት ሲባል፣
ሰዎች በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ 10ስለ ጽድቅ፣

14፥5 16፥6 ቍ22 16፥7 ዮሐ7፥39፤ 14፥16:26፤15፥26
16፥9 ዮሐ15፥2216፥10 ቍ5፤ሐሥ 3፥14፤7፥52፤
ሮሜ1፥17፤3፥21:22፤1ጴጥ3፥18
[ˣ]8 *ወይም የዓለምን ኀጢአት ይገልጣል*

የተለመደ ነበር፤ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ግን እርሱ ራሱ ፍሬ እንዲያፈሩ መረጣቸው እንጂ፣ ምርጫው የእነርሱ አልነበረም። በእኛ ጥረት ብቻ ፍሬ የምናፈራ መስሎን ብርቱ የጸሎት ሕይወት እንዲኖረን እንፈልጋለን፤ እዚህ ላይ የምናየው ግን ፍሬ እንድናፈራ የሚያስችለን ኢየሱስ እንደሆነ ነው፤ አብም ጸሎታችንን ይሰማል። *በስሜ፤* የ2፥23፤ 14፥13 ማብ ይመ።

15፥18-19 *ዓለም፤* እዚህ ላይ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ዕቅድ ተቀዋሚ የሆነውን፣ ምድራዊ ሥርዐት ነው (የ1፥9 ማብ ይመ)።

15፥19 *የ...አይደላችሁም፤* የክርስቲያን ዓይነተኛ መለዮ ከእግዚአብሔር ያገኘው አዲስ ሕይወት ስለ ሆነ፣ እግዚአብሔርን እንደሚቃወሙት ሰዎች አይደለም።

15፥21 *ይህን ያደርጉባችኋል፤* ክርስቲያኖች ከዓለም ባለመሆናቸው፣ ዓለም በእነርሱ ላይ ስደት ማስነሳቱ የማይቀር ነው። ለዚህም ዋናው መንሥኤ ዓለም አብን አለማወቁና አለመቀበሉ ነው (ከ16፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። *ስሜ፤* የ2፥23 ማብ ይመ።

15፥22 *ምክንያት የላቸውም፤* የተለየ ዕድል ማግኘት ኀላፊነትን ያስከትላል። አይሁድ፣ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ከገለጠላቸው ሌላ፣ የእግዚአብሔር ልጅ በመካከላቸው በመገኘቱ የታደሉ ነበሩ። ኢየሱስን አለመቀበላቸው ግን በደለኞችና ይቅርታ የማይገባቸው አድርጓቸዋል። ኢየሱስ ወደ እነርሱ ባይመጣም እንኳ ኀጢአተኞች መሆናቸው አልቀረም፤ የባሰውን በደለኞች ያደረጋቸው ግን እምቢተኞች ሆነው መገኘታቸው ነው (ቍ 24)።

15፥25 *የተጻፈው ቃል እንዲፈጸም፤* ኀጢአተኞች በተቻላቸው መንገድ ሁሉ ቢቃወሙትም፣ የእግዚአብሔር እቅድ ምን ጊዜም ተፈጻሚ ነው። *በሕጋቸው፤* የ10፥34፤ የ12፥34 ማብ ይመ።

15፥26 *የምልክላችሁ፤* የ14፥16፡ 26 ማብ ይመ። *የእውነት መንፈስ፤* የ14፥17 ማብ ይመ። *ከአብ የሚወጣው፤* መንፈስ ቅዱስ ከአብ ጋር ስላለው ዘላለማዊ አንድነት ሳይሆን፣ የአብን ተግባር ለማከናወን፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ ዓለም መላኩን ለማመልከት ሊሆን ይችላል። *አጽናኙ፤* የ14፥16 ማብ ይመ። *ይመሰክራል፤* የ1፥7 ማብ ይመ።

15፥27 *እናንተም ደግሞ፤* ኀላፊነታቸውን አክብዶ ሲገልጽ ነው። አማኞች ስለ ክርስቶስ የሚመሰክሩት በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነው፤ ይሁን እንጂ ስለ ምስክርነታቸው ኀላፊዎቹ ራሳቸው ናቸው። *ከመጀመሪያው፤* ሐዋርያት በተለየ ሁኔታ በክርስቶስ የተመረጡ፣ ከእርሱም የተማሩና፣ የክብሩን መገለጥ በዐይናቸው ያዩ በመሆናቸው ታማኝ ምስክሮች ናቸው (ሉቃ 24፥48፤ ሐሥ 10፥39፡ 41 ይመ)።

16፥2 *ከምኵራብ ያስወጧችኋል፤* የ9፥22 ማብ ይመ። *እግዚአብሔርን እንዳገለገለ፤* የትክክለኛ እምነት ተከታይ ነን ባዮች ራሳቸውን እንደ ታማኝ አገልጋይ በመቍጠር ክርስቲያኖችን በእጅጉ አሳደዋል (ሐሥ 26፥9-11፤ ገላ 1፥13-14)።

16፥3 *አብን፤* የ5፥17 ማብ ይመ። *ወይም እኔን፤* የአብና የወልድ አንድነት ተገልጾ እናያለን፤ ክርስቶስን አለማወቅ አብን አለማወቅ ነውና።

16፥5 *ከእናንተ፣ 'የምትሄደው የት ነው? ብሎ የሚጠይቀኝ የለም፤* ጴጥሮስ እንደዚህ ያለ ጥያቄ አቅርቦ ነበር (13፥36)፤ ነገር ግን ትኵረቱን ፈጥኖ ወደ ሌላ ቀይሮአል፤ ሥጋቱም ኢየሱስ ወዴት እንደሚሄድ ያለማወቁ ሳይሆን፣ ኢየሱስ ከተለያቸው በኋላ በእርሱና በሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ላይ ስለሚያጋጥማቸው ሁኔታ ነበር።

16፥6 *ልባችሁ በሐዘን ተሞልቶአል፤* እንዲህ ያለው ስሜት ያደረባቸው ኢየሱስ እንደሚለያቸው በማወቃቸው ነው።

16፥7 *እኔ ካልሄድሁ፤* እርሱ ካልሄደ፣ መንፈስ ቅዱስ የማይመጣበትን ምክንያት ኢየሱስ አልገለጸላቸውም፤ መንፈስ ቅዱስ ከመላኩ በፊት፣ በመስቀል ላይ የሚከናወነው የማዳን ሥራው አስፈላጊ መሆኑን ግን በግልጽ አስተምሮአቸዋል። *አጽናኙ፤* የ14፥16 ማብ ይመ። *እልካለሁ፤* የ14፥26 ማብ ይመ።

16፥8 *ዓለምን...ይወቅሳል፤* መንፈስ ቅዱስ በዓለም ላይ ከሚያከናውናቸው ሥራዎች አንዱ ነው። በመሠረቱ አዲስ ኪዳን የሚተርከው፣ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ስለሚያከናውነው ሥራ ነው።

16፥9 *ስለ ኀጢአት፤* መንፈስ ቅዱስ ካልወቀሳቸው በቀር ሰዎች ኀጢአተኞች መሆናቸውን መገንዘብ አይችሉም። *ሰዎች በእኔ ስለማያምኑ ነው፤* ምናልባትም ኀጢአተኝነታቸው አለማመናቸው ነው፤ ወይም አለማመናቸው የኀጢአተኝነታቸው ቋሚ ምስክር ነው። ዮሐንስ ሁለቱንም ሐሳቦች ልብ ሳይል አልቀረም።

16፥10 *ስለ ጽድቅ፤* በክርስቶስ መሥዋዕትነት የተገኘ

ወደ አብ ስለምሄድና ከእንግዲህ ስለማታዩኝ
ነው፤ [11]ስለ ፍርድም፣ የዚህ ዓለም ገዥ ስለ
ተፈረደበት ነው።
[12]"ብዙ የምነግራችሁ ነበረኝ፤ አሁን ግን
ልትሸከሙት አትችሉም። [13]የእውነት መን
ፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራ
ችኋል። እርሱ ከራሱ አይናገርም፤ የሚሰ
ማውን ብቻ ይናገራል፤ እንዲሁም ወደ ፊት
ስለሚሆነው ይነግራችኋል፤ [14]የእኔ ከሆነው
ወስዶ እንድታውቁ በማድረግ ያከብረኛል።
[15]የአብ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው፤ እንግዲህ፣
'የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ ያደርጋል'
ያልኋችሁ ለዚሁ ነው።
[16]"ከጥቂት ጊዜ በኋላ አታዩኝም፤ ይሁን
እንጂ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ታዩኛላችሁ።"

**የደቀ መዛሙርት ሐዘን ወደ ደስታ መለወጥ**

[17]ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንዶቹ፣ "'ከጥቂት
ጊዜ በኋላ አታዩኝም፤ ይሁን እንጂ ከጥቂት
ጊዜ በኋላ ደግሞ ታዩኛላችሁ' እንዲሁም፣
'ወደ አብ ስለምሄድ' ሲል ምን ማለቱ ነው?"
ተባባሉ፤ [18]"'ጥቂት ጊዜ' ማለቱስ ምን ይሆን?
የሚለውም ነገር አልገባንም" እያሉ ይጠያየቁ
ነበር።
[19]ኢየሱስም ሊጠይቁት እንደ ፈለጉ ባወቀ
ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ "እኔ፣ 'ከጥቂት ጊዜ
በኋላ ታዩኛላችሁ፤ ይሁን እንጂ ከጥቂት ጊዜ
በኋላ ደግሞ አታዩኝም' ስላልኋችሁ፣ ምን
ማለቴ እንደ ሆነ እርስ በርሳችሁ ትጠያየ
ቃላችሁ? [20]እውነት እላችኋለሁ፤ እናንተ
ታለቅሳላችሁ፤ ታዝናላችሁም፤ ዓለም ግን ሐሤት
ያደርጋል፤ ይሁን እንጂ ሐዘናችሁ ወደ ደስታ
ይለወጣል። [21]ሴት ቀኗ ደርሶ ስትወልድ ትጨ
ነቃለች፤ ከተገላገለች በኋላ ግን፣ ሰው ወደ
ዓለም ስለ መጣ ጭንቋን ትረሳለች፤ [22]ለእና
ንተም እንደዚሁ አሁን የሐዘን ጊዜ ነው፤
ሆኖም እንደ ገና ስለማያችሁ ደስ ይላችኋል፤
ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም። [23]በዚያ
ቀን ከእኔ ምንም አትለምኑም፤ እውነት እላ
ችኋለሁ፤ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ
ይሰጣችኋል። [24]እስከ አሁን በስሜ ምንም
አልለመናችሁም፤ ለምኑ ትቀበላላችሁ፤ ደስታ
ችሁም ሙሉ ይሆናል።
[25]"እስከ አሁን የነገርኋችሁ በምሳሌ ቢሆንም
እንኳ፣ ከእንግዲህ ግን ስለ አብ በምሳሌ ሳይ
ሆን በግልጽ የምናገርበት ጊዜ ይመጣል።
[26]በዚያ ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ ይህም
በእናንተ ፈንታ አብን እለምናለሁ ማለቴ
አይደለም፤ [27]ስለ ወደዳችሁኝና ከእግዚአብሔርም
እንደ ወጣሁ ስላመናችሁ አብ ራሱ ይወዳ
ችኋል። [28]ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤
አሁን ግን ዓለምን ትቼ ወደ አብ እሄዳለሁ።"
[29]ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አሉ፤
"እሁንም እኮ ያለ ምሳሌ በግልጽ እየተና

16፥11 ዮሐ12፥31
16፥12 ማር4፥33፤ 1ቆሮ3፥2
16፥13 መዝ25፥5፤ ዮሐ14፥17፡26
16፥15 ዮሐ17፥10
16፥16 ቁ-22፤ ዮሐ7፥33፤14፥18-24
16፥17 ቁ-5፡16
16፥20 ማር16፥10፤ ሉቃ23፥27፤ ዮሐ20፥20
16፥21 ኢሳ13፥8፤ 21፥3፤26፥17፤ ሚክ4፥9፤1ተሰ5፥3
16፥22 ቁ-6፡16፡20፤ ኤር31፥12
16፥23 ቁ-26፤ ማቴ7፥7፤ዮሐ14፥20
16፥24 ማቴ7፥7፤ ዮሐ3፥29
16፥25 ቁ-2፡29፤ መዝ78፥2፤ሕዝ 29፥49፤ማቴ13፥34፤ ማር4፥33፡34፤ ዮሐ10፥6
16፥26 ቁ-23፡24
16፥27 ቁ-30፤ ዮሐ13፥3፤14፥21፡23
16፥28 ቁ-5፡10፡17፤ ዮሐ13፥3
16፥29 ቁ-25

ጽድቅ ማለት ነው (ከሮሜ 1፥17፤ 3፥21-22 ጋር ያነጻጽሩ)። አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ጽድቅን የሚያገኘው፣ በመልካም ሥራው ሳይሆን፣ በመስቀል ላይ በተፈጸመው የክርስቶስ ሞት መሆኑን ከመንፈስ ቅዱስ በቀር ለሰው ማንም መግለጽ አይችልም። *ወደ አብ ስለምሄድ፤* የክርስቶስ ክብር ከተገለጠበት መንገድ አንዱ ዕርገቱ ነው፤ በዚህም እግዚአብሔር የክርስቶስን የማዳን ሥራ አጽድቆታል።

16፥11 *ስለ ፍርድ፤* ኢየሱስ ይህን ያለው እንዲሁ ስለ ድል ለመናገር ያህል ሳይሆን፣ ዲያብሎስ በተገቢው መንገድ ፍርዱን ተቀብሎ መሸነፉን ለመግለጽ ነው፤ ጥያቄው የኀይል ሳይሆን እግዚአብሔር ትክክለኛ ፍርድ የሚሰጥ መሆኑን የሚያመለክት ነው። *የዚህ ዓለም ገዥ፤* የ12፥31 ማብ ይመ።

16፥12 *አሁን ግን ልትሸከሙት አትችሉም፤* ይህም፣ 'አሁን ለማስተዋል ከምትችሉት በላይ ነው' ወይም፣ 'ያለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ ለማከናወን ከምትችሉት ሥራ በላይ ነው' ማለት ሊሆን ይችላል፤ በክርስቶስ ትምህርት ለመመላለስ ሁሉን የሚያስችል የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ አስፈላጊ ነውና።

16፥13 *የእውነት መንፈስ፤* የ14፥17 ማብ ይመ። *የሚሰማውን ብቻ፤* የሚሰማው ከአብ ይሁን ከወልድ አልተነገረንም፤ ሆኖም በሦስቱ አካላት መካከል ያለውን የጠበቀ አንድነት ጥቅሱ ያሳየናል። *ወደ ፊት ስለ ሚሆነው፤* ምናልባት ጠቅላላውን የክርስትናን መንገድ ወይም በሐዋርያት ጽሑፎች የተላለፈውን የእግዚአብሔር ፈቃድ መግለጥ ማለት ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ይህን በተናገረበት ወቅት፣ እነዚህ ገና ወደ ፊት የሚፈጸሙ ነበሩ።

16፥14 *ያከብረኛል፤* የ1፥14 ማብ ይመ። መንፈስ ቅዱስ ከራሱ ይልቅ ወልድ እንዲከበር ይሻል።

16፥15 *የአብ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው፤* ከ17፥10 ጋር ያነጻጽሩ። ሦስቱ አካላት አንድነታቸው የጠበቀ ነው።

16፥16 *ከጥቂት ጊዜ በኋላ...ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን፤* የመጀመሪያው ሐረግ ከስቅለቱ በፊት የነበረውን ጊዜ የሚያመለክት መሆኑን ጥቂቶች ይጠራጠራሉ፤ ሁለተኛውን ሐረግ በተመለከተ ግን እስከ ትንሣኤው ወይም መንፈስ ቅዱስ እስከ ወረደበት ቀን ወይም እስከ ዳግም ምጽአት ያለውን ጊዜ ሊያመለክት ይችላል የሚሉ የተለያዩ ትርጓሜዎች አሉ፤ እዚህ ላይ ግን የቋንቋው አገባብ፣ ከትንሣኤው በኋላ ወደሚለው ትርጓሜ ይበልጥ የሚያደላ ይመስላል።

16፥17 *ወደ አብ ስለምሄድ፤* ቁ- 10 ይመ። ኢየሱስ ይህን ጉዳይ 'ከጥቂት ጊዜ በኋላ' ከሚለው ሐሳብ ጋር አላያያዘውም፤ ሐዋርያቱ ግን ሁለቱ ሐሳቦች እንደ ተገናኙ አድርገው ቈጥረዋል።

16፥20 *ታለቅሳላችሁ፤* በ11፥33 እንደ ተመለከተው ሙሾ ማልቀስን የሚገልጽ ከመሆኑም በላይ፣ ጥልቅ ሐዘንና ስሜት በገሃድ መገለጡን ያመለክታል።

16፥21 *ሴት ቀኗ ደርሶ ስትወልድ፤* ልጅ በሚወለድበት ጊዜ ሥቃይና ደስታ ይፈራረቃሉ (ከኢሳ 26፥17-19፤ 66፥7-14፤ ከሆሴ 13፥13-14፤ ጋር ያነጻጽሩ)።

16፥22 *እንደ ገና ስለማያችሁ፤* በቁ- 16 እንደ ተገለጸው ሆኖ፣ የኢየሱስን ከትንሣኤ በኋላ መገለጥ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። *ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም፤* ትንሣኤ፣ በዓለም ፈተና የማይሻረውን ደስታ በማስገኘት፣ ነገሮችን ለዘለቄታው ይለውጣል።

16፥23 *በዚያን ቀን ከእኔ ምንም አትለምኑም፤* በጸሎት የሚቀርበውን ልመና ሳይሆን፣ አንድ ነገር ለማወቅ የሚቀርበውን ጥያቄ የሚመለከት ይመስላል፤ ምክንያቱም ከትንሣኤ በኋላ እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ አስፈላጊ ባለ መሆኑ ነው። ቀደም ሲል ደቀ መዛሙርቱ የሚፈልጉትን ነገር ኢየሱስን ይጠይቁ ነበር፤ ከትንሣኤው በኋላ ግን የሚፈልጉትን ነገር በኢየሱስ ስም በቀጥታ ወደ አብ ሊያቀርቡ እንደሚችሉ ያመለክታል (ቁ- 24፡ 26-27 እና ማብ ይመ)። *በስሜ፤* የ2፥23፤ የ14፥13 ማብ ይመ።

16፥24 *እስካሁን፤* ከዚህ ቀደም አብን ለምነዋል፤ ይሁን እንጂ በክርስቶስ ስም አብን አልለመኑም ነበር። *ደስታችሁ፤* የ15፥11 ማብ ይመ።

16፥25 *...የነገርኋችሁ በምሳሌ፤* በዚህ ክፍል በተናገረው ብቻ ሳይሆን በትምህርቱ ሁሉ ማለት ነው። *ጊዜ ይመጣል፤* ከትንሣኤ በኋላ ለማለት ነው።

16፥26 *በስሜ፤* የ2፥23፤ የ14፥13 ማብ ይመ። *እለምናለሁ ማለቴ አይደለም፤* ከሮሜ 8፥34፤ ከዕብ 7፥25፤ ከ1ዮሐ 2፥1 ጋር የሚቃረን አይደለም። እነዚህ ክፍሎች፣ የተሰቀለውና ከሞት የተነሣው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ መገኘቱ ራሱ እንደ ምልጃ መቈጠሩን ያስረዳሉ፤ በዚህም ክፍል በእኛ ፈንታ ልመና ማቅረብ እንደማያስፈልገውም መረዳት ይቻላል።

16፥27 *አብ ራሱ ይወዳችኋል፤* ክርስቶስ፣ ደቀ መዛሙርቱ ሲጸልዩ ወደ አብ በቀጥታ መቅረብ የሚችሉበትን ምክንያት ይገልጻል። ይኸውም ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ስለ ወደዱትና

ገርህ ነው:: 30አሁን ሁሉን ነገር እንደምታ
ውቅና ማንም ሊጠይቅህ እንደማያስፈልግ
ተረድተናል፤ ይህም ከእግዚአብሔር እንደ ወጣህ
እንድናምን አድርጎናል::"
31ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ "አሁ
ንስ አመናችሁ ማለት ነው?[የ] 32እነሆ፤ ሁላ
ችሁም በየፊናችሁ የምትበታተኑበት ጊዜ
ይመጣል፤ ያም ጊዜ አሁን ነው:: እኔንም
ብቻዬን ትተዉኛላችሁ፤ ይሁን እንጂ አባቴ
ከእኔ ጋር ስለ ሆነ ብቻዬን አይደለሁም::
33"በእኔ ሰላም እንዲኖራችሁ፣ ይህን ነግሬ
አችኋለሁ:: በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤
ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌ
ዋለሁ::"

## ኢየሱስ ስለ ራሱ መጸለዩ

17 ኢየሱስ ይህን ከተናገረ በኋላ፣ ወደ
ሰማይ ቀና ብሎ እንዲህ ሲል ጸለየ፤
"አባት ሆይ፤ ጊዜው ደርሶአል፤ ልጅህ ያከ
ብርህ ዘንድ ልጅህን አክብረው፤ 2ከአንተ
ለተቀበላቸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እን
ዲሰጥ በሰው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥተኸዋ
ልና:: 3እውነተኛ አምላክ የሆንኸውን አንተንና
የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ
ይህች የዘላለም ሕይወት ናት:: 4የሰጠኸኝን ሥራ
በመፈጸም በምድር አከበርሁህ:: 5እንግዲህ
አባት ሆይ፤ ዓለም ሳይፈጠር ከአንተ ጋር በነ
በረኝ ክብር በአንተ ዘንድ አክብረኝ::

16+30 ቍ27፤ 1ነገ17+24፤ዮሐ13+3
16+32 ቍ2:25፤ ማቴ26+31:56፤ ዮሐ8+16:29
16+33 ዮሐ14+27፤ 15+18-21፤ ሮሜ8+37፤1ዮሐ4+4፤ 5+4፤ራእ2+7:11:17: 26፤3+5:12:21፤21+7
17+1 ማቴ26+18፤ ዮሐ11+41፤12+23፤ 13+31:32
17+2 ቍ6:9:24፤ ዳን7+14፤ ማቴ25+46፤28+18፤ ዮሐ 6+37:39
17+3 ቍ8:18:21: 23:25፤ዮሐ3+17፤ ፊል3+8
17+4 ዮሐ13+31፤ 19+30
17+5 ቍ1፤ ዮሐ1+2፤ፊል2+6
17+6 ቍ2:26፤ ዮሐ1+18
17+8 ቍ3:14:18: 21:23:25:26፤ዮሐ 3+17፤13+3፤14+24
17+9 ቍ2፤ ሉቃ22+32
17+10 ዮሐ16+15
17+11 ቍ13:21-23 መዝ133+1፤ዮሐ 7+33፤10+30፤13+1
17+12 ማቴ1+22፤ ዮሐ6+39:70

## ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ጸለየ

6"ለእነዚህ ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን
ገልጬላቸዋለሁ:: የአንተ ነበሩ ለእኔ ሰጠ
ኸኝ፤ እነርሱም ቃልህን ጠብቀዋል:: 7የሰጠ
ኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደ ሆነ አሁን ዐውቀዋል፤
8ምክንያቱም የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸው
ተቀብለዋል፤ እኔም ከአንተ እንደ ወጣሁ
በእርግጥ ዐውቀዋል፤ አንተ እንደ ላክኸኝም
አምነዋል፤ 9እነርሱ የአንተ ስለ ሆኑ እጸል
ይላቸዋለሁ፤ ለሰጠኸኝና የአንተ ለሆኑት
እንጂ ለዓለም አልጸልይም:: 10የእኔ የሆነው
ሁሉ የአንተ ነው፤ የአንተ የሆነውም ሁሉ
የእኔ ነው፤ በእነርሱም ከብሬአለሁ:: 11ከእን
ግዲህ እኔ በዓለም አልቈይም፤ እነርሱ ግን
በዓለም ውስጥ ናቸው፤ እኔም ወደ አንተ
መምጣቴ ነው:: ቅዱስ አባት ሆይ፤ እኛ
አንድ እንደ ሆንን፣ እነርሱም አንድ እንዲ
ሆኑ በሰጠኸኝ በስምህ ጠብቃቸው:: 12እኔ ከእ
ነርሱ ጋር ሳለሁ፣ በሰጠኸኝ ስም ከለልኋ
ቸው፤ ጠበቅኋቸውም፤ የመጽሐፍ ቃል እንዲ
ፈጸም ከአንዱ ከጥፋት ልጅ በቀር ከእነርሱ
ማንም አልጠፋም::
13"አሁን ወደ አንተ መምጣቴ ነው፤ ነገር
ግን ደስታዬ በእነርሱ ዘንድ የተሟላ እንዲ
ሆን፣ አሁን በዓለም እያለሁ ይህን እናገራለሁ::

[የ]31 *ወይም በስተ መጨረሻው አመናችሁ!*

ስላመኑበት፣ በኢየሱስ ስም የሚያቀርቡትን ልመና እግዚአብሔር በፍቅር ይቀበላቸዋል ማለት ነው::

16+29 *ያለ ምሳሌ!* ቍ 25 እና ማብ ይመ::

16+30 *ከእግዚአብሔር እንደ ወጣህ እንድናምን፤* በዚህ ወንጌል የሚደጋገሙት ሁለት ፍሬ ሐሳቦች:- ማመን (የ1+7 ማብ ይመ) እና የኢየሱስ ከአብ መውጣት ናቸው (የ4+34፤ 17+3 :8 ማብ ይመ)::

16+32 *የምትበታተኑበት፤* ደቀ መዛሙርት እምነት ነበራቸው፤ እምነታቸው ግን ብርቱ ፈተናን ለመቋቋም ጽኑ አልነበረም:: ኢየሱስ እንደሚሰናከሉ ያውቃል፤ ሆኖም ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በሰዎች ጽናት ላይ ሳይሆን፣ ከወደቁ በኋላ እንኳ ሰዎችን አንሥቶ በሚጠቀም በእግዚአብሔር ኀይል ነው::

16+33 'በእኔ' እና 'በዓለም' (የ1+10 ማብ ይመ)፣ እንዲሁም 'በሰላም' እና 'በመከራ' መካከል ያለውን ንጽጽር ያስተውሉ:: *አሸንፌዋለሁ!* ሞት እፊቱ ቢደቀንም፣ ኢየሱስ በመጨረሻ ድል አድራጊ መሆኑን አረጋግጦአል::

*17+1-26!* ይህ የወንጌል ክፍል በጽሑፍ የተላለፈውን ረጅሙን የኢየሱስን ጸሎት የያዘ ነው::

17+1 *ወደ ሰማይ ቀና ብሎ፤* ጸሎት የሚያደርግ ሰው በግንባሩ የሚደፋበትን ጊዜ ቢኖርም (ማቴ 26+39)፣ ወደ ሰማይ ቀና ብሎ መጸለይም የተለመደ ነው (11+41፤ መዝ 123+1፤ ማር 7+34):: *አባት ሆይ፤* እግዚአብሔርን መጥሪያ ቃል ሲሆን፣ በዮሐንስ ወንጌል ብዙ ጊዜ ተጽፎ ይገኛል:: *ጊዜው!* የ2+4 ማብ ይመ:: *ያከብርህ ዘንድ...አክብረው፤* የ1+14፤ የ7+39፤ የ13+31 ማብ ይመ:: የአብና የወልድ ክብር በጥብቅ የተሳሰረ ነው፤ ኢየሱስ በሞቱ እግዚአብሔርን የሚያከብርበት ክብር፣ አማኞችን ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ይመራቸዋል (ቍ 2)::

17+2 *ሰጥተኸዋልና፤* በዚህ ምዕራፍ 'መስጠት' የሚለው ሐሳብ አጽንዖት አግኝቶአል (ቍ 4:6-9:11-12:14:22:24)፤ የ3+27 ማብ ይመ:: *የዘላለምን ሕይወት እንዲሰጥ!* የ3+15 ማብ ይመ:: *ከአንተ ለተቀበላቸው ሁሉ፤* አሁንም እግዚአብሔር ለድነት የሚያደርገው ጥሪ ትኵረት ተሰጥቶታል::

17+3 *የላክኸውንም፤* እዚህም ላይ የኢየሱስ ተልእኮ ተወስቶአል::

17+4 *አከበርሁህ፤* የክርስቶስ ተልእኮ የአባቱን ፈቃድ መፈጸም ነው:: *የሰጠኸኝን ሥራ፤* አብ ከሁሉ በላይ እንደ ሆነ ኢየሱስ አበክሮ ያሳያል::

17+5 *ከአንተ ጋር በነበረኝ ክብር...አክብረኝ፤* ኢየሱስ ቀድሞ ወደ ነበረው ክብሩ አብ እንዲመልሰው ይጠይቃል፤ ይኸውም እንደ ባሪያ ሆኖ ካገለገለበት ቦታ ወደ ክብሩ እንዲመለስ ነው:: ይህም የሆነው በትንሣኤውና በክብር በአብ ቀኝ በተቀመጠ ጊዜ ነው:: *ዓለም፤* ፍጥረተ ዓለም ማለት ነው (የቍ 14፤ የ1+9 ማብ ይመ):: 'ዓለም' የሚለው ቃል በዚህ ጸሎት ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል::

17+6 ስምህን ገልጬላቸዋለሁ፤ የ2+23፤ የ14+13 ማብ ይመ፤ ከ1+18 ጋር ያነጻጽሩ:: *ለእነዚህ...ለሰጠኸኝ!* እዚህም ላይ የመለኮትን ጥሪ እናያለን (ከ6+44 ጋር ያነጻጽሩ)::

17+7 *ሁሉ ከአንተ እንደ ሆነ፤* ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖራቸው የሚችለው አብ በኢየሱስ አማካይነት እንደሚሠራ ሲረዱ ብቻ ነው፤ ደቀ መዛሙርትም በመጨረሻ ይህንኑ ለማስተዋል በቅተዋል::

*17+8!* ስለ ደቀ መዛሙርት ሦስት ጉዳዮች ተጠቅሰዋል፤ 1) እንደ ፈሪሳውያንና እንደ ሌሎቹ ሰምተው እምቢተኞች ሳይሆኑ፣ ትምህርቱን በሙሉ ልብ ተቀብለዋል፤ 2) የኢየሱስን ጥንተ መለኮትነት በእርግጠኝነት ዐውቀዋል፤ የተገለጠላቸውን በመቀበላቸውም እውነቱን ይበልጥ እንዲያውቁ ረድቶአቸዋል፤ 3) አምነዋል (የ1+7 ማብ ይመ፤ ከ1+12፤ 20+31 ጋር ያነጻጽሩ)::

17+11 *ቅዱስ አባት ሆይ፤* በአዲስ ኪዳን ውስጥ እዚህ ላይ ብቻ የሚገኝ አጠራር ነው (ሆኖም ከ1ጴጥ 1+15-16፤ ከራእ 4+8፤ 6+10 ጋር ያነጻጽሩ) እግዚአብሔር ግርማ ሞገሱ የሚያስፈራ እንዲሁም አፍቃሪ አምላክ መሆኑን ያመለክታል:: *እነርሱም አንድ እንዲሆኑ!* የጸሎቱ የመጨረሻ ክፍል 'በአንድነት ላይ ከፍተኛ ትኵረት ያደርጋል:: እዚህ ላይ አንድነቱ ቀድሞውኑ የተሰጠ እንጂ ወደፊት የሚገኝ አይደለም:: ትርጕሙም፣ 'አንድ እንዲሆኑ' ሳይሆን 'አንድ እንደ ሆኑ እንዲቀጥሉ' ማለት ነው:: አንድነቱም በአብና በወልድ መካከል እንዳለው አንድነት ዐይነት እንዲሆን ነው:: ይህም አንድነት ከድርጅት አንድነት እጅግ የላቀ ነው፤ እንግዲህ በአሁኑ ጊዜ የአብያተ ክርስቲያን ተከፋፍሎ መገኘት የክርስቲያኖች ድክመት ውጤት ነው::

17+12 *ጠበቅኋቸውም፤* የክርስቶስ ኀይል አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ለመጠበቅ ብቃት አለው:: *ከአንዱ ከጥፋት ልጅ በቀር፤* በሌላ አባባል 'የዓመፅ ሰው' ማለት ነው (2ተሰ

14 ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔ ከዓለም እንዳ
ልደለሁ፣ እነርሱም ከዓለም ባለመሆናቸው ዓለም
ጠልቶአቸዋል:: 15 የምለምንህም ከክፉው እን
ድትጠብቃቸው እንጂ፣ ከዓለም እን ድታወ
ጣቸው አይደለም:: 16 እኔ ከዓለም እንዳል
ሆንሁ ሁሉ፣ እነርሱም ከዓለም አይደሉም::
17 ቃልህ እውነት ነው፤ በእውነትህ ቀድሳ
ቸው[a]:: 18 አንተ ወደ ዓለም እንደ ላክኸኝ
እኔም ወደ ዓለም ልኬአቸ ዋለሁ:: 19 እነርሱ
በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ፣ ራሴን ስለ
እነርሱ ቀድሻለሁ::

## ኢየሱስ ለአማኞች ሁሉ ጸለየ

20 "የእነርሱን ትምህርት ተቀብለው በእኔ
ለሚያምኑ ጭምር እንጂ ለእነዚህ ብቻ አል
ጸልይም፤ 21 ይህም፣ አባት ሆይ፤ አንተ በእኔ፣
እኔም በአንተ እንዳለሁ ሁሉም አንድ እንዲ
ሆኑ፣ እንዲሁም አንተ እኔን እንደ ላክኸኝ ዓለም
ያምን ዘንድ፣ እነርሱም በእኛ እንዲሆኑ ነው::
22 እኛ አንድ እንደ ሆንን እነርሱም አንድ
እንዲሆኑ፣ የሰጠኸኝን ክብር ሰጥቻቸዋለሁ::
23 ይህም እኔ በእነርሱ፣ አንተም በእኔ መሆንህ
ነው:: አንተ እንደ ላክኸኝና እኔን በወደድኸኝ
መጠን እነርሱንም እንደ ወደድሃቸው ዓለም
ያውቅ ዘንድ፣ አንድነታቸው ፍጹም ይሁን::
24 "አባት ሆይ፤ እነዚህ የሰጠኸኝ፣ እኔ

17፥14 ቍ16፤ዮሐ 8፥23፤15፥19
17፥13 ቍ11፤ ዮሐ 3፥29
17፥15 ማቴ5፥37
17፥16 ቍ14
17፥17 ዮሐ15፥3፤ 2ሳሙ 7፥28፤ 1ነገ 17፥24
17፥18 ቍ3:8: 21:23:25፤ዮሐ3፥17፤ 20፥21
17፥19 ቍ17
17፥21 ቍ3:8: 11:18:23:25፤ኤር 32፥39፤ዮሐ፤3፥17፤ 10፥38
17፥22 ዮሐ1፥14፤ 14፥20፤
17፥23 ቍ3:8:21: 18:25፤ዮሐ3፥17፤ 16፥27፤
17፥24 ቍ2:5፤ ማቴ25፥34፤ዮሐ 1፥2:14፤ 12፥26
17፥25 ቍ3:8:18: 21:23፤ ዮሐ 3፥17፤ 15፥21፤ 16፥3:27
17፥26 ቍ6፤ ዮሐ 15፥9
18፥1 ቍ26፤ 2ሳሙ 15፥23፤ ማቴ21፥1፤ 26፥36
18፥2 ሉቃ21፥37፤ 22፥39

ባለሁበት እንዲሆኑ ዓለም ሳይፈጠር ስለ
ወደድኸኝ የሰጠኸኝንም ፥ክብሬን እንዲያዩ
እፈልጋለሁ::
25 "ጻድቅ አባት ሆይ፤ ዓለም ባያውቅህም፣
እኔ ዐውቅሃለሁ፤ እነዚህም አንተ እንደ ላክኸኝ
ያውቃሉ:: 26 ለእኔ ያለህ ፍቅር በእነርሱ እን
ዲሆን፣ እኔም በእነርሱ እንድሆን፣ አንተን
እንዲያውቁ[z] አድርጌአለሁ፤ እንዲያውቁህም
አደርጋለሁ::

## ኢየሱስ በተቃዋሚዎቹ መያዙ

18፥3-11 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥47-56፤ ማር 14፥43-50፤ ሉቃ 22፥47-53

18 ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ ከደቀ መዛ
ሙርቱ ጋር ሆኖ የቄድሮንን ሸለቆ
ተሻገረ፤ ማዶ ወደ ነበረውም የአትክልት ስፍራ
ገቡ::
2 ብዙውን ጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር በዚያ ስለሚገናኝ፣ አሳልፎ የሰጠው ይሁ
ዳም ቦታውን ያውቅ ነበር:: 3 ይሁዳም ወታ
ደሮችን እንዲሁም ከካህናት አለቆችና
ከፈሪሳውያን የተላኩ ሎሌዎችን እየመራ
ወደ አትክልቱ ስፍራ መጣ፤ እነርሱም ችቦ፣
ፋኖስና የጦር መሣሪያ ይዘው ነበር::

[a]17 በግሪኩ *ሀጊያዞ* የሚለው ቅዱስ ለሆነ ተግባር መለየት ወይም መቀደስ ማለት ነው፤ ቍ 19 ይመ

[z]26 በግሪኩ *ስምህን እንዲያወቁ* ይላል

2፥3)፤ ይኸውም ከጥፋት ወገን ሆኖ ለመጨረሻው ጥፋት የተመደበ ማለት ነው (እዚህ ላይ ግን ዕጣ ፈንታው ቀድሞውኑ የተወሰነ ነው የሚል ሐሳብ የለም)::

17፥13 *ደስታዬ*፤ የ15፥11 ማብ ይመ::

17፥14 *ዓለም*፤ የእግዚአብሔርና የክርስቲያኖች ተቃዋሚ የሆነው ሥርዓት ማለት ነው (የቍ5፤ 1፥9 ማብ ይመ):: *ከዓለም ባለመሆናቸው*፤ እግዚአብሔርን የሚጻረር ዓለማዊ የሆነ ልቡና የላቸውም ማለት ነው፤ ይህም የሆነው 'ከመንፈስ በመወለዳቸው' (3፥8)፣ 'የእግዚአብሔር ልጆችም' በመሆናቸው ነው (1፥12)::

17፥15 *ከዓለም እንድታወጣቸው አይደለም*፤ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሥራቸውን የሚሠሩት ዓለም ውስጥ ሆነው ነው፤ ያ ሥራ እስከሚከናወን ድረስ፣ ተከታዮቹ ከዓለም እንዲለዩ ኢየሱስ አይፈልግም (ቍ 18):: *ከክፉው*፤ በዓለም ውስጥ በተለየ መንገድ በመሥራት ላይ ያለና (1ዮሐ 5፥19)፣ የእግዚአብሔር ጥበቃ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳይ ነው::

17፥17 *ቀድሳቸው*፤ ለተለየ አገልግሎት መጠራትን ያመለክታል:: *ቃልህም…በእውነትህ*፤ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተጻፈው፣ የእግዚአብሔር ቃል በአንድ ሰው ሕይወት ሠራ ማለት ቅድስና እውን ሆነ ማለት ነው:: የክርስቶስ ትምህርት ከእውነት ጋር ስላለው ግንኙነት ከ8፥31-32 ጋር ያነጻጽሩ::

17፥18 *እንደ ላክኸኝ…ልኬአቸዋለሁ፤* በዚህ ወንጌል ውስጥ ዐበይት ከሆኑት ሐሳቦች አንዱ የኢየሱስ መላክ ነው፤ ይህም ሐሳብ ለተከታዮቹ አርአያ እንዲሆን ቀርቦአል:: *ወደ ዓለም*፤ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመሄድ ብንናፍቅም፣ ተልእኮ አችንን የምንወጣው በዚሁ በምድር ላይ ነው::

17፥19 *እነርሱ…የተቀደሱ እንዲሆኑ፤* ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተው ሊያድን ብቻ ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሊለየን ነው:: *ራሴን…ቀድሻለሁ፤* ይህ አባባል ከነባር አስተሳሰብ ጋር የሚጣጣም አይመስልም፤ ይሁን እንጂ ቃሉ በግሪኩ የብሉይ ኪዳን ትርጕም ውስጥ ሥልጣነ ክህነት ስለሚሰጣቸው ካህናትና (ዘፀ28፥41) ስለሚቀርበው መሥዋዕት (ዘፀ28፥38፤ ዘኍ18፥9) ተጽፎ ይገኛል:: ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ራሱን በትሕትና ለይቶ ቀርቦአል፤ ይህም ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ ማለት ነው::

17፥20 *በእኔ ለሚያምኑ፤* ኢየሱስ ስለ ተከታዮቹ ተልእኮና ቅድስና ተናግሮአል (ቍ18-19)፤ ወንጌሉንም እንደ ሚያሰራጩ እርግጠኛ ሆኖ፣ ወንጌሉ ደርሶአቸው ለሚያምኑት ይጸልይላቸዋል፤ ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ወደፊት ለሚያምኑትም ጸልዮላቸዋል::

17፥21 *አባት ሆይ*፤ የቍ 1 ማብ ይመ:: *ሁሉም አንድ እንዲሆኑ፤* የቍ 11 ማብ ይመ:: *ዓለም ያምን ዘንድ*፤ የአማኞች አንድ መሆን ዓለማውያን የክርስቶስን ተልእኮ እንዲቀበሉ ያደርጋል:: የኢየሱስ ጸሎት በክርስቲያኖች መካከል መሠረት ለሌለው ና መራር ጥላቻ ለሚያስከትለው መከፋፈል ተግሣጽ ነው::

17፥22 *ክብር፤* የቍ.1 ማብ ይመ:: ክርስቶስ ትሑትና ቅን አገልጋይ እንደ ነበረ ሁሉ፣ ተከታዮቹም በዚሁ ባሕርይ ይታወቃሉ፤ የእግዚአብሔርም ክብር የሚገለጸው በእንደዚህ ዓይነቶቹ ላይ ነው:: *እኛ አንድ እንደ ሆንን እነርሱም አንድ እንዲሆኑ፤* በአማኞች መካከል ሊኖር የሚገባውን አንድነት ጌታ በድጋሚ ትኩረት ሰጥቶታል:: በአብና በወልድ መካከል ያለው አንድነት አሁንም በአርአያነት ተጠቅሶአል::

17፥23 *እኔ በእነርሱ፣ አንተም በእኔ፤* ሁለት ዓይነት የአንድነት መልኮች ተገልጸዋል፤ አብና ወልድ አንድ ናቸው፤ ስለዚህም ከወልድ ጋር ኅብረት ያለው ሁሉ፣ ከአብም ጋር ኅብረት አለው:: *አንድነታቸው ፍጹም ይሁን*፤ አሁንም በአንድነት ላይ አጽንዖት መደረጉ፣ ወንጌልን የማዳረስ ተልእኮ አስፈላጊነት ያሳያል:: እዚህ ላይ አንድነቱ የተመለከተው ከኢየሱስ ተልእኮ ጋር ብቻ ሳይሆን (ቍ 21)፣ እግዚአብሔር ክርስቶስን በወደደው መጠን ለሰዎችም ካለው ፍቅር ጋር ነው::

17፥24 *አባት ሆይ*፤ የቍ 1 ማብ ይመ:: *እፈልጋለሁ፤* 'ይህን እፈቅዳለሁ' ማለት ነው:: 'እፈልጋለሁ' የሚለው ቃል ጌታ ለተከታዮቹ ያለውን የመጨረሻ ቃሉንና ኪዳኑን ያሳያል:: ስለ ራሱ ሲጸልይም፣ 'እኔ እንደምፈልግ ሳይሆን፣ አንተ እንደ ምትፈልግ ይሁን' አለ (ማር 14፥36) *እኔ ባለሁበት እንዲሆኑ፤* ክርስቶስን በማመን የምናገኘው በረከት ነው:: *ክብሬን*፤ እዚህ ላይ የኢየሱስን ዘላለማዊ ታላቅነትና ግርማ ለማመልከት ሊሆን ይችላል (1ዮሐ 3፥2):: በሌላም በኩል ኢየሱስ በትሕትና በፈጸመው አገልግሎት ወደ ፊት በሚመጣው ሕይወት የሚኖረውን ክብር እንዲያዩና እንዲያደንቁ መጸለዩ ሊሆን ይችላል (ከኤፌ 2፥7 ጋር ያነጻጽሩ)::

17፥25 *ጻድቅ አባት ሆይ*፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የዚህ ዓይነት አጠራር የሚገኘው እዚህ ላይ ብቻ ነው ከቍ11 ጋር ያነጻጽሩ:: *ያውቃሉ፤* እግዚአብሔርን በቀጥታና በግል አላወቁትም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ክርስቶስን እንደ ላከው ዐውቀዋል፤ በክርስቶስ ተልእኮ አማካይነት እግዚአብሔርን ማወቅ፣ ዓለም ሊደርስበት ከሚችለው ከማንኛውም ዕውቀት በላይ ነው::

18፥1 *የቄድሮንን ሸለቆ ተሻገረ*፤ ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ የሚገኝና በዝናብ ወራት ብቻ ጐርፍ የሚወርድበት ሸለቆ ነው::

18፥2-3 *ይሁዳም*፤ የ6፥71 ማብ ይመ:: *ከካህናት አለቆች*

4 ኢየሱስም የሚደርስበትን ሁሉ ዐውቆ
ወጣና፣ “የምትፈልጉት ማንን ነው?” አላቸው።
5 እነርሱም፣ “የናዝሬቱን ኢየሱስን” አሉት።
ኢየሱስም፣ “እርሱ እኔ ነኝ” አላቸው። አሳ
ልፎ የሰጠውም ይሁዳ ከእነርሱ ጋር ቆሞ
ነበር። 6 ኢየሱስም፣ “እርሱ እኔ ነኝ” ባለ ጊዜ
ወደ ኋላ አፈግፍገው መሬት ላይ ወደቁ።
7 እንደ ገናም፣ የምትፈልጉት ማንን ነው?
ሲል ጠየቃቸው።
እነርሱም፣ “የናዝሬቱን ኢየሱስን” አሉት።
8 ኢየሱስም መልሶ፣ “ ‘እርሱ እኔ ነኝ’ ብያ
ችኋለሁ እኮ፤ እኔን የምትፈልጉ ከሆነ፣ እነዚህ፣
ይሂዱ ተዉአቸው” አለ፤ 9 ይህ የሆነው፣
“ከሰጠኸኝ ከእነዚህ አንድም አልጠፋብኝም”
ብሎ የተናገረው ቃል እንዲፈጸም ነው።
10 ሰይፍ ይዞ የነበረው ስምዖን ጴጥሮስም፣
ሰይፉን መዞ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ቀኝ
ጆሮ ቈረጠ፤ የአገልጋዩም ስም ማልኮስ ይባል
ነበር።
11 ኢየሱስም ጴጥሮስን፣ “ሰይፍህን ወደ
ሰገባው መልስ! አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠ
ጣምን?” አለው።

## ኢየሱስ በሊቀ ካህናቱ በሐና ፊት ቀረበ

18፥12፡13 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥57

12 ወታደሮቹም ከአዛዣቸውና ከአይሁድ ሎሌ
ዎች ጋር በመሆን ኢየሱስን ያዙት፤ አስረ
ውም፣ 13 በመጀመሪያ፣ የቀያፋ አማት ወደ
ነበረው ወደ ሐና አመጡት፤ ቀያፋም የዓ
መቱ ሊቀ ካህናት ነበር። 14 ቀያፋም፣ ‘ለሕ

18፥3 ቍ12፤ ሐሥ1፥16
18፥4 ቍ7፤ ዮሐ6፥64፤13፥1፡11
18፥5 ማር1፥24
18፥7 ቍ4
18፥9 ዮሐ6፥39
18፥11 ማቴ 20፥22
18፥12 ቍ3
18፥13 ቍ24፤ ማቴ26፥3
18፥14 ዮሐ11፥49-51
18፥15 ማቴ26፥3፡58፤ማር14፥54፤ ሉቃ 22፥54
18፥17 ቍ25
18፥18 ማር14፥54፡67፤ዮሐ21፥9
18፥20 ማቴ4፥23፤ 26፥55፤ዮሐ7፥26

ዝቡ ሲባል አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል’ ብሎ
አይሁድን የመከረ ነበር።

## የጴጥሮስ ክህደት

18፥16-18 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥69፡70፤ ማር 14፥66-68፤ ሉቃ 22፥55-57

15 ስምዖን ጴጥሮስና አንድ ሌላ ደቀ መዝሙር
ኢየሱስን ተከተሉት። ይህም ደቀ መዝሙር
በሊቀ ካህናቱ ይታወቅ ስለ ነበር፣ ከኢየሱስ
ጋር ወደ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ገባ፤ 16 ጴጥሮስ
ግን ከበሩ ውጭ ቀረ። በሊቀ ካህናቱ የታወ
ቀው ሌላው ደቀ መዝሙርም ተመለሰና በር
ጠባቂዋን አነጋግሮ ጴጥሮስን ይዞት ገባ።
17 በር ጠባቂዋም ጴጥሮስን፣ “አንተ ከዚህ
ሰው ደቀ መዛሙርት አንዱ አይደለህምን?”
አለችው።
እርሱም፣ “አይደለሁም” አለ።
18 ብርድ ስለ ነበር አገልጋዮቹና ሎሌዎቹ
ባያያዙት የከሰል ፍም ዙሪያ ለመሞቅ ቆመው
ሳሉ፣ ጴጥሮስም ከእነርሱ ጋር ቆሞ እሳት
ይሞቅ ነበር።

## ኢየሱስ በሊቀ ካህናቱ ፊት መቅረቡ

18፥19-24 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥59-68፤ ማር 14፥55-65፤ ሉቃ 22፥63-71

19 በዚያን ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ኢየሱስን ስለ
ደቀ መዛሙርቱና ስለ ትምህርቱ ጠየቀው።
20 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “እኔ
ለዓለም በግልጽ ተናግሬአለሁ፤ አይሁድ በተሰ
በሰቡበት ምኵራብ፣ በቤተ መቅደስም ሁል
ጊዜ አስተምሬአለሁ፤ በስውር የተናገርሁት
የለም። 21 ለምን እኔን ትጠይቀኛለህ? የሰሙ

*እንዲሁም ከፈሪሳውያን የተላኩ ሎሌዎች*፤ ከአይሁድ ሸንጎ ከተላኩት ከቤተ መቅደስ ጠባቂዎች ጋር ተመሳሳይ ሥራ ያላቸው ናቸው። *ችቦ*፤ የሚነድ የጭራሮ እስር ነው። *ፋኖስ*፤ የዝናብና የነፋስ መከላከያ ያለው በዘይት የሚሠራ መብራት።

18፥4 *(በእርሱ) የሚደርስበትን ሁሉ አውቆ*፤ ኢየሱስ ሳያውቀው በድንገት አልተያዘም።

18፥5 *እኔ ነኝ፤* 6፥35፤ 8፥58 እና ማብ ይመ። *ከእነርሱ ጋር*፤ ይሁዳ ከእነማን ጋር አብሮ እንደ ነበር ዮሐንስ እንዳንዘነጋ ያደርገናል።

18፥6 *መሬት ላይ ወደቁ*፤ አመጣጣቸው ተራ ሰው ለመያዝ ነበር፤ በድንግዝግዝ ብርሃን ያጋጠማቸው ግን፣ ግርማ ሞገስ ያለው ሰው ነበር።

18፥8 *እኔ ነኝ፤* ሦስት ጊዜ ተደጋግሞአል (ቍ 5፡6፡8)፤ ይህም በረጋ መንፈስ የተነገረ ነበር። *እነዚህ፣ ይሂዱ ተዉአቸው*፤ ኢየሱስ ወደ ሞት በሚሄድበት ጊዜ እንኳ ለደቀ መዛሙርቱ ያስብ ነበር። ሊይዙት የመጡት ሰዎች የሚፈልጉት እርሱን እንደ ሆነ በግልጽ ሁለት ጊዜ እንዲናገሩ አድርጎአቸዋል (ቍ 4-5፡7)።

18፥9 *እንዲፈጸም*፤ አብዛኛውን ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመጥቀስ የሚገባ ቃል ነው፤ የኢየሱስ ቃልና የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል አንድ በመሆናቸው፣ ኢየሱስ ቀደም ብሎ በዚሁ መጽሐፍ የተናገረው ቃል እዚህ ላይ ሲፈጸም እንገነዘባለን፤ 6፥39 እንዲሁም 17፥12 ይመ።

18፥10 *ስምዖን ጴጥሮስም*፤ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ሰይፍ ይዞ የተገኘው ጴጥሮስ እንደ ሆነና ጆሮው የተቈረጠውም ሰው ማልኮስ ይባል እንደ ነበር የሚነግረን ዮሐንስ ብቻ ነው።

18፥11 *ጽዋ*፤ ብዙውን ጊዜ ሥቃይን (መዝ 75፥8፤ ሕዝ 23፥31-34)፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቍጣ ያመለክታል (ኢሳ 51፥17፡22፤ ኤር25፥15፤ ራእ14፥10፤ 16፥19)። *አብ የሰጠኝ*፤ ሦስቱም ወንጌሎች ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ባደረገው ጸሎት ውስጥ ‘ጽዋ’ የሚለውን ቃል ጠቅሰዋል (ማቴ 26፥39፤ ማር 14፥36፤ ሉቃ 22፥42)፤ የጽዋው አመጣጥ ከእግዚአብሔር አብ እንደ ሆነ ዮሐንስ ይናገራል፤ ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ አለ መሆኑንም ያሳያል።

18፥12 *አሰረውም*፤ ያሰሩበት ምክንያት ግልጽ አይደለም፤ ይሁን እንጂ በዘመናችን ማንኛውም ወንጀለኛ ሲያዝ እጁ እንደ ሚታሰር ሁሉ፣ በዚያን ጊዜም እንደዚያ መታሰሩ የተለመደ ሊሆን ይችላል።

18፥13 *ሐና*፤ ሮማውያን በ15 ዓ.ም. ከሊቀ ካህናትነቱ ሽረውት ነበር፤ ከሥልጣኑ ይውረድ እንጂ በሕዝቡ ዘንድ በሊቀ ካህናትነት ሥልጣኑ እንዳለ ሳይቈጠር አልቀረም። በአይሁድ ሕግ መሠረት አንድ ሰው በተከሰሰበት ዕለት ፍርድ አይፈጸምበትም። በዮሐንስ ብቻ የተወሳው ይኸኛውና ቀያፋ ፊት የቀረበበት ሁለቱ የክስ ምርመራዎች፣ አቀራረባቸው ለተፈጸመው ድርጊት የሕግ ሽፋን ለመስጠት ሳይሆን አይቀርም። *የዓመቱ ሊቀ ካህናት*፤ የ11፥49 ማብ ይመ።

18፥14 *ቀያፋም...አይሁድን የመከረ ነበር*፤ 11፥49-50 ይመ። ዮሐንስ ትልቅ ጉዳይ አድርጎ ያቀረበው፣ ቀያፋ ሳይታወቀው የተነበየውን ትንቢት ነው፤ ‘አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል’ በማለት አስቀድሞ ብያኔ ከሰጠ ሰው ትክክለኛ ፍርድ አይጠበቅም ማለቱም ሊሆን ይችላል።

18፥15 *አንድ ሌላ ደቀ መዝሙር*፤ ምናልባት ዮሐንስ ራሱ ሊሆን ይችላል። *በሊቀ ካህናቱ ይታወቅ ስለ ነበር*፤ ከአጋጣሚ ትውውቅ በላይ መሆኑን ያመለክታል፤ ወደ ሊቀ ካህናቱ ቤት መግባት ስለሚችል ጴጥሮስን ይዞት ገብቶአል።

18፥17 *በር ጠባቂዋ*፤ ጴጥሮስ የመጀመሪያው ፈተና የገጠመው ከተናቀች በር ጠባቂ ሴት እንደ ነበር አራቱም ወንጌሎች ይተርካሉ። አጠያየቋ በግሪኩ፣ ‘አይደለሁም’ የሚለውን መልስ የሚጋብዝ ነው። ጴጥሮስም ቀላሉን ማምለጫ መንገድ መረጠ። ሌሎች ወንጌሎች የቀሩትን የጴጥሮስ ክህደቶች በተከታታይ የተፈጸሙ አድርገው አቅርበዋቸዋል፤ ይሁን እንጂ በመካከሉ ሌሎች ነገሮች ሳይከናወኑ አልቀሩም (ሉቃ 22፥58-59)።

18፥18 *ጴጥሮስም ከእነርሱ ጋር ቆሞ...ነበር*፤ በዚያ ብርዳማ ሌሊት ሌሎች ካሉበት አካባቢ ከእሳቱ ርቆ ለብቻው ቢቆም ኖሮ በቀላሉ በታየ ነበር።

18፥19 *ጠየቀው*፤ ክስ ለመመሥረት በቅድሚያ ምስክሮች መገኘት ስለ ነበረባቸው ጥያቄው በአግባቡ አልቀረበም፤ ተከሳሽም ከቀረበበት ክስ ነጻ መሆኑን እንዲያረጋግጥ አይፈለግበትም፤

ኙን ጠይቃቸው፤ እነሆ፤ የተናገርሁትን እነርሱ
ያውቃሉ።"
22ኢየሱስ ይህን በተናገረ ጊዜ፣ አጠገቡ
ቆመው ከነበሩት ሎሌዎች አንዱ፣ "ለሊቀ
ካህናቱ የምትመልሰው እንዲህ ነውን?" ብሎ
በጥፊ መታው።
23ኢየሱስም፣ "ክፉ ተናግሬ ከሆነ ክፉ
መናገሬን መስክር፤ እውነት ከተናገርሁ ግን
ለምን ትመታኛለህ?" አለው። 24ሐናም ኢየ
ሱስ ታስሮ እንዳለ ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ
ቀያፋ ላከው።ʾ

### የጴጥሮስ ሁለተኛና ሦስተኛ ክህደት

18፥25-27 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥71-75፤ ማር 14፥69-72፤ ሉቃ 22፥58-62

25ስምዖን ጴጥሮስም ቆሞ እሳት ሲሞቅ፣
"አንተ ከእርሱ ደቀ መዛሙርት አንዱ አይ
ደለህምን?" አሉት።
እርሱም፣ "አይደለሁም" ሲል ካደ።
26ከሊቀ ካህናቱ አገልጋዮች አንዱ ጴጥሮስ
ጆሮውን የቈረጠው ሰው ዘመድ፣ "በአትክ
ልቱ ስፍራ አንተን ከእርሱ ጋር አላየሁህም?"
ሲል ጠየቀው። 27ጴጥሮስም እንደ ገና ካደ፤
ወዲያውም ዶሮ ጮኸ።

18፥22 ቊ3፤ ማቴ16፥21፤ዮሐ19፥3
18፥23 ማቴ5፥39፤ ሐሥ23፥2-5
18፥24 ቊ13፤ ማቴ26፥3
18፥25 ቊ17፡18
18፥26 ቊ1፡10
18፥27 ዮሐ13፥38
18፥28 ቊ33፤ ማቴ27፥2፤ዮሐ 11፥55፤19፥9
18፥32 ማቴ20፥19፤ 26፥2፤ዮሐ3፥14፤ 8፥28፤12፥32፡33
18፥33 ቊ28፡29፤ ማቴ2፥2፤ሉቃ23፥3፤ ዮሐ19፥9

### ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት

18፥29-40 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥11-18፡20-23፤ ማር 15፥2-15፤ ሉቃ 23፥2፡3፡18-25

28አይሁድም ኢየሱስን ከቀያፋ ወደ ሮማ
ዊው ገዥ ግቢ ይዘውት ሄዱ፤ ጊዜውም ማለዳ
ነበር። አይሁድም ፋሲካን መብላት እንዲችሉ፣
ላለመርከስ ወደ ገዥው ግቢ አልገቡም። 29ስለ
ዚህ ጲላጦስ ወደ እነርሱ ወጥቶ፣ በዚህ ሰው
ላይ የምታቀርቡት ክስ ምንድን ነው?" ብሎ
ጠየቃቸው።
30እነርሱም፣ "ይህ ሰው ወንጀለኛ ባይሆን
ኖሮ፣ አንተ ፊት ባላቀረብነውም ነበር" ብለው
መለሱለት።
31ጲላጦስም፣ "እናንተ ራሳችሁ ወስዳችሁ
በሕጋችሁ መሠረት ፍረዱበት" አላቸው።
አይሁድም፣ "እኛማ በማንም ላይ የሞት
ፍርድ ለመፍረድ መብት የለንም" አሉት።
32ይህ የሆነው በምን ዐይነት ሞት እንደ
ሚሞት ለማመልከት ሲል ኢየሱስ የተናገረው
ቃል እንዲፈጸም ነው።
33ጲላጦስም ወደ ግቢው ተመልሶ ኢየ
ሱስን አስጠራና፣ "አንተ የአይሁድ ንጉሥ
ነህን?" ብሎ ጠየቀው።
34ኢየሱስም፣ "ይህ ሐሳብ የራስህ ነው? ወይስ

ʾ24 *ወይም ሐናም ወደ ቀያፋ እንደታሰረ ላከው*

ምናልባት ሐና የክሱን አቀራረብ እንደ ክስ ሳይሆን፣ እንደ መጀመሪያ ምርመራ ቈጥሮት ይሆናል።

18፥20 *በግልጽ ተናግሬአለሁ፤* ምስክር ማግኘት አስቸጋሪ አልነበረም (ቊ 21)። *በስውር...የለም፤* ደቀ መዛሙርቱን በግል ማስተማሩን መካዱ ሳይሆን፣ በግልጽ ካስተማራቸው ትምህርት የተለየ የሚያስከስስ ትምህርት አለማስተማሩን መግለጹ ነበር።

18፥22 *መታው፤* ይህም ሌላው ሕገ ወጥ ድርጊት ነበር።

18፥23 *መስክር፤* የፍርድ ቤት ቋንቋ ሲሆን፣ በሕጉ መሠረት እንዲፈጸም የሚያሳስብ ነው። ዮሐንስ በወንጌሉ በብዙ ስፍራዎች የምስክርነትን አስፈላጊነት አበክሮ ያሳያል (የ1፥7 ማብ ይመ)።

*18፥24፤* በማር 14፥53-15፥15 ላለው ክፍል በተለይ እንደ መግቢያ የተሰጠውን ማብ ይመ።

18፥25 *አሉት፤* ቀጥታ ትርጕሙ 'ጠየቁት' ማለት ነው። ማቴዎስ በ26፥71 ላይ ይህን ጥያቄ ያቀረበችው ሌላዋ በር ጠባቂ እንደሆነች ሲናገር፣ ማርቆስ ደግሞ በ14፥69 ይህቺው በር ጠባቂ ሴት እንደ ሆነች ያሳያል፤ ሉቃስ ግን በ22፥58 ጥያቄውን ያቀረበው ወንድ እንደ ሆነ ያመለክታል፤ ስለዚህ አንዳንዶች ይህን ክፍል አስቸጋሪ ሆኖ አግኝተውታል። ይሁን እንጂ በእሳት ዙሪያ የተሰበሰቡ አገልጋዮች ሲነጋገሩ ሳለ፣ አንዳንዶቹ ጥያቄውን በመቀለብ ደግመው ተናግረው ሊሆን ይችላል፤ ዮሐንስም 'እነርሱ' ሲል ሊተረጉም የሚችለው በዚሁ መልክ ነው። እንደ መጀመሪያው ጥያቄ (ቊ17) ይኸኛውም ጥያቄ በግሪኩ 'አይደለሁም' የሚለውን መልስ የሚጋብዝ ነው። ምናልባትም አገልጋዮቹ በሊቀ ካህናቱ ግቢ ውስጥ የኢየሱስ ተከታይ ይገኛል ብለው አልጠበቁ ይሆናል፤ ጠጕረ ልውጥ የሆነውን ሰው ግን መጠየቅ አስፈላጊ መሰላቸው።

18፥26 *ዘመድ፤* ዝምድናውን የገለጸልን ዮሐንስ ብቻ ነው። በአትክልቱ ስፍራና በሊቀ ካህናቱ ግቢ የነበረው ብርሃን ደብዛዛ ቢሆንም፣ ከሌላ ሰው ይልቅ ዘመድ የሆነ ሰው ወገኑን የጎዳበትን ባለ ሰይፍ መከታተሉ የማይቀር ነው። *አላየሁህም?* የዚህም ጥያቄ አቀራረብ በግሪኩ፣ 'አዎን አይተኸኛል' የሚያሰኝ ነው።

18፥27 *ዶሮ ጮኸ፤* በ13፥38 የተነገረው ቃል መፈጸሙን የሚያመለክት ነው።

18፥28 *ማለዳ ነበር፤* የካህናት አለቆች ለሠሩት ሥራ የሕግ ሽፋን ለመስጠት ሲሉ ለሁለተኛ ጊዜ በማለዳ የሸንጎ ስብሰባ አድርገዋል (ማር 15፥1)። እንግዲህ ጌታን ወደ ጲላጦስ የወሰዱት ከዚሁ ስብሰባ በኋላ ከንጋቱ 12:00-1:00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር ማለት ነው። *ፋሲካን መብላት፤* ሌሎቹ ሦስቱ ወንጌሎች ኢየሱስ ከአንድ ቀን በፊት ፋሲካን እንደበላ ስለሚናገሩ፣ አይሁድ ገና ፋሲካ አልበሉም ማለት የሦስቱን ወንጌሎች ታሪክ መቃረን ይሆናል። 'ፋሲካ' የሚለውም ቃል የሚያመለክተው የቂጣ በዓልን ጨምሮ ሰባት ቀን ሙሉ የሚቆየውን በዓል ነው፤ ብዛት ያላቸው የፋሲካ ማዕዶችም በዚህ ወቅት ይቀርባሉ። *ላለመርከስ፤* በሥርዐታቸው መሠረት ወደ አሕዛብ መኖሪያ ከገቡ ስለሚረክሱ ነው። *ሮማዊው ገዥ፤* አይሁድ በኢየሱስ ላይ ስላቀረቡት የክስ ቅደም ተከተል ዮሐንስ የጻፈው በመጠኑ ነው፤ ነገር ግን ተከሶ በሮማውያን ፊት ስለ መቅረቡ ብዙ ጽፏል (የ18፥24 ማብ ይመ)። በዚህ ጊዜ ዮሐንስ በገዥው መኖሪያ ግቢ በተደረገው ችሎት ላይ ተገኝቶ ሊሆን ይችላል።

18፥29 *ጲላጦስ፣* ሮማዊ ገዥ ሲሆን (የማር 15፥1 ማብ ይመ)፣ ለአይሁድ ሥርዐት አክብሮት የሚሰጥ ሰው ነበር። *የምታቀርቡት ክስ ምንድን ነው?* ክስ ሲቀርብ በቅድሚያ ሊነሣ የሚችል ጥያቄ ነው። አይሁድ ግን በሮም የሕግ ችሎት ሊቀርብ የሚችል ክስ ስላልነበራቸው መልስ መስጠቱ አስቸጋሪ ሆኖባቸዋል።

18፥31 *እናንተ ራሳችሁ ወስዳችሁ፤* ይህ አባባል የሚያሳየው፣ ክሱ ኢየሱስን ለሮም የሕግ ችሎት የሚያደርስ እንዳልነበረ ነው። *በማንም ላይ የሞት ፍርድ ለመፍረድ መብት የለንም፤* የአይሁድ ሸንጎ፣ በራሱ ሕግ መሠረት የሞት ፍርድ መፍረድ ይችላል፤ ነገር ግን ፍርዱ ተፈጻሚነት የሚኖረው የሮም ባለሥልጣናት ሲያጸድቁት ብቻ ነው። የፈለጉት ፍትሕን ሳይሆን፣ ሞቱን ብቻ ነበር። ይህን የመሰለ የሥልጣን ገደብ ባይኖር ኖሮ፣ የሮም መንግሥት ደጋፊዎች በአገሬው ተወላጆች ሞት እየተፈረደባቸው በቀላሉ በተወገዱ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ግን የሮም ገዥዎች በተወላጆቹ የሚበየነውን የሞት ፍርድ የደገፉ ይመስላል (ለምሳሌ፣ የእስጢፋኖስ ሞት፣ ሐሥ7)። ይሁን እንጂ፣ ብዙውን ጊዜ የሞትን ፍርድ ተፈጻሚ የሚያደርጉት ራሳቸው የሮም ባለሥልጣናት ብቻ ነበሩ።

18፥32 *በምን ዓይነት ሞት እንደሚሞት፤* ከ12፥32-33 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም በ12፥34 ላይ 'አለበት' ከሚለው ሐሳብ ጋር ያነጻጽሩ። በአይሁድ ሕግ የሞት ፍርድ የሚፈጸመው በድንጋይ በመውገር ነበር፤ የኢየሱስ ሞት የተፈጸመው ግን ርግማንን በተሸከመበት በመስቀል ላይ ነው (ዘዳ 21፥22-23)። በኢየሱስ ላይ የመስቀል ሞት በመፍረድ የገደሉት አይሁድ ሳይሆኑ ሮማውያን ናቸው፤ ይህም፣ ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ እግዚአብሔር ጠቅላላውን ሁኔታ መቈጣጠሩን ያሳያል (3፥14)።

18፥33 *አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን?* ጲላጦስ በመጀመሪያ ለኢየሱስ የሰነዘረው ጥያቄ ሲሆን፣ በአራቱም ወንጌሎች

ሌሎች ስለ እኔ የነገሩህ?" ሲል መለሰለት::
35ጲላጦስም መልሶ፣ "እኔ አይሁዳዊ ነኝን?
ወደ እኔ የላኩህ የራስህ ወገኖችና የካህናት
አለቆች ናቸው፤ ለመሆኑ ምን አድርገህ ነው?"
አለው::
36ኢየሱስም፣ "የእኔ መንግሥት ከዚህ ዓለም
አይደለም፤ ቢሆንማ ኖሮ አይሁድ እንዳይዙኝ
ሎሌዎቼ በተከላከሉልኝ ነበር፤ አሁን ግን
መንግሥቴ ከዚህ አይደለም" አለው::
37ጲላጦስም፣ "ታዲያ፣ ንጉሥ ነህ ማለት
ነዋ!" አለው::
ኢየሱስም፣ "እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ መና
ገርህ ትክክል ነው፤ የተወለድሁት፣ ወደዚህም
ዓለም የመጣሁት ስለ እውነት ለመመስከር
ነው፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ይሰማኛል" አለው::
38ጲላጦስም፣ "እውነት ምንድን ነው?" አለው፤
ይህን ከተናገረ በኋላም እንደ ገና ወደ አይሁድ
ወጥቶ እንዲህ አላቸው፤ "እኔ የሚያስከስስ
በደል አላገኘሁበትም፤ 39ነገር ግን በፋሲካ
አንድ እስረኛ እንድፈታላችሁ ልማድ አላችሁ፤
ስለዚህ፣ 'የአይሁድን ንጉሥ' እንድፈታላችሁ
ትፈልጋላችሁን?"
40እነርሱም እንደ ገና በመጮኽ፣ "የለም፤
እርሱን አይደለም! በርባንን ፍታልን!" አሉ::
በርባን ግን ወንበዴ ነበረ::

### ኢየሱስ እንዲሰቀል ተፈረደበት

19፥1-16 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥27-31፤ ማር 15፥16-20

**19** ጲላጦስም ኢየሱስን ወስዶ አስገረፈው::
2ወታደሮችም የእሾህ አክሊል ጐንጒነው
በራሱ ላይ አደረጉ፤ ሐምራዊ ልብስም አለበ
ሱት፤ 3እየተመላለሱም፣ "የአይሁድ ንጉሥ
ሆይ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን" እያሉ በጥፊ ይመቱት
ነበር::
4ጲላጦስም እንደ ገና ወደ ውጭ ወጥቶ፣
"እንግዲህ ወደ እናንተ ያወጣሁት ለክስ
የሚያደርስ ወንጀል እንዳላገኘሁበት እንድ
ታውቁ ነው" አላቸው:: 5ኢየሱስ የእሾህ አክ
ሊል ደፍቶ ሐምራዊ ልብስም ለብሶ ወጣ፤
ጲላጦስም፣ "እነሆ፤ ሰውየው!" አላቸው::
6የካህናት አለቆችና ሎሌዎቻቸውም ባዩት
ጊዜ፣ "ስቀለው! ስቀለው!" እያሉ ጮኹ::
ጲላጦስ ግን፣ "እናንተ ወስዳችሁ ስቀሉት፤
በእኔ በኩል ለክስ የሚያደርስ ወንጀል አላገ
ኘሁበትም" አላቸው::
7አይሁድም፣ "እኛ ሕግ አለን፤ ራሱን የእግ
ዚአብሔር ልጅ ስላደረገ በሕጋችን መሠረት
መሞት አለበት" አሉ::
8ጲላጦስ ይህን ሲሰማ የባሰውኑ ፈራ፤ 9ወደ
ግቢው ተመልሶ ኢየሱስን፣ "ከየት ነው የመ
ጣኸው?" በማለት ጠየቀው፤ ኢየሱስ ግን ምንም
አልመለሰለትም:: 10ጲላጦስም፣ "አታናግረኝምን?
ልፈታህ ወይም ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ
አታውቅም?" አለው::
11ኢየሱስም፣ "ከላይ ባይሰጥህ ኖሮ በእኔ
ላይ ሥልጣን ባልኖረህ ነበር፤ ስለዚህ ለአንተ
አሳልፎ የሰጠኝ ሰው የባሰ ኀጢአት አለበት"
አለው::
12ከዚያ በኋላ ጲላጦስ ኢየሱስን ሊፈታው
ፈለገ፤ አይሁድ ግን፣ "ይህን ሰው ብትፈታው
የቄሣር ወዳጅ አይደለህም፤ ራሱን ንጉሥ

18፥36 ማቴ3፥2፤ 26፥53፤ሉቃ17፥21፤ ዮሐ6፥15
18፥37 ዮሐ3፥32፤ 8፥47፤1ዮሐ 4፥6
18፥38 ሉቃ23፥4
18፥40 ሐሥ3፥14
19፥1 ዘዳ25፥3፤ ኢሳ50፥6፤53፥5፤ ማቴ27፥26
19፥3 ማቴ27፥29፤ ዮሐ18፥22
19፥4 ቁ6፤ሉቃ 23፥4፤ዮሐ 18፥38
19፥5 ቁ2
19፥6 ቁ4፤ሉቃ 23፥4፤ሐሥ3፥13
19፥7 ዘሌ24፥16፤ ማቴ26፥63-66፤ ዮሐ5፥18፤10፥33
19፥9 ማር14፥61፤ ዮሐ18፥33
19፥11 ዮሐ18፥ 28-30፤ሐሥ3፥13፤ ሮሜ13፥1
19፥12 ሉቃ23፥2

በተመሳሳይ መልክ የቀረበ ነው:: ገና ሲያየው፣ ጲላጦስ 'ኢየሱስ ዓመፀኛ ወንጀለኛ ነው' የሚለው ክስ ሆን ተብሎ በተቃዋሚዎች የተፈጠረ መሆኑን በቀላሉ መገመት በቻለ ነበር::

18፥34 *ይህ ሐሳብ የራስህ ነው?* በቁ33 ላይ የተሰነዘረው ጥያቄ ከራሱ ከጲላጦስ የመነጨ ከሆነ፣ ያ ጥያቄ፣ 'አንተ በምንግሥት ላይ የምታምፅ ነህን?' የሚለውን ሐሳብ ይጋብዛል፤ ነገር ግን የጥያቄው አመጣጥ ከአይሁድ ከሆነ፣ 'አንተ መሲሑ ንጉሥ ነህን?' የሚለውን ሐሳብ ያመለክታል::

18፥36 *የእኔ መንግሥት፤* ኢየሱስ መንግሥት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤ ነገር ግን መንግሥቱ በወታደር ኀይል የታነጸ እንዳልሆነ ግልጽ አድርጎአል፤ በወታደር ኀይል አልተመሠረተም፤ በመሣሪያም ብዛት አልጸናም::

18፥37 *ስለ እውነት ለመመስከር ነው፤* በዚህ ወንጌል ውስጥ ሁለቱ ዐበይት ጕዳዮች 'እውነት' እና 'ምስክርነት' ናቸው (1፥7 እና ማብ፣ የ1፥14 ማብ 14፥6 ይመ)::

18፥38 *እውነት ምንድን ነው?* ጲላጦስ በማፌዝ፣ 'እውነት ምን ይጠቅማል?' ማለቱ ሊሆን ይችላል፤ ወይም በቅንነት፣ 'እውነትን ማግኘት ቀላል አይደለምና እውነት ምንድን ነው?' ማለቱ ሊሆን ይችላል:: በዚያም ሆነ በዚህ ኢየሱስ ዐመፀኛ እንዳልሆነ ለጲላጦስ ግልጽ ነበር:: *እኔ የሚያስከስስ በደል አላገኘሁበትም፤* እውነትን ማስተማር ከሕግ ውጪ መሆን አይደለም (ቁ 37)፤ ጲላጦስም የተረዳው ይህንኑ ነበር::

18፥39 *ልማድ አላችሁ፤* በሌሎችም አገሮች በትልቅ በዓል ቀን እስረኛ ይፈታ እንደ ነበር የታወቀ ነው:: *የአይሁድን ንጉሥ፤* ዮሐንስ የኢየሱስን ንጉሥነት አሁንም በአጽንዖት ይጠቅሳል:: ጲላጦስ የኢየሱስን ንጉሥነት ማጕላቱ፣ እርሱ ራሱ ወዳሰበው የመፍታት ውሳኔ ሕዝቡ ይመራል ብሎ ሳያስብ አልቀረም::

18፥40 *በርባን፤* ወንበዴና ነፍሰ ገዳይ ነበር (ሉቃ23፥19):: ስሙ በአራማይክ ቋንቋ ሲሆን፣ ትርጕሙ፣ 'የአባ ወይም የአባት ልጅ' ማለት ነው:: በዚህም ሰው ምትክ፣ 'የአብ ልጅ' ሞተ::

*19፥1፤* ጲላጦስ የግርፋት ቅጣት ሲወስን፣ ቅጣቱ በአይሁድ ዘንድ እርካታን አስገኝቶ ኢየሱስን ለመፍታት የሚያስችለው መስሎት ነበር (የማር 15፥15 ማብ ይመ)::

19፥2 *እሾህ፤* ማንኛውንም እሾኻማ ተክል የሚያመለክት አጠቃላይ ቃል ነው:: *ሐምራዊ፤* ነገሥታትና ቤተ ሰቦቻቸው የሚለብሱት ቀላ ያለ የልብስ ዓይነት ነበር::

19፥6 *እናንተ...ስቀሉት፤* አይሁድ አንድን ሰው በመስቀል ላይ እንዲሞት መፍረድ እንደማይችሉ እያወቀ እንዲህ ማለቱ፣ በነገሩ መሰላቸቱን ያመለክታል:: *ለክስ የሚያደርስ ወንጀል፤* ኢየሱስ ከወንጀል ነጻ መሆኑን ጲላጦስ ለሦስተኛ ጊዜ ገለጸ (18፥38፤ 19፥4፤ እንዲሁም ሉቃ 23፥4:14:22 ይመ::)

19፥7 *መሞት አለበት፤* የጠቀሱት የቅጣት ዓይነት የእግዚአብሔርን ስም በመሰደብ የሚበየነውን ነው (ዘሌ24፥16)::

19፥8 *የባሰውኑ ፈራ፤* ጲላጦስ የፈራው፦ (1) ምናልባት የሕዝብ ዐመፅ ተነሥቶ አይሁድን መቈጣጠር ቢሳነው ከሮም ገዥዎች የሚከተለውን መዘዝ፣ (2) አማልክትን የሚፈራ ሰው ስለ ነበር (ቁ9፤ ማቴ27፥24)፣ የኢየሱስን ማንነት ከእነርሱ ጋር በማያያዝ ሊሆን ይችላል::

19፥9 *ኢየሱስ ግን ምንም አልመለሰለትም፤* ምክንያቱ ግልጽ አይደለም፤ ይሁን እንጂ ቀደም ብሎ ኢየሱስ ሌሎቹን ጥያቄዎች መልሶለታል፤ በዚህ ጊዜ ዝምታን የመረጠው፣ ምናልባት ጲላጦስ መልሱን ሊረዳ ወይም ሊያምን ስለማይችል ይሆናል::

19፥10 *ሥልጣን እንዳለኝ፤* ጲላጦስ ለሥልጣኑ የሚያስብ ሥጉ ሰው ነበር፤ ሁለተኛው ጥያቄው እርሱ ለኢየሱስ መስቀል ተጠያቂ እንደ ሆነ ያሳያል::

*19፥11፤* ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ ለጲላጦስ የመለሰው ቃል ነበር:: *ከላይ፤* በዓለም ላይ ያለ ሥልጣን ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተሰጠ ነው (ሮሜ13፥1):: *የባሰ ኀጢአት አለበት፤* አልፎ ለመስጠቱ መሣሪያ የሆነውን ይሁዳን ሳይሆን፣ ቀያፋን ለማመ ልከት የተሰነዘረ ነው:: 'የባሰ' የሚለውም ቃል፣ ኀጢአት የእስ ከፊ ደረጃ እንዳለው ያመለክታል፤ ስለዚህ ጲላጦስም

የሚያደርግ የቄሣር ተቃዋሚ ነው” በማለት
ጩኸታቸውን ቀጠሉ::
13 ጲላጦስም ይህን ሲሰማ ኢየሱስን ወደ
ውጭ አወጣው፤ ‘የድንጋይ’ ንጣፍ በተባለ፣
በአራማይክ ቋንቋ ‘ገበታ’ ብለው በሚጠሩት
ስፍራ፣ በፍርድ ወንበር ላይ ተቀመጠ። 14 ቀኑ
የፋሲካ በዓል መዘጋጀ፣ ጊዜውም ከቀኑ
ስድስት ሰዓት ያህል ነበር::
ጲላጦስም አይሁድን፣ “እነሆ ንጉሣችሁ!”
አላቸው::
15 እነርሱ ግን፣ አስወግደው! አስወግደው!
ስቀለው!” እያሉ ጮኹ::
ጲላጦስም፣ “ንጉሣችሁን ልስቀለውን?” አለ።
የካህናት አለቆችም፣ “ከቄሣር በቀር ሌላ
ንጉሥ የለንም” ብለው መለሱለት::
16 በመጨረሻም ጲላጦስ እንዲሰቅሉት አሳ
ልፎ ሰጣቸው::

## ስቅለት

19፥17-24 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥33-44፤ ማር 15፥22-32፤ ሉቃ 23፥33-43

ወታደሮቹም ኢየሱስን ይዘው ወሰዱት፤
17 እርሱም የራሱን መስቀል ተሸክሞ በአራ
ማይክ ‘ጎልጎታ’ ተብሎ ወደሚጠራው ‘የራስ
ቅል’ ወደ ተባለው ቦታ ወጣ:: 18 በዚያም ሰቀ
ሉት፤ ከእርሱም ጋር ሁለት ሰዎች፣ አንዱን
በዚህ በኩል፣ ሌላውን በዚያ በኩል ኢየ
ሱስንም በመካከል አድርገው ሰቀሉ::

19፥13 ማቴ27፥19፤ ዮሐ5፥2
19፥14 ቊ19:21 ማቴ27፥62፤ ማር 15፥25
19፥16 ማቴ27፥26፤ ማር15፥15፤ሉቃ23፥25
19፥17 ዘፍ22፥6፤ ሉቃ14፥27፤23፥33፡ 26፤ዮሐ5፥2
19፥18 ሉቃ23፥32
19፥19 ቊ14:21፤ ማር1፥24
19፥20 ዕብ13፥12
19፥21 ቊ14
19፥24 ቊ28:36፡ 37፤መዝ22፥18፤ ማቴ1፥22
19፥25 ማቴ12፥46፤ 27፥55:56፤ሉቃ8፥ 2፤ዮሐ20፥1:18

19 ጲላጦስም ጽሑፍ ጽፎ በመስቀሉ ላይ
አንጠለጠለው፤ ጽሑፉም፣ ‘የናዝሬቱ ኢየሱስ፣
የአይሁድ ንጉሥ’ የሚል ነበር:: 20 ኢየሱስ የተሰ
ቀለበት ቦታ ከከተማው አጠገብ ስለ ነበር
ብዙዎቹ አይሁድ ጽሑፉን አነበቡት፤ ጽሑ
ፉም፣ በአራማይክና በላቲን፣ በግሪክም ነበር::
21 የአይሁድ የካህናት አለቆች ጲላጦስን
በመቃወም፣ “እርሱ፣ ‘የአይሁድ ንጉሥ ነኝ’
እንዳለ ጻፍ እንጂ ‘የአይሁድ ንጉሥ’ ብለህ
አትጻፍ” አሉት::
22 ጲላጦስም፣ “በቃ፤ የጻፍሁትን ጽፌአለሁ”
ብሎ መለሰ::
23 ወታደሮቹ ኢየሱስን ከሰቀሉ በኋላ፣ እጀ
ጠባቡ ሲቀር፣ ልብሱን ወስደው ለእያንዳንዱ
አንድ አንድ እንዲዳረስ ለአራት ተከፋፈ
ሉት፤ እጀ ጠባቡም ከላይ እስከ ታች አንድ
ወጥ ሆኖ ያለ ስፌት የተሠራ ነበር::
24 ስለዚህ፣ “ዕጣ ተጣጥለን ለሚደርሰው
ይድረስ እንጂ አንቅደደው” ተባባሉ:: ይህም
የሆነው፣
“ልብሴን ተከፋፈሉት፤
በእጀ ጠባቤም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ” የሚለው
የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም ነው::
ወታደሮቹ ያደረጉትም ይህንኑ ነው::
25 በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱና የእ
ናቱ እኅት፣ እንዲሁም የቀልዮጳ ሚስት
ማርያምና መግደላዊት ማርያም ቆመው ነበር።

---

በእርግጥ ኀጢአተኛ ነበር ማለት ነው::

19፥12 *የቄሣር ወዳጅ አይደለህም*፤ አንዳንድ ሰዎች፣ ‘የቄሣር ወዳጆች’ የሚል በይፋ የሚታወቅ ማዕረግ ነበራቸው፤ እዚህ ላይ የገባው ግን በተራ ትርጕሙ ነው:: ጲላጦስ ኢየሱስን ቢፈታው፣ ቄሣር ፊት ክስ እንደሚቀርብበት ሁኔታው ያመለክታል:: ከዚህ በፊት ከነበረው ታሪኩ ሲታይም፣ ‘የቄሣር ወዳጅ አይደለህም’ የሚለውን ማስፈራሪያ ችላ ለማለት የሚበቃ ሰው አይደለም::

19፥13 *የድንጋይ ንጣፍ*፤ ‘ገበታ’ የሚለው የአራማይክ ቃል ትርጕም ‘የቤት ኮረብታ’ እንደ ማለት ሲሆን፤ ይህኛው ግን ለዚሁ ቦታ የተሰጠ ሌላ መጠሪያ ነው እንጂ፣ ከዚህ ስም ትርጕም ጋር የተያያዘ አይደለም::

19፥14 *ቀኑ …መዘጋጀ*፤ በተለመደው ሥርዐት፣ ሰዎች ለዕለተ ሰንበት የሚዘጋጁበት ቀን ዓርብ ዕለት ነበር፤ እዚህ ላይ ግን በፋሲካው ሳምንት ዋዜማ የዋለውን ዓርብ ለማለት ነው:: *ስድስት ሰዓት ያህል*፤ ማር 15፥25 ኢየሱስ ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ላይ እንደ ተሰቀለ ይናገራል:: በግሪክ አጻጻፍ የሦስት ቍጥርና የስድስት ቍጥር ቅርጽ ሊያሳስት ስለሚችል፣ በማርቆስ ወንጌል የሰፈረው የሰዓት አቈጣጠር ጽሑፉ ሲገለበጥ የተከሠተ የቀም ጸሓፊ ግድፈት ሊሆን ይችላል:: በሌላም በኩል ዮሐንስ የመዘገበው የሮማውያኑን የሰዓት አቈጣጠር ተከትሎ ሊሆን ይችላል፤ ይኸውም፣ ኢየሱስ ተከሶ ጲላጦስ ፊት የቀረበው ከንጋቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት (በሮማውያን ስድስት ሰዓት) ሲሆን፣ የተሰቀለውም ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት (በሮማውያኑ ዘጠኝ ሰዓት) ማለት ነው:: *አይሁድ*፤ የ1፥19 ማብ ይመ:: *እነሆ ንጉሣችሁ!* ዮሐንስ የኢየሱስን የበላይ ገዥነት እንድንዘነጋ አይሻም:: ጲላጦስ ይህን የተናገረው ከልብ ባይሆንም፣ ዮሐንስ ግን ኢየሱስ ንጉሥ መሆኑን አበክሮ ይገልጻል::

19፥15 *ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም*፤ በሮም መንግሥት ላይ የተነሡ ዐመፀኞች ላለመባል፣ መለኮታዊ ንጉሣቸውን ካዱ::

19፥17 *የራሱን መስቀልን ተሸክሞ*፤ አንድ መስቀል በተለያየ መልክ ወይም አሁን ባለው ዓይነት ቅርጽ ሊሠራ ይቻላል:: የተፈረደበትም ሰው የሚሰቀልበትን እንጨት እስከ መሰቀያው ቦታ ድረስ ተሸክሞ ይሄዳል:: ኢየሱስ መስቀሉን ተሸክሞ ሲጓዝ፣ የቀሬናው ስምዖን መስቀሉን በመሸከም አግዞታል፤ ይህም ኢየሱስ ከግርፋቱ የተነሣ ስለ ደከመ ሳይሆን አይቀርም:: *ጎልጎታ*፤ በአራማይክ ቋንቋ ‘የራስ ቅል’ ማለት ሲሆን፣ በግሪክ ‘ቀራንዮ’ (የማር 15፥22 ማብ እና ሉቃ 23፥33 ይመ):: በላቲን ‘ካልቨሪ’ ይባላል::

19፥18 *ሰቀሉት*፤ የማር 15፥24 ማብ ይመ:: ዮሐንስም ይህን አሠቃቂ ሁኔታ የገለጸው በአንድ የግሪክ ቃል ነው፤ የትኞቹም የወንጌል ጸሓፊዎች ኢየሱስ በሥጋው የተቀበለውን መከራ በጥልቀት አልገለጹም:: *አንዱን በቀኝ ሌላውን በግራ ጎን*፤ በዚህ መልክ የሰቀሉት የመጨረሻው ውርደት እንዲደርስበት አስበው ሊሆን ይችላል፤ እነርሱ ለጕዳት ያድርጉት እንጂ፣ ኢየሱስ በሁለቱ ሰዎች መካከል መሰቀሉ፣ “በሞቱ ከኀጢአተኞች ጋር ተቈጠረ” የሚለው ትንቢት መፈጸሙን ያረጋግጣል::

19፥19 *ጽሑፍ*፤ የወንጀለኛውን በደል የሚገልጽ ሰሌዳ በተሰቀለው ሰው መስቀል ራስጌ ይንጠለጠል ነበር:: *የአይሁድ ንጉሥ*፤ ‘ንጉሥ’ የሚለው ቃል አሁንም መሪ ሐሳብ ሆኖ ቀርቦአል::

19፥20 *አራማይክ*፤ አይሁድ ከዕብራይስጥ ጎን ለጎን ይነጋገሩባቸው ከነበሩት ቋንቋዎች አንዱ ነው:: *ላቲን*፤ የሮም መንግሥት ቋንቋ ነበር:: *ግሪክ*፤ በሮም ግዛት ሁሉ የጋራ መግባቢያ ቋንቋ ነበር:: ተንጠልጣዩ ጽሑፍ በሦስቱ ቋንቋዎች መጻፉ፣ በአራቱ ወንጌሎች መካከል ለሚታየው መለስተኛ የቃላት አገባብ ልዩነት አስተዋፅኦ ሳያደርግ አልቀረም::

19፥22 *ጲላጦስ*፣ ኢየሱስ እንዲሰቀል ሲፈርድ በቂ ምክንያት ሊኖረው ይገባል፤ ስለዚህ እንደዚያ ማለቱ በአይሁድ መቀለዱ አልነበረም፤ በሐሳቡም መጽናቱ፣ የኢየሱስ ንጉሥነት የመጨረሻውና የማይሻር መሆኑን ለማስገንዘብ ዮሐንስ ሳይረዳው አልቀረም::

19፥23 *እጀ ጠባብ*፤ ቅዱ እንደ ሸሚዝ ሆኖ፣ ከአንገት እስከ ጕልበት ወይም እስከ ቁርጭምጭሚት የሚደርስ ልብስ ነው:: *ያለ ስፌት የተሠራ*፤ ልብሱ አንድ ወጥ በመሆኑ ቀደው ሊካፈሉት አላመቻቸውም::

19፥24 በመዝ 22 የሰፈረው ሐሳብ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ ከነበረው ሁኔታ ጋር እጅግ የሚመሳሰል ነው:: ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ ያሰማው ቃል በዚሁ መዝሙር በመጀመሪያው ክፍል ላይ ሰፍሮ ይገኛል:: ወንጌል ጸሓፊዎቹ፣ በተለይም ማቴዎስና ዮሐንስ፣ ኢየሱስ በዚህ ወቅት የተናገረውን ከመዝ 22 ጋር አዛምደዋል:: በመዝ 22፥17 ‘አጥንቶቼ ሁሉ ተቈጠሩ’ ሲል፣ ወንበዴዎች ዳዊትን አግኝተው ልብሱን መግፈፋቸውን ማለቱ ሊሆን ስለሚችል፣ እዚህ ላይ ‘ልብሱን ተከፋፈሉት ከሚለው ጋር

26በዚያም ኢየሱስ እናቱንና የሚወ ደውም
ደቀ መዝሙር አጠገቧ ቆሞ ሲያያቸው እና
ቱን፣ "አንቺ ሴት ሆይ፤ ልጅሽ ይኸው"
አላት፤ 27ደቀ መዝሙሩንም፣ "እናትህ ይህ
ችው" አለው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ
ደቀ መዝሙር ወደ ቤቱ ወሰዳት::

### የኢየሱስ መሞት

19፥29-30 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥48-50፤ ማር 15፥36-37፤ ሉቃ 23፥36

28ከዚያም ኢየሱስ ሁሉ ነገር እንደ ተፈ
ጸመ ዐውቆ፣ የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም፣
"ተጠማሁ" አለ:: 29በዚያም የሆመጠጠ ወይን
የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር፤ እነርሱም ሰፍነግ
በወይን ጠጅ ነክረው፣ በሂሶጵ ዘንግ ወደ
አፉ አቀረቡለት፤ 30ኢየሱስም ሆምጣጤውን
ከተቀበለ በኋላ፣ "ተፈጸመ" አለ፤ ራሱን አዘ
ንብሎ፣ መንፈሱን አሳልፎ ሰጠ::
31ዕለቱ ለሰንበት መዘጋጃ ቀን ነበር::
አይሁድ፣ የተሰቀሉት ሰዎች ሬሳ በሰንበት
ቀን በመስቀል ላይ እንዳይውል ስለ ፈለጉና
ያም የተለየ ሰንበት ስለ ነበር፣ የተሰቀሉት
ሰዎች ጭናቸው ተሰብሮ በድናቸው እንዲ
ወርድ ጲላጦስን ለመኑት:: 32ስለዚህም ወታደ
ሮቹ መጥተው ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሎ የነበ
ረውን የመጀመሪያውን ሰው ጭን ሰበሩ፤
ደግሞም የሌላውን ጭን ሰበሩ:: 33ወደ ኢየ
ሱስ በመጡ ጊዜ ግን ሞቶ ስላገኙት ጭኖቹን
አልሰበሩም፤ 34ነገር ግን ከወታደሮቹ አንዱ
የኢየሱስን ጐን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም
ደምና ውሃ ፈሰሰ:: 35ይህን ያየው ሰው ምስ

19፥26 ማቴ12፥46፤ ዮሐ13፥23
19፥28 ቊ24:30: 36:37፤ ማቴ1፥22፤ ዮሐ13፥1
19፥29 መዝ69፥21
19፥30 ሉቃ12፥50፤ ዮሐ4፥34፤17፥4
19፥31 ቊ14:42፤ ዘዳ21፥23፤ኢሱ8፥29፤ 10፥26:27
19፥32 ቊ18
19፥34 ዘካ12፥10፤ 1ዮሐ5፥6:8፤ራእ1፥7
19፥35 ሉቃ24፥48፤ ዮሐ15፥27፤21፥24
19፥36 ቊ24:28: 37፤ዘፀ12፥46፤ዘኍ 9፥12፤መዝ34፥20፤ ማቴ1፥22
19፥37 ዘካ12፥10፤ ራእ1፥7
19፥38 ዮሐ7፥13
19፥39 ዮሐ3፥1፤ 7፥50
19፥40 ማቴ26፥12፤ ሉቃ24፥12፤ዮሐ11፥ 44፤20፥5:7
19፥42 ቊ14:31: 20:41

ክርነቱን ሰጥቶአል፤ ምስክርነቱም እውነት
ነው፤ እውነትን እንደሚናገርም ያውቃል፤ እና
ንተም እንድታምኑ ይመሰክራል:: 36ይህም
የሆነው፣ መጽሐፍ፣ "ከአጥንቱ አንድም አይ
ሰበርም" ያለው እንዲፈጸም፣ 37ሌላውም መጽሐፍ፣
"የወጉትም ያዩታል" ስለሚል ነው::

### የኢየሱስ መቀበር

19፥38-42 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥57-61፤ ማር 15፥42-47፤ ሉቃ 23፥50-56

38ከዚህ በኋላ የአርማትያሱ ዮሴፍ የኢየ
ሱስን በድን ለመውሰድ ጲላጦስን ለመነው፤
ዮሴፍም አይሁድን ስለ ፈራ በስውር የኢ
የሱስ ደቀ መዝሙር ነበር:: እርሱም ጲላጦ
ስን ካስፈቀደ በኋላ መጥቶ በድኑን ወሰደ::
39ከዚህ ቀደም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ
የነበረው ኒቆዲሞስ አንድ መቶ ሊትር[ሠ] ያህል
የሚመዝን የከርቤና የእሬት ቅልቅል ይዞ
መጣ:: 40እነርሱም የኢየሱስን በድን ወስደው
እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ ሽቱ ቀብተው
ከተልባ እግር በተሠራ ጨርቅ ከፈኑት::
41ኢየሱስ በተሰቀለበት ቦታም የአትክልት
ስፍራ ነበር፤ በአትክልቱም ስፍራ ማንም ያል
ተቀበረበት አዲስ መቃብር ነበር:: 42ዕለቱ
ለአይሁድ የሰንበት መዘጋጃ ቀን ስለ ነበርና
መቃብሩም ቅርብ ስለ ሆነ ኢየሱስን በዚያ
ቀበሩት::

[ሠ]39 ሠላሳ አራት ኪሎ ግራም ያህል ነው

ይገናኛል::

19፥25 *ቀልዮጳ*፤ በአዲስ ኪዳን በዚህ ስፍራ ብቻ የተጠቀሰ ስም ነው፤ በሉቃ 24፥18 ከተጠቀሰው 'ቀለዮጳ' ጋር አንድ አይደለም:: *መግደላዊት ማርያም*፤ በአራቱም ወንጌሎች፣ በስቅለቱና በትንሣኤው ትረካ ውስጥ ትገኛለች፤ በተረፈ ግን ስለ እርሷ የተጻፈው በሉቃስ 8፥2-3 ላይ ብቻ ነው::

19፥26 *የሚወደውም ደቀ መዝሙር*፤ የ13፥23 ማብ ይመ::

19፥27 *ወደ ቤቱ ወሰዳት*፤ ዮሐንስ፣ ማርያምን ለመንከባከብ ኀላፊነቱን ወሰዶአል ማለት ነው::

19፥28 *ተጠማሁ፤* ከመዝ 69፥21 ጋር ሊጣቀስ ይችላል (ከመዝ 22፥15 ጋር ያነጻጽሩ)::

19፥29 *የሆመጠጠ ወይን ጠጅ*፤ ተራ ሰዎች የሚጠጡት፣ መናኛ የወይን ጠጅ ነበር:: *ሰፍነግ*፤ በመስቀል ላይ የተሰቀለን ሰው ለማጠጣት አመች የሆነ፣ እንደ ስፖንጅ ፈሳሽን የሚመጥ ነገር ነው:: *ሂሶጵ*፤ ከዕፅዋት ስም አንዱ ነው:: ቀጥ ያለ ቁመት፣ ነጭ አበባና ጥሩ መዓዛ ያለው ተክል ነው፤ ጠጕራም በሆነው ቅጠሉና ቅርንጫፎቹ ፈሳሽ ነገር ለመቋጠር በመቻሉ፣ በመንጻት ሥርዐት ጊዜ ደም ለመርጨት በሚገባ ያገለግል ነበር (ዘፀ12፥22)::

19፥30 *ተፈጸመ*፤ በማቴ 27፥50፤ በማር 15፥37 የተገለጸው ታላቅ ድምፅ መሆን አለበት:: ኢየሱስ የሞተው የመጣበትን ተልእኮ በአሸናፊነት ከፈጸመ በኋላ ነው:: *ነፍሱንም አሳልፎ ሰጠ፤* ይህ አባባል ከተለመደው የአሟሟት አገላለጽ የተለየ ነው፤ ምናልባትም፣ ኢየሱስ በገዛ ፈቃዱ መሞቱን ያሳያል (10፥18)::

19፥31 *መዘጋጃ፤* የቊ 14 ማብ ይመ:: *አይሁድ*፤ የ1፥19 ማብ ይመ:: *የተለየ ሰንበት*፤ የፋሲካ በዓል የዋለበት ሰንበት ለማለት ነው:: የፋሲካ እራት ሐሙስ ማታ ተበልቶአል፤ የመዘጋጃ ቀን ዓርብ ነበረ፤ ሰንበትም ቅዳሜ ቀን ነው:: *ጭናቸው ተሰብሮ...*፤ እንዲህ ሲደረግ የተሰቀለው ሰው የሰውነቱን ክብደት መሸከም ስለማይችልና መተንፈስ አስቸጋሪ ስለሚሆንበት፣ ሞቱን ያፋጥነዋል::

*19፥34 የኢየሱስን ጎን...ወጋው*፤ የኢየሱስን መሞት ለማወቅ ተጨማሪ ማረጋገጫ ወይም የጭካኔ ተግባር ሊሆን ይችላል (ቊ 37፤ ኢሳ 53፥5፤ ዘካ 12፥10 ይመ፤ ከመዝ 22፥16 ጋር ያነጻጽሩ):: *ደምና ውሃ፤* አተረጓጐሙ ሊለያይ ቢችልም፣ ወንጌላዊው በአጽንዖት የመሰከረው የሚያጠራጥር አይደለም፤ ታምራዊ በሆነ መልኩ የደምና የውሃው መፍሰስ ድኅነትንና መንጻትን ያመለክታል (ከ1ዮሐ 5፥7-8 ጋር ያነጻጽሩ)::

19፥35 *ያየው ሰው*፤ ዮሐንስ ራሱ ነው:: ድርጊቱ ዐቢይና የተረጋገጠ መሆኑን ያመለክታል:: *እንድታምኑ ይመሰክራል*፤ የ1፥7 ማብ ይመ::

19፥36-37 *መጽሐፍ*፤ የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ እግዚአብሔር በማናቸውም ነገር ላይ ሥልጣን እንዳለው ዮሐንስ በድጋሚ ያሳያል:: ከተሰቀሉት ከሦስቱ፣ የኢየሱስ ጭን ብቻ አለመሰበሩና ከተለመደው ውጭ ጎኑን በጦር መወጋቱ ሁኔታውን ልዩ ያደርገዋል::

19፥38 *የአርማትያሱ፤* የማቴ27፥57 ማብ ይመ:: *ዮሴፍ*፤ ብዙ ሀብት የነበረው የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ሲሆን (ማቴ 27፥57)፣ የስቅለት ፍርድ በኢየሱስ ላይ ሲፈረድበትም፣ ከብዙኀኑ ጋር ያልተባበረ የአይሁድ ሸንጎ አባል ነበረ (ሉቃ23፥51):: *በስውር*፤ የአይሁድ ሸንጎ አባል ለነበረ ሰው የኢየሱስን ትምህርት በይፋ መደገፉ ቀላል አልነበረም:: የኢየሱስ የቅርብ ተከታዮች እንኳ ሸሽተው ስለ ነበር (ማር14፥50)፣ ከዮሴፍና ከኒቆዲሞስ በቀር መቃብሩን የሚያዘጋጅ ማንም አልነበረም:: *ጲላጦስን ካስፈቀደ በኋላ፤* ማስፈቀድ ያስፈለገው፣ የተሰቀሉ ወንጀለኞች መሞታቸው ሳይረጋገጥ ቢወሰዱ ነፍስ ሊዘሩ ስለሚችሉ ነው::

19፥39 *ኒቆዲሞስ፤* ይህ ሰው ኢየሱስ ሲቀበር ከዮሴፍ ጋር እንደ ነበር ያመለከተው ዮሐንስ ብቻ ነው:: *ሠላሳ አራት ኪሎ ግራም*፤ ብዙ ገንዘብ የፈሰሰበትና ለንጉሣውያን ቤተ ሰብ የመግነዝ ሥርዐት የሚደረገውን ዓይነት ነው (ከ 2ዜና 16፥14 ጋር ያነጻጽሩ)::

19፥40 *ከተልባ እግር በተሠራው ጨርቅ*፤ እንደ ፋሻ ያለ መጠቅለያ ነው፤ በሌሎች ወንጌሎች ግን እንደ ደበላ ያለ ትልቅ መከፈኛ እንደ ሆነ ተገልጾአል (ማቴ 27፥59፤ ማር 15፥46፤ ሉቃ 23፥53)::

19፥41 *አዲስ መቃብር*፤ ዮሴፍ ለራሱ ያዘጋጀው መቃብር ነበር (ማቴ 27፥60)::

## ኢየሱስ ከሞት ተነሣ

20፥1-8 ተጓ ምብ - ማቴ 28፥1-8፤ ማር 16፥1-8፤ ሉቃ 24፥1-10

20 በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን፣ በማለዳ
ገና ጨለማ ሳለ፣ መግደላዊት ማርያም
ወደ መቃብሩ ሄደች፤ ድንጋዩም ከመቃ
ብሩ መግቢያ ተንከባሎ አየች። 2ስለዚህም
ወደ ስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ይወደው ወደ
ነበረው ሌላው ደቀ መዝሙር እየሮጠች
መጥታ፣ "ጌታን ከመቃብር አውጥተው ወስደ
ውታል፤ የት እንዳኖሩትም አናውቅም" አለ
ቻቸው።
3"ከዚያም ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር
ወጥተው ወደ መቃብሩ ሄዱ። 4ሁለቱም
ይሮጡ ነበር፤ ሌላው ደቀ መዝሙርም ጴጥ
ሮስን ቀድሞት ከመቃብሩ ደረሰ። 5ጐንበስ
ብሎ ሲመለከት ከተልባ እግር የተሠራውን
ከፈን በዚያው እንዳለ አየ፤ ወደ መቃብሩ
ግን አልገባም። 6ይከተለው የነበረው ስምዖን
ጴጥሮስ ደረሰና ወደ መቃብሩ ገባ፤ እርሱም
ከተልባ እግር የተሠራውን ከፈን አየ፤ 7እን
ዲሁም በኢየሱስ ራስ ላይ ተጠምጥሞ የነበ
ረውን ጨርቅ አየ፤ ይህም ጨርቅ ከከፈኑ
ተለይቶ እንደ ተጠቀለለ ነበር። 8ከዚያም
አስቀድሞ ከመቃብሩ የደረሰው ሌላው ደቀ
መዝሙር ወደ ውስጥ ገባ፤ አይቶም አመነ፤
9ይኸውም ኢየሱስ ከሙታን መነሣት እንዳ
ለበት ገና ከመጽሐፍ ስላልተረዱ ነበር።

## ኢየሱስ ለመግደላዊት ማርያም ታየ

10ከዚያም በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው
ወደየቤታቸው ሄዱ፤ 11ማርያም ግን ከመቃብሩ
ውጭ ቆማ ታለቅስ ነበር፤ እያለቀሰችም መቃ
ብሩን ለማየት ጐንበስ አለች። 12የኢየሱስ
ሥጋ በነበረበት ቦታ፣ ነጫጭ ልብስ የለበሱ
ሁለት መላእክት አንዱ በራስጌ ሌላው በግርጌ
ተቀምጠው አየች።
13እነርሱም፣ "አንቺ ሴት፤ ለምን ታለቅ
ሻለሽ?" ብለው ጠየቋት።
እርሷም፣ "ጌታዬን ወስደውታል፤ የት እን
ዳኖሩትም አላውቅም" አለች። 14ይህን ብላ
ዘወር ስትል ኢየሱስ በዚያው ቆሞ አየች፤
ኢየሱስ መሆኑን ግን አላወቀችም።
15እርሱም፣ "አንቺ ሴት፤ ለምን ታለቅሻለሽ?
ማንንስ ትፈልጊአለሽ?" አላት።
እርሷም የአትክልቱ ቦታ ጠባቂ መስሎ
አት፣ "ጌታዬ፤ አንተ ወስደኸው ከሆነ፣ እባ
ክህ እንድወስደው፣ የት እንዳኖርኸው ንገ
ረኝ" አለችው።
16ኢየሱስም፣ "ማርያም" አላት።
እርሷም፣ ወደ እርሱ ዘወር ብላ በአራማይክ
ቋንቋ፣ "ረቡኒ!" አለችው፤ ትርጒሙም
"መምህር ሆይ" ማለት ነው።
17ኢየሱስም፣ "ገና ወደ አብ ስላላረግሁ፣
አትንኪኝ፤ ይልቁንስ ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ፣
'ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላኬና
ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ' ብሎአል ብለሽ
ንገሪያቸው" አላት።
18መግደላዊት ማርያምም፣ ወደ ደቀ መዛ
ሙርቱ መጥታ፣ "ጌታን እኮ አየሁት!" አለች፤
እርሱ ያላትንም ነገረቻቸው።

20፥1 ቊ18፤ሉቃ 8፥2፤ማቴ27፥60፡66፤ ዮሐ19፥25
20፥2 ቊ13 ዮሐ13፥23፤
20፥3 ሉቃ24፥12
20፥5 ቊ11፤ ዮሐ19፥40
20፥7 ዮሐ11፥44
20፥8 ቊ4
20፥9 ሉቃ24፥26፡46፤ሐሥ2፥24፤ማቴ 22፥29፤ዮሐ2፥20
20፥11 ቊ5
20፥12 ማቴ28፥2፡3፤ ማር 16፥5፤ሉቃ24፥4፤ ሐሥ1፥10፤5፥19፤ 10፥30
20፥13 ቊ2፡15
20፥14 ማር16፥9፤ ሉቃ24፥16፤ ዮሐ 21፥4
20፥15 ቊ13
20፥16 ማቴ23፥7፤ ዮሐ5፥2
20፥17 ማቴ28፥10፤ ዮሐ7፥33
20፥18 ቊ1፤ሉቃ 24፥10፡22፡23

19፥42 *መዘጋጃ፤* የቊ 14 ማብ ይመ። *ቅርብ፤* ጀንበር አቈልቍላ፣ ሰንበት ገብቶ ሥራ የማይሠራበት ሰዓት ስለ ደረሰ፣ አቅራቢያ ላይ ወደሚገኘው መቃብር ቶሎ መውሰዱ አስፈላጊ ነበር።

20፥1 *ገና ጨለማ ሳለ፤* ማርቆስ፣ 'ጠዋት ማለዳ ላይ' ይላል (ማር 16፥2)። ዮሐንስ ሴቶቹ ከቤት የተነሡበትን ጊዜ ሲጠቅስ፣ ማርቆስ ደግሞ መቃብሩ ቦታ የደረሱበትን ማመልከቱ ይሆናል። *መግደላዊት ማርያም፤* የ19፥25 ማብ ይመ፤ ከማር 16፥9 ጋር ያነጻጽሩ። *ሄደች፤* ብቻዋን እንዳልሄደች ሌሎቹ ወንጌሎች ያመለክታሉ (ማቴ 28፥1፤ ማር 16፥1፤ ሉቃ 23፥55-24፥1)፤ ዮሐንስ ግን እዚህ ላይ መግደላዊት ማርያምን ብቻ አጕልቶ ይሳያል።

20፥2 *ወደ ስምዖን ጴጥሮስ፤* ክህደት የታየበት ሰው ቢሆንም፣ ከደቀ መዛሙርት መካከል ጐልቶ ይታይ የነበረው ጴጥሮስ ነው። *ኢየሱስ ይወደው ወደ ነበረው፤* የ13፥23 ማብ ይመ። *አናውቅም (እኛ)፤* ከማርያም ጋር ሌሎች ሴቶች እንደ ነበሩ ያመለክታል (ማቴ28፥1፤ ማር16፥1፤ ሉቃ24፥10)፤ ዮሐንስ ግን እነማን እንደ ሆኑ አልገለጸም። *እንዳኖሩትም፤* ማርያም በዚያ ወቅት ስለ ትንሣኤ አለመገንዘቧን ያሳያል።

20፥7 *እንደ ተጠቀለለ፤* የተከፈነበት ጨርቅ አቀማመጥ መቃብሩን ሌባ እንደ በረበረው ዓይነት ሳይሆን፣ በሥርዐት መቀመጡን ያመለክታል፤ ይህም የትንሣኤውን ታምር ያሳያል።

20፥8 *አይቶም አመነ፤* ከቊ 29 ጋር ያነጻጽሩ። ዮሐንስ እዚህ ላይ የሚገልጸው የራሱን እምነት ሳይሆን የኢየሱስን ትንሣኤ እውነትነት ነው።

20፥9 *መነሣት እንዳለበት፤* በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በትንቢት ተነግሮ ነበር፤ ስለዚህ ትንሣኤው በእግዚአብሔር ፈቃድ የተፈጸመ ነው። *መጽሐፍ፤* ስለ ትንሣኤው በመጀመሪያ ለማወቅ የቻሉት መቃብሩንና በመቃብሩ ውስጥ የነበረውን ሁኔታ በማየት ነው፤ መጽሐፍ ያለውን ለመረዳት የቻሉት ግን ከጊዜ በኋላ ነው። የመጽሐፉን የትንቢት ቃል ቀደም አድርገው በመረዳት፣ ከመጽሐፉ ትንቢት ጋር የሚገጥም የትንሣኤ ትረካ እንዳልፈጠሩ የታወቀ ነው።

20፥11 *ማርያም፤* ኢየሱስ በመጀመሪያ የተገለጠው ለመግደላዊት ማርያም ነው፤ ይኸውም በዚያን ጊዜ በጣም አዝና ስለ ነበር ሊሆን ይችላል። *ታለቅስ ነበር፤* በ11፥33 እንደ ተጻፈው ድምፅ በማሰማት የሚደረግ ዋይታ ማለት ነው።

20፥12 *ሁለት መላእክት፤* ማቴዎስ የጻፈው አንድ መልአክ ብሎ ነው (ማቴ 28፥2)፤ ማርቆስ አንድ ወጣት ሲል (ማር 16፥5)፣ ሉቃስ ደግሞ የሚያንጸባርቅ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ይላል (ሉቃ 24፥4፡23)። የሉቃ 24፥4 ማብ ይመ።

20፥14 *ኢየሱስ መሆኑን ግን አላወቀችም፤* ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ፣ ብዙውን ጊዜ ሰዎች ማንነቱን አላወቁም ነበር (21፥4 ማቴ 28፥17፤ ሉቃ 24፥16፡37)። መልኩ ድሮ ከነበረው የተለየ ሆኖ በመታየቱ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ሆን ብሎ ማንነቱ እንዳይታወቅ አድርጎ ይሆናል። በሌላም በኩል ይነሣል የሚል ሐሳብ ጨርሶ እንዳልነበራት ያሳያል።

20፥16 *ማርያም፤* የእርሱ የሆኑት ድምፁን ይሰማሉ (ከ10፥3-4 ጋር ያነጻጽሩ)። *ረቡኒ፤* ቃሉ አራማይክ ሲሆን፣ 'ረቢ' (መምህር) የሚለው ቃል የራስ መሆንን የሚያሳይ ነው። በግሪኩ አዲስ ኪዳን ውስጥ ከዚህኛው በተጨማሪ ሌላ ቦታ የሚገኘው በማርቆስ ወንጌል ብቻ ነው (ማር 10፥51)። ቃሉ 'መምህሬ' (የእኔ አስተማሪ) ማለት ቢሆንም፣ በጥንት የአይሁድ እምነት በጸሎት ውስጥ እግዚአብሔርን ለመጥራት ካልሆነ፣ ሰውን ለመጥራት የዋለበት ሁኔታ አለ ለማለት አያስደፍርም። ይሁን እንጂ የዮሐንስ አገላለጽም ማርያም ኢየሱስን በአምላክነቱ ጠራችው ለማለት አያስችልም።

20፥17 *ገና...ስላላረግሁ፤* ሊያርግ ጥቂት ጊዜ እንደ ቀረው የሚያመለክት ይመስላል። *አትንኪኝ፤* ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ካልሆነ በቀር (16፥5-16 ይመ)፣ ከትንሣኤ በኋላ ማርያም እንደ ተለመደው ልትቀርበው እንደማትችል ማሳሰቡ ይሆናል። *ወንድሞቼ፤* ደቀ መዛሙርቱን ማለት ነው (ከቊ 18፤ ከማቴ 12፥50፤ ከዕብ 2፥11-18 ጋር ያነጻጽሩ)። *ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፤* እግዚአብሔር ለክርስቶስም ለአማ

## ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ታየ

19በዚያኑ ዕለት፣ በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን
በምሽት፣ ደቀ መዛሙርቱ አይሁድን በመ
ፍራት በሮቹን ቈልፈው ተሰብስበው ሳለ፣
ኢየሱስ መጣና በመካከላቸው ቆሞ፣ "ሰላም
ለእናንተ ይሁን" አላቸው:: 20ይህንም ብሎ
እጆቹንና ጐኑን አሳያቸው፤ ደቀ መዛሙርትም
ጌታን ባዩት ጊዜ እጅግ ደስ አላቸው::
21ኢየሱስም እንደ ገና፣ "ሰላም ለእናንተ
ይሁን፤ አብ እኔን እንደ ላከኝ፣ እኔም እና
ንተን እልካችኋለሁ" አላቸው:: 22ይህን ካለ
በኋላም፣ እፍ አለባቸውና እንዲህ አላቸው፤
"መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ 23የሰዎችን ኀጢአት
ይቅር ብትሉ፣ ኀጢአታቸው ይቅር ይባልላ
ቸዋል፤ ኀጢአታቸውን ይቅር ባትሉ ግን፣
ይቅር አይባልላቸውም::"

## ኢየሱስ ለቶማስ ታየ

24በዚህ ጊዜ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ የሆነው፣
ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ፣ ኢየሱስ በመጣ
ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አልነበረም::
25ሌሎች ደቀ መዛሙርትም፣ "ጌታን አየነው
እኮ!" አሉት::
እርሱ ግን፣ "በምስማር የተቸነከሩትን የእ
ጆቹን ምልክቶች ካላየሁ፣ ምስማሮቹ በነበሩ
በት ቦታ ጣቴን ካላደረግሁ፣ በጐኑም
እጄን ካላስገባሁ አላምንም" አለ::
26ከስምንት ቀን በኋላም፣ ደቀ መዛሙርቱ
በቤት ውስጥ ነበሩ፤ ቶማስም ከእነርሱ ጋር
ነበር፤ በሮቹ ተቈልፈው ነበር፣ ኢየሱስ ግን
መጥቶ በመካከላቸው ቆመና፣ "ሰላም ለእናንተ
ይሁን" አላቸው:: 27ከዚያም ቶማስን፣ "ጣትህን
ወደዚህ አምጣ፤ እጆቼንም ተመልከት፤ እጅህን
ዘርጋና በጐኔ አስገባ፤ አትጠራጠር፤ እመን"
አለው::
28ቶማስም፣ "ጌታዬ፤ አምላኬም!" አለው::
29ኢየሱስም፣ "አንተ ስላየኸኝ አምነሃል፤
ሳያዩ የሚያምኑ ግን ብፁዓን ናቸው" አለው::
30ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፉ ሌሎች
አያሌ ታምራዊ ምልክቶችን በደቀ መዛሙርቱ
ፊት አድርጓል፤ 31ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ
ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ ሆነ እንድ
ታምኑ[ጭ]፣ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ሕይ
ወት እንዲኖራችሁ ይህ ተጽፎአል::

## ደቀ መዛሙርቱ ዓሣ በታምር መያዛቸው

21 ከዚያም በኋላ ኢየሱስ በጥብርያዶስ
ባሕር[*] እንደ ገና ለደቀ መዛሙርቱ
ታየ፤ በዚህም ሁኔታ ተገለጠ 2ስምዖን
ጴጥሮስ፣ ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ፣ የቃና
ዘገሊላው ናትናኤል፣ የዘብዴዎስ ልጆችና
ከደቀ መዛሙርቱ ሌሎች ሁለት አንድ ላይ
ነበሩ፤ 3ስምዖን ጴጥሮስም፣ "ዓሣ ላጠምድ
መሄዴ ነው" አላቸው፤ እነርሱም፣ "እኛም ከአ
ንተ ጋር እንሄዳለን" አሉት:: ወጥተውም ወደ
ጀልባዋ ገቡ፤ በዚያ ሌሊት ግን ምንም አላጠ
መዱም::
4ሲነጋም፣ ኢየሱስ በባሕሩ ዳርቻ ቆመ፤
ደቀ መዛሙርቱ ግን ኢየሱስ መሆኑን አላወቁም
ነበር::

ጭ31 አንዳንድ ቅጆች *በማመን እንድትድኑ* ይላሉ
*1 የገሊላ ባሕር ማለት ነው

20+19 ቊ21:26፤ ሉቃ24+36-39፤ ዮሐ7+13፤14+27
20+20 ሉቃ24+39:40፤ዮሐ16+20:22፤ 19+34
20+21 ቊ19፤ማቴ 28+19፤ዮሐ3+17፤ 17+18
20+22 ዮሐ7+39፤ ሐሥ2+38፤8+15-17፤19+2፤ገላ 3+2
20+23 ማቴ16+19፤ 18+18
20+24 ዮሐ11+16
20+25 ቊ20፤ ማር16+11
20+26 ቊ21፤ ዮሐ14+27
20+27 ቊ25፤ ሉቃ24+40
20+29 ዮሐ3+15፤ 1ጴጥ1+8
20+30 ዮሐ2+11፤ 21+25
20+31 ማቴ4+3፤ 25+46፤ዮሐ3+15፤ 19+35
21+1 ቊ14፤ዮሐ 6+1፤20+19:26
21+2 ማቴ4+21፤ ዮሐ1+45፤2+1፤ 11+16
21+3 ሉቃ5+5
21+4 ሉቃ24+16፤ ዮሐ20+14

ኞችም አባት ነው፤ ይሁን እንጂ አብ የአማኞች አባት የሆነው፣ ለወልድ የባሕርይ አባቱ በሆነው መልኩ ሳይሆን፣ በእምነት ስለ ተቀበሉት በጸጋ ነው (1+12:14:18:34 ይመ)::

20+19 *ደቀ መዛሙርቱ፡* ከ 'ዐሥራ ሁለቱ' ሐዋርያት (ቊ 24) በተጨማሪ ሌሎቹን አማኞች ሳይመለከት አይቀርም:: *አይሁድ፡* የ1+19 ማብ ይመ:: *ሰላም ለእናንተ ይሁን፡* የተለመደ የዕብራውያን ሰላምታ መግለጫ ነው (ከዳን 10+19 ጋር ያነጻጽሩ):: ደቀ መዛሙርት የስቅለት ዕለት ትተውት ሸሽተው ስለ ነበር፣ ይገሥጸናል፤ ይወቅሰናልም ብለው አስበው ነበር፤ ኢየሱስ ግን አረጋጋቸው (የ14+27 ማብ ይመ)::

20+20 *እጆቹንና ጐኑን፡* ቊስሉ የት ላይ እንደ ነበር አሳያቸው ማለት ነው:: ዮሐንስ የኢየሱስን የእግር ቊስል አልጠቀሰም:: ደቀ መዛሙርቱ፣ በሉቃስ 24+37 እንደ ተጻፈው፣ መንፈስ የታያቸው መሰላቸው፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ የተወጋውን ቦታ ቊስሉን በማሳየት ማንነቱን ገለጸላቸው::

20+21 *ሰላም ለእናንተ ይሁን፡* የቊ 19 ማብ ይመ:: *እልካችኋለሁ፤* የ17+18 ማብ ይመ::

20+22 *መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤* ይኸኛው ከኀምሳ ቀን በኋላ በጰንጠቆስጤ ቀን (ሐሥ 2) ከሚሆነው፣ የተለየ በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን መሞላት ነው፤ ደቀ መዛሙርቱ የተቀበሉትን አደራ ለመፈጸም የእግዚአብሔር ርዳታ ያስፈልጋቸዋል::

20+23 ቀጥታ ትርጕሙ፣ 'ኀጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ይቅር ተብለዋል፤ ይቅር ያላላችኋቸው ይቅር አልተባሉም' ማለት ነው:: ሆኖም የቃሉ ፍሬ ሐሳብ እኛ እንዲሁ ይቅር ስላልን እግዚአብሔር የሰዎችን ኀጢአት ይቅር ይላል ወይም እንዲሁ ይቅር ስላላልንም ይቅርታ አያደርግም ማለት አይደለም:: ወንጌልን የሚያስተምሩ ሁሉ ኀጢአትን ይቅር የሚሉበትና የማይሉበት ሁኔታ እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል፤ ይኸውም የወንጌልን ትምህርት የሰሙት ሰዎች ልባቸውን ለክርስቶስ ቢያመቻቹ ኀጢአታቸው ይቅር ይባላል፤ ካላመቻቹም ኀጢአታቸው ይቅር አይባልም ማለት ነው:: ኀጢአትን ይቅር ማለት የሚችል ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው (ማር 2+7)::

20+24 *ቶማስ፡* የ11+16 ማብ ይመ::

20+25 *ካላየሁ... ካላስገባሁ አላምንም፡* ከፍተኛ ጥርጣሬ ያለው ሰው ከዚህ ዓይነት አቋም ብዙም ርቆ አይሄድም::

20+26 *ሰላም፡* ቊ 19 እና 21፤ እንዲሁም የ14+27 ማብ ይመ::

20+28 *ጌታዬ፤ አምላኬም!* የኢየሱን አምላክነት የሚያሳይ ከፍተኛ የእምነት መግለጫ ነው (የ1+1 ማብ ይመ)::

20+29 *ሳያዩ የሚያምኑ፤* በዚህ ጊዜ ጌታን ሳያዩ ያመኑት ጥቂት መሆን አለባቸው፤ ዮሐንስ የጠቀሳቸው ሰዎች ሁሉ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ራሱ በፈቀደ መልክ አይተውታል፤ አባባሉ ወደ ፊት የሚያምኑትንም ይመለከታል::

20+30 *ታምራዊ ምልክቶች፡* የ2+11 ማብ ይመ:: ዮሐንስ ያን ጊዜ ከተደረጉት ከብዙዎቹ ታምራት ውስጥ የተወሰኑትን መርጦ ጽፎአል:: *በደቀ መዛሙርቱ ፊት፡* ኢየሱስ፣ ሥራውን ለመመስከር በሚችሉት ሁሉ ፊት ታምራቱን አድርጎአል:: ዮሐንስ አሁንም ለምስክርነት ከፍተኛ ትኵረት ይሰጣል (የ1+7 ማብ ይመ)::

20+31 *ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ ሆነ፤* እምነት ሲባል መሠረት ሊኖረው እንደሚገባ ያመለክታል:: *ክርስቶስ፡* የ1+25 ማብ ይመ:: ይህ ወንጌል የተጻፈው የኢየሱስን መሲሕነት ለማሳየትና ወንጌሉን የሚያነቡ ሁሉ በእርሱ እንዲያምኑ ታስቦ ነው:: *እንድታምኑ፤* ዮሐንስን ለወንጌል ስርጭት የነበረውን ዓላማ ያመለክታል (የ1+7 ማብ ይመ):: *አምናችሁም...ሕይወት እንዲኖራችሁ፤* ይህም የዮሐንስን የወንጌል ስርጭት ዓላማ የሚገልጽ ነው፤ ወደ ሕይወት የሚያደርስ እምነት እንዲኖረን ያሻናል (የ1+4፤ የ3+15 ማብ ይመ):: *በስሙ፤* ማንነቱንና የቆመለትን ዓላማ ያመለክታል (የ2+23 ማብ ይመ)::

21+1 *የጥብርያዶስ ባሕር፡* የ6+1 ማብ ይመ::

21+2 *ስምዖን ጴጥሮስ፡* የማር 1+16 ማብ ይመ:: *ቶማስ፡* የ11+16 ማብ ይመ:: *የዘብዴዎስ ልጆች፡* በዚህ ወንጌል ውስጥ

5እርሱም፣ “ልጆች፣ ዓሣ አላችሁ?” አላቸው።
እነርሱም፣ “የለንም” አሉት።
6እርሱም፣ “መረባችሁን ከጀልባው በስተ ቀኝ
ጣሉ፤ ዓሣ ታገኛላችሁ” አላቸው። እነር
ሱም በጣሉ ጊዜ ከዓሣው ብዛት የተነሣ
መረቡን መጐተት አቃታቸው።
7ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙ
ርም፣ ጴጥሮስን፣ “ጌታ እኮ ነው!” አለው።
ስምዖን ጴጥሮስም፣ ‘ጌታ እኮ ነው!’ የሚለውን
ቃል በሰማ ጊዜ፣ አውልቆት የነበረውን መደ
ረቢያ ልብስ ታጠቀና ዘሎ ወደ ባሕሩ
ገባ። 8ሌሎች ደቀ መዛሙርት ግን ከባሕሩ
ዳርቻ የራቁት ሁለት መቶ ክንድ ያህል* ብቻ
ስለ ነበር፣ ዓሣ የሞላበትን መረብ እየሳቡ
በጀልባዋ መጡ። 9ወደ ምድርም በደረሱ
ጊዜ፣ ዓሣ በላዩ የነበረበት የከሰል ፍምና
እንጀራ አዩ።
10ኢየሱስም፣ “አሁን ካጠመዳችሁት ዓሣ
እስቲ አምጡ” አላቸው።
11ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ወደ ጀልባዋ
ወጥቶ መረቡን ወደ ምድር ጐተተው፤
መረቡንም መቶ አምሳ ሦስት ትልልቅ ዓሣ
ሞልተውት ነበር፤ ይህን ያህል ቢይዝም
መረቡ አልተቀደደም። 12ኢየሱስም “ኑ፤ ቍርስ
ብሉ” አላቸው። ጌታ እንደ ሆነ ዐውቀው ስለ
ነበር፣ ከደቀ መዛሙርቱ፣ “አንተ ማን
ነህ?” ብሎ ለመጠየቅ የደፈረ አልነበረም።
13ኢየሱስም መጥቶ እንጀራውን አንሥቶ ሰጣ
ቸው፤ ዓሣውንም ሰጣቸው። 14እንግዲህ ኢየሱስ
ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ
ሲታይ ይህ ሦስተኛ ጊዜ ነው።

21፥6 ሉቃ5፥4-7
21፥7 ዮሐ13፥23
21፥9 ቍ10፡13፤ ዮሐ18፥18
21፥13 ቍ9
21፥14 ዮሐ20፥19፡26
21፥15 ማቴ6፥33፡35፤ሉቃ12፥32፤ ዮሐ13፥37
21፥16 2ሳሙ5፥2፤ ሕዝ34፥2፤ማቴ2፥6፤ ዮሐ10፥11፤ ሐሥ20፥28፤ 1ጴጥ5፥2፡3
21፥17 ቍ16፤ ዮሐ13፥38፤16፥30
21፥19 ማቴ4፥19፤ ዮሐ12፥33፤13፥36፤ 18፥32፤2ጴጥ1፥14
21፥20 ቍ7፤ ዮሐ13፥23፡25

## ኢየሱስ ጴጥሮስን ወደ ቀድሞ ቦታው መለሰው

15በልተው ካበቁ በኋላ፣ ኢየሱስ ስምዖን ጴጥ
ሮስን፣ “የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፤ ከእነዚህ
አብልጠህ ትወደኛለህን?” አለው።
እርሱም፣ “አዎን፤ ጌታ ሆይ፤ እንደም
ወድህ አንተ ታውቃለህ” አለው።
ኢየሱስም፣ “ጠቦቶቼን መግብ” አለው።
16ኢየሱስም ለሁለተኛ ጊዜ፣ “የዮና ልጅ፣
ስምዖን ሆይ፤ በእውነት ትወደኛለህን?” አለው።
እርሱም፣ “አዎን፤ ጌታ ሆይ፤ እንደም
ወድህ አንተ ታውቃለህ” አለው።
ኢየሱስም፣ “በጎቼን ጠብቅ” አለው።
17ሦስተኛም ጊዜ፣ “የዮና ልጅ፣ ስምዖን
ሆይ፤ ትወደኛለህን?” አለው።
ጴጥሮስም ሦስተኛ ጊዜ ኢየሱስ፣ ‘ትወደ
ኛለህን?’ ብሎ ስለ ጠየቀው ዐዘነ፣ “ጌታ
ሆይ፤ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንደምወድህም
ታውቃለህ” አለው።
ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “በጎቼን መግብ።
18እውነት እልሃለሁ፤ ወጣት ሳለህ ልብስህን
ራስህ ለብሰህ ወደ ፈለግህበት ትሄድ ነበር፤
ስትሸመግል ግን እጅህን ትዘረጋለህ፤ ሌላም
ሰው ልብስህን አስታጥቆህ ልትሄድ ወደ
ማትፈልግበት ይወስድሃል።” 19ኢየሱስ ይህን
ያለው ጴጥሮስ በምን ዐይነት ሞት እግዚ
አብሔርን እንደሚያከብረው ለማመልከት ነው።
ከዚህ በኋላም፣ “ተከተለኝ” አለው።
20ጴጥሮስ ወደ ኋላው ዘወር ሲል፣ ኢየሱስ
ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር ሲከተላቸው
አየ፤ ይህም ደቀ መዝሙር ያን ጊዜ ራት

*8 ዘጠና ሜትር ያህል ነው

ስማቸው አልተጠቀሰም (ማቴ 4፥21 ይመ)።

21፥3 *በዚያ ሌሊት፤* በጥንት ዘመን ዓሣ አጥማጆች ዓሣ የሚያጠምዱት በሌሊት ነበር።

21፥4 *ኢየሱስ መሆኑን አላወቁም ነበር፤* ከመግደላዊት ማርያም ሁኔታ ጋር ያነጻጽሩ (የ20፥14 ማብ ይመ)።

21፥7 *ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር፤* የ13፥23 ማብ ይመ። *መደረቢያ ልብስ፤* በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህን የመሰለ የልብስ ዓይነት ተጠቅሶ የሚገኘው እዚህ ላይ ብቻ ነው። አይሁድ ሰላምታን እንደ ሃይማኖት ሥርዐት ስለሚቈጥሩ፣ ሰላምታ በሚሰጡበት ጊዜ ልብስ መደረብ ነበረባቸው። ጴጥሮስም ልብሱን የለበሰው ለጌታ ሰላምታ ለማቅረብ ራሱን ለማዘጋጀት ሊሆን ይችላል፤ ወደ ባሕርም የዘለለው በተለመደው ችኵል ባሕርይው ከሌሎቹ ቀድሞ ጌታ ዘንድ ለመድረስ ሳይሆን አይቀርም።

21፥9 *የከሰል ፍምና፤* በ18፥18 ላይ የተጠቀሰውን ይመ።

21፥11 *ጴጥሮስ...መረቡን ወደ ምድር ጎተተው፤* ቀደም ሲል፣ ጴጥሮስ ከሌሎች ጋር ሆኖ በጀልባዋ ውስጥ ማስገባት ያቃታቸውን፣ ዓሣ የሞላበት መረብ (ቍ 6)፣ እርሱ ዘሎ ከወረደ በኋላ ሌሎች በባሕር ላይ እየጐተቱ ያመጡትን (ቍ6) ተቀብሎ በመጐተት ወደ ምድር አወጣ ማለት ነው። *አልተቀደደም፤* በሉቃ 5፥6 ከተጠቀሰው መረብ ጋር በማነጻጸር የቀረበ ሐሳብ ነው።

21፥14 *ሦስተኛ ጊዜ፤* ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለተለያዩ ሰዎች ቢገለጥም፣ ብዙዎች ደቀ መዛሙርት አንድ ላይ እያሉ ሲገለጥ ግን ይህ ሦስተኛው ጊዜ ነው (20፥19-23፡24-29)።

21፥15-17 *ትወደኛለህን?* ኢየሱስ ለጴጥሮስ ካቀረባቸው ሦስት ጥያቄዎች፣ ‘ትወደኛለህን?’ ለሚለው ለሦስተኛው ጥያቄ የገባው የግሪክ ቃል ከመጀመሪያዎቹ ይለያል፤ በሦስቱም የጴጥሮስ መልሶች የቃሉ አገባብ እንዲሁ የተለያየ ነው። ዮሐንስ ለቋንቋ አገባብ ጥራት ሲል መጠነኛ የቃላት ልዩነት የሚያደርግ በመሆኑ፣ እዚህም ላይ ቃላቱን የሚለዋውጠው የተለየ ትርጕም እንዲያስገኝ አስቦ አይመስልም። በተጨማሪም በዚህ ወንጌል ውስጥ በየትኛውም ቦታ በእነዚህ ሁለት ቃላት መካከል የትርጕም ለውጥ አልተመለከተም። በዚህ ክፍል ውስጥ ሁለቱ ቃላት ጎን ለጎን ገብተው ይገኛሉ፤ አገባባቸውም ሆን ተብሎ ስለ ሆነ፣ ለቋንቋ ጥራት የታሰበ ይመስላል። ‘በእውነት ትወደኛለህን?’ የሚለው ጥያቄ፣ በፍጹም ልብ መውደድ የሚለውን ግንዛቤ ያመለክታል። ‘ፍቅር’ ሲባል እናት ለልጇ ያላትን ዓይነት ተፈጥሮአዊ ፍቅርን ይመለከታል፤ በሌላም በኩል በረጋ መንፈስ ሳይሆን ከግንፍል ስሜት የሚመጣውንም ፍቅር ያካትታል። በየትኛውም መልክ ቢተረጐም፣ ጴጥሮስ ወደ ነበረበት በጎ ሁኔታ መለስ እንዲል እየተደረገ እንኳ፣ ትኵረት የተሰጠው ጉዳይ ጴጥሮስ ኢየሱስን ስለ መውደዱ ነበር።

21፥15 *ከእነዚህ አብልጠህ፤* ‘እነዚህን ሰዎች ከምትወዳቸው’ ወይም ‘እነዚህ ሰዎች እኔን ከሚወዱኝ’ በይበልጥ፣ ወይም ‘ለእነዚህ ዓሣ ማጥመጃዎች ካለህ ፍቅር’ ይልቅ ትወደኛለህን ማለት ሊሆን ይችላል። ጴጥሮስ “ከሌሎቹ የበለጠ እወድሃለሁ” ብሎት ስለ ነበር (ከ13፥37፤ ከማቴ 26፥33፤ ከማር 14፥29 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ሁለተኛው ትክክለኛ ትርጕም ሳይሆን አይቀርም። ጴጥሮስ የተጠየቀው ከዚህ በፊት ከተናገረው አንጻር መሆኑ ትዝ አላለውም፤ ኢየሱስም ተጨማሪ ማብራሪያ አልሰጠውም። *ጠቦቶቼን መግብ፤* ምናልባት፣ ‘በጎቼን ጠብቅ’ (ቍ16)፣ ‘በጎቼን መግብ’ (ቍ17) ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል።

21፥17 *አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤* የጴጥሮስ መልስ አበክሮ የሚያመለክተው ራሱ ለጌታ ያለውን ፍቅር ብቻ ሳይሆን፣ ክርስቶስ ሁሉን እንደሚያውቅ ነው።

21፥18-19 *እጅህን ትዘረጋለህ...በምን ዓይነት ሞት፤* እጅን የሚያዘረጋ አሟሟት ስቅለትን ስለሚያመለክት፣ የጥንት ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስ የሞተው በመስቀል ላይ (ያውም ተዘቅዝቆ) እንደ ሆነ ታምን ነበር፤ ጴጥሮስ በሰማዕትነት ተሰቅሎ

ሲበሉ ወደ ኢየሱስ ደረት ተጠግቶ፣ “ጌታ
ሆይ፤ አሳልፎ የሚሰጥህ ማን ነው?” ያለው
ነበር። [21]ጴጥሮስም ባየው ጊዜ፣ “ጌታ ሆይ፤
እርሱስ?” ብሎ ጠየቀ።
[22]ኢየሱስም፣ “እስክመለስ ድረስ በሕይወት
እንዲኖር ብፈልግ እንኳ አንተን ምን ቸገረህ?
አንተ ራስህ ተከተለኝ” አለው። [23]በዚህ ምክ
ንያት ይህ ደቀ መዝሙር አይሞትም የሚል
ወሬ በወንድሞች መካከል ተሰራጨ። ኢየሱስ
ግን፣ “እስክመለስ ድረስ በሕይወት እንዲኖር
ብፈልግ አንተን ምን ቸገረህ?” አለው እንጂ
እንደማይሞት አልነገረውም።
[24]ስለ እነዚህ የሚመሰክረውና ይህን የጻፈው
ይኸው ደቀ መዝሙር ነው፤ ምስክርነቱም
እውነት እንደ ሆነ እናውቃለን።
[25]ኢየሱስ ያደረጋቸው ሌሎችም ብዙ ነገ
ሮች አሉ፤ ሁሉም ነገር ቢጻፍ፣ ለተጻፉት
መጻሕፍት ሁሉ ዓለም በቂ ቦታ የሚኖረው
አይመስለኝም።

21+22 ቍ19፤ ማቴ4+19፤16+27
21+23 ሐሥ1+16
21+24 ዮሐ15+27፤ 19+35
21+25 ዮሐ20+30

እንደሚሞት የሚያመለክት ትንቢት እንደ ነበርም ይታመናል።

21+20 *ኢየሱስ ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር*፤ የ13+23 ማብ ይመ። *ያን ጊዜ ራት ሲበሉ*፤ 13+23-25 ይመ።

21+22 *እስክመለስ ድረስ*፤ ዳግም ምጽአትን በግልጽ የሚያመለክት ነው።

21+24 *ስለ እነዚህ* መጽሐፉን በሙሉ በተመለከተ መሆን አለበት። *የሚመሰክረው...ደቀ መዝሙር*፤ በዚህ ወንጌል ውስጥ ተጀምሮ እስከሚጨረስ ድረስ፣ ‘ምስክርነት’ ዐቢይ ርዕስ ሆኖ የቀረበ ሐሳብ ነው (የ1+7 ማብ ይመ)። መስካሪው ተወዳጁ ደቀ መዝሙር እንደ ሆነ እዚህ ላይ እንገነዘባለን። *የጻፈው*፤ ተወዳጁ ደቀ መዝሙር ምስክር ብቻ ሳይሆን፣ መጽሐፉንም የጻፈው እርሱ ራሱ ነው። *እናውቃለን*፤ ጸሓፊው በጊዜው ከነበሩትና እውነቱን አስረግጠው ከሚያውቁት አንዱ ነበር ማለት ነው።

21+25 *ሌሎችም ብዙ ነገሮች*፤ በ20+30 ላይ እንደ ተጠቀሰው፣ ጸሓፊው ፍሬ ነገሮችን ብቻ መርጦ እንደ ጻፈ ያረጋግጣል። *ዓለም በቂ ቦታ የሚኖረው አይመስለኝም*፤ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቀረበው ታሪክ መጠነኛ ነው፤ ሆኖም ማወቅ የሚገባንን ያህል እንድናውቅ በቂ ሐሳብ ተጽፎ ቀርቦልናል።